


# ክፍል አንድ

# ዐሥርቱ ትእዛዛት

## እንደ ቤተ ሰብ መሪ ቀለል ባለ መንገድ የቤተ ሰቡን አባላት ማስተማር ያስፈልጋል

### *የመጀመሪያው ትእዛዝ*

**ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ።**

*ይህ ምን ማለት ነው?* ከሁሉም ነገር በላይ እግዚአብሔርን መፍራት፣ መውደድ እና መታመን ይኖርብናል ማለት ነው።

### *ሁለተኛው ትእዛዝ*

**የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ**

*ይህ ምን ማለት ነው?* እግዚአብሔርን እየፈራንና እየወደድን በችግራችን ጊዜ ልንጠራው፣ ልንጸልይ፣ ልንወድሰው እና ልናመሰግነው እንጂ በስሙ ልንራገም፣ ልንምል፣ ለሰይጣናዊ ሥራዎች ልናውለው፣ ልንዋሽበት፣ ልናታልልበት አይገባም።

### *ሦስተኛው ትእዛዝ*

**የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ ዐስብ**

*ይህ ምን ማለት ነው?* እግዚአብሔርን እየፈራንና እየወደድን ቅዱስ ቃሉን ልንጠብቅ፣ በደስታ ልናደምጥና ልንማር ያስፈልጋል እንጂ ቃሉንና ስብከትን ልናቃልል አይገባም።

### *አራተኛው ትእዛዝ*

**አባትህንና እናትህን አክብር**

*ይህ ምን ማለት ነው?* እግዚአብሔርን እየፈራንና እየወደድን ወላጆቻችንን እና ሌሎች የሥልጣን አካላትን ልናከብራቸው፣ ልናገለግላቸው፣ ልንታዘዛቸው ብሎም ልንወዳቸው እና ልናስደስታቸው ያስፈልጋል እንጂ ልንንቅና ልናስቆጣ አይገባም።

### *አምስተኛው ትእዛዝ*

**አትግደል**

*ይህ ምን ማለት ነው?* እግዚአብሔርን እየፈራንና እየወደድን ባልንጀራችንን በሚያስፈልገው ቁሳዊ አቅርቦት ልንረዳው እና ልንደግፈው ያስፈልጋል እንጂ አካላዊ ጉዳትም ሆነ ጥቃት ልናደርስበት አይገባም።

## *ስድስተኛው ትእዛዝ*

### አታመንዝር

*ይህ ምን ማለት ነው?* እግዚአብሔርን እየፈራንና እየወደድን በቃልም ሆነ በሥራችን ከምንዝርና የጸዳ ንጹሕ ሕይወት ልንኖር የሚያስፈልግ ሲሆን ባልና ሚስትም እርስ በእርሳቸው ሊዋደዱ እና ሊከባበሩ ይገባል፡፡

## *ሰባተኛው ትእዛዝ*

### አትስረቅ

*ይህ ምን ማለት ነው?* እግዚአብሔርን እየፈራንና እየወደድን ባልንጀራችን እንዲሻሻልና ገቢውና ንብረቱ እንዲጠበቅ ልናግዘው ይገባል እንጂ ገንዘብ ወይም ንብረት ልንወስድበት ወይም እምነት በማጉደል ለማግኘት መጣር አያስፈልግም፡፡

## *ስምንተኛው ትእዛዝ*

### በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር

*ይህ ምን ማለት ነው?* እግዚአብሔርን እየፈራንና እየወደድን ስለ ባልንጀራችን ልንከላከልለት፣ ስለ እርሱ መልካምን ልንናገር፣ እንዲሁም ማናቸውንም ነገሮች በርኅራኄ ልናብራራ ይገባል እንጂ ሐሰትን ልንናገር፣ ልንከዳው፣ ልናማው፣ መልካም ስሙን ልናጎድፍ አይገባም፡፡

## *ዘጠነኛው ትእዛዝ*

### የባልንጀራህን ቤት አትመኝ

*ይህ ምን ማለት ነው?* እግዚአብሔርን እየፈራንና እየወደድን ባልንጀራችን ያለው እንዲጠበቅለት ማገዝ ይኖርብናል እንጂ ቤቱንና ርስቱን ለማግኘት ማሤር ወይም አግባብነት ያላቸው በሚመስሉ መንገዶች የራሳችን ማድረግ አይገባንም፡፡

## *ዐሥረኛው ትእዛዝ*

### የባልንጀራህን ሚስት ሎሌውንም ገረዱንም በሬውንም አህያውንም ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማናቸውንም አትመኝ

*ይህ ምን ማለት ነው?* እግዚአብሔርን እየፈራንና እየወደድን ለባልንጀራችን ተግባራቸውን እንዲፈጽሙ እና አብረውት እንዲቆዩ መምከር ይገባናል እንጂ የባልንጀራችንን ሚስት፣ ሠራተኞችን፣ እንስሳቱን እንዲኮበልሉ ማነሣሣት ወይም እንዲቃወሙት ማድረግ አይገባም፡፡

(የትእዛዛቱ ክፍል የተወሰደው ከዘጸአት 20፡3፣7፣8፣ 12-17 ነው)

## *የትእዛዛቱ ማጠቃለያ*

***እግዚአብሔር ስለ እነዚህ ትእዛዛት ምን አለ?***

**‹‹አትስገድላቸው፣ አታምልካቸውምም በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ ለሚወድዱኝ፣ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና›› (ዘጸአት 20፡5-6)፡፡**

*ይህ ምን ማለት ነው?* እግዚአብሔር እነዚህን ትእዛዛት የሚተላለፈውን ሰው ሁሉ እንደሚቀጣ ማስጠንቀቂያ እየሰጠ ነው፡፡ ስለዚህም ቊጣውን ልንፈራ ይገባል፤ ስለሆነም ትእዛዛቱን መተላለፍ የለብንም፡፡ ነገር ግን በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህን ትእዛዛት ለሚጠብቁ ሁሉ ጸጋውንና በረከቱን ሁሉ ሊሰጥ ቃል ገብቷል፡፡ ስለሆነም በእርሱ ልንታመንና ልንወደው ብሎም ትእዛዛቱን በደስታ ልንፈጽም ያስፈልጋል፡፡



## የእምነት መግለጫ

**እንደ ቤተ ሰብ መሪ ቀለል ባለ መንገድ**
**የቤተ ሰቡን አባላት ማስተማር ያስፈልጋል**

### *የመጀመሪያው አንቀጽ*
### ፍጥረት

**እኔ ሁሉን በሚችል፣ ሰማይንና ምድርን በፈጠረ በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ።**

*ይህ ምን ማለት ነው?* እግዚአብሔር እኔንና ፍጥረታትን በሙሉ እንደ ፈጠረን አምናለሁ፤ አካሌን፣ ነፍሴን፣ ዐይኖቼን፣ ጆሮዎቼን እንዲሁም ሁሉንም የአካል ክፍሎቼን፣ አመክኖአዊ አስተሳሰቤንም ሆነ ስሜቶቼን የሰጠኝ ሲሆን፣ እስካሁንም ይንከባከባቸዋል።

ያለኝን ሁሉና በተጨማሪም ልብስ፣ ጫማ፣ ምግብ፣ መጠጥ፣ ቤትና ቤተ ሰብ፣ ሚስትና ልጆች፣ መሬትና እንስሳት የሚሰጠኝ እርሱ ነው። ይህን ሰውነቴንና ኑሮዬን ለመደገፍ የሚያስፈልገኝን ሁሉ በየዕለቱ እንደ ባለጠግነቱ መጠን ያቀርብልኛል።

ከማናቸውም አደጋ ይታደገኛል፣ ይከላከልልኛል፣ ከክፉም ሁሉ ይጠብቀኛል።

ይህን የሚያደርገውም የሚገባኝና የበቃሁ ሆኜ ሳይሆን ከአባትነቱ፣ ከመለኮታዊ ቸርነቱና ምሕረቱ የተነሣ ብቻ ነው። ለዚህም የእኔ ተግባር  እርሱን ማመስገንና ማወደስ፣ ማገልገልና መታዘዝ ነው።

ይህም የጸና እውነት ነው።

### *ሁለተኛው አንቀጽ*
### *መዋጀት*

**ደግሞም በአንድ ልጁ፣ በመንፈስ ቅዱስ በተፀነሰ፣ ከድንግል ማርያም በተወለደ፣ በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን መከራ በተቀበለ፣ በተሰቀለ፣ በሞተ፣ በተቀበረ፣ ወደ ሲኦልም በወረደ፣ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን በተነሣ፣ ወደ ሰማይም በወጣ፣ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ ቀኝ በተቀመጠ፣ በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ ከዚያም በሚመለስ፣ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ።**

*ይህ ምን ማለት ነው?* ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ አምላክ፣ ከዘላለም የአብ አንድያ ልጅ፣ እንዲሁም ከድንግል ማርያም የተወለደ እውነተኛ ሰው፣ እርሱ ጌታዬ መሆኑን አምናለሁ።

የጠፉሁትንና በኰነኔ ያለሁትን ሰው ከኃጢአትም ሁሉ፣ ከሞት፣ ከዲያብሎስ ኃይል፣ በወርቅ እና በብር ሳይሆን በቅዱስና በክቡር ደሙ፣ ያለ ኃጢአት በሆነ መከራና ሞቱ ዋጀኝ።

ይህም እርሱ ከሙታን ተነሥቶ ለዘላለም እንደሚኖርና እንደሚገዛ እኔም የእርሱ ሆኜ በመንግሥቱ ውስጥ በዘላለማዊ ጽድቅ፣ ንጽሕናና ብፅዕና እንድኖርና እንዳገለግል ነው።

ይህም የጸና እውነት ነው።

## *ሦስተኛው አንቀጽ*
## ቅድስና

**ደግሞም በመንፈስ ቅዱስ፣ በአንዲት ቅድስት የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን፣ በቅዱሳን አንድነት፣ በኃጢአት ስርየት፣ በሥጋ ትንሣኤ በዘላለም ሕይወት አምናለሁ። አሜን።**

*ይህ ምን ማለት ነው?* በራሴ ማስተዋል እና ኃይል በኢየሱስ ክርስቶስ፣ በጌታዬ ማመንም ሆነ ወደ እርሱ መምጣት እንደማልችል ዐውቃለሁ፤ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በወንጌል እንደ ጠራኝ፣ በስጦታዎቹም አብርሆትን እንደ ሰጠኝ፣ እንደ ቀደሰኝና በእውነተኛ እምነት እንደሚጠብቀኝ አምናለሁ።

በተመሳሳይ ሁኔታም እርሱ ይጠራል፣ ይሰበስባል፣ አብርሆትን ይሰጣል፤ እንዲሁም በምድር ላይ ያለችውን መላዋን ቤተ ክርስቲያን ይቀድሳል፣ እንዲሁም በኢየሱስ ክርስቶስ በአንዲት እውነተኛ እምነት ይጠብቃል።

በዚህች ቤተ ክርስቲያን የእኔንም ሆነ የአማኞችን ሁሉ ኃጢአት በየዕለቱ እንደ ምሕረቱ ይቅር ይላል።

በመጨረሻውም ቀን እኔንና ሙታንን ሁሉ ያሥነሣል፤ ለእኔና በክርስቶስ ለሆኑት አማኞች ሁሉ የዘላለምን ሕይወት ይሰጠናል።

ይህ የጸና እውነት ነው።



## የጌታችን ጸሎት

### እንደ ቤተ ሰብ መሪ ቀለል ባለ መንገድ የቤተ ሰቡን አባላት ማስተማር ያስፈልጋል

**በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ስምህ ይቀደስ፣ መንግሥትህ ትምጣ፣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን፤ የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን፣ እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን፤ ከክፉ አድነን እንጂ ወደ ፈተናም አታግባን። መንግሥት ያንተ ናትና ኃይልም፣ ክብርም ለዘላለሙ። አሜን።**

### *መግቢያ*

### በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ

*ይህ ምን ማለት ነው?* በእነዚህ ቃላት እግዚአብሔር እውነተኛ አባታችን እኛም እውነተኛ ልጆቹ እንደሆንን እንድናምን በርኅራኄ ይጋብዘናል፤ የተወደዱ ልጆች ውድ አባታቸውን እንደሚጠይቁ እኛም በቅዱስ ድፍረትና በመተማመን ልንጠይቀው እንችላለን።

### *የመጀመሪያው ጸሎት*

### ስምህ ይቀደስ

*ይህ ምን ማለት ነው?* የእግዚአብሔር ስም በርግጥ በራሱ ቅዱስ ነው፤ ሆኖም በዚህ ጸሎታችን ውስጥ በእኛም መሐል ቅድስናው እንዲጠበቅ ይገባል።

*የእግዚአብሔር ስም በቅድስና የሚጠበቀው እንዴት ነው?* የእግዚአብሔር ስም በቅድስና የሚጠበቀው የእግዚአብሔር ቃል በእውነትና በንጽሕና ሲሰበክ፣ እኛም እንደ እግዚአብሔር ልጆች እንደ ቃሉ የተቀደሰ ሕይወት መኖር ስንችል ነው። በሰማይ የምትኖር ውድ አባታችን ሆይ፣ ይህን ማድረግ እንድንችል እርዳን! ነገር ግን ከእግዚአብሔር ቃል የተቃረነ ኑሮ የሚኖርና የሚያስተምር በመካከላችን የእግዚአብሔርን ስም ያሰድባል። የሰማይ አባት ሆይ፣ ከዚህ አድነን!

### *ሁለተኛው ጸሎት*

### *መንግሥትህ ትምጣ*

*ይህ ምን ማለት ነው?* የእግዚአብሔር መንግሥት በርግጥ በእኛ ጸሎት ሳይሆን በራሷ የምትመጣ ናት፤ በዚህ ጸሎት ግን ወደ እኛም ደግሞ እንድትመጣ ነው።

*የእግዚአብሔር መንግሥት እንዴት ትመጣለች?* የእግዚአብሔር መንግሥት የምትመጣው በጸጋው ቅዱስ ቃሉን እንድናምን፣ በአሁኑ ዘመንና በሚመጣው ዓለም እግዚአብሔርን በመምሰል እንድንኖር የሰማይ አባታችን ቅዱስ መንፈሱን በሚሰጠን ጊዜ ነው።

## *ሦስተኛው ጸሎት*

## ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን

*ይህ ምን ማለት ነው?* የእግዚአብሔር መልካምና ቸር ፈቃዱ ያለ እኛ ጸሎት እንኳ ትፈጸማለች። በዚህ ጸሎት የምንለምነው ግን በእኛ መካከል ደግሞ እንድትሆን ነው።

*የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዴት ትፈጸማለች?* የእግዚአብሔር ፈቃድ የእግዚአብሔርን ስም እንዳንቀድስ ወይም መንግሥቱ እንዳትመጣ የሚከላከል ማናቸውም የክፉ ዕቅድ፣ የዲያብሎስ ዓላማ፣ ዓለምና ኃጢአታዊ ባሕርያችን በሚሰብርበት ጊዜና እስከ ሞት ድረስ በቃሉና በእምነት ሲያበረታንና ሲጠብቀን ነው።

ይህ የእርሱ መልካምና ቸር ፈቃዱ ነው።

## *አራተኛው ጸሎት*

## የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን

*ይህ ምን ማለት ነው?* እግዚአብሔር በርግጥ፣ ያለ ጸሎት እንኳ ለሰዎች ሁሉ ለክፉዎች እንኳ ሳይቀር የዕለት እንጀራ ይሰጣል። በዚህ ጸሎት ግን እግዚአብሔር ይህንን እንድንረዳና የዕለት እንጀራችንን በምስጋና እንድንቀበለው ይመራናል።

*የዕለት እንጀራ ማለት ምን ማለት ነው?* የዕለት እንጀራ ለሰውነታችን የሚያስፈልግና የሚደግፈን ማናቸውም ነገር ማለትም ምግብ፣ መጠጥ፣ ልብስ፣ ጫማ፣ ቤት፣ ቤተ ሰብ፣ እንስሳት፣ ገንዘብ፣ ቁሳቁስ፣ ትጉህ ባል ወይም ሚስት፣ ትጉሃን ልጆች፣ ትጉሃን ሠራተኞች፣ የታመኑና ትጉሃን ገዢዎች፣ መልካም አስተዳዳሪዎች፣ መልካም የአየር ሁኔታ፣ ሰላም፣ ጤንነት፣ ራስን መግዛት፣ መልካም ስም፣ መልካም ወዳጆች፣ የታመኑ ጎረቤቶችና የመሳሰሉትም ናቸው።

## *አምስተኛው ጸሎት*

## እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን።

*ይህ ምን ማለት ነው?* በዚህ ልመና ውስጥ የምንጸልየው በሰማይ ያለ አባታችን ወደ ኃጢአታችን እንዳይመለከት ወይም እነርሱን በመመልከቱ ጸሎታችን ተቀባይነት እንዳያጣ ነው። ለምንጸልየው ጸሎትም የተገባን ስለሆንን አይደለም። ነገር ግን የምንለምነውን ሁሉ በጸጋው እንዲሰጠን ነው፤ ምክንያቱም በየዕለቱ ስለምንበድል፣ ከቅጣት ውጪ አንዳችም አይገባንም። ስለዚህ እኛም በቅንነት ይቅር እንላለን፣ በደስታም ለበደሉን መልካም እናደርጋለን።

## *ስድስተኛው ጸሎት*

## ወደ ፈተና አታግባን

*ይህ ምን ማለት ነው?* እግዚአብሔር ማንንም አይፈትንም። በዚህ ጸሎት ዲያብሎስ፣ ይህ ዓለምና ኃጢአታዊ ተፈጥሮአችን እንዳያታልሉን ወይም ወደ ተሳሳተ እምነት፣ ተስፋ መቍረጥና ወደ ሌላ የከፋ ውርደት፣ እንዲሁም ወደ ጉስቁልና እንዳንወድቅ እንዲጠብቀንና

እንዲታደገን እንለምናለን። ምንም እንኳ በእነዚህ ነገሮች ብንጠቃም በመጨረሻ እንድናሸንፋቸውና ድል እንድናደርጋቸው እንለምናለን።

### *ሰባተኛው ጸሎት*

### ከክፉ አድነን እንጂ

*ይህ ምን ማለት ነው?* በዚህ የማጠቃለያ ጸሎት የምንለምነው የሰማይ አባታችን ሥጋችንን፣ ነፍሳችንን፣ ንብረታችንና ስማችንን ከክፉ ሁሉ እንዲያድነን በመጨረሻም የፍጻሜው ሰዓት ሲመጣ ብፅዕና የተሞላው ፍጻሜ እንዲሰጠን፤ በቸርነቱም ከዚህ የሐዘን ሸለቆ ወደ መንግሥተ ሰማይ ወደ ራሱ እንዲወስደን ነው።

### *ማጠቃለያ*

### *መንግሥት ያንተ ናትና ኃይል፣* ክብርም ለዘላለሙ።** *አሜን።*

*ይህ ምን ማለት ነው?* ይህ ማለት እነዚህ ልመናዎች በሰማይ ያለውን አባታችንን የሚያስደስቱና በእርሱም የተሰሙ መሆናቸውን እርግጠኛ መሆን እንችላለን። ምክንያቱም እርሱ ራሱ በዚህ ዓይነት መንገድ እንድንጸልይ ስላዘዘንና እንደሚሰማንም ቃል ስለ ገባልን ነው፡ ፡ አሜን ማለት አዎን፣ ይሁን ማለት ነው።

---

* እነዚህ ቃሎች በትንሹ የሉተር የክርስትና ትምህርት ውስጥ አልተጠቀሱም።



# የጥምቀት ቅዱስ ምሥጢር

## እንደ ቤተ ሰብ መሪ ቀለል ባለ መንገድ የቤተ ሰቡን አባላት ማስተማር ያስፈልጋል

### *አንደኛ*

### *ጥምቀት ምንድን ነው?*

*ጥምቀት ውሃ ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ትእዛዝ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የተዋሀደ ነው፡፡*

### *የትኛው የእግዚአብሔር ቃል ነው?*

ክርስቶስ ጌታችን በማቴዎስ ወንጌል የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ እንዲህ ይላል፡- *‹‹እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፣ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው››* (ማቴዎስ 28፡19)፡፡

### *ሁለተኛ*

### *ጥምቀት የሚሰጠው ጥቅም ምንድን ነው?*

*የእግዚአብሔር ቃል እና ተስፋዎቹ እንደሚመሰክሩት የኃጢአት ይቅርታ ይሰጣል፣ ከሞትና ከዲያብሎስ ይታደጋል፣ በተጨማሪም ይህን ለሚያምኑ ሁሉ ዘላለማዊ የሆነ ድነት ይሰጣል፡፡*

### *እነኚህ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃላት የትኞቹ ናቸው?*

ጌታችን ክርስቶስ በማርቆስ የመጨረሻ ምዕራፍ እንደሚናገረው፡ *‹‹ያመነ የተጠመቀም ይድናል፣ ያላመነ ግን ይፈረድበታል፡፡››* (ማርቆስ 16፡16)

### *ሦስተኛ*

### *ውሃ እንዴት እንደነዚህ ዓይነት ታላላቅ ነገሮች ሊያደርግ ይችላል?*

*በርግጥ ይህንን የሚሠራው ውሃው ብቻውን አይደለም፤ እነኚህን ነገሮች የሚሠራው በውሃው እና ከውሃው ጋር የሚሠራው የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ በውሃው ላይ የተነገረው ይህ የእግዚአብሔር ቃል እና በቃሉ ላይ ያለ እምነት አንድ ላይ ይህን ተአምራት ያደርጋሉ፡፡ ያለ እግዚአብሔር ቃል ውሃው ተራ ውሃ ሲሆን ጥምቀት ሊሆን አይችልም፡፡ ውሃው ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ሲሆን ግን ጥምቀት ይሆናል፤ ያኔ ሕይወት ሰጪ ውሃ፣ በጸጋ*

የተትረፈረፈና በመንፈስ ቅዱስ ለአዲስ ልደት የሚሆን መታጠብን ይሰጣል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ በቲቶ መልእክቱ በሦስተኛው ምዕራፉ ላይ እንዲህ ይላል፡-

‹‹እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ፣ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለ ነበረው ሥራ አይደለም ያን መንፈስም፣ በጸጋው ጸድቀን በዘላለም ሕይወት ተስፋ ወራሾች እንድንሆን፣ በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ላይ አትርፎ አፈሰሰው፡፡ ቃሉ የታመነ ነው›› (ቲቶ 3፡5-8)፡፡

## *አራተኛ*

## *እንደዚህ ዓይነቱ በውሃ ማጥመቅ ምንን ያመለክታል?*

በንስሐና በመጸጸት በእኛ ውስጥ ያለውን አሮጌውን አዳም በየዕለቱ ከኃጢአቶቹና ከክፉ ምኞቶቹ ጋር መስመጥና መሞት እንዳለበት በሌላም በኩል የአዲሱን ሰው በየዕለቱ ከፍ ብሎ መውጣት ብሎም በእግዚአብሔር ፊት በጽድቅ እና በንጽሕና በሕያውነት ለዘላለም ሊኖር መነሣት እንዳለበት ያሳያል፡፡

## *ይህ የተጻፈው የት ነው?*

ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ ምዕራፍ 6 እንዲህ ጽፏል፦ ‹‹እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፣ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን›› (ሮሜ 6፡4)፡፡



## ኑዛዜ

### ክርስቲያኖች እንዴት ኑዛዜን መማር እንዳለባቸው

### *ኑዛዜ ምንድን ነው?*

ኑዛዜ ሁለት ክፍሎች አሉት፡፡

በመጀመሪያ ኃጢአታችንን እንናዘዛለን እናም

ሁለተኛ የኃጢአታችንን ስርየት እንቀበላለን፤ እርሱም ከእግዚአብሔር ከራሱ እንደምንቀበል ከካህኑ እንቀበላለን፡፡ በመጠራጠር ሳይሆን በእግዚአብሔር ፊት በሰማይ የኃጢአታችንን ይቅርታ በጽኑ በማመን ነው፡፡

### *መናዘዝ ያለብን የትኛውን ኃጢአት ነው?*

በእግዚአብሔር ፊት ለኃጢአታችን ሁሉ ይቅርታ እንለምናለን፣ በጌታ ጸሎት ጊዜ እንደምናደርገው ያላስተዋልናቸውን በደሎች እንኳ ጨምረን እንናዘዛለን፤ በመጋቢው ፊት ግን የምንናዘዛቸው ኃጢአቶች የምናውቃቸውንና በልባችን የሚሰሙንን ነው፡፡

### *እነዚህ የትኞቹ ናቸው?*

በዐሥርቱ ትእዛዛት መሠረት በሕይወት ውስጥ ያለህን ስፍራ ተመልከት፤ አባት፣ እናት፣ ወንድ ልጅ፣ ሴት ልጅ፣ ባል፣ ሚስት ወይስ ሠራተኛ ነህ? ባለመታዘዝ፣ ባለመታመን ወይም በስንፍና ተገኝተህ ይሆን? ንዴት፣ ጭካኔ ወይም ጸብ ጫሪነት ይታይብህ ይሆን? በቃል ወይም በሥራህ ሌሎችን ጎድተህ ይሆን? በስርቆት፣ በቸልተኝነት ወይም የሆነ ነገር በማባከን ወይም በሆነ ነገር ጉዳት አድርሰህ ይሆን?

### አጠር ያለ ኑዛዜ

(የሚከተለውን ቅጽ ሉተር ያዘጋጀበት መነሻ ዐሳብ በጊዜው ለሚገኙ ክርስቲያኖች ለግል ኑዛዜያቸው ብሎ ነው፡፡ በዚህ ዘመን ለሚሆን የተናጠል ኑዛዜ ግን፣ የሉተራንን የአገልግሎት መጽሐፍ ገጽ 292-93 ይመልከቱ)

***ተናዛዡ እንዲህ ይላል፤***

ውድ ኑዛዜዬን ተቀባይ ሆይ ኑዛዜዬን ትሰማ ዘንድ ከዚያም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም የኃጢአቴን ይቅርታ እንድታውጅልኝ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

እኔ ምስኪን ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር ፊት ስለ ኃጢአቶቼ ሁሉ እናዘዛለሁ፡፡ በተለይም እንደ ወንድ ወይም ሴት አገልጋይ ባሪያ፣ ወዘተ. በጌታዬ ላይ እምነት ማጉደሌን ስናዘዝ ሐዘን ይሰማኛል፤ በዚህም አድርግ የተባልኩትን አላደረኩም፡፡ እርሱን ከማስቆጣቴም በላይ የእርግማንን ቃል እንዲናገር ምክንያት ሆኛለሁ፡፡ በቸልተኝነቴ ምክንያት ኪሳራ አድርሻለሁ፡፡

በቃል እና በሥራዬም ሌላውን ሰው አበሳጭቻለሁ። ከሥራ ባልደረቦቼ ጋር ጸብ ውስጥ ገብቻለሁ። በቤት እመቤቲቱ ላይ አጉረምርሜያለሁ፤ እንዲሁም ረግሜአታለሁ። ስለዚህ ሁሉ አዝናለሁ፤ እናም ጸጋህን እለምናለሁ። የተሻለ ማድረግም እፈልጋለሁ።

***የቤቱ ጌታ ወይም እመቤት እንዲህ ሊሉ ይችላሉ፤***

በታማኝነት ልጆቼን፣ አገልጋዮቼን እና ሚስቴን ወይም ባሌን ለእግዚአብሔር ክብር አለመምራቴን በተለይ በፊትህ እናዘዛለሁ። ተራግሜአለሁ። በማይገባ ቃል እና ምግባር መጥፎ ምሳሌ ሆኛለሁ። ስለ ባልንጀራዬ ክፉ በመናገሬ ጎድቼዋለሁ። ከሚገባው በላይ አስከፍያለሁ፣ ተራ እና የማይረባ እቃ ሸጬያለሁ፤ ለዚያም የማይገባውን ዋጋ ተቀብያለሁ።

(ተናዛዡ የተላለፈውን የእግዚአብሔር ትእዛዛት እንዲሁም ከራሱ የሥራ ድርሻ ጋር በማያያዝ የሰራውን ማናቸውንም ኃጢአት ይናዘዝ)

አንድ ሰው ግን በእነዚህ ወይም ከእነዚህ በከፉ ኃጢአቶች ውስጡን ሸክም ካልተሰማው ራሱን ማስጨነቅ አይኖርበትም፣ ወይም ደግሞ ሌሎች ኃጢአቶችን በመፍጠር ኑዛዜን ራስን ማሰቃያ ማድረግ አይኖርበትም። ከዚያ  ይልቅ የሚያውቃቸውን አንድ ሁለቱን ኃጢአቶች መናዘዝ ይችላል፤ በተለይም የርግማን ቃል ማውጣቴን እናዘዛለሁ፣ ያልተገቡ ቃላት አውጥቻለሁ፤ ይህን ወይም ያንን ቸል ብያለሁ፣ ወዘተ. ያ ይበቃል።

ምንም የምትጠቅሰው ነገር ከሌለ ግን (በርግጥ ይህ በአብዛኛው ሊሆን የሚቻል አይደለም)፣ ምንም የምትጠቅሰው ነገር ሳይኖር በኑዛዜ ተቀባዩ ፊት መደበኛ የሆነውን ኑዛዜ በመጠቀም የኃጢአትህን ይቅርታ ተቀበል።

***ከዚያም ኑዛዜ ተቀባዩ እንዲህ ይበል፡-***

እግዚአብሔር ይማርህ እምነትህንም ያጽና። አሜን።

***በተጨማሪም፤***

የእኔ ይቅርታ የእግዚአብሔር ይቅርታ መሆኑን ታምናለህ?

አዎን፣ ውድ ኑዛዜ ተቀባዬ ሆይ።

***ከዚያም እንዲህ ይበለው፣***

እንደ እምነትህ እንዲሁ ይሁንልህ። እኔም በጌታችን በኢየሱስ ትእዛዝ የኃጢአትህን ይቅርታ በአብ፣ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አስታውቅሃለሁ። አሜን። በሰላም ሂድ።

ኑዛዜ ተቀባዩ በህሊናቸው ውስጥ ከባድ ሸክም ያለባቸውን፣ ወይም ሐዘንና ሰቆቃ የሞላባቸውን ለማጽናናትና እምነታቸውን ለማጽናት ተጨማሪ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃሎችን ስለሚያውቅ ሊጠቀምባቸው ይችላል።

ይህ እንደ አጠቃላይ የኑዛዜ መመሪያ እንዲሆን ብቻ የታሰበ ነው።

## ***የመክፈቻዎቹ ሥልጣን ምንድን ነው?*** [*]

[*] ይህ ጥያቄ በሉተር በራሱ የተጠናከረ ላይሆን ይችላል ሆኖም ግን ትምህርቱን የሚያንጸባርቅ ከመሆኑም በላይ በርሱ ዘመን በነበሩት እትሞች በክርስትና ትምህርቶቹ የተካተቱ ናቸው።

የመክፈቻዎቹ ሥልጣን ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን በምድር በኃጢአታቸው ንስሐ የሚገቡትን ኃጢአተኞች ይቅርታ ለመስጠት ንስሐ የማይገቡትን ደግሞ ንስሐ እስካልገቡ ድረስ የኃጢአት ይቅርታቸውን መያዝ ነው።

## *ይህ የተጻፈው የት ነው?*

ይህ ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ በ20ኛው ምዕራፉ ላይ የተናገረው ነው፡-

ጌታ ኢየሱስ በደቀ መዛሙርቱ ላይ እፍ አለባቸውና እንዲህ አለ፣ ‹‹መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ። ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው›› (ዮሐንስ 20፡22-23)።

## *በዚህ ቃል መሠረት የምታምነው ምንድን ነው?*

የተጠሩ የክርስቶስ አገልጋዮች እንደ መለኮታዊ ትእዛዝ ሲያገለግሉ በተለይም ንስሐ ያልገባ ኃጢአተኛን ከክርስቲያኖች ማኅበር በግልጽ ሲያስወግዱ እና የሚናዘዘውን የኃጢአት ይቅርታውን ሲያውጁ የተሻለ እንዲያደርግም ሲናገሩ ክርስቶስ ውዱ ጌታችን እርሱ ራሱ ከእኛ ጋር እንደሚያደርገው ሁሉ ይህ በሰማይ እንኳ የተረጋገጠና ተቀባይነት ያለው መሆኑን አምናለሁ።



# የመሰዊያው ቅዱስ ምሥጢር

## እንደ ቤተ ሰብ መሪ ቀለል ባለ መንገድ
## የቤተ ሰቡን አባላት ማስተማር ያስፈልጋል

### *የመሰዊያው ቊርባን ምንድን ነው?*

እኛ ክርስቲያኖች እንድንበላውና እንድንጠጣው በራሱ በክርስቶስ የተመሠረት ህብስትና ወይኑ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ሥጋና ደም ነው።

### *ይህ የተጻፈው የት ነው?*

ቅዱሳን ወንጌላውያን ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ እና ቅዱስ ጳውሎስ ስለዚህ ጽፈዋል፡-

‹‹ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንሥቶ አመሰገነ፣ ቆርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸውና እንዲህ አለ፡- እንካችሁ፣ ብሉ፤ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው። ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት።››

እንደዚሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን ደግሞ አንሥቶ፣ አመስግኖ ሰጣቸውና እንዲህ አለ፣ ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው፤ ስለ ብዙዎች የኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ ነው፣ በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት።››

### *ይህን የመብላት እና የመጠጣት ጥቅም ምንድን ነው?*

‹‹ስለ እናንተ ለኃጢአት ይቅርታ የተሰጠ እና የፈሰሰ›› የሚሉት እነዚህ ቃላት በቅዱስ እራት ውስጥ የኃጢአት ስርየት፣ ሕይወት እና ድነት እንደተሰጠን ያመለክቱናል። ምክንያቱም የኃጢአት ይቅርታ ባለበት ሕይወት እና ድነት አለና ነው።

### *ቁሳዊ መብል እና መጠጥ ይህንን ታላቅ ነገር እንዴት ሊሠራ  ይችላል?*

በርግጥ ይህንን የሚያደርገው መብሉ እና መጠጡ አይደለም፡- ነገር ግን እነዚህ የተጻፉ ቃሎች ‹‹ለኃጢአት ይቅርታ ስለ እናንተ የተሰጠ እና የፈሰሰ›› የሚሉት ቃላት ከቁሳዊ መብል እና መጠጥ ጋር መዋሃዳቸው በቅዱስ ቊርባን ውስጥ ዋና ነገር ነው። ይህንን ቃል ለሚያምን ማንኛውም ሰው ቃሉን በትክክል ‹‹የኃጢአት ይቅርታ›› ይለዋል።

### *ይህንን ቅዱስ እራት ለመቀበል የተገባው ማነው?*

ጾምና አካላዊ ዝግጅቶች ተገቢ የሆኑ ውጫዊ ስልጠናዎች ናቸው። ‹‹ለኃጢአት ይቅርታ ስለ እናንተ የተሰጠ እና የፈሰሰ›› የሚሉትን እነዚህ ቃላቶች የሚያምን ያ ሰው በእውነት የተገባውና የተዘጋጀ ነው።

ነገር ግን ‹‹ስለ እናንተ›› የሚለው ቃል ልቦች ሁሉ እንዲያምኑ ግድ ስለሚል ማንም እነዚህን ቃላት የማያምን ወይም የሚጠራጠር ሰው ያልተገባውና ያልተዘጋጀ ነው።



# ክፍል 2

# የየዕለት ጸሎት

## የቤተ ሰቡ መሪ የቤተ ሰብ አባላቱን ጠዋትና ማታ እንዴት በጸሎት መምራት እንዳለበት

### *የማለዳ ጸሎት*

*በማለዳ ከእንቅልፍ ስትነሳ በቅዱስ መስቀል ምልክት አማትብና እንዲህ በል፡-*

በአብ፣ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም። አሜን።

*ከዚያም ተንበርክከህ ወይም ቆመህ የእምነት መግለጫውን ወይም የጌታን ጸሎት ጸልይ፡ ፡ ከወደድክ ደግሞ የሚከተለውን አጠር ያለ ጸሎት ማድረግ ትችላለህ፡-*

ሰማያዊ አባት ሆይ በተወደደው ልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ሌሊቱን በሙሉ ከማናቸውም አደጋና ከሚጎዳ ነገር ስለጠበቅሽኝ አመሰግንሃለሁ፤ በዚህ ቀን ደግሞ በሥራዬና በሕይወቴ ሁሉ አንተን ደስ እንዳሰኝህ ከኃጢአትና ከማናቸውም ክፋት አድነኝ። እራሴን፣ ነፍሴን፣ ሥጋዬንና ሁሉን ነገር በእጆችህ አስረክባለሁ። የጠላት ሠራዊት በእኔ ላይ ኃይል እንዳይኖረው ቅዱስ መልአክህ ከእኔ ጋር ይሁን። አሜን።

*ዐሥርቱ ትእዛዛትን ወይም የጽሞናህ ጊዜህ እንዳመለከትህ እየዘመርክ በደስታ ወደ ሥራህ ሂድ።*

### *የምሽት ጸሎት*

*በምሽት ወደ አልጋህ ስትሄድ በቅዱስ መስቀል ምልክት አማትብና እንዲህ በል፡-*

በአብ፣ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም። አሜን።

*ከዚያም ተንበርክከህ ወይም ቆመህ የእምነት መግለጫውን ወይም የጌታን ጸሎት ጸልይ፡ ፡ ከወደድክ ደግሞ የሚከተለውን አጠር ያለ ጸሎት ማድረግ ትችላለህ፡-*

ሰማያዊ አባት ሆይ በተወደደው ልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ቀኑን በሙሉ ከማናቸውም አደጋና ከሚጎዳ ነገር በጸጋህ ስለጠበቅሽኝ አመሰግንሃለሁ፤ በቀኑ ውሎዬ የሠራሁትን ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር በለኝ። ሌሊቱንም በቸርነትህ ጠብቀኝ። ነፍሴን፣ ሥጋዬን እና ሁሉን ነገር በእጆችህ አስረክባለሁ። የጠላት ሠራዊት በእኔ ላይ ኃይል እንዳይኖረው ቅዱስ መልአክህ ከእኔ ጋር ይሁን። አሜን።

*ከዚህ በኋላም በደስታ ወደ መኝታህ ሂድ።*

## የቤተ ሰቡ መሪ የቤተ ሰቡን አበላት እንዴት በረከትን እንደሚጠይቁ እና ምስጋና ማቅረብ እንዳለባቸው ማስተማር እንዳለበት

### *በረከትን መጠየቅ*

*ልጆችና የቤተ ሰቡ አባላት ወደ መመገቢያ ጠረጴዛ ሲሄዱ እጃቸውን በማጣመር በቅዱስ ፍርሃት መሆን ይኖርባቸዋል እናም እንዲህ ይበሉ፦*

የሁሉ ዓይን አንተን ተስፋ ያደርጋል አንተም ምግባቸውን በየጊዜው ትሰጣቸዋለህ። አንተ እጅህን ትከፍታለህ፣ ሕይወት ላለውም ሁሉ መልካምን ታጠግባለህ (**መዝሙር** 145፡15-16)።

*ከዚያም የጌታ ጸሎትና የሚከተለው ይጸለይ፦*

ጌታ እግዚአብሔር ሰማያዊ አባታችን ሆይ ከተትረፈረፈው ቸርነትህ የተቀበልነውን ይህን ስጦታህን እና እኛንም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ባርከን። አሜን።

### *ምስጋናን ማቅረብ*

*ከምግብ በኋላም በተመሳሳይ ሁኔታ እጃቸውን አጣምረው በቅዱስ ፍርሃት ሆነው እንዲህ ይበሉ፦*

እግዚአብሔርን አመስግኑ ቸር ነውና፣ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። . . . ለሥጋ ሁሉ ምግብን የሚሰጥ . . . ለሚጠሩት ለቁራዎች ጫጩቶች ለእንስሶችም ምግባቸውን ይሰጣል። የፈረስን ኃይል አይወድድም፣ በሰውም እግሮች አይደሰትም። እግዚአብሔር በሚፈሩት፣ በምሕረቱም በሚታመኑት ይደሰታል (**መዝሙር** 136፡1፣ 25፤ 147፡9-11)።

*ከዚያም የጌታችን ጸሎትና የሚከተለው ጸሎት ይጸለይ፦*

ሰማያዊ አባት ጌታ እግዚአብሔር ሆይ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከአንተ ስለተቀበልነው ሁሉ ካንተ ጋር ሆኖ በሚኖረውና በሚነግሠው በመንፈስ ቅዱስ ለዘላለም ዓለም እናመሰግንሃለን። አሜን።



# ክፍል 3
# የኃላፊነት ዝርዝር

### *አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተለያዩ ቅዱስ ሥርዓቶችና ሥልጣኖች ስላላቸው ተግባራት እና ኃላፊነት ማስጠንቀቂያ የሚሰጡ ናቸው።*

### *ለጳጳሳት፣ ለመጋቢያን እና ለሰባኪዎች*

እንግዲህ ኤጲስ ቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል፤ የማይነቀፍ፣ የአንዲት ሚስት ባል፣ ልከኛ፣ ራሱን የሚገዛ፣ እንደሚገባው የሚሠራ፣ እንግዳ ተቀባይ፣ ለማስተማር የሚበቃ፣ የማይሰክር፣ የማይጨቃጨቅ ነገር ግን ገር የሆነ፣ የማይከራከር፣ ገንዘብን የማይወድ ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር፤ **1ጢሞቴዎስ 3፡2-4**፡፡

በትዕቢት ተነፍቶ በዲያብሎስ ፍርድ እንዳይወድቅ፣ አዲስ ክርስቲያን አይሁን። **1ጢሞቴዎስ 3፡6**

ሕይወት በሚገኝበት ትምህርት ደግሞ ሊመክር ተቃዋሚዎቹንም ሊወቅስ ይችል ዘንድ፣ እንደተማረው በታመነ ቃል ይጽና። **ቲቶ 1፡9**

### *ሰሚዎቹ ለመጋቢዎቻቸው ማድረግ የሚገባቸው*

እንዲሁ ደግሞ ወንጌልን የሚሰብኩ ከወንጌል ቀለብ እንዲቀበሉ ጌታ ደንግጎአል። **1ቆሮንቶስ 9፡14**

ነገር ግን ቃሉን የሚማር ከሚያስተምረው ጋር መልካምን ነገር ሁሉ ይከፋፈል። አትሳቱ፤ እግዚአብሔር አይዘበትበትም። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና። **ገላትያ 6፡6-7**

በመልካም የሚያስተዳድሩ ሽማግሌዎች፣ ይልቁንም በመስበክና በማስተማር የሚደክሙት፣ እጥፍ ክብር ይገባቸዋል። መጽሐፍ፣ ‹‹የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር››፣ ደግሞ ‹‹ለሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋል ይላልና›› **1ጢሞቴዎስ 5፡17-18**

ወንድሞች ሆይ፣ በመካከላችሁ የሚደክሙትን በጌታም የሚገዙአችሁን የሚገሥጹአችሁንም ታውቁ ዘንድ፣ ስለ ሥራቸውም በፍቅር ከመጠን ይልቅ ታከብሩአቸው ዘንድ እንለምናችኋለን። እርስ በርሳችሁ በሰላም ሁኑ። **1ተሰሎንቄ 5፡12-13**

ለዋኖቻችሁ ታዘዙና ተገዙ፤ እነርሱ ስሌትን እንደሚሰጡ አድርገው፣ ይህንኑ በደስታ እንጂ በሐዘን እንዳያደርጉት፣ ይህ የማይጠቅማችሁ ነበርና፣ ስለ ነፍሳችሁ ይተጋሉ። **ዕብራውያን 13፡17**

## *ስለ ሕዝባዊ አስተዳደር*

ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለ ሥልጣኖች ይገዛ። ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉትም ባለ ሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው። ስለዚህ ባለ ሥልጣንን የሚቃወም የእግዚአብሔርን ሥርዓት ይቃወማል፤ የሚቃወሙትም በራሳቸው ላይ ፍርድን ይቀበላሉ። ገዦዎች ለክፉ አድራጊዎች እንጂ መልካም ለሚያደርጉ የሚያስፈሩ አይደሉምና። ባለ ሥልጣንን እንዳትፈራ ትወዳለህን? መልካሙን አድርግ ከእርሱም ምስጋና ይሆንልሃል፤ ለመልካም ነገር ለአንተ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና። በከንቱ ግን ሰይፍ አይታጠቅምና ክፉ ብታደርግ ፍራ፤ቍጣውን ለማሳየት ክፉ አድራጊውን የሚበቀል የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና።**ሮሜ** 13:1-4

## *ስለ ዜጐች*

እንኪያስ የቄሣርን ለቄሣር የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር አስረክቡ አላቸው። **ማቴዎስ** 22:21

ስለዚህ ስለ ቍጣው ብቻ አይደለም ነገር ግን ስለ ሕሊና ደግሞ መገዛት ግድ ነው። ስለዚህ ደግሞ ትገብራላችሁና፤ በዚህ ነገር የሚተጉ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸውና። ለሁሉ የሚገባውን አስረክቡ፤ ግብር ለሚገባው ግብርን፣ ቀረጥ ለሚገባው ቀረጥን፣ መፈራት ለሚገባው መፈራትን፣ ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ። **ሮሜ** 13:5-7

እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነት ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር፣ ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ። ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው። 1**ጢሞቴዎስ** 2: 1-3

ለገዦችና ለባለ ሥልጣኖች የሚገዙና የሚታዘዙ፣ ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጁ፣ ማንንም የማይሰድቡ፣ የማይከራከሩ፣ ገሮች፣ ለሰው ሁሉ የዋህነትን ሁሉ የሚያሳዩ እንዲሆኑ ኣሳስባቸው። **ቲቶ** 3:1

ስለ ጌታ ብላችሁ ለሰው ሥርዓት ሁሉ ተገዙ፤ ለንጉሥም ቢሆን፣ ከሁሉ በላይ ነውና፤ ለመኳንንትም ቢሆን፣ ክፉ የሚያደርጉትን ለመቅጣት በጎም የሚያደርጉትን ለማመስገን ከእርሱ ተልከዋልና ተገዙ። 1**ጴጥሮስ** 2:13-14

## *ለባሎች*

እንዲሁም፣ እናንተ ባሎች ሆይ፣ ደካማ ፍጥረት ስለ ሆኑ ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ፤ ጸሎታችሁ እንዳይከለከል አብረው ደግሞ የሕይወትን ጸጋ እንደሚወርሱ አድርጋችሁ አክብሩአቸው። 1**ጴጥሮስ** 3:7

ባሎች ሆይ፣ ሚስቶቻችሁን ውደዱ መራራም አትሁኑባቸው። **ቈላስይስ** 3:19

## *ለሚስቶች*

ሚስቶች ሆይ፣ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ፤ **ኤፌሶን** 5:22

እንዲህ በቀድሞ ዘመን በእግዚአብሔር ተስፋ ያደረጉት ቅዱሳት ሴቶች ደግሞ ለባሎቻቸው ሲገዙ ተሸልመው ነበርና፤ እንዲሁም ሣራ ለአብርሃም። ጌታ ብላ እየጠራችው ታዘዘችለት፤ እናንተም ከሚያስደነግጥ ነገር አንዳች እንኳ ሳትፈሩ መልካም ብታደርጉ ልጆችዋ ናችሁ። 1**ጴጥሮስ** 3:5-6

### *ለወላጆች*

እናንተም አባቶች ሆይ፣ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሣጽ አሳድጉአቸው እንጂ አታስቆጡአቸው። **ኤፌሶን** 6፡4

### *ለልጆች*

ልጆች ሆይ፣ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ፣ ይህ የሚገባ ነውና። መልካም እንዲሆንልህ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝም አባትህንና እናትህን አክብር፤ እርስዋም የተስፋ ቃል ያላት ፊተኛይቱ ትእዛዝ ናት። **ኤፌሶን** 6፡1-3

### *ለማናቸውም ዓይነት ሠራተኞች*

ባሪያዎች ሆይ፣ ለክርስቶስ እንደምትታዘዙ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ በልባችሁ ቅንነት በሥጋ ጌቶቻችሁ ለሆኑ ታዘዙ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደሚያደርጉ እንደ ክርስቶስ ባሪያዎች እንጂ ለሰው ደስ እንደምታሰኙ ለታይታ የምትገዙ አትሁኑ። ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምትገዙ በትጋትና በበጎ ፈቃድ ተገዙ፤ ባሪያ ቢሆን ወይም ጨዋ ሰው፣ እያንዳንዱ የሚያደርገውን መልካም ነገር ሁሉ ከጌታ በብድራት እንዲቀበለው ታውቃላችሁና። **ኤፌሶን** 6፡5-8

### *ለአሠሪዎች እና ለተቆጣጣሪዎች*

እናንተም ጌቶች ሆይ፣ ዛቻውን ትታችሁ እንዲሁ አድርጉላቸው፣ በእነርሱና በእናንተ ላይ የሚገዛው ጌታ በሰማይ እንዳለ ለሰው ፊትም እንዳያደላ ታውቃላችሁና። **ኤፌሶን** 6፡9

### *ለወጣቶች*

እንዲሁም፣ ጕበዞች ሆይ፣ ለሽማግሌዎች ተገዙ፤ ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ፣ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና፣ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል። እንግዲህ በጊዜው ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከኃይለኛው ከእግዚአብሔር እጅ በታች ራሳችሁን አዋርዱ። **1ጴጥሮስ** 5፡5-6

### *ለመበለቶች*

ብቻዋንም ኖራ በእውነት ባልቴት የምትሆን በእግዚአብሔር ተስፋ ታደርጋለች፣ ሌትና ቀንም በልመና በጸሎትም ጸንታ ትኖራለች፤ ቅምጥሊቱ ግን በሕይወትዋ ሳለች የሞተች ናት። **1ጢሞቴዎስ** 5፡5-6

### *ለሁሉም ሰው*

ትእዛዝ ሁሉ . . . ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ በሚለው ቃል ተጠቅልሎአል። **ሮሜ** 13፡9

. . . ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ. . . ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ። **1ጢሞቴዎስ** 2፡1

*እያንዳንዳችን የእርሱን ትምህርት በጥንቃቄ እንማር*
*የቤተ ሰቡም አባላት በሚገባ ይጠብቀው።*



# ክፍል 4
# የክርስቲያን ጥያቄዎች እና መልሶቻቸው[*]

### ወደ ቅዱስ ቊርባን ለሚቀርቡ ታስቦ በዶክተር ማርቲን ሉተር አማካይነት የተዘጋጀ

ከኑዛዜ እና ከአሥርቱ ትእዛዛት፣ ከእምነት መግለጫ፣ ከጌታ ጸሎት እና ከቅዱስ ጥምቀት እንዲሁም ከቅዱስ ቊርባን  በመቀጠል መጋቢው ወይም ክርስቲያኖች እነዚህን ጥያቄዎች ራሳቸውን ሊጠይቁ ይችላሉ፡-

1. ኃጢአተኛ መሆንህን ታምናለህን?
   አዎን፣ አምናለሁ፡፡ እኔ ኃጢአተኛ ነኝ፡፡
2. ይህንን በምን አወቅህ?
   ልጠብቃቸው ካልቻልኳቸው አሥርቱ ትእዛዛት
3. በኃጢአትህ ተጸጽተሃል?
   አዎን፣ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ስለ ሠራሁ ተጸጽቻለሁ፡፡
4. በኃጢአትህ ምክንያት ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚገባህ ምንድን ነው?
   የእርሱ ቊጣ እና ደስ አለመሰኘት፣ ጊዜያዊ ሞትና ዘላለማዊ ጥፋት፡፡ **ሮሜ 6፡21፣ 23** ተመልከት፡፡
5. ለመዳን ተስፋ ታደርጋለህ?
   አዎን፣ ተስፋዬ ያ ነው፡፡
6. በማን ትታመናለህ?
   በውዱ ጌታዬ በኢየሱስ ክርስቶስ፡፡
7. ክርስቶስ ማነው?
   የእግዚአብሔር ልጅ፣ እውነተኛ አምላክ እና ሰው፡፡
8. ስንት አማልክት አሉ?
   አንድ ብቸኛ፣ ሆኖም በአካል ሦስት ናቸው፤ አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ
9. በክርስቶስ እንድትታመን ያደረገህ እርሱ የሠራልህ ነገር ምንድን ነው?
   ለኃጢአቴ ይቅርታ በመስቀል ላይ ስለ እኔ በመሞት ደሙን አፈሰሰልኝ፡፡
10. አብስ ስላንተ ሞቷል?
    አልሞተም፡፡ አብ እንደ መንፈስ ቅዱስ ሁሉ አምላክ ብቻ ነው፤ ወልድ ግን እውነተኛ አምላክም ሰውም ነው፡፡ ስለ እኔ ደሙን አፍስሶአል፣ ሞቶአልም፡፡

[*] "የክርስቲያን ጥያቄዎች እና መልሶቻቸው" በሉተር እንደ ተዘጋጀ የሚታመን ሲሆን በትንሹ የክርስትና ትምህርት ውስጥ የተካተቱትም በ1551 ነው፡፡

11. ይህንን በምን ተረዳህ?

ከቅዱስ ወንጌላት፣ ቅዱሳን ምሥጢራት ከተመሰረቱበት ቃል፣ ሥጋውንና ደሙን በቅዱስ እራቱ ስወስድ እንደ ቃል ኪዳን ነው።

*12. ይህ ቅዱስ እራቱ የተመሰረተው በምን ቃል ላይ ነው?*

ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንሥቶ አመሰገነ፣ ቆርሶም። ‹‹እንካችሁ ብሉ፤ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት›› አለ።

እንደዚሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን ደግሞ አንሥቶ። ‹‹ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው፤ በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት›› አለ።

*13. እውነተኛው ሥጋ እና ደም በዚህ ቅዱስ እራቱ ውስጥ እንዳለ ታምናለህን?*

አዎን፣ አምናለሁ።

*14. ይህን እንድታምን የሚያደርግህ ምንድን ነው?*

እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው፤ ሁላችሁ ከዚህ ጠጡ፣ ደሜ ነው። የሚለው የክርስቶስ ቃል፡ ።

*15. ሥጋውን በበላንና ደሙን በጠጣን ጊዜ እንዲሁም የድነታችንን መያዣ ቃል ኪዳን በተቀበልን ጊዜ ምን ማድረግ ይኖርብናል?*

በጠጣችሁ ጊዜ ለመታሰቢያዬ አድርጉት ብሎ እንዳስተማረን የደሙን መፍሰስና ሞቱን ማሰብና ማወጅ ይኖርብናል።

*16. ሞቱን ማሰብና ማወጅ ያለብን ምክንያቱ ምንድን ነው?*

በመጀመሪያ ለኃጢአታችን ሙሉ ክፍያ መስጠት የሚችል ሌላ ምንም አይነት ፍጥረት እንደሌለ መረዳት እንድንችል ነው። ክርስቶስ እውነተኛ አምላክ እና ሰው ብቻ ያንን ማድረግ ይችላል። ሁለተኛ ኃጢአት አስፈሪ ነገር መሆኑንም እንድናስተውል እና ጠንካራ አቋም እንዲኖረን ነው። በሦስተኛ ደረጃ በክርስቶስ ብቻ እና በእርሱ ባለን እምነት በመዳናችን እንድንደሰት እና እንድንጽናና ነው።

*17. ለኃጢአትህ ሙሉ ክፍያ ለመስጠት ክርስቶስን ምን አነሳሳው?*

ለአብ፣ ለእኔና ለሌሎች ኃጢአተኞች ያለው ታላቅ ፍቅር፣ ይህም በዮሐንስ 14፤ ሮሜ 5፤ ገላትያ 2 እና ኤፌሶን 5 ላይ ተጽፎ ይገኛል።

*18. በመጨረሻም፣ ወደ ቅዱስ ምሥጢሩ መቅረብ የምትሻው ለምንድን ነው?*

ክርስቶስ ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ ስለ ኃጢአቴ እንደ ሞተ ማመንን እንድለማመድ እንዲሁም እግዚአብሔርን እና ባልንጀራዬን መውደድ እንድማር።

*19. አንድ ክርስቲያን በየጊዜው ቅዱስ ምሥጢሩን እንዲወስድ የሚያበረታታው እና የሚያነሣሣው ነገር ምንድን ነው?*

በመጀመሪያ የክርስቶስ ትእዛዝና ተስፋ ሲሆን፤ ከትእዛዙ፣ ከማበረታታቱና ተስፋ የተነሣ የፍላጎት ግፊት ተሰጥቶታል።

*20. ነገር ግን ስለ ቅዱስ ምሥጢሩ አስፈላጊነት መረዳቱ ባይኖርህ ወይም ምንም አይነት ራብ እና ጥማት ባይኖርህ ምን ታደርጋለህ?*

ለእንደዚህ ዓይነት ሰው ከዚህ የተሻለ ምክር የለውም፤ በመጀመሪያ ሥጋና ደም እንዳለው ለማረጋገጥ ሰውነቱን መዳሰስ አለበት። ከዚያ ግን ቃሉ **በገላትያ** 5 እና **በሮሜ** 7 ያለውን ሊያምን ይገባዋል። በሁለተኛ ደረጃ በዓለም ውስጥ እየኖረ መሆኑን ዙሪያውን በመመልከት ያረጋግጥ እንዲሁም ኃጢአትና ችግር እንዳለ ያስታውስ፤ በቅዱሳት መጽሐፍት **በዮሐንስ** 15-16 **እና 1ዮሐንስ** 2 **እና** 5 **ተጽፏል**።

በሦስተኛም ዲያብሎስም በቀን እና በሌሊት ከውስጥ እና ከውጭ ሰላም በማሳጣት ከሐሰቱና ከነፍሰ ገዳይነቱ ጋር በቅዱሳት መጽሐፍት **በዮሐንስ** 8 **እና** 16፤ **1ጴጥሮስ** 5፤ **ኤፌሶን** 6 **እና 2ጢሞቴዎስ** 2 እንደ ተጻፈ በዙሪያው እንዳለ ያስተውል።

***ማስታወሻ፤*** እነዚህ ጥያቄዎች እና መልሶች የልጆች ጨዋታዎች ሳይሆኑ በታላቅ ጥንቃቄ፣ ዓላማ፣ ብፅዕና እና ትጋት ባላቸው በዶክተር ሉተር ለወጣትም ሆነ ለሽማግሌ ተብሎ የተዘጋጀ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ በገላትያ 6 ላይ እንደ ጻፈው ‹‹አትሳቱ፣ እግዚአብሔር አይዘበትበትም›› በማለት እንደ ጻፈው ለዚህ ጉዳይ ትኩረት መስጠት እና በቁም ነገር ልንመለከተው ይገባል።

## የትንሹ የክርስትና ትምህርት

### ማብራሪያ

---

*የሉተርን ትንሹን የክርስትና ትምህርት ለመረዳትና ለመተግበር ሲባል ከዚህ የሚከተለው ማብራሪያ እንደ ሌሎቹ የጥንት እትሞች በዶክተር ሉተር የተጻፈ አይደለም። ይህ የማብራሪያ ክፍል ግን ሉተራዊነት ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ከሉተር ትንሹ የክርስትና ትምህርት ጋር በመደበኛነት ተጨምረው ይወጡ ነበር። ስለሆነም ይህ ማብራሪያ በአብዛኛው መሠረት ያደረገው የጆን ኮንራድ ዲየትሪች (1575-1639)፣ የካርል ፈርዲናንድ ዊልም ዋልተር (1811 -1887)፣ የሄንሪች ክርስቲያን ሽዋን (1819-1905) እንዲሁም በ1943 በሲኖዶሳዊ ኮሚቴ የተዘጋጀውን የክርስትና ትምህርት ነው።*

---



## መግቢያ

### *1. ክርስትና ምንድን ነው?*

ክርስትና እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት የሚሰጠው ሕይወት እና ድነት ነው።

1. **ዮሐንስ** 14፡6 *እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤* በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።
2. **ዮሐንስ** 17፡3 እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።
3. **የሐዋርያት *ሥራ*** 4፡12 *መዳንም* በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።
4. **የሐዋርያት *ሥራ*** 11፡26 ደቀ *መዛሙርትም መጀመሪያ* በአንጾኪያ ክርስቲያን ተባሉ።
5. **1ኛ ዮሐንስ** 5፡11-12 እግዚአብሔርም የዘላለምን ሕይወት እንደ ሰጠን ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው። ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም።

*ማስታወሻ፡-* ክርስትና በ*መጀመሪያ* ‹‹*መንገድ*›› ይባል ነበር። (**የሐዋርያት *ሥራ*** 9፡2፤ 24፡14፣22)

### *2. ስለ አዳኛችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር እውነት የታወቀው የት ነው?*

ይህ እውነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተብራርቷል፤ ብሉይ ኪዳን፣ የአዳኙን መምጣት ተስፋ ሲሰጥ አዲስ ኪዳን ግን ስለ መጣው አዳኝ ይተርክልናል።

6. ***ዕብራውያን*** 1፡1-2 ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፣ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን።
7. **ሉቃስ** 24፡27 ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ ስለ እርሱ በመጻሕፍት ሁሉ የተጻፈውን ተረጐመላቸው።
8. **ዮሐንስ** 20፡31 ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ታምኑ ዘንድ፣ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፎአል።
9. **ኤፌሶን** 2፡20 [እናንተ] በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፣ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤

10. **1ዮሐንስ** 1፡1-2 ሕይወትም ተገለጠ አይተንማል እንመሰክርማለን፣ ከአብ ዘንድ የነበረውንም ለእኛም የተገለጠውን የዘላለምን ሕይወት እናወራላችኂለን።

### *3. መጽሐፍ ቅዱስን ‹‹ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል›› ብለን የምንጠራው ለምንድን ነው?*

*መጽሐፍ ቅዱስ* ‹‹ቅዱስ የእግዚአብሔር *ቃል*›› የተባለበት ምክንያት እግዚአብሔር *መን*ፈስ ቅዱስ ለተመረጡት ጸሐፊዎቹ የሚጽፉትን *ቃ*ላት (ቃለ እስትንፋሱን) ስለ ሰጣቸው ነው:: ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እና እውነት ከመሆኑም በላይ ስህተት የሌለበት (ስሕተት አልባ) ነው።

11. **ዮሐንስ** 10፡35 *መጽሐፉ* ሊሻር አይቻልምና።
12. **ማርቆስ** 8፡38 እኔ በአባቴ ዘንድ ያየሁትን እናገራለሁ፤ እናንተም ደግሞ በአባታችሁ ዘንድ ያያችሁትን ታደርጋላችሁ።
13. **ዮሐንስ** 14፡26 አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኂችሁን ሁሉ ያሳስባችኂል።
14. **የሐዋርያት *ሥራ*** 24፡14 ነገር ግን ይህን እመሰክርልሃለሁ፤ በሕጉ ያለውን በነቢያትም የተጻፉትን ሁሉ አምኜ የአባቶቼን አምላክ እነርሱ ኑፋቄ ብለው እንደሚጠሩት መንገድ አመልካለሁ።
15. **2ጢሞቴዎስ** 3፡16-17 የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ *ሥራ* ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።
16. **2ጴጥሮስ** 1፡21 ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፣ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።

*ማስታወሻ፡-* እግዚአብሔር ብሉይ ኪዳንን በእብራይስጥ እና በአረማይክ አዲስ ኪዳንን ደግሞ በግሪክ ሰጥቷል። ትርጉሞቹን በመገልበጥ ጊዜ የሚፈጠር ስህተት የእግዚአብሔር እስትንፋስ (የቃሉ መገለጥ) አካል አይደለም።

### *4. መጽሐፍ ቅዱስን በትክክል ለመረዳት ቁልፉ ምንድን ነው?*

ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የዓለም አዳኝ የቃሉ ማዕከል እና ልብ ስለሆነ የቃሉን እውነተኛ ትርጉም ለመረዳት ቁልፉ ኢየሱስ ነው።

17. **ዮሐንስ** 5፡39 እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኂልና እነርሱን ትመረምራላችሁ፤ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው።
18. **የሐዋርያት *ሥራ*** 10፡43 በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኃጢአቱን ስርየት እንዲቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል።
19. **ዮሐንስ** 1፡18 *መቼም* ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፤ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው።
20. **2ጢሞቴዎስ** 3፡15 ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፣ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን አውቀሃል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ፡- ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቃል ማዕከል መሆኑን በራሱ ተብራርቷል (**ሉቃስ** 24፡13-27)

***5. የሰው አመክንዮ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቃል ለመረዳት እንዴት ይጠቅማል?***

*ሀ. ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል በሰዋዊ ቋንቋ የተሰጠ ነው። ዐሳቡን ለመረዳት የቋንቋውን ሕግጋት ማለትም ሰዋሰዉን እና አመክንዮን መተግበር ያስፈልገናል። እንደ ቃሉ አገልጋይ አመክንዮን መጠቀም ያስፈልጋል፤ ሆኖም ግን የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ለትክክለኛ መረዳት አስፈላጊ ነው።*

21. ***መዝሙር*** 119:73 *እጆችህ ሠሩኝ አበጃጁኝም እንዳስተውል አድርገኝ፣ ትእዛዛትህንም እማራለሁ።*
22. ***ማቴዎስ*** 13:19 *የመንግሥትን ቃል ሰምቶ በማያስተውል ሁሉ፣ ክፉው ይመጣል፣ በልቡ የተዘራውንም ይነጥቃል፤ በመንገድ ዳር የተዘራው ይህ ነው።*
23. ***ማቴዎስ*** 22:37 *ኢየሱስም እንዲህ አለው፦ ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም ዐሳብህም ውደድ።*
24. ***የሐዋርያት ሥራ*** 17:11 *እነዚህም በተሰሎንቄ ከሚኖሩት ይልቅ ልበ ሰፊዎች ነበሩና። ነገሩ እንደዚሁ ይሆንን? ብለው ዕለት ዕለት መጻሕፍትን እየመረመሩ ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ።*

*ለ. ከሌሎች መጻሕፍት በተለየ ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እና እውነት ነው። የተቀደሰውን ቃል ጥያቄ ውስጥ መጣልም ሆነ ያለመቀበል ስሕተት ነው (ለምሳሌ፡- በታሪካዊ ትችት እንደሚሆነው)*

25. **ሮሜ** 3:4 *እንዲህ አይሁን፤ ‹‹በቃልህ ትጸድቅ ዘንድ ወደ ፍርድ በገባህም ጊዜ ትረታ ዘንድ›› ተብሎ እንደ ተጻፈ፣ ሰው ሁሉ ውሸተኛ ከሆነ እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን።*
26. **2ቆሮንቶስ** 10:5 *የሰውንም ዐሳብ በእግዚአብሔርም እውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን።*
27. **ቈላስይስ** 2:8 *በፍልስፍና በከንቱም መታለል ማንም እንዳይማርካችሁ ተጠበቁ።*
28. **2ጴጥሮስ** 3:15-16 *በአንድ አካልም የተጠራችሁለት ደግሞ የክርስቶስ ሰላም በልባችሁ ይግዛ። የምታመሰግኑም ሁኑ። የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ። በጥበብ ሁሉ እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገሥጹ። በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ።*

    *ማስታወሻ፡-* **1ቆሮንቶስ** 1 *እና* 2 *ተመልከት።*

***6. መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት ልብ ልንለው የሚገባ መሠረታዊ ልዩነት ምንድን ነው?***

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘውን ሕግና ወንጌል በትክክል መለየት አለብን።

29. **ዮሐንስ** 1:17 *ሕግ በሙሴ ተሰጥቶ ነበርና፤ ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ።*
30. **2ቆሮንቶስ** 3:6 *ፊደል ይገድላልና መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል።*

***7. እግዚአብሔር በሕግ ውስጥ የሚያስተምረንና የሚያደርገው ምንድን ነው?***

በሕግ ውስጥ እግዚአብሔር የሚያዘው የመልካም *ሥራ* ዐሳቦችን፣ *ቃልንና* ተግባርን እንዲሁም *ኃጢአትን* ይኮንናል፣ ይቀጣልም።

31. ***ማርቆስ*** 12:30-31 *አንተም በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ዐሳብህ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ … ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ።*
32. **ዮሐንስ** 5:45 *የሚከሳችሁ አለ፤ እርሱም ተስፋ የምታደርጉት ሙሴ ነው።*
33. **ሮሜ** 3: 20 *ኃጢአት በሕግ ይታወቃልና።*

***8. እግዚአብሔር በወንጌል የሚያስተምረውና የሚሠራው ምንድን ነው?***

እግዚአብሔር በወንጌል በኢየሱስ ክርስቶስ የድነታችን የምሥራች፣ የኃጢአት ይቅርታ፣ እምነትን፣ ሕይወትንና በመልካም *ሥራ* እርሱን የማስደሰት ኃይል ይሰጣል።

34. **ዮሐንስ** 3፡16 በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።

35. **ዮሐንስ** 6፡63 ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው፤ ሥጋ ምንም አይጠቅምም፤ እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው ሕይወትም ነው።

36. **ሮሜ** 1፡16 በወንጌል አላፍርምና፤ አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው፣ ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና።

37. **ቈላስይስ** 1፡6 ይህም በዓለም ሁሉ ደግሞ እንዳለ ወደ እናንተ ደርሶአል፣ የእግዚአብሔርንም ጸጋ በእውነት ከሰማችሁበትና ካወቃችሁበት ቀን ጀምሮ፣ በእናንተ ደግሞ እንዳለ እንዲሁ በዓለም ፍሬ ያፈራል ያድግማል።

## *9. ትንሹ የክርስትና ትምህርት የክርስትና መሠረተ እምነትን እንዴት ያጠቃልለዋል?*

ትንሹ የክርስትና ትምህርት የክርስትና መሠረተ እምነት በስድስት ዋና ዋና ክፍሎች ያጠቃልለዋል፤ እነርሱም፡- አሥርቱ ትእዛዛት፣ የእምነት መግለጫ፣ የጌታ ጸሎት፣ ቅዱስ ጥምቀት፣ ኑዛዜ እና የመሠዊያው ቅዱስ ምሥጢር ናቸው።

## *10. የክርስትና ትምህርት ምንድን ነው?*

የክርስትና ትምህርት  የመመሪያ መጽሐፍ ሲሆን ጥያቄዎችንና መልሶችን የያዘ ነው።

*ማስታወሻ፡-* ከክርስትና ትምህርት ጋር የሚዛመደው ቃል ካቴኩዩመን (ተማሪ) የሚለው ነው።

## *11. ትንሹን የክርስትና ትምህርታችንን የጻፈው ማነው?*

የቤተ ክርስቲያን አዳሽ የሆነው ማርቲን ሉተር ሲሆን ጊዜውም 1529 ነው።

## *12. የትንሹ የክርስትና ትምህርት ስድስት ዋና ዋና ክፍሎች ከመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ የተወሰዱበት ምክንያት ምንድን ነው?*

የትንሹ የክርስትና ትምህርት ዋና ዋና ክፍሎች የተወሰዱት ከመጽሐፍ ቅዱስ ሲሆን ምክንያቱ ደግሞ የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ብቸኛው የክርስትና እምነት እና ሕይወት የመጨረሻው ባለሥልጣን በመሆኑ ነው።

‹‹የነቢያትን እና የሐዋርያትን ቃል ማለትም ብሉይ እና አዲስ ኪዳንን ንጹሕ፣ ኩልል ያለ የእስራኤል ምንጭ መሆኑን በሙሉ ልባችን እንቀበላለን። የትኞቹም መመህራን ሆነ አስተምህሮ የመመዘኛ መስፈርታችንም ነው። . . .

‹‹እኛም . . . በአንድ ልብ ይህን የተረጋገጠ ከእግዚአብሔር ቃል የተቀዳ የጋራ አስተምህሮ የምንቀበል ሲሆን፣ ሁሉም ጽሑፎች የተረጋገጡ እና ተቀባይነት ያላቸው ናቸው።›› (የስምምነቱ መመሪያ ኤስ ዲ ሕግ እና ደንብ 3፣10)

38. **ማቴዎስ** 15፡9 የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል ብሎ በእውነት ትንቢት ተናገረ።

39. **ገላትያ** 1፡8 ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፣ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፣ የተረገመ ይሁን።



## ዐሥርቱ ትእዛዛት

### *13. ዐሥርቱ ትእዛዛት ምንድን ናቸው?*

ዐሥርቱ ትእዛዛት የእግዚአብሔር ሕግ ናቸው።

*ማስታወሻ፦* እግዚአብሔር ትእዛዛቱን በዚህ *ሥርዓት* ሰጥቶአል፤ *ነገር ግን* በቍጥር አላስቀመጣቸውም (**ዘዳግም** 5፡6-21፤ **ዘጸአት** 20፡1-17)።

### *14. እግዚአብሔር ሕግጋቱን እንዴት ሰጠ?*

እግዚአብሔር ሕዝቡን ሲፈጥር ሕጉን በልባቸው ላይ ይጽፋል። በኋላም ዐሥርቱን ትእዛዛት በሁለት ጽላቶች ጻፋቸው በሙሴም በኩል አሳወቃቸው።

40. **ሮሜ** 2፡14-15 ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፣ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፣ የተረገመ ይሁን። እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው፣ ዐሳባቸውም እርስ በርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ፦* እግዚአብሔር ትእዛዛቱን የጻፈው በቀጥታ ለእስራኤላዊያን ነው (**ዘጸአት** 19፡19-20፤ 31፡18)። በመጽሐፍ ቅዱስ፣ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሦስት አይነት ሕግጋት አሉ፤ የሥነ ምግባር ሕግ፣ ለሰዎች ሁሉ ከእግዚአብሔር እና ከሰዎች ጋር የሚኖራቸውን ግኙነት የሚናገር፤ ሥርዓታዊ ሕግ፣ በብሉይ ኪዳን ያሉትን ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች የሚቆጣጠር እና ፖለቲካዊ ሕግ፣ እስራኤል እንደ አገር የሚተዳደርበት ሕግ። የሥነ ምግባር ሕግ ብቻ ግን በልብ ላይ የተጻፈ ነው።

### *15. ከ 1-3 ያሉት የትእዛዛቱ ማጠቃለያ (የመጀመሪያው ጽላት)*

ኢየሱስም እንዲህ አለው፦ ‹‹ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም ዐሳብህም ውደድ።›› (**ማቴዎስ** 22፡37፤ **ዘዳግም** 6፡5 ተመልከት)

### *16. ከ4-10 ያሉት የትእዛዛቱ ማጠቃለያ (ሁለተኛው ጽላት)*

‹‹ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች፣ እርስዋም፦ ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት።›› (**ማቴዎስ** 22፡39፤ **ዘሌዋውያን** 19፡ 18 ተመልከት)

### *17. የትእዛዛቱ ሁሉ ማጠቃለያ ምንድን ነው?*

ፍቅር የትእዛዛቱ ሁሉ ማጠቃለያ ነው።

41. **ሮሜ** 13፡10 ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም፤ ስለዚህ ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው።

*18. እግዚአብሔር በዐሥርቱ ትእዛዛት ውስጥ ‹‹እናንተ ይህን አድርጉ!›› ሲል ማንን ማለቱ ነው?*

እኔን እና የሰው ዘርን ማለት ነው፡፡

42. **ማቴዎስ** 5፡19 እንግዲህ ከእነዚህ ከሁሉ ካነሱት ትእዛዛት አንዲቱን የሚሽር ለሰውም እንዲሁ የሚያስተምር ማንም ሰው በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ ታናሽ ይባላል፤ የሚያደርግ ግን የሚያስተምርም ማንም ቢሆን እርሱ በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይባላል፡፡
43. **ሮሜ** 3፡19 እንግዲህ ከእነዚህ ከሁሉ ካነሱት ትእዛዛት አንዲቱን የሚሽር ለሰውም እንዲሁ የሚያስተምር ማንም ሰው በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ ታናሽ ይባላል፤ የሚያደርግ ግን የሚያስተምርም ማንም ቢሆን እርሱ በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይባላል፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ-* ኢየሱስ የእነዚህን ትእዛዛት ትርጉም በሚገባ አብራርቷል (**ማቴዎስ** 5)

> ***የመጀመሪያው ትእዛዝ***
>
> ***[እግዚአብሔር]***
> ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይኑሩህ፡፡
> *ይህ ምን ማለት ነው?* እግዚአብሔርን ልንፈራ፣ ልንወድድ እንዲሁም ከምንም ነገር በላይ ልንታመነው ይገባል፡፡

*19. ብቸኛው እውነተኛ አምላክ ማነው?*

እውነተኛው አምላክ ሥላሴ ነው፤ አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ፣ ሦስት አካላት በአንድ መለኮት (ቅድስት ሥላሴ)

44. **ዘኍልቁ** 6፡24-26 እግዚአብሔር ይባርክህ፣ ይጠብቅህም፤ እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልህ፣ ይራራልህም፣ እግዚአብሔር ፊቱን ወደ አንተ ያንሣ፣ ሰላምንም ይስጥህ፡፡
45. **ዘዳግም** 6፡4 እስራኤል ሆይ፣ ስማ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው፡፡
46. **ማቴዎስ** 28፡19 እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፣ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፡፡
47. **1ቆሮንቶስ** 8፡4 ከአንዱም በቀር ማንም አምላክ እንደሌለ እናውቃለን፡፡
48. **2ቆሮንቶስ** 13፡14 የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔርም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን፡፡ አሜን፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ-* ኢየሱስ በዮርዳኖስ በተጠመቀበት ጊዜ አብ ከሰማይ መሰከረለት መንፈስ ቅዱስም በርግብ መልክ ወረደበት (**ማቴዎስ** 3፡16-17)፡፡

*20. እግዚአብሔር በመጀመሪያው ትእዛዝ የሚከለክለው ነገር ምንድን ነው?*

እግዚአብሔር ሌሎች አማልክት እንዲኖሩን (አመንዝራነትን) አይፈቅድም፡፡

49. **ኢሳይያስ** 42፡8 እኔ እግዚአብሔር ነኝ ስሜ ይህ ነው ክብሬን ለሌላ፣ ምስጋናዬንም ለተቀረጹ ምስሎች አልሰጥም።
50. ***ማቴዎ*ስ** 4፡10 *ያን ጊዜ ኢየሱስ፦ ሂድ፣ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም* ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአልና አለው።
51. **1ቆሮንቶስ** 8፡4 ጣዖት ሁሉ በዓለም ከንቱ እንደ ሆነ ከአንዱም በቀር ማንም አምላክ እንደሌለ እናውቃለን።
52. **1ዮሐንስ** 5፡21 ልጆች ሆይ፣ ከጣዖታት ራሳችሁን ጠብቁ።

*21. ሰዎች ሌሎች አማልክት የሚኖራቸው መቼ ነው?*

ሌሎች አማልክት የሚኖራቸው፤

*ሀ. ማንኛውንም ፍጥረት እንደ አምላክ ሲቆጥሩት እና ሲያመልኩት ነው፤*

53. ***መዝሙ*ር** 115፡4 የአሕዛብ ጣዖታቶች የወርቅና የብር፣ የሰው እጅ *ሥራ* ናቸው።
54. **ፊልጵስዩስ** 3፡19 *መጨረሻቸው ጥፋት ነው፣ ሆዳቸው አምላካቸው ነው፣* ክብራቸው በነውራቸው ነው፣ ዐባቸው ምድራዊ ነው።
55. **ራእይ** 9፡20 በእነዚህም *መቅሠፍቶች ያልተገደሉት* የቀሩቱ ሰዎች ለአጋንንትና ያዩ ወይም ይሰሙ ወይም ይሄዱ ዘንድ ለማይችሉ ከወርቅና ከብር ከናስም ከድንጋይም ከእንጨትም ለተሠሩ ለጣዖቶች እንዳይሰግዱ ስለ እጃቸው *ሥራ* ንስሐ አልገቡም።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ-* እስራኤል የወርቅ ጥጃ አመለከ (**ዘጸአት** 32)። ሕዝቡ ባኦልን አመለከ (**1*ነገሥ*ት** 18፡18-29)። ፍልስጤማዊያን ዳጎንን አምላካቸው አደረጉት (***መ*ሳፍንት** 16፡ 23-24)።

ለ. ሰዎች *ሥ*ሉስ በሆነው አምላክ ሳያምኑ ሲቀሩ (የሐዋርያት የእምነት መግለጫ ተመልከት)።

56. **ማቴዎስ** 28፡19 እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፣ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው።
57. **ዮሐንስ** 5፡23 ወልድን የማያከብር የላከውን አብን አያከብርም።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ፦* የኢየሱስ ጥምቀት (**ማቴዎስ** 3፡13-17)።

ሐ. የሰው ልጆች እግዚአብሔርን ብቻ መፍራት፣ መውደድ እና መታመን ሲገባቸው ሌላ ማንኛውንም ሰው ሲፈሩ፣ ሲወዱ ወይም ሲታመኑ፤

58. ***መዝሙ*ር** 14፡1 ሰነፍ በልቡ፤ አምላክ የለም ይላል። በ*ሥራ*ቸው ረከሱ፣ ጐሰቈሉ በጎ ነገርን የሚሠራ የለም።
59. **ምሳሌ** 11፡28 በባለጠግነቱ የሚተማመን ሰው ይወድቃል።
60. **ምሳሌ** 3፡5 በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር *ታመን*፣ በራስህም ማስተዋል አትደገፍ።
61. **ማቴዎስ** 10፡28 *ሥጋንም* የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ፤ ይልቅስ ነፍስንም *ሥጋንም* በገሃነም ሊያጠፉ የሚቻለውን ፍሩ።
62. **ማቴዎስ** 10፡37 ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤ ከእኔ ይልቅም ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም።

63. **ኤፌሶን** 5፡5 ይህን እወቁ፤ አመንዝራም ቢሆን ወይም ርኵስ ወይም የሚመኝ እርሱም ጣዖትን የሚያመልክ በክርስቶስና በእግዚአብሔር መንግሥት ርስት የለውም።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ*፡- ባለጸጋው ሰው ከእግዚአብሔር ይልቅ ስለ ውድ ልብሶች እና ስለ ጥሩ ምግቦች ያስብ ነበር (**ሉቃስ** 16፡19-31)። የባቢሎንን ግንብ የገነቡ ሰዎች ከእግዚአብሔር ይልቅ ያስመዘገቡት ስኬት የበለጠ አስፈላጊ መስሎ ታያቸው (**ዘፍጥረት** 11፡1-9)። ጎልያድ በአካላዊ ግዝፈቱ እና ጉልበቱ ታመነ (1**ሳሙኤል** 17)። ኤሊ ከእግዚአብሔር ይልቅ ልጆቹን አከበረ (1**ሳሙኤል** 2፡12-34)። ጴጥሮስ እግዚአብሔርን ከመውደድ ይልቅ መከራን ፈራ (**ማቴዎስ** 26፡69-75)።

*መ. ሰዎች ሥሉስ የሆነውን አምላክ ከማያመልክ ከሌላ ሰው ጋር ለማምለክ ሲጠመዱ፤*

64. **2ቆሮንቶስ** 6፡14-15 ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ፤ ጽድቅ ከዓመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው? ክርስቶስስ ከቤልሆር ጋር ምን መስማማት አለው? ወይስ የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው?

## *22. እግዚአብሔር በመጀመሪያው ትእዛዝ መሠረት ከእኛ የሚጠብቀው ምንድን ነው?*

እግዚአብሔር ከምንም ነገር በላይ እንድንፈራው፣ እንድንወደው እና እንድንታመነው ይፈልግብናል።

*ሀ.* እግዚአብሔርን ከማንኛውም ነገር አብልጠን መፍራት ስንል እርሱ ብቻ ከፍ ያለ ልዑል መሆኑን አውቀን ጥልቅ አክብሮት ሲኖረን፣ በኑሮዋችን ስናከብረው እና ደስ የማያሰኘውን ስናስወግድ ነው።

65. **ዘፍጥረት** 17፡1 እኔ ኤልሻዳይ ነኝ በፊቴ ተመላለስ፣ ፍጹምም ሁን።

66. **መዝሙር** 33፡8 ምድር ሁሉ እግዚአብሔርን ትፍራው፣ በዓለም የሚኖሩ ሁሉም ከእርሱ የተነሣ ይደንግጡ።

67. **መዝሙር** 96፡4 እግዚአብሔር ታላቅ ምስጋናውም ብዙ ነውና፣ በአማልክትም ሁሉ ላይ የተፈራ ነውና።

68. **ምሳሌ** 8፡13 እግዚአብሔርን መፍራት ክፋትን ይጠላል።

69. **ማቴዎስ** 10፡28 ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ፤ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ*፡- ሦስቱ ሰዎች ከንጉሡ እቶን እሳት ይልቅ እግዚአብሔርን ፈሩ (**ዳንኤል** 3)።

ለ. እግዚአብሔርን ከማናቸውም ነገር አብልጠን ስንወደው ከእርሱ ከአምላካችን ጋር ብቻ በመጣበቅ መላው ሕይወታችን ለእርሱ አገልግሎት ሲውል ነው።

70. **መዝሙር** 73፡25-26 በሰማይ ያለኝ ምንድር ነው? በምድርስ ውስጥ ከአንተ ዘንድ ምን እሻለሁ? የልቤ አምላክ ሆይ፣ ልቤና ሥጋዬ አለቀ እግዚአብሔር ግን ለዘላለም እድል ፈንታዬ ነው።

71. **ማቴዎስ** 22፡37 ኢየሱስም እንዲህ አለው፦ ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም ዐሳብህም ውደድ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ-* አብርሃም ከገዛ ልጁ ይልቅ እግዚአብሔር አምላኩን ወደደ (**ዘፍጥረት** 22)፡፡ ዮሴፍ ከጲጢፋራ ሚስት የቀረበለትን ፈተና መቋቋም ቻለ (**ዘፍጥረት** 39)፡፡

ሐ. ሕይወታችንን በምንምራበት ጊዜ ሙሉ በሙሉ በእርሱ ጥበቃና በእርሱ እርዳታ በሚያስፈልገን ሁሉ ከሁሉ በላይ በእግዚአብሔር እንደገፋለን፡፡

72. **መዝሙር** 118፡8 በሰው ከመታመን ይልቅ በእግዚአብሔር መታመን ይሻላል፡፡

73. **ምሳሌ** 3፡5 በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፣ በራስህም ማስተዋል አትደገፍ፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ-* ዳዊት ከጎልያድ ጋር ሲጋጠም እግዚአብሔርን ታምኖ ነበር (1**ሳሙኤል** 17፡37፣ 46-47)፡፡ አብራም እግዚአብሔር ጥበቃ እንደሚያደርግለት በመተማመን የገዛ አገሩንና ዘመዶቹን ትቶ እግዚአብሔር ወዳሳየው ምድር ወጣ (**ዘፍጥረት** 12፡1-9)፡፡ ዳንኤል ራሱን ለእግዚአብሔር ጥበቃ አሳልፎ ሰጠ (**ዳንኤል** 6)፡፡

### *23. ይህንን እና ሌሎቹን ትእዛዛት ሊጠብቅ የሚችል ማነው?*

ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር እነዚህን ትእዛዛት ሁሉ በፍጽምና መጠበቅ የሚችል ማንም የለም፡፡ በእርሱ የሚታመኑትም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ትእዛዛቱን ለመጠበቅ ይጋደላሉ፡፡

74. **መክብብ** 7፡20 በምድር ላይ መልካምን የሚሠራ ኃጢአትንም የማያደርግ ጻድቅ አይገኝምና፡፡

75. 1ኛ **ዮሐንስ** 1፡8 ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፣ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም፡፡

76. **ዮሐንስ** 14፡15 ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ፡፡

77. **ፊልጵስዩስ** 2፡13 ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና፡፡

### *ሁለተኛው ትእዛዝ*

***[የእግዚአብሔር ስም]***

የአምላክህን የእግዚአብሔር ስም በከንቱ አትጥራ፡፡

*ይህ ምን ማለት ነው?* እግዚአብሔርን ልንፈራ እና ልንወድ እንጂ በስሙ ልንራገም፣ ልንምል፣ ለሰይጣናዊ አስማቶች ልናውለው፣ ልንዋሽበት፣ ልናታልልበት አይገባም፤ ይልቁንስ በችግራችን ጊዜ ልንጠራው፣ ልንጸልይ፣ ልንወድሰው እና ልናመሰግነው ያስፈልጋል፡፡

### *24. በዚህ እና በሌሎቹም ትእዛዛት ‹‹እግዚአብሔርን መፍራት እና መውደድ›› አለብን ስንል ምን ማለታችን ነው?*

የትእዛዛት ሁሉ ፍጻሜ እግዚአብሔርን ከመፍራት እና ከመውደድ መመንጨት አለበት፡፡

78. **መዝሙር** 111፡10 የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፣ ለሚያደርጓትም ሁሉ ደኅና ማስተዋል አላቸው ምስጋናውም ለዘላለም ይኖራል፡፡

79. **ዮሐንስ** 14፡23 የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ-* ኢየሱስ ጴጥሮስን ይወደው እንደሆን ከጠየቀው በኋላ በጎቹን እንዲጠብቅ አሳሰበው (**ዮሐንስ** 21፡15-17)፡፡

### *25. የእግዚአብሔር ስም ምንድን ነው?*

እግዚአብሔር፣ ራሱን ለእኛ እየገለጠልን ያለው፣ ማንነቱንና ባሕርያቱን ነው።

80. **ዘጸአት** 3፡14 እግዚአብሔርም ሙሴን፦ «ያለና የሚኖር» እኔ ነኝ አለው፤ እንዲህ ለእስራኤል ልጆች። «ያለና የሚኖር» ወደ እናንተ ላከኝ ትላለህ አለው።
81. **ኢሳይያስ** 9፡6 ሕፃን ተወልዶልናልና፣ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።
82. **ኤርምያስ** 23፡6 በዘመኑም ይሁዳ ይድናል እስራኤልም ተዘልሎ ይቀመጣል፣ የሚጠራበትም ስም፦ እግዚአብሔር ጽድቃችን ተብሎ ነው።
83. **ማቴዎስ** 1፡21 ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ።
84. **ማቴዎስ** 18፡20 ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና።
85. **ማቴዎስ** 28፡19 እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፣ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው።
86. **ዮሐንስ** 1፡1 በመጀመሪያው ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፣ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ*- እግዚአብሔር ስሙን ለሙሴ ገለጠ (**ዘጸአት** 3፡12-15)።

### *26. እግዚአብሔር በሁለተኛው ትእዛዝ ላይ የሚከለክለን ነገር ምንድን ነው?*

በሁለተኛው ትእዛዝ ላይ እግዚአብሔር የሚከለክለን ስሙን ያለአግባብ እንዳንጠቀም ነው።

87. **ዘጸአት** 20፡7 እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና።

### *27. የእግዚአብሔር ስም ያላግባብ ጥቅም ላይ የሚውለው እንዴት ነው?*

የእግዚአብሔር ስም ሰዎች ያለ አግባብ የሚጠቀሙት፦

ሀ. የእግዚአብሔር ስም ያለአግባብ በቸልተኝነት ሲጠራ (**ዘጸአት** 20፡7 **ተመልከት**)።

ለ. በስሙ ስንራገም፣ ስንምል፣ ለሰይጣናዊ አስማቶች ስናውለው፣ ስንዋሽበት ወይም ስናታልልበት ነው።

### *28. በስሙ መራገም ማለት ምን ማለት ነው?*

በእግዚአብሔር ስም መራገም ማለት፦

ሀ. ስለ እርሱ ክፉ በመናገር እግዚአብሔርን መስደብ ወይም በእርሱ ላይ መዘበት ነው፤

88. **ዘሌዋውያን** 24፡15 ማናቸውም ሰው አምላኩን ቢሰድብ ኃጢአቱን ይሸከማል።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ*- ኢየሱስ በመስቀል ላይ በዋለበት ጊዜ ዘበቱበት (**ማቴዎስ** 27፡39-43)። የሶርያ የጦር አለቃ የእስራኤልን አምላክ ተሳደበ (**2ነገሥት** 18፡28-35፤ 19፡21-22)። ጥቂት አይሁዳውያን ኢየሱስን አጋንንት አለብህ አሉት (**ዮሐንስ** 8፡48-49)።

ለ. በሆነ ሰው ላይ ወይም ቁስ ላይ የእግዚአብሔር ቊጣ እና ቅጣት እንዲፈስ መጥራት፤

89. ***ያዕቆብ*** 3፡9-10 በእርሱ ጌታንና አብን እንባርካለን፤ በእርሱም እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠሩትን ሰዎች እንረግማለን፤ ከአንድ አፍ በረከትና መርገም ይወጣሉ። ወንድሞቼ ሆይ፣ ይህ እንዲህ ሊሆን አይገባም።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ-* ኢየሱስ ለፍርድ በቀረበበት ጊዜ የነበሩት ሰዎች ራሳቸውንና ልጆቻቸውን *ረገሙ* (**ማቴዎስ** 27፡25)። ጴጥሮስ *ተራገመ* (**ማቴዎስ** 26፡74)። *ያዕቆብ* እና ዮሐንስ የሰማሪያ ሰዎችን እግዚአብሔር በእሳት እንዲያጠፋቸው ለመኑ (**ሉቃስ** 9፡51-55)።

### 29. *በእግዚአብሔር ስም መማል ማለት ምንድን ነው?*

በእግዚአብሔር ስም መማል ማለት እውነተኛ ምስክርነትን ለመስጠት የምንናገረው ወይም ቃል የምንገባው ሲሆን ከዋሸንና ቃላችንን ካፈረስን ግን ቅጣትን የምንቀበልበት ነው።

### *30. በእግዚአብሔር ስም እንድንምል የተፈቀደልንና የሚያስፈልገን ጊዜ መቼ ነው?*

ለእግዚአብሔር ክብር የሚሆን ሲሆን እና ለባልንጀራችን ጥቅም በእግዚአብሔር ስም መሐላ ለማድረግ ተፈቅዶልናል ደግሞም ተገቢ ነው። ለዚህ ለምሳሌነት የሚቀርቡትም የፍርድ ቤት ምስክርነት፣ ኃላፊነት ላለበት ሥራ የምንገባው መሐላ እና የጋብቻ ቃል ኪዳን ናቸው።

90. **ሮሜ** 13፡1 ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለ ሥልጣኖች ይገዛ።

91. **ዘኍልቁ** 30፡2 ሰው ለእግዚአብሔር ስእለት ቢሳል፣ ወይም ራሱ በመሐላ ቢያስር፣ ቃሉን አይስበር ከአፉ እንደ ወጣው ሁሉ ያድርግ።

92. **ዘዳግም** 6፡13 አምላክህን እግዚአብሔርን ፍራ እርሱንም አምልክ በስሙም ማል።

93. ***ዕብራውያን*** 6፡16 ሰዎች ከእነርሱ በሚበልጠው ይምላሉና፣ ለማስረዳትም የሆነው መሐላ የሙግት ሁሉ ፍጻሜ ይሆናል።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ-* ኢየሱስ ለመሐላ ራሱን አስገዝቷል (**ማቴዎስ** 26፡63-64)። አብርሃም ሎሌውን አምሎታል (**ዘፍጥረት** 24፡3)።

### *31. መሐላ የተከለከለው መቼ ነው?*

*መሐላ* የተከለከለው በሐሰት፣ *ያለማስተዋል*፣ ወይም *ለኃጢአት*፣ ላልተረጋገጠ ነገር ወይም ለማያስፈልግ ጉዳይ ሲውል ነው።

94. **ዘሌዋውያን** 19፡12 በስሜም በሐሰት አትማሉ፣ የአምላካችሁንም ስም አታርክሱ እኔ እግዚአብሔር ነኝ።

95. ***ማቴዎስ*** 5፡33-37 *ደግሞ ለቀደሙት፡- በውሸት አትማል ነገር ግን መሐላዎችህን ለጌታ* ስጥ እንደተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ። ከቶ አትማሉ፤ በሰማይ አይሆንም የእግዚአብሔር ዙፋን ነውና፤ በምድርም አይሆንም የእግሩ መረገጫ ናትና፤ በኢየሩሳሌምም አይሆንም የታላቁ ንጉሥ ከተማ ናትና፤ በራስህም አትማል፣ አንዲቱን ጠጉር ነጭ ወይም ጥቁር ልታደርግ አትችልምና። ነገር ግን ቃላችሁ አዎን አዎን ወይም አይደለም አይደለም ይሁን፤ ከእነዚህም የወጣ ከክፉው ነው።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ-* ጴጥሮስ በሐሰት ማለ እናም የሐሰት ምስክርነት ሰጠ (**ማቴዎስ** 26፡72)። የተወሰኑ አይሁድ የነፍስ ግድያ ለመፈጸም መሐላ ገቡ (**የሐዋርያት ሥራ** 23፡ 12)። ሔሮድስ ባልታወቀ እና አላስፈላጊ ለሆነ ጉዳይ መሐላውን ሰጠ (**ማቴዎስ** 14፡ 6-9)። ዮፍታሔ የማይረባ መሐላ አደረገ (**መሳፍንት** 11፡30-40)።

## *32. የእግዚአብሔርን ስም ለሰይጣናዊ ተግባር ማዋል ምን ማለት ነው?*

የእግዚአብሔርን ስም ለሰይጣናዊ ተግባር ማዋል ማለት፤

*ሀ.* የእግዚአብሔርን ስም በመጠቀም በዲያብሎስ አማካይነት ልዕለ ተፈጥሮአዊ ነገሮችን ማድረግ ሲሆን፣ ይህም ሟርተኛነትን፣ መናፍስት መጥራትን፣ የወደፊቱን መጠንቆልን፣ ሙታን ማማከርን ወይም ሌሎች አምልኮተ አጋንንት ልምምዶችን ያጠቃልላል፡፡

96. **ዘዳግም** 18፡10-12 ወንድ ልጁን ሴት ልጁን በእሳት የሚያሳልፍ፣ ምዋርተኛም፣ ሞራ ገላጭም፣ አስማተኛም፣ መተተኛም፣ በድግምት የሚጠነቍልም፣ መናፍስትንም የሚጠራ፣ ጠንቋይም፣ ሙታን ሳቢም በአንተ ዘንድ አይገኝ፡፡ ይህንም የሚያደርግ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ነው ስለዚህም ርኵሰት አምላክህ እግዚአብሔር ከፊትህ ያሳድዳቸዋል፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ፡-* የግብጽ ጠንቋዮች በዲያብሎስ እገዛ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ነገሮች አደረጉ (**ዘጸአት** 7-8)፡፡ የአስቄዋ ልጆች የኢየሱስን ስም በመጠቀም አጋንንቶችን ሊያወጡ ሞከሩ ሆኖም እምነት አልነበራቸውም (**የሐዋርያት ሥራ** 19፡13-29)፡፡

*ለ.* ይህንን እና ተመሳሳይ የሆኑ ሰይጣናዊ ተግባሮችን ወይም አምልኮተ ሰይጣን ከሚያደርጉ ሰዎች ጋር መተባበር፣ ርዳታ መሻት፤

97. **ዘሌዋውያን** 19፡31 ወደ መናፍስት ጠሪዎችና ወደ ጠንቋዮች አትሂዱ እንዳትረክሱባቸውም አትፈልጉአቸው እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ፡-* ንጉሥ ሳዖል የጠንቋይዋን እገዛ ፈለገ (1**ሳሙኤል** 28)፡፡

*ሐ.* የከዋክብትን ቆጠራ ወይም ተመሳሳይ መንገዶችን በመከተል ጥንቆላ ማድረግ፤

98. **መክብብ** 7፡14 በመልካም ቀን ደስ ይበልህ በክፉም ቀን ተመልከት ሰው ከእርሱ በኋላ መርምሮ ምንም እንዳያገኝ እግዚአብሔር ይህንም ያንም እንደዚያ ሠርቶአል፡፡

## *33. በእግዚአብሔር ስም መዋሸት ወይም ማታለል ምን ማለት ነው?*

በእግዚአብሔር ስም መዋሸት እና ማታለል ማለት፤

*ሀ.* የሐሰት አስተምህሮን እንደ እግዚአብሔር ቃል ወይም መገለጥ ማስተማር፤

99. **ዘዳግም** 12፡32 እኔ የማዝዝህን ነገር ሁሉ ታደርገው ዘንድ ጠብቅ ምንም በእርሱ ላይ አትጨምር፣ ከእርሱም ምንም አታጕድል፡፡

100. **ኤርምያስ** 23፡31 እነሆ፣ ከምላሳቸው ትንቢትን አውጥተው፡- እርሱ ይላል በሚሉ ነቢያት ላይ ነኝ፣ ይላል እግዚአብሔር፡፡

101. **ማቴዎስ** 15፡9 የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል ብሎ በእውነት ትንቢት ተናገረ፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ፡-* ሐሰተኛ ነቢይ በሐሰት የእግዚአብሔርን ነቢይ ከማሳቱም በላይ ለሞት እንዲዳረግ አድርጎታል (1**ነገሥት** 13፡11-30)፡፡

*ለ.* የማያምን ልብ እና ኃጢአት የተሞላ ሕይወት ይዞ ክርስቲያን እንደ ሆኑ ማስመሰል፤

102. **ማቴዎስ** 7፡21 በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፣ ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ፣ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም፡፡

103. **ማቴዎስ** 15፡8 ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፣ ልቡ ግን ከእኔ በጣም የራቀ ነው፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ-* ብዙ ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ግብዞች ነበሩ (**ማቴዎስ** 23፡13-33)፡፡ ሐናንያ እና ሰጲራ ግብዞች ነበሩ (**የሐዋርያት ሥራ** 5፡1-11)፡፡

### *34. እግዚአብሔር በሁለተኛው ትእዛዝ መሠረት ከእኛ የሚጠብቀው ነገር ምንድን ነው?*

በማናቸውም ችግራችን ጊዜ የእግዚአብሔርን ስም ልንጠራ፣ ልናወድሰው እና ልናመሰግነው ይገባል፡፡

104. **መዝሙር** 50፡15 በመከራ ቀን ጥራኝ፣ አድንህማለሁ አንተም ታከብረኛለህ፡፡
105. **መዝሙር** 103፡1 ነፍሴ ሆይ፣ እግዚአብሔርን ባርኪ፣ አጥንቶቼም ሁሉ፣ የተቀደሰ ስሙን፡፡
106. **መዝሙር** 118፡1 እግዚአብሔርን አመስግኑ፣ ቸር ነውና ምሕረቱ ለዘላለም ናትና፡፡
107. **ዮሐንስ** 16፡23 በዚያን ቀንም ከእኔ አንዳች አትለምኑም፡፡ እውነት እውነት እላችኊለሁ፣ አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኊል፡፡
108. **ኤፌሶን** 5፡20 ሁልጊዜ ስለ ሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምላካችንንና አባታችንን ስለ ሁሉ አመስግኑ፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ-* ዐሥሩ ለምጻሞች ወደ ኢየሱስ ተጣሩ (**ሉቃስ** 17፡11-13)፡፡ አመስጋኙ እንግዳ ሰው ስለ ፈውሱ ተመልሶ ምስጋና ከመስጠቱም በላይ እግዚአብሔርን አከበረ (**ሉቃስ** 17፡15-16)፡፡ ሐና ልጅ እንዲሰጣት ልመናዋን አቀረበች ቀጥላም አመሰገነች (1**ሳሙኤል** 1-2)፡፡ የማርያም ዝማሬ (አድናቆት፣ **ሉቃስ** 1፡46-55)፡፡ የዘካርያስ ዝማሬ (የባርኮት ቃል፣ **ሉቃስ** 1፡68-79)፡፡

## *ሦስተኛው ትዕዛዝ*

> [*የእግዚአብሔር ቃል*]
> የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ ዐስብ፡፡
> *ይህ ምን ማለት ነው?* እግዚአብሔርን እየፈራንና እየወደድን ስብከትንና ቃሉን እንዳንንቅ ነገር ግን ቅዱስ አድርገን እንድንይዘው፣ በደስታ እንድንሰማውና እንድንማረው ነው፡፡

### *35. የሰንበት ቀን ምንድን ነው?*

በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ሰባተኛውን ቀን (ቅዳሜን) ለዕረፍትና ለአምልኮ የተገባ ቀን አድርጎ ለይቶታል (ሰንበት ማለት ‹‹ማረፍ›› ማለት ነው፡፡)

109. **ዘጸአት** 35፡2 ‹‹ስድስት ቀን ሥራ ይደረጋል፤ ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር የዕረፍት ሰንበት የተቀደሰ ቀን ይሆንላችኊል››
110. **ዘሌዋውያን** 23፡3 ‹‹ስድስት ቀን ሥራ ይሠራል፣ በሰባተኛው ቀን ግን የዕረፍት ሰንበት ነው፣ የተቀደሰ ጉባዔ ይሆንበታል፡፡››

### *36. ሰንበትንና ሌሎች የብሉይ ኪዳን በዓላትን እንድንጠብቅ እግዚአብሔር ይፈልግብናል?*

ሰንበት ዕረፍታችን ወደሆነው ወደ ኢየሱስ የሚያመለክት ምልክት ነው፡፡ ኢየሱስ አዳኛችንና ጌታችን ሆኖ ስለ መጣ ከዚህ በኊላ የሰንበትን ቀንና ሌሎች የብሉይ ኪዳን በዓላትን እንድንጠብቅ እግዚአብሔር አይፈልግብንም፡፡

111. **ማቴዎስ** 11፡28 ‹‹እናንተ ደካሞች፣ ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፣ ወደ እኔ ኑ፣ እኔም አሳርፋችኋለሁ፡፡››

112. **ማቴዎስ** 12፡8 ‹‹የሰው ልጅ የሰንበት ጌታ ነውና››

113. **ቆላስይስ** 2፡16-17 እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ ወይም ስለ በዓል ወይም ስለ ወፍ መባቻ ወይም ስለ ሰንበት ማንም አይፍረድባችሁ፤ እነዚህ ሊመጡ ያሉት ነገሮች ጥላ ናቸውና፣ አካሉ ግን የክርስቶስ ነው፡፡

114. **ዕብራውያን** 4፡9-10 እንግዲያስ የሰንበት ዕረፍት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ቀርቶላቸዋል፡፡ ወደ ዕረፍቱ የገባ፣ እግዚአብሔር ከሥራው እንዳረፈ እርሱ ደግሞ ከሥራው አርፎአልና፡፡

### *37. ቤተ ክርስቲያን በተወሰኑ ቀናት ብቻ የኅብረት አምልኮ እንድታደርግ እግዚአብሔር ይፈልግባታል?*

ሀ. ክርስቲያኖች በኅብረት እንዲያመልኩ እግዚአብሔር ይፈልግባቸዋል፡፡

115. **የሐዋርያት ሥራ** 2፡42-46 በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቁረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር … በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቆረሱ፣ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር፡፡

116. **ዕብራውያን** 10፡25 በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደሆነው፣ መሰብሰባችንን አንተው፣ እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ፡፡

ለ. እርሱ የትኛውንም ቀን አልወሰነም፡፡

117. **ሮሜ** 14፡5-6 ይህ ሰው አንድ ቀን ከሌላ ቀን እንዲሻል ያስባል፣ ያ ግን ቀን ሁሉ አንድ እንደሆነ ያስባል፣ እያንዳንዱ በገዛ አዕምሮው አጥብቆ ይረዳ፡፡ ቀንን የሚያከብር ለጌታ ብሎ ያከብራል፡፡

118. **ገላትያ** 4፡10-11 ቀንና ወርን ዘመንንም ዓመትንም በጥንቃቄ ትጠብቃላችሁ፡፡ ምናልባት በከንቱ ለእናንተ ደክሜአለሁ ብዬ እፈራችኋለሁ፡፡

ሐ. ክርስቶስ በዕለተ እሁድ ከሙታን ስለ ተነሣ ቤተ ክርስቲያን የኅብረት አምልኮዋን በተለይ በእሁድ ቀን ታደርጋለች፡፡

119. **ሉቃስ** 24፡1-2 ከሳምንቱ በመጀመሪያ ቀን (ሴቶች) ያዘጋጁትን ሽቱ ይዘው ከእርሱም ጋር አንዳንዶቹ ወደ መቃብሩ እጅግ ማልደው መጡ፡፡ ድንጋዩንም ከመቃብሩ ተንከባሎ አገኙት፡፡

120. **የሐዋርያት ሥራ** 20፡7 ከሳምንቱም በመጀመሪያ ቀን እንጀራ ለመቁረስ ተሰብስበን ሳለን፣ ጳውሎስ በነገው ሊሄድ ስላሰበ ከእነርሱ ጋር ይነጋገር ነበር፣ እስከ መንፈቀ ሌሊትም ነገሩን አስረዘመ፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፦ **ኢየሱስ ለቀደ መዛሙርቱ ታያቸው (ዮሐንስ 20፡19-31)፡፡***

### *38. ሦስተኛውን ትዕዛዝ የምንተላለፈው መቼ ነው?*

ሦስተኛውን ትዕዛዝ የምንተላለፈው ስብከትንና የእግዚአብሔርን ቃል በምንንቅበት ጊዜ ነው፡፡

*39. ይህ የሚሆነው እንዴት ነው?*

ስብከትንና የእግዚአብሔርን ቃል የምንንቀው

*ሀ. የኅብረት አምልኮዎች ላይ ሳንካፈል በምንቀርበት ጊዜ፣*

*ለ. በእግዚአብሔር ቃልና በቅዱሳት ሚስጥራቱ ሳንገለገል ስንቀር፣*

*ሐ. የእግዚአብሔር ቃልና ቅዱሳት ሚስጥራትን በቸልተኝነትና በግዴለሽነት በምንካፈልበት ጊዜ ነው።*

121. ዮሐንስ 8፡47 ከእግዚአብሔር የሆነ የእግዚአብሔርን ቃል ይሰማል፤ እናንተ ከእግዚአብሔር አይደላችሁምና ስለዚህ አትሰሙም።

122. ሉቃስ 10፡16 የሚሰማችሁ እኔን ይሰማል፣ እናንተንም የጣለ እኔን ይጥላል፣ እኔንም የጣለ የላከኝን ይጥላል።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፦ ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ጥምቀትን አቃለሉ* (**ሉቃስ** 7፡30) *ሳዖል የእግዚአብሔርን ቃል ተቃወመ* (**1ሳሙኤል** 15፡10-23)።

*40. እግዚአብሔር በሦስተኛው ትዕዛዝ ከእኛ የሚፈልገው ምንድን ነው?*

*ሀ. ስብከትንና የእግዚአብሔርን ቃል ቅዱስ አድርገን እንድንይዘው ነው።*

123. **ኢሳይያስ** 66፡2 ነገር ግን ወደዚህ ወደ ትሁት፣ መንፈሱም ወደ ተሰበረ፣ በቃሌም ወደሚንቀጠቀጥ ሰው እመለከታለሁ።

124. **1ተሰሎንቄ** 2፡13 ስለዚህም የመልዕክትን ቃል እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ከእኛ በተቀበላችሁ ጊዜ፣ በእውነት እንዳለ በእናንተ በምታምኑ ደግሞ እንደሚሠራ እንደ እግዚአብሔር ቃል እንጂ እንደ ሰው ቃል አድርጋችሁ ስላልተቀበላችሁት… ።

*ለ. በደስታ ልንሰማው፣ ልንማረውና ልናሰላስለው ይፈለግብናል።*

125. **ኢያሱ** 1፡8 የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፣ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው።

126. **መዝሙር** 26፡8 አቤቱ፣ የቤትህን ሥፍራ የክብርህንም ማደሪያ ቦታ ወደድሁ።

127. **ሉቃስ** 11፡28 ብፁዓንስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚጠብቁት ናቸው።

128. **የሐዋርያት ሥራ** 2፡42 በሐዋርያትም ትምህርትና በሕብረት እንጀራውንም በመቁረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር።

129. **ቆላስያስ** 3፡16 የክርስቶስ ቃል በሙላት ይኑርባችሁ፤ በጥበብ ሁሉ እርስ በእርሳችሁ አስተምሩና ገስፁ፤ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፦ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ቃል በደስታ ይሰማና ይማር ነበር* (**ሉቃስ** 2፡41-52)። *ማርያም በኢየሱስ እግር አጠገብ ተቀምጣ ቃሉን ትማር ነበር* (**ሉቃስ** 10፡39)። *ማርያም የእግዚአብሔርን ቃል በልቧ ትጠብቅና ታሰላስለው ነበር* (**ሉቃስ** 2፡19)። *የቤርያ ሰዎች ቅዱሳት መጻሕፍትን በየቀኑ ይመረምሩ ነበር* (**የሐዋርያት ሥራ** 17፡11)።

*ሐ. ስብከትንና የእግዚአብሔርን ቃል ትምህርት እንድናከብርና እንድንደግፍ ነው።*

130. **ገላትያ** 6፡6-7 ነገር ግን ቃሉን የሚማር ከሚያስተምረው ጋር መልካምን ነገር ሁሉ ይከፋፈል። አትሳቱ፣ እግዚአብሔር አይዘበትበትም። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፡-* ድኻይቱ መበለት የመቅደሱን አገልግሎት ለመደገፍና ካህናቱን ለማገዝ ገንዘብ ሰጠች (**ማርቆስ** 12፡41-44)፡፡

*ማስታወሻ፡-* የተግባራት ሰንጠረዥ *ሥር* ‹‹የሚሰሙት ለቁሶቻቸው ያላቸው ኃላፊነት›› የሚለውን ተመልከት፡፡

*መ.* የእግዚአብሔርን *ቃል* በትጋት እንድናሰራጭ ነው፡፡

131. **ማርቆስ** 16፡15 እንዲህም አላቸው፡- ‹ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ፡፡››

### *41. የመጀመሪያዎቹ ሦስት ትዕዛዛት (የመጀመሪያው ፅላት ክፍል) ስለ ራሳችን ምን ያሳዩናል?*

ኃጢአት እንደሠራንና የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚገባን ያሳዩናል፡፡

132. ሮሜ 3፡22-23 ልዩነት የለምና፤ ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፡፡

### *42. የእግዚአብሔርን ሕግ ሙሉ በሙሉ የጠበቀው ማን ብቻ ነው?*

እግዚአብሔር - ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው፡፡

133. ዮሐንስ 8፡46 ከእናንተ ስለ ኃጢአት የሚወቅሰኝ ማን ነው?

134. ዕብራውያን 4፡15 ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ፣ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም፡፡

### *43. ክርስቶስ ሕጉን ሙሉ በሙሉ መጠበቁ እኛን የሚጠቅመን እንዴት ነው?*

ክርስቶስ በእግዚአብሔር ፊት ምትካችን እንደ መሆኑ መጠን የአዳኛችን ሕጉን ሙሉ በሙሉ መጠበቁ እኛን የማዳን ሥራው አካል ሲሆን በእርሱ ምክንያትም በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ተደርገን ተቆጥረናል፡፡

135. ገላትያ 4፡4-5 ነገር ግን የዘመኑ ፍፃሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ፡፡

### *44. የእግዚአብሔር ሕግ ኃጢአታችንን ከማሳየቱ በተጨማሪ የሚሠራልን ሥራ ምንድን ነው?*

እግዚአብሔር በአሥርቱ ትዕዛዛት ፍቃዱ ምን እንደ ሆነ አስታውቆናል፡፡ ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ይናፍቃሉ፡፡

136. **1ተሰሎንቄ** 4፡3 ይህ የእግዚአብሔር ፍቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነውና፡፡

### *45. ከ4-10 ያሉት ትዕዛዛት (ሁለተኛው ክፍል) ማጠቃለያ ምንድን ነው?*

‹‹ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ፡፡›› (ማቴዎስ 22፡39)

### *46. ባልንጀራችን ማነው?*

ሰዎች ሁሉ ባልንጀሮቻችን ናቸው፡፡

137. *ገላትያ* 6፡10 እንግዲያስ ጊዜ ካገኘን ዘንድ ለሰው ሁሉ ይልቁንም ለሃይማኖት ቤተ ሰዎች መልካም እናድርግ።

138. **ማቴዎስ** 5፡44 ጠላቶቻችሁን ውደዱ ለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፡- ደጉ ሣምራዊ ለባልንጀራው ርኅራኄን አሳይቷል* (**ሉቃስ** 10፡ 25- 37)።

## *47. ባልንጀሮቻችንን መውደድ ያለብን እንዴት ነው?*

ባልንጀሮቻችንን እንደ ራሳችን ልንወዳቸውና ይህንንም ፍቅር በሁለተኛው ክፍል ላይ ያሉትን ትዕዛዛት በመጠበቅ ልናሳያቸው ይገባል።

139. **ማቴዎስ** 7፡12 እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትፈልጉትን ሁሉ እናንተም ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው፤ ሕግም ነብያትም ይህ ነውና።

### *አራተኛው ትዕዛዝ*

*[የእግዚአብሔር ወኪሎች]*

አባትና እናትህን አክብር

*ይህ ምን ማለት ነው?* ወላጆቻችንንና ሌሎች ባለሥልጣኖችን እንዳንንቃቸው ወይም እንዳናስቆጣቸው ነገር ግን እንድናከብራቸው፣ እንድናገለግላቸውና እንድንታዘዛቸው፣ እንዲሁም እንድንወዳቸውና እንድናስደስታቸው፣ እግዚአብሔርን ልንፈራና ልንውድ ይገባል።

## *48. ወላጆችና ሌሎች ባለሥልጣናት የተባሉት እነማን ናቸው?*

አባቶች፣ እናቶችና አሳዳጊዎች ወላጆች ሲሆኑ ሌሎች ባለሥልጣኖች ማለት እግዚአብሔር በቤታችን፣ በመንግሥታችን፣ በትምህርት ቤት፣ በምንሠራበት ቦታና በቤተ ክርስቲያን በእኛ ላይ የሾማቸው ሁሉ ናቸው።

*ማስታወሻ፡- መንፈሳዊ ሥልጣንን* በተመለከተ የተግባራት ዝርዝር በሚለው *ሥር* የሚሰሙት ለቁሶቻቸው *ያላባቸው ኃላፊነት* እና በተጨማሪም በእምነት *መግለጫው ሥር* ‹‹*የመክፈቻዎቹ ሥልጣን*›› የሚለውን ተመልከት።

## *49. እግዚአብሔር በአራተኛው ትዕዛዝ የሚከለክለው ምንን ነው?*

ወላጆቻችንንና ሌሎች ባለሥልጣኖችን ባለማክበር ወይም ባለመታዘዛችን ወይም በሌላ በማናቸውም ዓይነት ኃጢአት እንዳናስቆጣቸውና እንዳንንቃቸው ይከለክለናል።

140. ምሳሌ 23፡22 የወለደህን አባትህን ስማ፣ እናትህም ባረጀች ጊዜ አትናቃት።

141. ሮሜ 13፡2 ስለዚህ ባለሥልጣንን የሚቃወም የእግዚአብሔርን *ሥርዓት* ይቃወማል የሚቃወሙትም በራሳቸው ላይ ፍርድን ይቀበላሉ።

*ማስታወሻ፡-* በተግባራት ዝርዝር *ሥር* ‹‹ለማናቸውም ዓይነት ሠራተኞች›› የሚለውን ተመልከት።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፡- የዔሊ ልጆች በክፋታቸው አባታቸውን አሳዘኑት (**1ሳሙኤል** 2፡ 12፣ 23፣ 25)። አቤሴሎም በአባቱ በንጉሡ ላይ አመጸ (**2ሳሙኤል** 15)።*

***50. በአራተኛው ትዕዛዝ እግዚአብሔር ምን እንድናደርግ ይፈልግብናል?***

እግዚአብሔር የሚፈልግብን

*ሀ.* ወላጆቻችንንና ሌሎች ባለሥልጣናትን እንደ እግዚአብሔር ወኪሎች ተመልክተን እንድናከብራቸው ነው፡፡

142. **ኤፌሶን** 6፡2-3 ‹‹*መልካም እንዲሆንልህ ዕድሜህን በምድር ላይ እንዲረዝም* አባትና እናትህን አክብር (እርሷም የተስፋ ቃል ያላት ፊተኛይቱ ትዕዛዝ ናት፡፡)››

*ማስታወሻ፡-* በተግባራት ዝርዝር ሥር ‹‹ለወላጆች›› እና ‹‹ለልጆች›› የሚለውን ተመልከት፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፡- ዮሴፍ አባቱን አከበረ (**ዘፍጥረት** 46፡29)፡፡ ንጉሥ ሰሎሞን እናቱን አከበረ (1**ነገሥት** 2፡19)፡፡ ኤልሳዕ መምህሩን አከበረ (2**ነገሥት** 2፡12)፡፡*

*ለ.* ወላጆቻችንና ሌሎች ባለሥልጣኖች የሚፈልጉትንና የሚጠይቁንን በደስታ በማሟላት እንድናገለግላቸው ነው፡፡

143. 1**ጢሞቴዎስ** 5፡4 *ማንም ባልቴት ግን ልጆች ወይም የልጅ ልጆች ቢኖሯት እነርሱ አስቀድመው ለገዛ ቤተ ሰዎቻቸው እግዚአብሔርን መምሰል ያሳዩ ዘንድ፣ ለወላጆቻቸውም ብድራትን ይመልሱላቸው ዘንድ ይማሩ፣ ይህ በእግዚአብሔር ፊት መልካምና የተወደደ ነውና፡፡*

144. **ሮሜ** 13፡7 *ለሁሉ የሚገባውን አስረክቡ ግብር ለሚገባው ግብርን፣ ቀረጥ ለሚገባው ቀረጥን፣ መፈራት ለሚገባው መፈራትን፣* ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፡- ዮሴፍ ለአባቱ የሚያስፈልገውን ሰጠው(**ዘፍጥረት** 47፡11-12)፡፡ ኢየሱስ ለእናቱ የሚያስፈልጋትን ሰጣት (**ዮሐንስ** 19፡26)፡፡*

*ሐ.* ወላጆቻችንንና ሌሎች ባለሥልጣኖችን እግዚአብሔር በእኛ ላይ በሾመበት በማናቸውም ነገር እንድንታዘዛቸው ነው፡፡

145. **ቆላስይስ** 3፡20 ልጆች ሆይ፣ይህ ለጌታ ደስ የሚያሰኝ ነውና በሁሉ ለወላጆቻችሁ ታዘዙ፡፡

146. **ቲቶ** 3፡1 ለገዥዎችና ለባለሥልጣኖች የሚገዙና የሚታዘዙ፣ ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጁ … እንዲሆኑ አሳስባቸው፡፡

147. **የሐዋርያት** *ሥራ* 5፡29 ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል፡፡

*ማስታወሻ፡- ‹‹ለማናቸውም ዓይነት ሠራተኞች››፣ ‹‹ለአሠሪዎችና ተቆጣጣሪዎች››* እና ‹‹የዜጎች›› የሚለውን የተግባራት ዝርዝር ውስጥ ተመልከት፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፡-* ኢየሱስ ለማርያምና ለዮሴፍ ታዛዥ ነበር (**ሉቃስ** 2፡51)፡፡ ዮናታን የዳዊትን ሕይወት ይታደግ ዘንድ አባቱን አልታዘዘም፤ በመሆኑም ከሰዎች ይልቅ ለእግዚአብሔር ታዘዘ (1**ሳሙኤል** 20፡31-33)፡፡

*መ.* ወላጆቻችንንና ሌሎች ባለሥልጣኖችን እንደ እግዚአብሔር ውድ ስጦታዎች ቆጥረን እንድንወዳቸውና ደስ እንድናሰኛቸው ነው፡፡

148. **ምሳሌ** 23፡22 የወለደህን አባትህን ስማ፣ እናትህን በአረጀች ጊዜ አትናቃት፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፡-* ሩት አማትዋ ኑህሚንን ትወድና ደስ ታሰኛት ነበር (**መጽሐፈ ሩት**)

*ሠ.* በዕድሜ ለገፋት አክብሮትን እንድናሳይ ነው፡፡

149. **ዘሌዋውያን** 19፡32 በሸበታሙ ፊት ተነሳ፣ ሽማግሌውንም አክብር፣ አምላክህንም ፍራ።

### *51. እግዚአብሔር ከዚህ ትዕዛዝ ጋር ያያያዘው የትኛውን ተስፋ ነው?*

*… መልካም እንዲሆንልህ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝም ኤፌሶን 6፡3።*

> **አምስተኛው ትዕዛዝ**
>
> ***[የእግዚአብሔር የሕይወት ስጦታ]***
> አትግደል
> *ይህ ምን ማለት ነው?* ባልንጀራችን ላይ አደጋ እንዳናደርስ ወይም አካሉን እንዳንጎዳው ነገር ግን በሚያስፈልገው ቁሳዊ ፍላጎቱ ሁሉ እንድንረዳውና እንድንደግፈው እግዚአብሔርን ልንፈራና ልንወድ ይገባል።

### *52. እግዚአብሔር በአምስተኛው ትዕዛዝ ምን እንዳናደርግ ይከለክለናል?*

ሀ. እግዚአብሔር የባልንጀራችንን ሕይወት (በመግደል፣ በውርጃ) ወይም የራሳችንን ሕይወት እንዳናጠፋ (ራስን በራስ ማጥፋትን) ይከለክለናል።

150. **ዘፍጥረት** 9፡6 የሰውን ደም የሚያፈስ ሁሉ ደሙ ይፈሳል፤ ሰውን በእግዚአብሔር መልክ ፈጥሮታልና።

151. **ማቴዎስ** 26፡52 ሠይፍ የሚያነሱ ሁሉ በሠይፍ ይጠፋሉ… ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፦ ቃየል ወንድሙን አቤልን ገደለው **(ዘፍጥረት 4፡8)**። ዳዊት በሌሎች አማካይነት ኦሪዮንን ገደለ **(2ሳሙኤል 11፡15)**። በግዴለሽነት መግደል **(ዘጸአት 21፡29 እና ዘዳግም 22፡8)**። ይሁዳ ራሱን ገደለ **(ማቴዎስ 27፡5)**።*

***ውርጃ***

ያልተወለዱ ነገር ግን ሕይወት ያላቸው ፅንሶች ከተፀነሱበት ጊዜ ጀምሮ በእግዚአብሔር ፊት ሰዎች ናቸው። ውርጃ የሰውን ሕይወት ማጥፋት እንደ መሆኑ የሌላውን ሰው ማለትም የእናቲቱን ሕይወት ለማትረፍ ካልሆነ በስተቀር ግብረገባዊ አማራጭ አይደለም።

152. **ኤርምያስ** 1፡5 በሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ፣ ከማኅፀንም ስትወጣ ቀድሼሃለሁ።

153. ***መዝሙር*** 139፡16 ያልተሠራ አካሌን ዐይኖችህ አዩኝ፤ የተፈጠሩ ቀኖቼ ሁሉ አንድ ስንኳ ሳይኖር በመጽሐፍህ ተጻፉ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፦* መጥምቁ ዮሐንስ ገና በእናቱ ማኅፀን ውስጥ እያለ በደስታ ዘለለ። ይህንን በማድረጉ መጥምቁ ዮሐንስና ኤልሳቤጥ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ያልተወለደውን ኢየሱስን እንደ ጌታ ዕውቅና ሰጡት ***(ሉቃስ 1፡41-44)።***

***ሥቃይ የሚያስቆም ግድያ***

የከፋ አካል ጉዳት ያላቸው፣ ደካሞች፣ ረዳት የሌላቸውና በዕድሜ የገፉት በእግዚአብሔር ፊት በእርሱ ሕይወት የተሰጣቸውና በእርሱ ብቻ ሕይወታቸው የሚቋረጥባቸው ሰዎች ናቸው።

154. **ምሳሌ** 6፡16-17 እግዚአብሔር የሚጠላቸው ስድስት ነገሮች ናቸው፣ ሰባትንም ነፍሱ አጥብቃ ትፀየፈዋለች፦ ትዕቢተኛ ዐይን፣ ሐሰተኛ ምላስ፣ ንፁሕ ደምን የምታፈስ እጅ።

155. **ምሳሌ** 31፡8 አፍህን ስለ ዲዳው ክፈት፣ ተስፋ ስለሌላቸውም ሁሉ ተፋረድ።

156. **የሐዋርያት ሥራ** 17፡25 እርሱም ሕይወትንና እስትንፋስህን ሁሉንም ለሁሉ ይሰጣልና።

***ራስን በራስ ማጥፋት***

የእኔ ሕይወት በእርሱ ብቻ ሊቋረጥ የሚገባው የእግዚአብሔር ስጦታ ነው።

157. **ኤርምያስ** 31፡3 እግዚአብሔር ከሩቅ ተገለጠለት፤ በዘላለም ፍቅር ወድጄሃለሁ ስለዚህ ለአንተ ያለኝን ታማኝነት ቀጠልኩኝ።

158. **ሉቃስ** 12፡22 ለደቀ መዛሙርቱም እንዲህ አለ፦ ስለዚህ እላችኋለሁ፣ ለነፍሳችሁ በምትበሉት ወይም ለሰውነታችሁ በምትለብሱት አትጨነቁ።

ለ. እግዚአብሔር በባልንጀራችን አካል ላይ አደጋ እንዳናደርስ ወይም እንዳንጎዳው ይከለክለናል፤ ያም በምንሠራው ወይም በምናደርገው እንዳናጠፋው፣ ዕድሜውን እንዳናሳጥር ወይም የእርሱን ወይም የእርሷን ሕይወት መራራ እንዳናደርግ ነው።

159. **ዘዳግም** 32፡39 አሁንም እኔ ብቻዬን እኔ እንደ ሆንሁ፣ ከእኔም በቀር አምላክ እንደሌለ እዩ፤ እኔ እገድላለሁ፣ አድንማለሁ፤ እኔ እመታለሁ፣ እፈውስማለሁ፤ ከእጄም የሚያድን የለም።

160. **ሮሜ** 12፡19 ተወዳጆች ሆይ፣ ራሳችሁ አትበቀሉ፣ ለቁጣው ፈንታ ስጡ እንጅ፤ ‹‹በቀል የእኔ ነው፣ እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ ይላል ጌታ ተብሎ ተጽፏልና።››

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፦* የዮሴፍ ወንድሞች ዮሴፍን ጎዱት በክፋታቸውም የአባታቸውን ሕይወት መራራ አደረጉት (**ዘፍጥረት** 37፡23-35)። ግብፃውያን ከባድ *ሥራ* በማሠራት የእሥራኤላውያንን ሕይወት አስመረሩ (**ዘጸአት** 1)

ሐ. እግዚአብሔር በባልንጀራችን ላይ እንዳንቆጣና ጥላቻን በልባችን ውስጥ እንዳናቆይ ይከለክለናል።

161. **ማቴዎስ** 5፡22 እኔ ግን እላችኋለሁ፣ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል።

162. **1ዮሐንስ** 3፡15 ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ ነው፣ ነፍሰ ገዳይ የሆነ ሁሉ የዘላለም ሕይወት በእርሱ እንዳይኖር ታውቃላችሁ።

163. **ማቴዎስ** 15፡19 ከልብ ክፉ ሃሳብ፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ በውሸት መመስከር፣ ስድብ ይወጣልና።

164. **ኤፌሶን** 4.26 ተቆጡ ኃጢአትንም አታድርጉ በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፦* አይሁድ ቁጣቸውን በእስጢፋኖስ ላይ አሳዩ (**የሐዋርያት** *ሥራ* 7፡54)። ቃየን እንዳይቆጣ እግዚአብሔር አስጠነቀቀው (**ዘፍጥረት** 4፡5-7)።

***53. ማንኛውም ሰው የሌላውን ሰው ሕይወት የማጥፋት ሥልጣን አለው?***

አዎን! ምድራዊ የሆነ መንግሥት እንደ እግዚአብሔር አገልጋይ ወንጀለኞችን ሊገድልና ፍትሃዊ ጦርነቶችን ሊዋጋ ይችላል።

165. **ሮሜ** 13፡4 ለመልካም ነገር ለአንተ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና። በከንቱ ግን ሠይፍ አይታጠቅምና ክፉ ብታደርግ ፍራ ቁጣውን ለማሳየት ክፉ አድራጊውን የሚበቀል የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና።

### *54. በአምስተኛው ትዕዛዝ እግዚአብሔር የሚፈልግብን ምንድን ነው?*

ሀ. ባልንጀራችንን ለአካሉ በሚያስፈልገው ሁሉ እንድንረዳውና እንድናግዘው ነው።

166. ሮሜ 12፡20 ጠላትህ ግን ቢራብ አብላው ቢጠማ አጠጣው፤ ይህን በማድረግህ በራሱ ላይ የእሳት ፍም ትከምራለህና።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፦* አብርሃም ሎጥን ከጠላቶቹ አዳነው (**ዘፍጥረት** 14፡12-16)። *ዳዊት የሳኦልን ሕይወት ጠበቀ **(1ሳሙኤል 26፡1-12)**። ደጉ ሣምራዊ* በወንበዴዎች እጅ የወደቀውን ሰው ረዳው (**ሉቃስ** 10፡33-35)።

ለ. ለባልንጀራችን መሐሪ፣ ደግና ይቅር ባይ መሆን አለብን።

167. **ማቴዎስ** 5፡5፣7፣9 የዋሆች ብፁዓን ናቸው፣ ምድርን ይወርሳሉና … የሚምሩ ብፁዓን ናቸው፣ ይማራሉና… የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው፣ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና።

168. **ማቴዎስ** 6፡15 ለሰዎች ግን ኃጢአታቸውን ይቅር ባትሉ አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም።

169. **ኤፌሶን** 4፡32 እርስ በርሳችሁም ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ፣ እግዚአብሔርም ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፦* ኢየሱስ *አሥሩን ለምጻሞች ማራቸው* (**ሉቃስ** 17፡11-19)። የመቶ አለቃው ለታመመው ባሪያው ደግ ነበር (**ማቴዎስ** 8፡5-13)። ዮሴፍ ለወንድሞቹ ይቅር ባይ ነበር (**ዘፍጥረት** 45፡1-16)።

ሐ. ባልንጀራችን *ዕፆችንና* ሌሎች አካልና *አዕምሮን* የሚጎዱ *ማናቸውንም ነገሮች* እንዳይጠቀም ልንከላከልና እርሱም እንዲከላከል ልናግዘው ይገባል።

170. 2**ቆሮንቶስ** 7፡1 *ሥጋና መንፈስን* ከሚያረክስ ሁሉ እራሳችንን እናንጻ።

## *ስድስተኛው ትዕዛዝ*

*[የእግዚአብሔር ስጦታ የሆነው ጋብቻ]*

*አታመንዝር*

*ይህ ምን ማለት ነው?* በምናደርገውና በምንናገረው ሕይወታችንን በንጽሕናና በጨዋነት እንድንመራ እንዲሁም ባልና ሚስት እርስ በእርሳችን በፍቅርና በመከባበር እንድንኖር እግዚአብሔርን ልንፈራና ልንወድ ይገባናል።

### *55. ያታዊ ግንኙነታችንን በንፅሕናና በጨዋነት የምንመራው እንዴት ነው?*

ሀ. *ፆታዊነት* የእግዚአብሔር *መልካም ስጦታ* እንደሆነ በመገንዘብ።

171. **ዘፍጥረት** 1፡27፣31 እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው… እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ፣ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ።

ለ. *ጋብቻን* በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል የሕይወት ዘመን አንድነት እንዲሆን የተሰጠ የእግዚአብሔር ተቋም በመሆኑ ማክበር።

172. **ዘፍጥረት** 2፡24-25 ስለዚህ ሰው አባትና እናቱን ይተዋል፣ በሚስቱም ይጣበቃል፤ *ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። አዳምና ሚስቱ ሁለቱም ራቁታቸውን ነበሩ፣ አይተፋፈሩም ነበር።*

173. **ማርቆስ** 10፡6-9 ከፍጥረት *መጀመሪያ ግን ‹‹እግዚአብሔር ወንድና ሴት አደረጋቸው››፣ ‹‹ስለዚህ ሰው አባትና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፣ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ››፤ ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለት አይደሉም። እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው።*

*ሐ. የግብረ ሥጋን ግንኙነትን ለትዳር ጓደኛችን ብቻ በመጠበቅ ነው።*

174. *ዕብራውያን* 13፡4 *መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንፁሕ ይሁን ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል።*

*መ. እግዚአብሔር ደስ በሚሰኝበት መንገድ ወሲባዊ ፍላጎትን እንድንቆጣጠረው ነው።*

175. **ቲቶ** 2፡11-12 *ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ፀጋ ተገልጧልና ይህም ፀጋ፣ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊ ምኞት ክደን ... ራሳችንን በመግዛትና በፅድቅ እግዚአብሔርን በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል።*

*ማስታወሻ፡- በተጨማሪም 1ኛ ተሰሎንቄ 4፡1-7ን ተመልከት።*

## *56. እግዚአብሔር በስድስተኛው ትዕዛዝ የሚከለክለን ምንድን ነው?*

*ሀ. የትዳር ታማኝነትን በማጉደል ምክንያት ካልሆነ በስተቀር* (*ዝሙት ወይም ክህደት*) *እግዚአብሔር ፍቺን ይከለክላል።*

176. **ማቴዎስ** 19፡6 *ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለት አይደሉም። እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው።*

177. **ማቴዎስ** 19፡9 *ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን ፈትቶ ሌላይቱን የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል፣ የተፈታችውንም የሚያገባ ያመነዝራል።*

178. **1ቆሮንቶስ** 7፡15 *የማያምን ግን ቢለይ ይለይ፤ ወንድም ቢሆን ወይም እህት እንዲህ በሚመስል ነገር አይገዙም።*

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፡ ዳዊት ከኦሪዮን ሚስት ጋር አመነዘረ* (**2ሳሙኤል** 11)። *ሄሮድስ የወንድሙን ሚስት ለራሱ ወሰደ* (**ማርቆስ** 6፡18)።

*ለ. እግዚአብሔር ባልተጋቡ ሰዎች መካከል የሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነትን ይከለክላል።*

179. **1ቆሮንቶስ** 6፡18 *ከዝሙት ሽሹ።*

180. 1ቆሮንቶስ 6፡9-10 *ሴሰኞች ቢሆኑ ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀላጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ ... የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።*

181. **ሮሜ** 1፡24፣26-27 *ስለዚህ እርስ በእርሳቸው ሥጋቸውን ሊያዋርዱ እግዚአብሔር በልባቸው ፍትወት ወደ እርኩስነት አሳልፎ ሰጣቸው ... ሴቶቻቸውም ለባህርያቸው የሚገባውን ሥራ ለባህሪያቸው በማይገባው ለወጡ፤ እንዲሁም ወንዶች ደግሞ ለባህሪያቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘት ትተው እርስ በእርሳቸው በፍትወታቸው*

ተቃጠሉ፤ ወንዶችም በወንዶች ነውር አድርገው በስህተታቸው የሚገባውን ብድራት በራሳቸው ተቀበሉ።

182. **1ቆሮንቶስ** 6፡9-10 ወይስ አመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ ሴሰኞች ቢሆኑ ወይንም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀላጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካራሞች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።

ሐ. እግዚአብሔር ንፁሕ ያልሆነ የወሲብ አሳብና ፍላጎትን ይከለክላል።

183. **ማቴዎስ** 5፡28 እኔ ግን እላችኋለሁ፣ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ አመንዝሯል።

184. **ማቴዎስ** 15፡19 ከልብ ክፉ አሳብ፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ በውሸት መመስከር፣ ስድብ ይወጣልና።

### *57. እግዚአብሔር በስድስተኛው ትዕዛዝ የሚፈልግብን ምንድን ነው?*

ሀ. እግዚአብሔር የወሲብ ኃጢአት ፈተናዎችን ሁሉ እንድናስወግድ ይፈልግብናል።

185. **ዘፍጥረት** 39፡9 እንዴት ይህን ትልቅ ክፉ ነገር አደርጋለሁ? በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ?

186. **1ቆሮንቶስ** 6፡18 ከዝሙት ሽሹ። ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጪ ነው፤ ዝሙትን የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ይሠራል።

ለ. በምናስበውና በምናደርገው ንፁሐን እንድንሆን እግዚአብሔር ይፈልግብናል።

187. **ኤፌሶን** 5፡3-4 ለቅዱሳን እንደሚገባ ግን ዝሙትና ርኩሰት ሁሉ ወይም መመኘት በእናንተ ዘንድ ከቶ አይሰማ፤ የሚያሳፍር ነገርም የስንፍና ንግግርም ወይም ዋዛ የማይገቡ ናቸውና አይሁኑ ይልቁን ምስጋና እንጂ።

188. **ፊልጵስዩስ** 4፡8 በቀረውስ ወንድሞች ሆይ፣ እውነተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ፣ ጭምትነት ያለበትን ነገር ሁሉ፣ ፅድቅ የሆነውን ነገር ሁሉ፣ ንጹሕ የሆነውን ነገር ሁሉ፣ ፍቅር ያለበትን ነገር ሁሉ፣ መልካም ወሬ ያለበትን ነገር ሁሉ፣ በጎነት ቢሆን ምስጋናም ቢሆን፣ እነዚህን አስቡ።

ሐ. ወሲባዊ ተፈጥሮአችንን እርሱን ደስ በሚያሰኘው መንገድ እንድንጠቀምበት እግዚአብሔር ይፈልግብናል።

189. 1ቆሮንቶስ 6፡19-20 ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።

### *58. እግዚአብሔር በተለይ ከተጋቡ ሰዎች የሚፈልግባቸው ምንድን ነው?*

የተጋቡ ሰዎች እርስ በእርስ እንዲዋደዱ፣ እንዲከባበሩና እንዲቀባበሉ እግዚአብሔር ይፈልግባቸዋል። ሚስት ከእግዚአብሔር ዘንደ ለባሏ የተሰጠች ረዳት ናት፤ እንዲሁም ባል ለሚስቱ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ራስ ነው።

190. **ዘፍጥረት** 2፡18 እግዚአብሔር አምላክም አለ፡- ‹‹ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት፡፡››

191. **1ቆሮንቶስ** 7፡4 ሚስት በገዛ *ሥጋዋ* ላይ *ሥልጣን* የላትም፤ *ሥልጣን* የባሏ ነው እንጂ እንዲሁም ደግሞ ባል በገዛ *ሥጋው* ላይ *ሥልጣን* የለውም፤ *ሥልጣን* የሚስቱ ነው እንጂ፡፡

192. **ኤፌሶን** 4፡32 እርስ በእርሳችሁም ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ፤ እግዚአብሔርም ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ፡፡

193. **ኤፌሶን** 5፡21-23፤25 ለእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ፡፡ ሚስቶች ሆይ፣ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ፤ ክርስቶስ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደ ሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና … ባሎች ሆይ፣ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፡፡

*ማስታወሻ፡- ተግባራት ከሚለው ሠንጠረዥ ሥር* ‹‹ለባሎች›› እና ‹‹ለሚስቶች›› የሚለውን ተመልከት፡፡

*ሰባተኛው ትዕዛዝ*

*[የእግዚአብሔር የሀብት ስጦታ]*

አትስረቅ

*ይህ ምን ማለት ነው?* የባልንጀራችንን ገንዘብ ወይም ንብረት በማታለል እንዳንወስድበት ነገር ግን ንብረቱንና ገቢውን ያሻሽላልና ይጠብቅ ዘንድ እናግዘው ዘንድ እግዚአብሔርን ልንፈራና ልንወድ ይገባናል ማለት ነው፡፡

### *59. እግዚአብሔር በሰባተኛው ትዕዛዝ የሚከለክለን ምንድን ነው?*

የሚያስፈልጉንን ነገሮች በዝርፊያ፣ በስርቆትና በየትኛውም ዓይነት የማታለል መንገድ ለማግኘት እንዳንሞክር እግዚአብሔር ይከለክለናል፡፡

194. **ዘሌዋውያን** 19፡35 በፍርድ፣ በመለካትም፣ በመመዘንም፣ በመስፈርም አመጻ አታድርጉ፡፡

195. **መዝሙር** 37፡21 *ኃ*ጢአተኛ ይበደራል አይከፍልምም፤ ጻድቅ ግን ይራራል ይሰጣልም፡፡

196. **ኤፌሶን** 4፡28 የሰረቀ ከእንግዲህ ወዲህ አይስረቅ፣ ነገር ግን በዚያ ፈንታ ለጎደለው የሚያካፍለው እንዲኖርለት በገዛ እጆቹ መልካምን እየሠራ ይድከም፡፡

197. **2ተሰሎንቄ** 3፡10 ሊሠራ የማይወድ አይብላ፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፡-* አካን ልብስ፣ ብርና ወርቅ ደብቆ በወሰደ ጊዜ ሠረቀ (ኢያሱ 7፡ 20-22)፡፡ ይሁዳ ሌባ ነበር (ዮሐንስ 12፡6)፡፡ ግያዝ በመዋሸትና በማጭበርበር ስጦታውን ለራሱ አደረገ (2*ነገሥት* 5፡20-24)፡፡

### *60. በሰባተኛው ትዕዛዝ እግዚአብሔር ምን እንድናደርግ ይፈልግብናል?*

*ሀ.* ባልንጀራችን ንብረቱንና ገቢውን እንዲያሻሽልና እንዲጠብቅ እንድናግዘው ነው፡፡

198. **ማቴዎስ** 7፡12 እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትፈልጉትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው፡፡

199. **ፊልጵስዩስ** 2፡4 እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት፣ ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፦* አብርሃም የመሬቱን ምርጫ ለሎጥ ሰጠው (ዘፍጥረት 13፡9)። አብርሃም ሎጥን ከጠላቶቹ ታደገው የሎጥን ንብረትም አስመለሰ (ዘፍጥረት 14፡12-16)።

ለ. ባልንጀራችንን በሚያስፈልገው ሁሉ ልናግዘው ይገባል።

200. **ማቴዎስ** 5፡42 ለሚለምንህ ስጥ፣ ከአንተም ይበደር ዘንድ ከሚወደው ፊቀቅ አትበል።

201. **ዕብራውያን** 13፡16 ነገር ግን መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ እንዲህ ያለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና።።

202. **1ዮሐንስ** 3፡17 ነገር ግን የዚህ ዓለም ገንዘብ ያለው፣ ወንድሙም የሚያስፈልገውን ሲያጣ አይቶ ያልራራለት ማንም ቢሆን፣ የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ እንዴት ይኖራል?

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፦* ዘኬዎስ በሐሰት የወሰደውን በአራት እጥፍ ሊመልስና ካለው ሁሉ ግማሹን ለድሆች ሊሰጥ ቃል ገባ (ሉቃስ 19፡8)። ደጉ ሣምራዊ ባልንጀራውን ረዳው ካህኑና ሌዋዊው ግን አላደረጉትም ነበር (ሉቃስ 10፡29-37)።

**ስምንተኛው ትዕዛዝ**

***[የእግዚአብሔር የመልካም ስም ስጦታ]***

በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር

*ይህ ምን ማለት ነው?* እግዚአብሔርን እየፈራንና እየወደድን ስለ ባልንጀራችን ሐሰትን እንዳንናገር፣ እንዳናማው ወይም መልካም ስሙን እንዳናጎድፍ ነገር ግን እንድንከላከልለት ስለ እርሱ መልካም እንድንናገርና ሁሉን ነገር በቅንነት እንድናስረዳው ይገባናል ማለት ነው።

### *61. እግዚአብሔር በስምንተኛው ትዕዛዝ የሚከለክለው ምንን ነው?*

ሀ. እግዚአብሔር በፍርድ ቤት ወይም በሌላ ቦታ ስለ ባልንጀራችን ሐሰትን እንዳንናገር፣ እርሱን ወይም ስለ እርሱ እንዳንዋሽ ወይም እውነቱን ከባልንጀራችን እንዳንደብቅ ይከለክለናል።

203. **ምሳሌ** 19፡5 ሐሰተኛ ምላስ ሳይቀጣ አይቀርም፣ በሐሰትም የሚናገር አያመልጥም።

204. **ኤፌሶን** 4፡25 ስለዚህ ውሸትን አስወግዳችሁ፣ እርስ በእርስ ብልቶች ሆነናልና እያንዳንዳችሁ ከባልንጀሮቻችሁ ጋር እውነትን ተናገሩ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፦* በኢየሱስ ላይ የሐሰት ምስክሮች መሰከሩበት (ማቴዎስ 26፡59-61)። የሐሰት ምስክሮች በናቡቴ ላይ መሰከሩበት (1*ነገሥት* 21፡13)። ግያዝ ኤልሣዕን ዋሸው (2*ነገሥት* 5፡22-25)።

ለ. እግዚአብሔር ባልንጀራችንን እንዳንከዳው ይኸውም ሚስጥሮቹን እንዳናወጣበት ይከለክለናል።

205. **ምሳሌ** 11፡13 ለሐሜት የሚሄድ ሚስጥሩን ይገልጣል፤ በመንፈስ የታመነ ግን ነገሩን ይሰውራል።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ- ዶይቅ አቢሜሌክን ከዳው* (1**ሳሙኤል** 22፡6-9)፡፡ *ይሁዳ ኢየሱስን ከዳው **(ማቴዎስ 26፡14-16)፡፡***

ሐ. እግዚአብሔር ባልንጀራችንን እንዳናማው ወይም ስሙን እንዳናጎድፍ ይከለክለናል፡፡

206. **ማቴዎስ** 18፡15 ወንድምህ ቢበድልህ፣ ሄደህ አንተና እርሱ ብቻችሁን ሆናችሁ ውቀሰው፡ ፡

207. **ሉቃስ** 6፡37 አትፍረዱ አይፈረድባችሁምም አትኮንኑ አትኮነኑምም፡፡

207. **ያዕቆብ** 4፡11 ወንድሞች ሆይ፣ እርስ በእርሳችሁ ክፋትን አትነጋገሩ፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፦ አቤሴሎም የአባቱን ስም አጠፋ **(2ሳሙኤል 15፡1-6)፡፡***

## *62. በስምንተኛው ትዕዛዝ እግዚአብሔር የሚፈልግብን ምንድን ነው?*

ሀ. ለባልንጀራችን እንድንከላከልለት ነው፣ ይኸውም ስለ እርሱ እንድንናገር ባልንጀራችንን ከሐሰተኛ ክሶች እንድንጠብቀው ይገባናል ማለት ነው፡፡

209. **ምሳሌ** 31፡8-9 አፍህን ስለ ዲዳው ክፈት፣ ተስፋ ስለ ሌላቸውም ሁሉ ተፋረድ፡፡

ለ. ስለ ባልንጀራችን በጎን መናገር አለብን፣ ይኸውም የባልንጀራችንን መልካም ተግባሮችና ባህርያት ማድነቅ መቻል አለብን ማለት ነው፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፦ ዮናታን ስለ ዳዊት መልካምን ተናገረ **(1ሳሙኤል 19፡4)፡፡*** የቅፍርናሆም ሰዎች ስለ የመቶ አለቃው መልካም ቃል ተናገሩ (**ሉቃስ** 7፡4-5)፡፡ ኢየሱስ ስለ ቀባችው ሴት መልካም ተናገረ (ማርቆስ 14፡3-9)፡፡

ሐ. በነገሮች ሁሉ ላይ የቀና ትርጉም መስጠት አለብን ይኸውም የባልንጀራችንን ተግባር በተቻለን መጠን በቀና መንገድ መተርጎም ይኖርብናል ማለት ነው፡፡

210. **1ቆሮንቶስ** 13፡7 ፍቅር ሁሉን ይታገሳል፣ ሁሉን ያምናል፣ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፣ በሁሉ ይጸናል፡፡

211. **1ጴጥሮስ** 4፡8 ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ይሸፍናልና፡፡

> ### *ዘጠነኛው ትዕዛዝ*
>
> ***[ስለ መርካት የእግዚአብሔር ስጦታ]***
> የባልንጀራህን ቤት አትመኝ
> *ይህ ምን ማለት ነው?* እግዚአብሔርን እየፈራንና እየወደድን የባልንጀራችንን ውርስ ወይም ቤት ትክክል በሚመስል መንገድ ለማግኘት እንዳናሴር ነገር ግን ለእርሱ ተጠብቆለት እንዲገለገልበት ልናግዘው ይገባናል ማለት ነው፡፡

## *63. መመኘት ምንድን ነው?*

*መመኘት ማለት የባልንጀራችን የሆነውን ማንኛውንም ወይም የትኛውንም ነገር የራሳችን ለማድረግ የምንፈልግበት ኃጢአታዊ ፍላጎት ነው፡፡*

212. **ሮሜ** 7፡8 ኃጢአት … ምኞትን ሁሉ በትዕዛዝ ሠራብኝ፡፡

213. **ማቴዎስ** 15፡9 ከልብ ክፉ አሳብ፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ በውሸት መመስከር፣ ስድብ ይወጣልና፡፡

64. እግዚአብሔር በዘጠነኛው ትዕዛዝ የሚከለክለን ምን ዓይነቱን ምኞት ነው?

የባልንጀራችንን ንብረት በግልጽም ሆነ በማጭበርበር የራሳችን ለማድረግ የምንፈልግበት ኃጢአታዊ ፍላጎትን ሁሉ እግዚአብሔር ይከለክላል።

214. **ሚክያስ** 2፡1-2 በደልን ለሚያስቡ ክፋትንም ለሚያደርጉ ወዮላቸው! ... በእርሻው ላይ ይመኛሉ፣ በግዴታም ይይዙታል፤ በቤቶችም ላይ ይመኛሉ፣ ይወስዷቸውማል፤ ሰውንና ቤቱን፣ ሰውንና ርስቱንም ይነጥቃሉ።

215. **1ጢሞቴዎስ** 6፡8-10 ምግብና ልብስ ከኖረን ግን እርሱ ይበቃናል። ዳሩ ግን ባለጠጎች ሊሆኑ የሚፈልጉ በጥፋትና በመፍረስ ሰዎችን በሚያሰጥምና በሚያሰንፍ በሚጎዳ በብዙ ምኞትና በፈተና በወጥመድም ይወድቃሉ። ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና፣ አንዳንዶችም ይህን ሲመኙ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ስቃይ ራሳቸውን ጎዱ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፦* አካአብ የናቡቴን የወይን ቦታ ተመኘ ትክክል በሚመስል መንገድም አገኘው (1*ነገሥት* 21፡1-16)።

*65. እግዚአብሔር በዘጠነኛው ትዕዛዝ የሚፈልግብን ምንድን ነው?*

እግዚአብሔር በሰጠን ነገር እንድንረካና ባልንጀራችን ከእግዚአብሔር የተሰጠውን እንዲጠብቅ ልንደግፈው ነው።

216. **ፊልጵስዩስ** 4፡11 ይህንን ስል ስለ ጉድለት አልልም፣ የምኖርበት ኑሮ ይበቃኛል ማለትን ተምሬአለሁና።

217. **1ጢሞቴዎስ** 6፡6 ኑሮዬ ይበቃኛል ለሚለው ግን እግዚአብሔርን መምሰል እጅግ ማትረፊያ ነው።

218. *ዕብራውያን* 13፡5 ‹‹አካሄዳችሁ ገንዘብን ያለመውደድ ይሁን፣ ያላችሁ ይብቃችሁ እርሱ ራሱ፦ አልለቅህም ከቶም አልተውህም ብሎአልና።››

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፦* ጳውሎስ ምኞትን አሸነፈ (**የሐዋርያት** *ሥራ* 20፡32-35)።

### *አሥረኛው ትዕዛዝ*

*[ስለ መርካት የእግዚአብሔር ስጦታ]*

የባልንጀራህን ሚስት ወይም ወንድ አገልጋዩን ወይም ሴት አገልጋዩን ወይም በሬውን ወይም አህያውን ወይም የባልንጀራህ የሆነውን ማናቸውንም ነገር አትመኝ።

*ይህ ምን ማለት ነው?* እግዚአብሔርን እየፈራንና እየወደድን የባልንጀራችንን ሚስት፣ ሠራተኞች እንስሶች በማባበልምም ሆነ በኃይል እንዳንወስድበት ወይም እንዲያምጹበት እንዳናነሳሳቸው ነገር ግን አብረውት እንዲቆዩና ኃላፊነታቸውን እንዲፈጽሙ መገፋፋት አለብን ማለት ነው።

*66. በአሥረኛው ትዕዛዝ እግዚአብሔር የሚከለክለው የትኛውን ምኞት ነው?*

የባልንጀራችንን ሚስት ወይም ሠራተኞች እንድንወስድ የሚያደርግን የትኛውም ኃጢአታዊ ፍላጎት እግዚአብሔር ይከለክላል።

219. **ሉቃስ** 12፡15 ‹‹የሰው ሕይወት በገንዘቡ ብዛት አይደለምና ተጠንቀቁ፣ ከመጎምጀትም ሁሉ ተጠበቁ አላቸው፡፡››

220. **ቆላስያስ** 3፡5 እንግዲህ በምድር ያሉትን ብልቶቻችሁን ግደሉ፣ እነዚህም ዝሙትና ርኵሰት ፍትወትም ክፉ ምኞትም ጣዖትንም ማምለክ የሆነ መጎምጀት ነው፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፦ ዳዊት የኦርዮንን ሚስት ተመኘ ወሰዳትም* (2**ሳሙኤል** 11፡2-4)፡፡ አቤሴሎም የሕዝቡን ልብ ከዳዊት ሰረቀ (2**ሳሙኤል** 15፡1-6)፡፡

### *67. በአሥረኛው ትዕዛዝ እግዚአብሔር የሚፈልግብን ምንድን ነው?*

እግዚአብሔር በሰጠን እረዳቶች እንድንረካና የባልንጀሮቻችን ረዳቶች ለባልንጀራችን ታማኞች እንዲሆኑ እንድናበረታታቸው ይፈልግብናል፡፡

221. **ፊልጵስዩስ** 2፡4 እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት፣ ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፦ ጳውሎስ የኮበለለውን ባሪያ ወደ ጌታው ወደ ፊልሞና መልሶታል **(ፊልሞና)፡፡***

### *68. በተለይም በመጨረሻዎቹ ሁለት ትዕዛዛት እግዚአብሔር በጥብቅ የሚያሳስበን ምንድን ነው?*

ሀ. በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ፍላጎትና መመኘት በእርግጥ ኃጢአትና ፍርድ የሚገባው ነው፡፡

222. **ዘፍጥረት** 3፡6 ሴቲቱም ዛፉን ለመብላት ያማረ እንደ ሆነ፣ ለዐይንም እንደሚያስጎመጅ፣ ለጥበብም መልካም እንደ ሆነ አየች፣ ከፍሬውም ወሰደችና በላች፡፡

223. **ያዕቆብ** 1፡14-15 ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል፡፡ ከዚህ በኋላ ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች፤ ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች፡፡

ለ. እግዚአብሔር እርሱን እንድንወደውና ቅዱስ ፍላጎቶች እንዲኖሩን ይፈልጋል፡፡

224. **መዝሙር** 37፡4 በእግዚአብሔር ደስ ይበልህ የልብህንም መሻት ይሰጥሃል፡፡

225. **መዝሙር** 119፡35-36 እርሷን ወድጄአለሁና የትዕዛዝህን መንገድ ምራኝ፡፡ ልቤን ወደ ምሥክርህ አዘንብል፣ ወደ ስስትም አይሁን፡፡

226. **ፊልጵስዩስ** 4፡8 በቀረውስ ወንድሞች ሆይ፣ እውነተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ፣ ጭምትነት ያለበትን ነገር ሁሉ፣ ጽድቅ ያለውን ነገር ሁሉ፣ ንፁሕ የሆነውን ነገር ሁሉ፣ ፍቅር ያለበትን ነገር ሁሉ፣ መልካም ነገር ያለበትን ሁሉ፣ በጎነት ቢሆን ምስጋናም ቢሆን፣ እነዚህን አስቡ፡፡

### *የትዕዛዛቱ መደምደሚያ*

*ስለ እነዚህ ትዕዛዛት ሁሉ እግዚአብሔር የሚለው ምንድን ነው?*
እርሱ እንዲህ ይላል ‹‹በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ፤ ለሚወዱኝ፣ ትዕዛዜን ለሚጠብቁ እስከ ሺ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና›› (**ዘጸአት** 20፡5-6)፡፡

> *ይህ ምን ማለት ነው?* እነዚህን ትዕዛዛት የሚተላለፉትን ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚቀጣቸው ያስጠነቅቃል፡፡ ስለሆነም ቁጣውን ልንፈራና ትዕዛዛቱን በመቃወም ምንም ነገር ማድረግ አይኖርብንም፡፡ እነዚህን ትዕዛዛት ለሚጠብቁት ሁሉ ግን ፀጋንና በረከትን ሁሉ ሊሰጣቸው ተስፋ ይገባል፡፡ ስለዚህ እኛ ደግሞ ልንወደው በእርሱ ልንታመንና የሚያዘንን በደስታ ልንፈጽም ይገባል፡፡

### *69. ለምንድን ነው እግዚአብሔር ራሱን ቀናተኛ አምላክ ብሎ የጠራው?*

ምክንያቱም እግዚአብሔር ቅዱስ ስለ ሆነ ነው፡፡

ሀ. እርሱ ኃጢአትን ይጠላል፣ ሙሉና ፍፁም መታዘዝንም በጥብቅ ይፈልጋል፤

ለ. የምንሰጠውን ፍቅርና ክብር ከሌሎች ጣዖት ጋር አይጋራም፤

ሐ. የሚጠሉትን እነርሱን ይቀጣቸዋል፡፡

227. **መዝሙር** 5፡4-5 አንተ በደልን የማትወድ አምላክ ነህና፤ ክፉ ከአንተ ጋር አያድርም፡፡ በከንቱ የሚመኩ በዐይኖችህ ፊት አይኖሩም፣ ክፉ አድራጊዎችን ሁሉ ጠላህ፡፡

228. **ኢሳይያስ** 42፡8 እኔ እግዚአብሔር ነኝ ስሜ ይኼ ነው ክብሬን ለሌላ፣ ምስጋናዬንም ለተቀረጹ ምስሎች አልሰጥም፡፡

229. **መዝሙር** 6፡9 ከእኔ በራቀው በአመንዝራ ልባቸውና ጣዖቶቻቸውን በተከተሉ በአመንዝራ ዐይኖቻቸው የተሰበርሁትን እኔን … ፡፡

230. **ያዕቆብ** 4፡12 ሕግን የሚሰጥና የሚፈርድ አንድ ነው፤ እርሱም ሊያድን ሊያጠፋም የሚችል ነው፡፡

### *70. እግዚአብሔር እርሱን በሚጠሉት ትዕዛዛቱን በሚተላለፉት ላይ ምን እንደሚያደርግ ነው ያስጠነቀቀው?*

ምድራዊ ቅጣት፣ አካላዊ ሞትና ዘላለማዊ ጥፋት እንደሚሆንባቸው አስጠንቅቋል፡፡

231. **ዘሌዋውያን** 26፡18 እስከዚህም ድረስ ባትሰሙ፣ ስለ ኃጢአታችሁ በቅጣታችሁ ላይ ሰባት እጥፍ እጨምራለሁ፡፡

232. **ሮሜ** 6፡23 የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፡፡

233. **ገላትያ** 3፡10 በሕግ መጽሐፍ በተጻፉት ሁሉ ፀንቶ የማይኖር የማያደርግም ሁሉ የተረገመ ነው፡፡

### *71. እርሱን የሚጠሉትን እስከ ሦስተኛና አራተኛ ትውልድ ድረስ ስለ አባቶቻቸው ኃጢአት ልጆቻቸውን እንደሚቀጣ ሲያስጠነቅቅ እግዚአብሔር ምን ማለቱ ነው?*

ልጆች፣ የልጅ ልጆችና የልጅ ልጅ ልጆች እነርሱም እግዚአብሔርን ቢጠሉና የወላጆቻቸውን ክፉ መንገዶች ቢከተሉ ስለ አባቶቻቸው ኃጢአት በምድራዊ ሕይወታቸው እግዚአብሔር ይቀጣቸዋል፡፡

234. **ሕዝቅኤል** 18፡20 ኃጢአትን የምትሠራ ነፍስ እርሷ ትሞታለች፤ ልጅ የአባቱን ኃጢአት አይሸከምም፣ አባትም የልጁን ኃጢአት አይሸከምም የጻድቁን ፅድቅ በራሱ ላይ ይሆናል፣ የኃጢአተኛውም ኃጢአት በራሱ ላይ ይሆናል፡፡››

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፦* የክፉዎቹ የአካብና የኤልዛቤል ቤተ ሰቦች ተደመሰሱ (2*ነገሥት* 9፡7-8፤ 10፡11)። እስራኤል ባለመታዘዝዋና በክፋትዋ ምክንያት በምርኮ ተወሰደች (2ዜና 36፡ 17-21)።

### *72. እግዚአብሔር ይህን በመሰለ ቅጣት ለምን ያስጠነቅቃል?*

እግዚአብሔር ይህን በመሰለ ቅጣት የሚያስጠነቅቀን ቁጣውን እንድንፈራና ትዕዛዛቱን የሚጻረር ተግባር እንዳንፈጽም ሊያደርገን ነው።

235. **መክብብ** 12፡13-14 ይህ የሰው ሁለንተናው ነውና እግዚአብሔርን ፍራ፣ ትዕዛዙንም ጠብቅ። እግዚአብሔር *ሥራን* ሁሉ የተሰወረውንም ነገር ሁሉ፣ መልካምም ቢሆን ክፉም ቢሆን፣ ወደ ፍርድ *ያመጣዋ*ልና።

236. **ማቴዎስ** 10፡28 *ሥጋንም* የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ ይልቅስ ነፍስንም *ሥጋንም* በገሃነም ሊያጠፋ የሚችለውን ፍሩ።

### *73. እግዚአብሔር እርሱን የሚወዱትንና ትዕዛዞቹን የሚጠብቁትን የሚባርካቸው እንዴት ነው?*

በእርሱ በሚያምኑትና እግዚአብሔርን በሚፈሩ ዘሮቻቸው ላይ የማያቋርጥ ፍቅሩንና መልካም ስጦታዎቹን ያዘንብባቸዋል።

237. **1ጢሞቴዎስ** 4፡8 እግዚአብሔርን መምሰል ግን የአሁንና የሚመጣው ሕይወት ተስፋ ስላለው ለነገር ሁሉ ይጠቅማል።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፦* እግዚአብሔር ኢዮብን ስለ ታማኝነቱ ባረከው (ኢዮብ 42፡10-17)።

## *የሕግ መፈጸም*

### *74. እግዚአብሔር ትዕዛዛቱን እንዴት ባለ ጥንቃቄ እንድንጠብቃቸው ነው የሚፈልገው?*

እግዚአብሔር ትዕዛዛቱን በአሳባችን፣ በፍላጎታችን፣ በቃላችንና በ*ሥራ*ችን በፍፁምነት እንድንጠብቃቸው ይፈልግብናል።

238. **ዘሌዋውያን** 19፡2 እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተ ቅዱሳን ሁኑ።

239. ***ያዕቆብ*** 2፡10 ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ ፣ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም ቢኖር በሁሉ በደለኛ ይሆናል።

### *75. የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት በፍፁምነት እንዳንጠብቅ የሚከላከለን ምንድን ነው?*

የማይቻል የሚያደርገው ኃጢአተኛው ተፈጥሮአችን ነው።

240. **መዝሙር** 14፡3 ሁሉ አመፁ በአንድነትም ረከሱ፤ በጎ ነገርን የሚሠራ የለም አንድም ስንኳ የለም።

241. **መክብብ** 7፡20 በምድር ላይ መልካምን የሚሠራ ኃጢአትንም የማያደርግ ጻድቅ አይገኝምና።

242. **ኢሳይያስ** 64፡6 ሁላችን እንደ እርኩስ ሰው ሆነናል፣ ጽድቃችንም ሁሉ እንደ መርገም ጨርቅ ነው።

243. **1ዮሐንስ 1፡8** ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፣ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፡-* ሐዋርያው ጳውሎስ ሕግን ለመፈጸም ባለመቻሉ አዝኗል (**ሮሜ** 7፡15-20)።

### *76. ታዲያ ሕግን በመጠበቅ መዳን የሚችል ሰው አለ?*

የለም፤ ሕጉ ሰውን ሁሉ ይኮንናል።

244. *ገላትያ* 3፡10-11 ‹‹ከሕግ *ሥራ* የሆኑት ሁሉ ከእርግማን በታች ናቸውና፤ በሕግ መጽሐፍ በተጻፉት ሁሉ ፀንቶ የማይኖር የማያደርግም ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፏልና። ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሏልና ማንም በእግዚአብሔር ፊት በሕግ እንዳይጸድቅ ግልጥ ነው።››

## *የሕጉ ዓላማዎች*

### *77. ታዲያ ሕጉ የሚያገለግለው የትኞቹን ዓላማዎች ነው?*

ሀ. በመጀመሪያ፣ የኃጢአት አመፅ ገንፍሎ እንዳይፈስ ለመቆጣጠር ይጠቅመናል፣ በዓለም ውስጥ *ሥርዓትን* ደግሞ ያስጠብቃል (*መገደብያ*)።

245. **1ጢሞቴዎስ** 1፡9 ለበደለኞችና ለማይታዘዙ፣ ለአመጸኞችና ለኃጢአተኞች፣ ቅድስና ለሌላቸውና ለርኩሳን፣ አባትና እናትን ለሚገድሉ … ለሌላ ነገር ሁሉ ሕግ እንደ ተሠራ እንጂ ለጻድቅ እንዳልተሠራ ሲያውቅ ነው።

246. **ሮሜ** 2፡14-15 ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ከባህሪያቸው የሕግን ትዕዛዝ ሲያደርጉ፣ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸውም እንኳ ለራሳቸው ሕግ ናቸውና እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው፣ አሳባቸውም እርስ በእርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ *ሥራ* ያሳያሉ።

ለ. ሁለተኛ፣ ሕጉ ይከሰናል ኃጢአታችንንም ያሳየናል (*መስተዋት*)።

247. **ሮሜ** 3፡20 ኃጢአት በሕግ ይታወቃልና።

248. **ሮሜ** 7፡7 ነገር ግን በሕግ ባይሆን ኃጢአትን ባላወቅሁም ነበር፤ ሕጉ፡- አትመኝ ባላለ ምኞትን ባላወቅሁም ነበርና። ‹‹አትመኝ››

ሐ. ሦስተኛ፣ እኛ ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን ሕይወት ለመምራት ምን ማድረግ እንዳለብንና እንደሌለብን ሕጉ ያስተምረናል። እንደ ሕጉ ለመኖር የሚያስችለው ሕግ የሚመጣው ከወንጌል ነው።

249. ***መዝሙር*** 111፡9 ጎልማሳ መንገዱን በምን ያነጻል? ቃልህን በመጠበቅ ነው።

250. ***መዝሙር*** 119፡105 ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴም ብርሃን ነው።

251. **1ዮሐንስ** 4፡9፣11 በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በኛ ዘንድ ተገለጠ። በእርሱ በኩል በሕይወት እንድንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና… ወላጆች ሆይ፣ እግዚአብሔር እንዲህ አድርጎ ከወደደን እኛ ደግሞ እርስ በእርሳችን ልንዋደድ ይገባናል።

*ማስታወሻ፡- **ሉቃስ 10፡27ን** ተመልከት።*

## *ኃጢአት*

### *78. ኃጢአት ምንድን ነው?*

የእግዚአብሔርን ሕግ የሚጻረረው አሳብ፣ ፍላጎት፣ ቃልና ድርጊት ሁሉ ኃጢአት ነው።

252. **1ዮሐንስ 3፡4** ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ አመጽን ደግሞ ያደርጋል፣ ኃጢአትም አመጽ ነው።

*ማስታወሻ፡-* የኃጢአት ሌላው ስም አለመታዘዝ (**ሮሜ** 5፡19)፣ በደል (**ማቴዎስ** 6፡12)፣ በደልና መተላለፍ (**ዘጸአት** 34፡7)፣ መሰሰት (**ማቴዎስ** 18፡5)፣ ጥሰት (**ሮሜ** 5፡17)፣ አለመጽደቅ (**ሮሜ** 6፡13)፣ ጥፋት (**ቆላስይስ** 3፡25)።

### *79. ኃጢአትን ወደ ዓለም ያመጣው ማን ነው?*

ዲያብሎስ አዳምና ሔዋንን በመፈታተን፣ እነርሱም ነጻ ፈቃዳቸውን ለፈተናው በመስጠታቸው ኃጢአትን ወደ ዓለም አመጣ።

253. **1ዮሐንስ 3፡8** ኃጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው፣ ዲያብሎስ ከመጀመሪያው ኃጢአትን ያደርጋልና።

253. ***ሮሜ 5፡12*** ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፡-* የሰው ውድቀት (**ዘፍጥረት** 3፡1-7)።

### *80. ስንት ዓይነት ኃጢአቶች አሉ?*

ኃጢአት ሁለት ዓይነት ነው፣ የውርስ ኃጢአትና የግብር ኃጢአት።

### *81. የውርስ ኃጢአት ምንድን ነው?*

የውርስ ኃጢአት በወላጆቻችን በኩል ከአዳም የወረስነው የሰብአዊ ተፈጥሮአችን ሁለንተና ሙሉ በሙሉ መበላሸቱ ነው።

255. **መዝሙር** 51፡5 እነሆ በአመጻ ተጸነስሁ እናቴም በኃጢአት ወለደችኝ።

256. **ዮሐንስ** 3፡6 ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፣ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው።

257. **ሮሜ** 5፡12 ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት፣ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስለ አደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ።

258. **ኤፌሶን** 4፡22 ፊተኛ ኑሮአችሁን እያሰባችሁ እንደሚያታልል ምኞት የሚጠፋውን አሮጌውን ሰው አስወግዱ።

### *82. የውርስ ኃጢአት በሰብአዊ ተፈጥሮ ላይ ያደረገው ምንድን ነው?*

### *የውርስ ኃጢአት*

ሀ. በሰዎች ሁሉ ላይ በደለኝነትና ኩነኔን አምጥቷል።

259. **ሮሜ** 5፡19 በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢአተኞች ሆኑ።

260. **ኤፌሶን** 2፡3 (እኛ) እንደ ሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን።

ለ. ኃጢአት ሰውን ሁሉ መንፈሳዊ ዕውር፣ ምውት እና የእግዚአብሔር ጠላት በማድረግ ያለ እግዚአብሔር ፍቅርና እውነተኛ ፍርሐት አስቀረ።

261. **ዘፍጥረት** 8፡21 የሰው ልብ አሳብ ከታናሽነቱ ጀምሮ ክፉ ነው።

262. **1ቆሮንቶስ** 2፡14 ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም፤ በመንፈስም የሚመረመር ስለሆነ ሊያውቀው አይችልም፡፡
263. **ኤፌሶን** 2፡1 በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ፡፡
264. **ሮሜ** 8፡7 ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና፤ ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና፣ መገዛትም ተስኖታል፡፡

ሐ. እያንዳንዱን ሰው ሁሉን ዓይነት የተግባር ኃጢአት እንዲሠራ ምክንያት ይሆነዋል፡፡

265. **ማቴዎስ** 7፡17 መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ ያደርጋል፣ ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬ ያደርጋል፡፡
266. **ገላትያ** 5፡19-21 የሥጋ ሥራ የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣኦትን ማምለክ፣ ሙዋርት፣ ጥል፣ ክርክር፣ ቅንአት፣ ቁጣ፣ አድመኝነት፣ መለያየት፣ መናፍቅነት፣ ምቀኝነት፣ መግደል፣ ስካር፣ ዘፋኝነት፣ ይህንም የሚመስል ነው፡፡

## *83. የተግባር ኃጢአት ምንድን ነው?*

የተግባር ኃጢአት የትኛውም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የሚቃረን በአሳብ፣ በፍላጎት፣ በቃል ወይም በሥራ የሚገለጥ ድርጊት ነው፡፡

267. **ማቴዎስ** 15፡19 ከልብ ክፉ አሳብ፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ በውሸት መመስከር፣ ስድብ ይወጣልና፡፡
268. **ያዕቆብ** 1፡15 ከዚህ በኋላ ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች፤ ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች፡፡
269. **ያዕቆብ** 4፡17 እንግዲህ በጎ ለማድረግ አውቆ ለማይሠራው ኃጢአት ነው፡፡ (የቸልተኝነት ኃጢአት)

## ሕግና ወንጌል

## *84. እግዚአብሔር የኃጢአት ይቅርታን የሚሰጠው ከየት ብቻ ነው?*

ክርስቶስ ሕግን በመፈፀሙ፣ ስለ እኛ መከራን በመቀበሉና በመሞቱ ምክንያት ከበደል፣ ከቅጣትና ከኃጢአት ኃይል ነጻ መሆናችንንና ለዘላለም መዳናችንን የምሥራች በሚነግረን በወንጌል ብቻ እግዚአብሔር የኃጢአት ይቅርታን ይሰጠናል፡፡

270. **ዮሐንስ** 3፡16 በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና፡፡
271. **ሮሜ** 1፡16 በወንጌል አላፍርምና … ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና፡፡
272. **ሮሜ** 10፡4 የሚያምኑ ሁሉ ይጸድቁ ዘንድ ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነውና፡፡
273. **ገላትያ** 3፡13 በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፏልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን፡፡
274. **ቆላስይስ** 1፡13-14 እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፣ ቤዛነቱንም እርሱንም የኃጢአትን ሥርየት ወደ አገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን፡፡

### *85. በሕግና በወንጌል መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?*

ሀ. ሕግ ምን ማድረግ እንዳለብንና እንደሌለብን ያስተምረናል፤ ወንጌል እግዚአብሔር ለድነታችን የሠራውንና አሁንም የሚሠራውን ያስተምረናል፡፡

ለ. ሕግ ኃጢአታችንንና የእግዚአብሔርን ቁጣ ያሳየናል፤ ወንጌል አዳኛችንንና የእግዚአብሔርን ጸጋ ያሳየናል፡፡

ሐ. ሕግ ለሰዎች ሁሉ ግን ደግሞ በተለይ ለማይፀፀቱ ኃጢአተኞች መሰበክ አለበት፤ ወንጌል ለኃጢአተኞች፣ በኃጢአታቸው ምክንያት ልባቸው ለታወከባቸው መሰበክ አለበት፡፡



## የሐዋርያት የእምነት መግለጫ

***86. የእምነት መግለጫ ምንድን ነው?***

*የእምነት መግለጫ ማለት የምናምነው፣ የምናስተምረውና የምንመሰክረው ቃል ነው።*

275. **ሮሜ** 10፡10 ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መሥክሮ ይድናልና።

***አምናለሁ***

***87. ‹‹በእግዚአብሔር አምናለሁ›› ማለት ምን ማለት ነው?***

እግዚአብሔርንና ተስፋዎቹን አምናለሁ በቅዱሳት መጻሕፍትም ያስተማረውን እቀበላለሁ ማለት ነው።

276. ***መዝሙር*** 31፡14 አቤቱ፣ እኔ ግን በአንተ ታመንሁ፤ ‹‹አንተ አምላኬ ነህ›› አልሁ።

277. ***መዝሙር*** 37:5 መንገድህን ለእግዚአብሔር አደራ ስጥ፣ በእርሱም ታመን።

278. **ሮሜ** 10፡17 እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው።

279. ***ዕብራውያን*** 11፡1 እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፣ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው።

***88. ‹‹እናምናለን›› ሳይሆን ‹‹አምናለሁ›› የምንለው ለምንድን ነው?***

እያንዳንዱ ለራሱ ወይም ለራሷ ማመን አለበት/ባት፣ ማንም በሌላው እምነት ሊድን አይችልም።

280. ***ዕንባቆም*** 2፡4 ጻድቅ በእምነቱ በሕይወት ይኖራል።

281. ***ሉቃስ*** 7፡50 እምነትሽ አድኖሻል፤ በሰላም ሂጂ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፦* ሰነፎቹ ልጃገረዶች ከልባሞቹ ልጃገረዶች ዘይት ማግኘት አልቻሉም (**ማቴዎስ** 25፡1-13)።

***89. ቤተ ክርስቲያን የምትጠቀምባቸው ሦስቱ የእምነት መግለጫዎች የትኞቹ ናቸው?***

የሐዋርያት፣ የኒቂያና የአትናቲዎስ የእምነት መግለጫዎች ናቸው።

***90. በሉተር የክርስትና ማስተማሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ የትኛው የእምነት መግለጫ ነው?***

የሐዋርያት የእምነት መግለጫ ነው።

### *91. የሐዋርያት የእምነት መግለጫ ለምን ተባለ?*

የሐዋርያት የእምነት መግለጫ የተባለው በራሳቸው በሐዋርያቱ ስለ ተጻፈ አይደለም፣ ነገር ግን እግዚአብሔር በሐዋርያቱ አማካይነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሰጠውን መሠረተ-እምነት (የክርስትና ትምህርት) በአጭሩ ስለሚያብራራ ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት እግዚአብሔርን በሥላሴነቱ ስለሚገልጡት የእምነት መግለጫውም ሥላሴያዊ ነው። ክርስቲያኖች በአብ፣ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ሥላሴ ስም ይጠመቃሉ።

282. **ማቴዎስ** 28፡19 እንግዲህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኂቸው … ደቀ መዛሙርቴ አድርጓቸው።
283. **ኤፌሶን** 4፡4-6 በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤ አንድ ጌታ፤ አንድ እምነት፤ አንዲት ጥምቀት፤ ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ።

### *92. ሥላሴ ራሱን የሚገልጠው እንዴት ባሉ መንገዶች ነው?*

*ሀ.* በፍጥረተ-ዓለም መኖር አማካይነት (በተፈጥሮ እግዚአብሔርን ማወቅ)

284. **መዝሙር** 19፡1 ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፣ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል።
285. **ሮሜ** 1፡19-20 እግዚአብሔር ስለ ገለጠላቸው፣ ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ነውና። የማይታየው ባህርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና።
286. **ዕብራውያን** 3፡4 እያንዳንዱ ቤት በአንድ ሰው ተዘጋጅቷልና፣ ሁሉን ያዘጋጀ ግን እግዚአብሔር ነው።

ለ. በሕሊና አማካይነት (በተፈጥሮ እግዚአብሔርን ማወቅ)

287. **ሮሜ** 2፡15 እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው፤ አሳባቸውም እርስ በእርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ።

ሐ. እግዚአብሔር ራሱንና በክርስቶስ የድነት ስጦታውን በተለይ በግልጽ በሚገለጥባቸው በቅዱሳት መጻሕፍቱ አማካይነት ነው። (በመገለጥ የሆነ እግዚአብሔርን ማወቅ)

288. **ዮሐንስ** 20፡31 ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ታምኑ ዘንድ፣ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ (የኢየሱስ ሥራ) ተጽፏል።
289. **2ጢሞቴዎስ** 3፡15 ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፣ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን አውቀሃል።
290. **ዕብራውያን** 1፡1-2 ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነብያት ተናግሮ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን።

### *93. እግዚአብሔር ማን ነው?*

እግዚአብሔር ማን መሆኑን በቃሉ ውስጥ ነግሮናል፦

*ሀ. መንፈስ ነው (የሥጋን አካል ያልለበሰ እኔ ባይ ማንነት ያለው)*

291. **ዮሐንስ** 4፡24 እግዚአብሔር መንፈስ ነው።

ለ. ዘላለማዊ ነው (መጀመሪያና መጨረሻ የለውም)

292. **መዝሙር** 90፡1-2 አቤቱ አንተ ለትውልድ ሁሉ መጠጊያ ሆንህልን፡፡ ተራሮች ሳይወለዱ፣ ምድርም ዓለምም ሳይሠሩ፣ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ አንተ ነህ፡፡
293. **1ጢሞቴዎስ** 1፡17 ብቻውን አምላክ ለሚሆን ለማይጠፋው ለማይታየውም ለዘመናት ንጉሥ ምስጋናና ክብር እስከ ዘላለም ድረስ ይሁን አሜን፡፡

ሐ. አይለወጥም (ኢሚዩቴብል)

294. **መዝሙር** 102፡27 አንተ ግን ያው አንተ ነህ፣ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም፡፡
295. **ሚልክያስ** 3፡6 እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም፡፡
296. **ያዕቆብ** 1፡17 በጎ ስጦታ ሁሉ ፍፁምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፣ መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ፡፡

መ. ኃያል፣ ሁሉን ቻይ (ኦምኒፖተንት)

297. **ዘፍጥረት** 17፡1 እኔ ኤልሻዳይ ነኝ፡፡
298. **ማቴዎስ** 19፡26 በእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉ ይቻላል፡፡

ሠ. ሁሉን ያውቃል (ኦምኒሼንት)

299. **መዝሙር** 139፡1-4 አቤቱ፣ መረመርኸኝ፣ አወቅኸኝም፡፡ አንተ መቀመጤንና መነሳቴን አወቅህ አሳቤን ሁሉ ከሩቅ አስተዋልህ፡፡ ከአፌ ቃል ሳይወጣ፣ አቤቱ አንተ አስቀድመህ ሁሉን ታውቃለህ፡፡
300. **ዮሐንስ** 21፡17 ጌታ ሆይ አንተ ሁሉን ታውቃለህ፡፡

ረ. በሁሉ ቦታ ይገኛል (ኦምኒፕረዘንት)

301. **ኤርምያስ** 23፡24 ሰው በስውር ቢሸሸግ እኔ አላየውምን? ሰማይንና ምድርንስ የሞላሁ እኔ አይደለሁምን? ይላል እግዚአብሔር፡፡
302. **የሐዋርያት ሥራ** 17፡27 ቢሆንም ከእያንዳንዳችን የራቀ አይደለም፡፡

ሰ. ቅዱስ ነው (ኃጢአት የለበትም፤ ኃጢአትን ይጠላል)

303. **ዘሌዋውያን** 19፡2 እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝ፡፡
304. **መዝሙር** 5፡4-5 አንተ በደልን የማትወድ አምላክ ነህና ክፉ ከአንተ ጋር አያድርም፡፡ በከንቱ የሚመኩ በዐይኖችህ ፊት አይኖሩም፤ ክፉ አድራጊዎችን ሁሉ ጠላህ፡፡
305. **ኢሳይያስ** 6፡3 ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፡፡

ሸ. ጻድቅ (ፍትሃዊና የማያዳላ)

306. **ዘዳግም** 32፡4 አለቱ፣ ሥራውም ፍጹም ነው፤ መንገዱም ሁሉ የቀና ነው፣ የታመነ አምላክ ክፋትም የሌለበት፡፡

ቀ. ታማኝ (ቃል ኪዳኑን የሚጠብቅ)

307. **2ጢሞቴዎስ** 2፡13 ባናምነው እርሱ የታመነ ሆኖ ይኖራል፣ ራሱን ሊክድ አይችልምና፡፡

በ. ቸር ነው (ደግ፣ በጎነታችንን የሚፈልግ)

308. **መዝሙር** 118፡1 እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ ቸር ነውና ምሕረቱ ለዘላለም ናትና፡፡
309. **መዝሙር** 145፡9 እግዚአብሔር ለሚታገሱት ቸር ነው፤ ምሕረቱም በሥራው ላይ ነው፡፡

ተ. መሐሪ ነው (ሐዘኔታን የተሞላ)

310. **ኤርምያስ** 3፡12 መሐሪ ነኝና … ይላል እግዚአብሔር፡፡

311. **ቲቶ 3:5** እንደ ምሕረቱ መጠን … አዳነን እንጂ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለ ነበረው ሥራ አይደለም፡፡

ቸ. ደግነት (ያልተቆጠበ በጎነትን የሚያሳይ፣ ይቅር ባይ)

312. **ዘጸአት 34:6-7** እግዚአብሔር መሐሪ፣ እግዚአብሔር ሞገስ ያለው፣ ታጋሽም፣ ባለ ብዙ ቸርነትና እውነት፣ እስከ ሺህ ትውልድም ቸርነትን የሚጠብቅ፣ አበሳንና መተላለፍን ኃጢአትንም ይቅር የሚል፡፡

ኀ. ፍቅር

313. **ዮሐንስ 3:16** በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና፡፡

314. **1ዮሐንስ 4:8** እግዚአብሔር ፍቅር ነው፡፡

*ማስታወሻ፡-* የእግዚአብሔር ባህርያት እግዚአብሔር ማን እንደሆነ ይነግሩናል፡፡ እግዚአብሔር እያንዳንዱን ባህሪውን፣ ሁሉንም ባህርያቱን እና ከእነዚህ ባህሪያቱ ሁሉ የላቀም ነው፡፡

### *94. ብቸኛው እውነተኛ አምላክ ማን ነው?*

ብቸኛው እውነተኛ አምላክ ሥላሴ ነው፤ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ አንድ መለኮት በሦስት ለየብቻቸው በሆኑ አካላት (ቅድስት ሥላሴ)፡፡

### *95. ሦስቱ መለኮታዊ አካላት ተለያይተው የሚታወቁት እንዴት ነው?*

አብ ወልድን ከዘላለም ወልዶታል፤ ወልድ ከዘላለም ከአብ ተወልዷል፤ መንፈስ ቅዱስ ከዘላለም ከአብና ከወልድ ይሠርጻል፡፡ የመፍጠር ሥራ በተለይ ለአብ፣ የማዳን ሥራ ለወልድ፣ የመቀደስ ሥራ ለመንፈስ ቅዱስ ውሏል፡፡

315. **መዝሙር 2:7** አንተ ልጄ ነህ፣ እኔ ዛሬ ወለድሁህ፡፡

316. **ዮሐንስ 15:26** ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል፡፡

317. **ገላትያ 4:6** ልጆችም ስለ ሆናችሁ እግዚአብሔር አብ አባት ብሎ የሚጮህ የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ ላከ፡፡

## *የመጀመሪያው አንቀጽ*

**ፍጥረት**

እኔ ሁሉን በሚችል ሰማይና ምድርን በፈጠረ በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ፡፡

*ይህ ምን ማለት ነው?* እግዚአብሔር እኔንና ፍጥረትን በሙሉ እንደ ፈጠረ አምናለሁ፡፡ እርሱ ነፍስና ሥጋን፣ ዐይን፣ ጆሮና መላው የአካል ክፍሌን የሚያመዛዝን ችሎታንና ስሜቶችን ሁሉ ሰጥቶኛል፡፡ ደግሞም ይንከባከባቸዋል፡፡

በተጨማሪም እግዚአብሔር ልብስና ጫማ፣ ምግብና መጠጥ፣ ቤትና መኖሪያ፣ ሚስትና ልጆችን፣ መሬትና እንስሳትን እንዲሁም ያለኝን ሁሉ

> የሰጠኝ እርሱ ነው፡፡ ይህንን ሥጋዬንና ሕይወቴን ለመደገፍ የሚያስፈልገኝን ሁሉ በየዕለቱ አትረፍርፎ ይሰጠኛል፡፡
> እርሱ ከማንኛውም አደጋ ይጠብቀኛል፤ እንዲሁም ከክፉ ሁሉ ይጋርደኛል፣ ያድነኛልም፡፡
> ይህንን ሁሉ የሚያደርገው ከእኔ መልካም ሥራ ወይንም የተገባኝ ስለ ሆንኩኝ ሳይሆን ከአባታዊ፣ መለኮታዊ በጎነቱና ቸርነቱ የተነሣ ነው፡፡ ስለ እነዚህ ሁሉ እርሱን ማመስገንና ማወደስ፣ ማገልገልና መታዘዝ ተግባሬ ነው፡፡
> ይህ ፍጽም እውነት ነው፡፡

### *96. የሥላሴ የመጀመሪያው አካል ‹‹አባት›› የተባለው ለምንድን ነው?*

ሀ. እግዚአብሔር የጌታዬ የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ነው ደግሞም በክርስቶስ በማመኔ የእኔም አባት ነው፡፡

318. **ማቴዎስ** 3፡17 እነሆም ድምፅ ከሰማያት መጥቶ፡- ‹‹በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ፡፡››
319. **ዮሐንስ** 20፡17 እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁም አርጋለሁ፡፡
320. **ገላትያ** 3፡26 በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና፡፡

ለ. ደግሞም ፈጥሮአቸዋልና እግዚአብሔር የሰዎች ሁሉ አባት ነው፡፡ አስረግጦ ለመናገር፣ አንድ የሰው ዘር ብቻ ነው ያለው፣ ምክንያቱም ሰዎች ሁሉ እኩል የአዳምና የሔዋን ልጆች ናቸው በእኩልም በክርስቶስ ተዋጅተዋልና፡፡

321. **ሚልክያስ** 2፡10 ለሁላችን አንድ አባት ያለን አይደለምን? አንድ አምላክ የፈጠረን አይደለምን?
322. **የሐዋርያት ሥራ** 17፡26 በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩ የሰውን ወገኖች ሁሉ ከአንድ ፈጠረ፡፡
323. **1ቆሮንቶስ** 15፡22 ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና፡፡
324. **ኤፌሶን** 3፡14-15 ስለዚህ ምክንያት በሰማይና በምድር ያለ አባትነት ሁሉ ከሚሰየምበት ከአብ ፊት እንበረከካለሁ፡፡

    *የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፡-* የጠፋው ልጅ (**ሉቃስ** 15፡11-32)፡፡

## *እግዚአብሔር እኔንና መላውን ፍጥረት ፈጠረ*

### *97. ሁሉን ቻዩ እግዚአብሔር አብ ‹‹ሰማይንና ምድርን የፈጠረ›› የሚባለው ለምንድን ነው?*

ምክንያቱም እርሱ ሁሉን ነገር በስድስት ቀናት ውስጥ በቃሉ ብቻ ከምንም ነገር ፈጥሯልና፡፡

325. **ዘፍጥረት** 1፡1 በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ፡፡

326. ***መዝሙር*** 33፡6፣9 በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ፀኑ፣ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ … እርሱ ተናግሯልና፣ ሆኑም፤ እርሱ አዘዘ፣ ፀኑም።

327. ***ዕብራውያን*** 11፡3 ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ፣ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፦* ፍጥረት (**ዘፍጥረት** 1-2)።

### *98. ‹‹ሰማይና ምድር›› ማለት ምን ማለት ነው?*

የሚታዩትና የማይታዩት ነገሮች ሁሉ ማለት ነው።

328. **ቆላስይስ** 1፡16 የሚታዩትና የማይታዩትም … በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና።

## *መላእክት*

### *99. በተለይ ለእኛ የሚያስፈልጉን በእግዚአብሔር የተፈጠሩ የማይታዩ ፍጥረታት የትኞቹ ናቸው?*

መላእክት ናቸው።

*ማስታወሻ-* መልአክ ‹‹መልእክተኛ›› ማለት ነው። በድነት ታሪክ ውስጥ አስፈላጊ ጉዳዮችን እንዲያስታውቁ እግዚአብሔር አዘውትሮ መላእክትን ተጠቅሟል፤ የመጥምቁ ዮሐንስን መወለድ (**ሉቃስ** 1፡1-20)፣ የኢየሱስን መወለድ (**ሉቃስ** 1፡6-38፤ **ማቴዎስ** 1፡18-21)፤ የኢየሱስን ትንሣኤ (**ሉቃስ** 24፡4-7)፤ የኢየሱስን ዕርገትና ዳግመኛ መምጣት (**የሐዋርያት ሥራ** 1፡10-11)።

### *100. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መላእክት በተጨማሪ የሚነግረን ምንድን ነው?*

ሀ. ቅዱስ ሆነው የተፈጠሩ መንፈሳዊ ፍጥረታት ናቸው።

329. **ዘፍጥረት** 1፡31 እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ፣ እነሆም እጅግ መልካም ነበር። ማታም ሆነ ጠዋትም ሆነ፣ ስድስተኛ ቀን።

ለ. ጥቂቶቹ መላእክት በእግዚአብሔር ላይ አመፁ። እነርሱም ዲያብሎሶች ወይም አጋንንት ናቸው።

330. **2ጴጥሮስ** 2፡4 እግዚአብሔር ኃጢአትን ላደረጉ መላእክት ሳይራራላቸው ወደ ገሃነም ጥሎ በጨለማ ጉድጓድ ለፍርድ ሊጠበቁ አሳልፎ ሰጣቸው።

ሐ. ቅዱሳኑ መላእክት ብዙዎችና ኃይለኞችም ናቸው። እነርሱ እግዚአብሔርን ያገለግላሉ እኛንም ያግዛሉ።

331. **ዳንኤል** 7፡10 ሺህ ጊዜ ሺህ ያገለግሉት ነበር፣ እልፍ አዕላፋትም በፊቱ ቆመው ነበር።

332. **ሉቃስ** 2፡13 ድንገትም ከመልአኩ ጋር እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ብዙ የሰማይ ሠራዊት ነበሩ።

333. ***መዝሙር*** 103፡20-21 ቃሉን የምትፈጽሙ፣ ብርቱዎችና ኃያላን፣ የቃሉንም ድምፅ የምትሰሙ መላእክቱ ሁሉ፣ እግዚአብሔርን ባርኩ። ሠራዊቱ ሁሉ፣ ፈቃዱን የምታደርጉ አገልጋዮቹ፣ እግዚአብሔርን ባርኩ።

334. ***መዝሙር*** 91፡11-12 *በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና እግርህም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሱሃል።*

335. ***ዕብራውያን*** 1፡14 *ሁሉ መዳንን ይወርስ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን?*

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፡-* አንዱ መልአክ ከሰናክሬም ሠራዊት 185,000 ገደለ (2***ነገሥት*** 19፡35)። ኤልሳዕና አገልጋዩ በሠማይ ሠራዊት ተጠበቁ (2***ነገሥት*** 6፡15-17)። አንድ መልአክ ጴጥሮስን ከወህኒ አወጣው (***የሐዋርያት ሥራ*** 12፡5-11)።

*መ.* ክፉዎቹ መላእክትም ብዙዎችና ኃይለኞች ናቸው። እግዚአብሔርን ይጠላሉ፣ መልካም የሆነውን ሁሉ በተለይም በክርስቶስ ማመንን ለማጥፋት ይፈልጋሉ።

336. ***ማርቆስ*** 5፡9 *ኢየሱስም ‹‹ስምህ ማነው?›› ብሎ ጠየቀው። ‹‹ብዙዎች ነንና ስሜ ሌጌዎን ነው›› አለው።*

337. ***ኤፌሶን*** 6፡12 *መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፣ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዢዎች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳዊያን ሠራዊት ጋር ነው እንጅ።*

338. ***ማርቆስ*** 4፡15 *ቃልም በተዘራበት በመንገድ ዳር የሆኑት እነዚህ ናቸው፣ በሰሙት ጊዜም ሠይጣን ወዲያው መጥቶ በልባቸው የተዘራውን ቃል ይወስዳል።*

339. ***ዮሐንስ*** 8፡44 *እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ። እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበር እውነትም በእርሱ ስለሌለ በእውነት አልቆመም። ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፣ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና።*

340. **1ጴጥሮስ** 5፡8-9 *በመጠን ኑሩ ንቁም፣ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞራልና፤ በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ በእምነት ፀንታችሁ ተቃወሙት።*

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፡-* እባብ ሔዋንን ወደ ኃጢአት መራት (**ዘፍጥረት** 3፡1-5)። ሰይጣን የኢዮብን ጥፋት ፈለገ (**ኢዮብ** 2)። ፈታኙ ኢየሱስን ለማሳት ሞከር (**ማቴዎስ** 4፡1-11)።

## ሰብዓዊ ፍጥረት

### *101. ሰብዓዊ ፍጥረታት እንማን ናቸው?*

ሰብዓዊ ፍጥረታት እጅግ አስፈላጊ የሆኑ የሚታዩ ፍጥረታት ናቸው። በምድር ሁሉ ላይ ሥልጣን እንዲኖራቸው እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን በራሱ አምሣል ፈጠራቸው።

341. **ዘፍጥረት** 2፡7 *እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፣ ባፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት፣ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ።*

342. **ዘፍጥረት** 1፡26-28 *እግዚአብሔርም አለ፡- ‹‹ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር፤ የባህር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፣ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፣ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ። እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። እግዚአብሔርም ባረካቸው፣ እንዲህም*

አላቸው፡- ብዙ፣ ተባዙ፣ ምድርንም ሙሏት፣ ግዙአትም፤ የባህርን ዓሣዎችና ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዟቸው፡፡››

343. **ማርቆስ** 10፡6 [ኢየሱስም አለ]፡- ‹‹ከፍጥረት *መጀመሪያ ግን እግዚአብሔር ወንድና ሴት አደረጋቸው፡፡››*

### *102. ‹‹እግዚአብሔር ፈጠረኝ›› የምንለው ለምንድን ነው?*

እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ወንድና ሴት ፈጠራቸው፣ እያንዳንዳችንንም እርሱ ፈጠረን፡፡

344. **ዘፍጥረት** 1፡28 ‹‹እግዚአብሔርም ባረካቸው፣ እንዲህም አላቸው፡- ብዙ፣ ተባዙ፣ ምድርንም ሙሏት፣ ግዟትም፤ የባህርን ዓሣዎችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዟቸው፡፡››

345. **መዝሙር** 139፡13 አቤቱ፣ አንተ ኩላሊቴን ፈጥረሃልና፣ በእናቴም ሆድ ሰውረኸኛል፡፡

346. **ኤርምያስ** 1፡5 በሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ ...፡፡

### *103. በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሕይወትን የፈጠረው እንዴት ነበር?*

እግዚአብሔር ሕይወት ያላቸውን ነገሮች በሙሉ፣ እፅዋትንና እንስሳትን ካለምንም ነገር በቃሉ ብቻ ፈጠራቸው፡፡ በተለይ ሰብዓዊ ፍጡርን ከምድር አፈር ፈጠረው፣ ከዚያም የራሱን እስትንፋስ ሕይወት አድርጎ ሰጠን፡፡

347. **ዘፍጥረት** 2፡7 እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም የሕይወትን እስትንፋስ እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ፡፡

348. **መዝሙር** 139፡14 ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃለሁ፤ ሥራህ ድንቅ ነው፣ ነፍሴም እጅግ ታውቀዋለች፡፡

### *104. ሕይወት ያላቸው ነገሮች እንዲባዙ እግዚአብሔር የሚጠቀምበት ዕቅድ ምንድን ነው?*

እግዚአብሔር ሕይወት ያላቸውን ነገሮች ‹‹እንደየወገናቸው›› እንዲባዙ ፈጠራቸው፡፡ ዕፀዋት፣ እንስሳትና ሰዎች የራሳቸውን ዓይነት ሕይወት ያለው ነገር ብቻ ማባዛት ይችላሉ፡፡

349. **ዘፍጥረት** 1፡21 እግዚአብሔርም ታላላቆች አንበሪዎችን፣ ውኃይቱ እንደ ወገኑ ያስገኘቻቸውንም ተንቀሳቃሾቹንም ሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ፣ እንደ ወገኑ የሚበሩትንም ወፎች ሁሉ ፈጠረ፤ እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ ሆነ አየ፡፡

350. **ዘፍጥረት** 1፡24 እግዚአብሔርም አለ፡- ‹‹ምድር ሕያዋን ፍጥረታትን እንደ ወገኑ፣ እንስሳትንና ተንቀሳቃሾችን የምድር አራዊትንም እንደ ወገኑ፣ ታውጣ፤ እንዲሁም ሆነ››

### *105. ክርስቲያኖች የፍጥረት መጀመሪያን አስመልክቶ ለዝግመተ ለውጥ ፅንሰ አሳብ አግባብነት ያለው ምላሻቸው ምንድን ነው?*

ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ቃል ስለ ፍጥረት የሚያስተምረውን በእምነት ይቀበላሉ፡፡ የዝግመታዊ ለውጥ ፅንሰ አሳብ በሳይንሳዊ መንገድ የተረጋገጠ አይደለም፡፡

351. ***ዕብራውያን*** 11፡3 ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ፣ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን፡፡

352. **2ጴጥሮስ** 3፡5-6 *ሰማያት ከጥንት ጀምረው ምድርም በእግዚአብሔር ቃል ከውኃ ተጋጥማ በውኃ መካከል እንደ ነበሩ ወደው አያስተውሉምና።*

353. **1ጢሞቴዎስ** 6፡20-21 *በውሸት እውቀት ከተባለ ለዓለም ከሚመች ከከንቱ መለፍለፍና መከራከር እየራቅህ፣ የተሰጠኽን አደራ ጠብቅ፤ ይህ ‹‹ዕውቀት›› አለን ብለው፣ አንዳንዶች ስለ እምነት ስተዋልና።*

### *106. የእግዚአብሔር አምሣል ምን ነበር?*

የእግዚአብሔር አምሣል ይህ ነበር፡-

*ሀ. አዳምና ሔዋን እግዚአብሔር ለመታወቅ በሚፈልገው ሁኔታ በእውነት ያወቁትና ሙሉ በሙሉ በእርሱ ደስ ይሰኙበት ነበር።*

354. **ቆላስይስ** 3፡10 *የፈጠረውንም ምሣሌ እንዲመስል ዕውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታል።*

*ለ. የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርጉ ቅዱሳንና ጻድቅ ነበሩ።*

355. **ኤፌሶን** 4፡24 *ለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሣሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ።*

### *107. ሰዎች አሁንም የእግዚአብሔር አምሣል አላቸው?*

*የላቸውም፣ የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን እግዚአብሔርን ባልታዘዙትና በኃጢአት በወደቁ ጊዜ ይህ አምሣል ጠፍቶባቸዋል። ፈቃዳቸውና የማሰብ ችሎታቸው እግዚአብሔርን የማወቅና የማስደሰት አቅም አጣ። እግዚአብሔር የራሱን አምሣል በክርስቲያኖች ውስጥ ለማደስ ጀምሯል፣ ነገር ግን ሙሉ በሙሉ ይህ የሚታየው በሰማይ ብቻ ነው።*

356. **ዘፍጥረት** 3፡8-10 *እነርሱም ቀኑ በመሸ ጊዜ የእግዚአብሔርን የአምላክን ድምፅ ከገነት ውስጥ ሲመላለስ ሰሙ፣ አዳምና ሚስቱም ከእግዚአብሔር ከአምላክ ፊት በገነት ዛፎች መካከል ተሸሸጉ። እግዚአብሔር አምላክም አዳምን ጠርቶ ‹‹ወዴት ነህ?›› አለው። እርሱም አለ፡- ‹‹በገነት ድምፅህን ሰማሁ፣ ራቁቴንም ስለ ሆንሁ ፈራሁ፣ ተሸሸግሁም።››*

357. **ዘፍጥረት** 5፡3 *አዳምም … ልጅንም በምሣሌው እንደ መልኩ ወለደ።*

358. **1ቆሮንቶስ** 2፡14 *ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም፤ በመንፈስም የሚመረመር ስለሆነ ሊያውቀው አይችልም።*

359. **መዝሙር** 17፡15 *እኔ ግን በጽድቅ ፊትህን አያለሁ፤ ክብርህን ሳይ እጠግባለሁ።*

## *እግዚአብሔር አሁንም እኔና ፍጥረቱን በሙሉ ይንከባከባል*

### *108. በሥነ ፍጥረት ውስጥ ያለው ሁሉ አሁንም በእግዚአብሔር ላይ የሚደገፈው እንዴት ነው?*

*እግዚአብሔር በጥበቡና በኃይሉ ሁሉንም ነገር ደግፎ ያቆያል።*

360. **መዝሙር** 36፡6 *አቤቱ፣ ሰውንና እንስሳን ታድናለህ።*

361. **መዝሙር** 147፡4 *የከዋክብትንም ብዛት ይቆጥራል፣ ሁሉንም በየስማቸው ይጠራቸዋል።*

362. **ዕብራውያን** 1፡3 *እርሱም (ልጁ) የክብሩ መንፀባረቅና የባህርዩ ምሳሌ ሆኖ፣ ሁሉም በሥልጣኑ ቃል እየደገፈ …።*

363. **ቆላስይስ** 1፡17 (ኢየሱስ) ከሁሉ በፊት ነው ሁሉም በእርሱ ተጋጥሚል።

### *109. ክፋትና መከራ ለምን በዚህ ዓለም ውስጥ ኖረ?*

ክፋትና መከራ በዓለም ውስጥ የኖረው በኃጢአት ምክንያት ነው። ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ መከራ ሞትና ትንሣኤ እግዚአብሔር በኃጢአትና በሞት ላይ ያለውን ኃይል ገልጧል። እግዚአብሔር ሁሉን በሚችልበት ኃይሉ እርሱን ለሚወዱት ሁሉም ነገር ለበጎ እንዲሆን ያደርጋል።

364. **ሮሜ** 6፡23 የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና የእግዚአብሔር የፀጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው።

365. **ሮሜ** 8፡28 እግዚአብሔርን ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።

366. **ሮሜ** 8፡37 በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።

### *110. እግዚአብሔር እኔን ለመንከባከብ ምን ያደርጋል?*

ሀ. እርሱ ምግብና ልብስን፣ ቤትና ቤተሰብን፣ ሥራና ጨዋታን እንዲሁም ለየዕለቱ የሚያስፈልገኝን ሁሉ ይሰጠኛል።

367. **መዝሙር** 145፡15-16 የሁሉ ዐይን አንተን ተስፋ ያደርጋል፤ አንተም ምግባቸውን በየጊዜው ትሰጣቸዋለህ። አንተ እጅህን ትከፍታለህ፣ ሕይወት ላለውም ሁሉ መልካምን ታጠግባለህ።

368. **1ጴጥሮስ** 5፡7 እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፦* እግዚአብሔር ኖኅንና ልጆቹን ተንከባከባቸው ***(ዘፍጥረት 9፡1-3)።*** እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በምድረበዳ ተንከባከባቸው (***ዘዳግም*** 8፡3-4)። በረሃቡ ወቅት እግዚአብሔር ኤልያስን፣ ባልቴቲቱንና ልጇን ተንከባከባቸው (1***ነገሥት*** 17)። ***መዝሙር*** 37 እና 104ን ተመልከት።

ለ. ‹‹ከማንኛውም አደጋ ይጠብቀኛል፤ እንዲሁም ከክፉ ሁሉ ይጋርደኛል፣ ያድነኛልም።››

369. **ዘፍጥረት** 50፡20 እናንተ ክፉ ነገርን አሰባችሁብኝ እግዚአብሔር ግን ዛሬ እንደ ሆነው ብዙ ሕዝብ እንዲድን በማድረግ ለመልካም አሰበው።

370. ***መዝሙር*** 31፡15 ዘመኖቼ በእጅህ ናቸው።

371. ***ማቴዎስ*** 10፡29-30 ሁለት ድንቢጦች በአምስት ሣንቲም ይሸጡ የለምን? ከነእርሱም አንዲቱን ያለአባታችሁ ፈቃድ በምድር ላይ አትወድቅም። የእናንተስ የራሳችሁ ፀጉር ሁሉ እንኳ ተቆጥሯል።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፦* ሰዶም ከመጥፋቱ በፊት ሎጥ ወደ ተራሮቹ እንዲሸሽ እግዚአብሔር አመለከተው (**ዘፍጥረት** 19)። እግዚአብሔር እስራኤልን ከባርነት ነፃ አውጥቶ በመንገዳቸው መራቸው፣ ጠበቃቸውም (**ዘጸአት** 13፡14)። ***መዝሙር*** 37 እና 73ን ተመልከት።

### *111. እግዚአብሔር ይህንን የሚያደርግልን ለምንድን ነው?*

‹‹ይህንን ሁሉ የሚያደርገው ስለ መልካም ሥራዬ ወይም የተገባኝ ስለ ሆንኩ ሳይሆን ከአባታዊ፣ ከመለኮታዊ በጎነቱና ቸርነቱ የተነሣ ነው።››

372. **ዘፍጥረት** 32፡10 ለባሪያህ ከሠራኸው ከምሕረትህና ከእውነትህም ሁሉ ትንሽ ስንኳ የማይገባኝ ነኝ፡፡

373. ***መዝሙር*** 103፡13 አባት ለልጆቹ እንደሚራራ እንዲሁ እግዚአብሔር ለሚፈሩት ይራራል፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፦ የቅፍርናሆሙ የመቶ አለቃ ጌታ ከቤቱ ጣሪያ ሥር ይገባ* ዘንድ እርሱ ብቁ እንዳልሆነ ተናዘዘ ***(ሉቃስ 7፡6-7)፡፡***

### *112. ስለ ቸርነቱ ሁሉ ለሰማዩ አባታችን የምንመልሰው ምንድን ነው?*

*የሚከተለውን ማድረግ ተግባራችን ነው፡-*

*ሀ. ‹‹እርሱን ማመስገንና ማወደስ፣ ማገልገልና መታዘዝ፤*

374. ***መዝሙር*** 116፡12 ስላደረገልኝ ሁሉ ለእግዚአብሔር ምን እመልሳለሁ?

375. ***መዝሙር*** 118፡1 እግዚአብሔርን አመስግኑ፣ ቸር ነውና ምሕረቱም ለዘላለም ናትና፡፡

*ለ. የፍጥረቱ መልካም መጋቢዎች መሆን፡፡*

376. **ዘፍጥረት** 2፡15 እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በኤደን ገነት አኖረው፡፡

*ማስታወሻ፦* የአየር፣ የአፈርና የውኃ መበከልን ስንከላከል ቆሻሻን በአግባቡ ስናስወግድ፣ የተፈጥሮ ሃብትን ሳናባክን ስንጠቀም፣ ኃይልን ከማባከን ይልቅ ስንቆጥብ፣ በተቻለ መጠን ቁሳቁሶችን መልሰን ወይም በሌላ መልክ መጠቀም ስንችልና እግዚአብሔር ለፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ ዋጋ በምንሰጥበትና በምንንከባከብበት ጊዜ መልካም መጋቢዎች ነን፡፡

### *113. የመጀመሪያውን አንቀፅ ማብራሪያ ‹‹ይህ ፍፁም እውነት ነው›› በሚሉ ቃላት የምንደመድመው ለምንድን ነው?*

በዚህ አንቀፅ ውስጥ የምመሰክረው ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል በሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልፅ ትምህርት ተሰጥቶበታል፡፡ ስለሆነም በጽኑ አምነዋለሁ፡፡

## *ሁለተኛው አንቀጽ*

### *ድነት*

ደግሞም በአንድ ልጁ በመንፈስ ቅዱስ በተፀነሰ፣ ከድንግል ማርያም በተወለደ፣ በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን መከራን በተቀበለ፣ በተሰቀለ፣ በሞተ፣ በተቀበረ፣ ወደ ሲዖል በወረደ፣ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን በተነሣ፣ ወደ ሰማይ በወጣ፣ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ ቀኝ በተቀመጠ፣ በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ ከዚያ በሚመለስ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ፡፡

*ይህ ምን ማለት ነው?* እውነተኛ አምላክ የሆነው፣ በዘላለማዊነት ከአብ የተወለደው፣ እንዲሁም ደግሞ እውነተኛ ሰው የሆነውና ከድንግል ማርያም የተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታዬ መሆኑን አምናለሁ፡፡ እርሱም እኔን የጠፋሁትንና ኩነኔ የተፈረደብኝን ሰው ተቤዥቶኛል፡፡ በወርቅና በብር ሳይሆን ዳሩ ግን ቅዱስና ክቡር በሆነው ደሙ እንዲሁም

> ያለ ኃጢአቱ በተሰቀለው መከራና በሞቱ ከኃጢአት፣ ከሞትና ከዲያብሎስ ኃይል ገዝቶኝ ነፃ አውጥቶኛል። ይህን ሁሉ ያደረገው እኔ የእርሱ ገንዘብ እንድሆን፣ በመንግሥቱ ውስጥ በእርሱ ሥር እንድኖር፣ እንዲሁም እርሱ ከሞት እንደ ተነሣና ለዘላለም ሕያው ሆኖ እንደሚገዛ እኔም በዘላለማዊ ፅድቅ፣ ንፅሕናና ብፅዕና እንዳገለግለው ነው።
> ይኸ ፍፁም እውነት ነው።

### *ኢየሱስና ክርስቶስ የሚሉት ስሞች*

### *114. ይህ አንቀፅ የሚናገረው ስለ ማን ነው?*

አንቀፁ የሚናገረው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ስለ አካሉና ስለ ሥራው ነው።

### *115. ለምን ኢየሱስ ተባለ?*

ኢየሱስ የሚለው ስም ትርጉም ‹‹ጌታ ያድናል›› ማለት ነው። ኢየሱስ የተፅውዖ ስሙ ነው።

377. **ማቴዎስ** 1፡21 ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ።

378. **ዮሐንስ** 4፡42 እርሱም በእውነት ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት እንደ ሆነ እናውቃለን።

379. **የሐዋርያት ሥራ** 4፡12 መዳንም በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች የለምና።

### *116. ክርስቶስ የተባለውስ ለምንድን ነው?*

በግሪክ ክርስቶስ ወይም በዕብራይስጥ መሲህ የተባለው መጠሪያ ትርጉሙ ‹‹የተቀባ›› ማለት ነው። ኢየሱስ ነብያችን፣ ካህናችንና ንጉሣችን ይሆን ዘንድ ያለልክ በመንፈስ ቅዱስ ተቀብቷል።

*ማስታወሻ፦ መቀባት ነብያትን፣ ካህናትንና ነገሥታትን ለተለየ ሥራ የሚለዩበት መንገድ ነበር።*

380. **መዝሙር** 45፡7 ከባልንጀሮችህ ይልቅ እግዚአብሔር አምላክህ የደስታ ዘይትን ቀባህ።

381. **ዮሐንስ** 3፡34 እግዚአብሔር የተላከው የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራልና እግዚአብሔር መንፈሱን ሰፍሮ አይሰጥምና።

382. **የሐዋርያት ሥራ** 10፡38 እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በኃይልም ቀባው።

*ማስታወሻ፦* የሚከተሉት የኢየሱስ ሌሎች መጠሪያዎች ናቸው፦ የእግዚአብሔር መልአክ (**ዘጸአት** 14፡19)፤ ታዳጊ (**ኢሳይያስ** 59፡20)፤ አማኑኤል (**ማቴዎስ** 1፡23)፤ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ (**ማቴዎስ** 16፡16)፤ የሰው ልጅ (**ማቴዎስ** 25፡31)፤ ቃል (**ዮሐንስ** 1፡14)፤ ጌታ (**ዮሐንስ** 20፡28)። ስሞቹ ወንጌል በቀላሉ የሚነግረን ናቸው።

### *117. ‹‹በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ›› ብለህ በምትመሰክርበት ጊዜ ይህ ምን ማለት ነው?*

ይህ ማለት ኢየሱስ ክርስቶስን ከኃጢአት፣ ከሞትና ከዲያብሎስ ብቸኛ አዳኜ መሆኑን አውቃለሁ፤ እታመንበታለሁም ደግሞም የዘላለምን ሕይወት እንደሚሰጠኝ አምናለሁ ማለት ነው።

383. **ዮሐንስ** 17፡3 እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።

384. **ዮሐንስ** 3፡36 በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም።

385. **2ጢሞቴዎስ** 1፡12 *ያመንሁትን አውቃለሁና፣ የሰጠኝንም አደራ እስከዚያ ቀን ድረስ ሊጠብቅ እንዲችል ተረድቻለሁ።*

386. **ሮሜ** 10፡10 ሰው በልቡ አምኖ ይፀድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናል።

## የኢየሱስ ክርስቶስ ሁለቱ ባሕርያት

### *118. ኢየሱስ ክርስቶስ ማን ነው?*

ኢየሱስ ክርስቶስ ‹‹ከዘላለም ከአብ የተወለደ እውነተኛ አምላክና ደግሞም ከድንግል ማርያም የተወለደ ሰው›› ነው።

### *119. ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ አምላክ መሆኑን እንዴት ታውቃለህ?*

ቅዱሳት መጻሕፍት የሚከተለውን በማስተማር በግልጽ አምላክ ብለው ስለሚጠሩት ነው።

*ሀ.* ኢየሱስ *መለኮታዊ* ስሞች አሉት።

387. **ዮሐንስ** 20፡28 ቶማስም፡- ‹‹ጌታዬ አምላኬም! ብሎ መለሰለት።››

388. **ሮሜ** 9፡5 ከእነርሱም ክርስቶስ በ*ሥጋ መ*ጣ፣ እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው።

389. **1ዮሐንስ** 5፡20 እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው።

*ማስታወሻ፡-* እነኚህ ስሞች የክብር ስሞች ብቻ አይደሉም ነገር ግን ለእግዚአብሔር ብቻ እውነት ሊሆኑ የሚችሉና ኢየሱስ ማን እንደ ሆነ በትክክል የሚነግሩን ናቸው።

ለ. ኢየሱስ *መለኮታዊ* ባሕርያት (*ማዕረጎች* ወይም ጠባያት) አሉት። እርሱ፡-

1. ዘላለማዊ ነው (*መጀመሪያና መጨረሻ የለውም*)፤

390. **ዮሐንስ** 1፡1-2 በ*መጀመሪያ*ው *ቃ*ል ነበረ፣ *ቃ*ልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፣ *ቃ*ልም እግዚአብሔር ነበረ። ይህ በ*መጀመሪያ*ው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ።

2. *አይለወጥም*

391. ***ዕብራውያን*** 13፡8 ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ዘላለምም *ያው* ነው።

3. *ሁሉን ቻይ ነው* (*ኦምኒፓተንት*)

392. **ማቴዎስ** 28፡18 *ሥ*ልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ።

4. *ሁሉን አዋቂ ነው* (*ኦምኒሼንት*)

393. **ዮሐንስ** 21፡17 *ጌታ ሆይ፣ አንተ ሁሉን ታውቃለህ*።

5. በሁሉም *ሥ*ፍራ ይገኛል (*ኦምኒፕሬዘንት*)

394. **ማቴዎስ** 28፡20 እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከአንተ *ጋ*ር ነኝ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፡* ተአምራዊ የዓሣ ማጥመድ (**ሉቃስ** 5፡4-6፤ **ዮሐንስ** 21፡6)። ኢየሱስ የናትናኤልን ስምና ጠባይ ያውቃል (**ዮሐንስ** 1፡48)። ኢየሱስና ሴቲቱ በያዕቆብ የውኃ ጉድጓድ አጠገብ (**ዮሐንስ** 4፡17-18)።

*ማስታወሻ፦* በተጨማሪም **ማቴዎስ** 21፡1-7፤ 26፡20-25፤ **ሉቃስ** 18፡31-33፤ 22፡8-13ን ተመልከት፡፡

ሐ. ኢየሱስ (እግዚአብሔር ብቻ ሊሠራ የሚችለውን ) መለኮታዊ ሥራዎችን ይሠራል፡፡

1. ኃጢአትን ያስተሰርያል (ይቅር) ይላል፡፡

395. **ማቴዎስ** 9፡6 በምድር ላይ ኃጢአትን ለማስተስረይ የሰው ልጅ ሥልጣን አለው፡፡

2. እርሱ ፈጥሯል

396. **ዮሐንስ** 1፡3 ሁሉ በእርሱ ሆነ፣ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም፡፡

3. ይፈርዳል

397. **ዮሐንስ** 5፡27 ይፈርድ ዘንድ (አብ) ሥልጣን ሰጠው፡፡

4. ይጠብቃል

398. **ዕብራውያን** 1፡3 በሥልጣኑ ቃል ዓለማትን ደግፎ ይይዛል፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፦* በቃና ሠርግ ላይ ኢየሱስን ውኃውን ወደ ወይን በመለወጥ ክብሩን ገለጠ፡፡ ***(ዮሐንስ 2፡1-11)፡፡*** ማዕበሉን ገሰፀው (**ሉቃስ** 8፡22-25)፡፡ ሽባውን ፈወሰ (**ማቴዎስ** 9፡1-8)፡፡ አልአዛርን ከሞት አስነሣው (**ዮሐንስ** 11፡38-44)፡፡ ከሙታን ተነሣ (**ማቴዎስ** 28፡6-7)፡፡

መ. ኢየሱስ መለኮታዊ ክብርና ምሥጋናን ይቀበላል፡፡

399. **ዮሐንስ** 5፡22-25 ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ፣ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም፡፡ ወልድን የማያከብር የላከውን አብን አያከብርም፡፡

400. **ዕብራውያን** 1፡6 የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉም ለእርሱ ይስገዱ፡፡

*ማስታወሻ፦* **ፊልጵስዩስ** 2፡10፤ **ራእይ** 5፡12-13ን ተመልከት፡፡

***120. ደግሞም ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ሰው መሆኑን እንዴት ታውቃለህ?***

ምክንያቱም ቅዱሳት መጻሕፍት፦

ሀ. በግልጽ ሰው ብለው ይጠሩታል፤

401. **1ጢሞቴዎስ** 2፡5 አንድ እግዚአብሔር አለና፣ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፣ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፡፡

ለ. እርሱ የሰው ሥጋና ነፍስ እንዳለው ይናገራሉ፤

402. **ሉቃስ** 24፡39 እኔ ራሴ እንደሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን እዩ በእኔ እንደምታዩት፣ መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና እኔን ዳስሳችሁ እዩ

403. **ማቴዎስ** 26፡38 ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዘነች

ሐ. ስለ ሰውነቱ ቢናገሩም ስሜቶቹና ተግባሮቹ ግን ያለ ኃጢአት ነበሩ፡፡

404. **ማቴዎስ** 4፡2 ተራበ

405. **ዮሐንስ** 11፡35 ኢየሱስ አነባ

406. **ዮሐንስ** 19፡28 ኢየሱስም … ‹‹ተጠማሁ›› አለ፡፡

407. **ዕብራውያን** 4፡14-16 እንግዲህ በሰማያት ያለፈ ትልቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን፣ ፀንተን ሃይማኖታችንን እንጠብቅ፡፡ ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ፣ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም፡፡

እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፡* ኢየሱስ መከራን ተቀበለና ሞተ (**ማቴዎስ** 26-27)። ኢየሱስ አንቀላፋ (**ማርቆስ** 4፡38)። ኢየሱስ ተወለደ (**ሉቃስ** 2)።

### *121. ስለዚህ በኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ሰውነት የተዋሃዱት ሁለቱ ባሕርያት የትኞቹ ናቸው?*

በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ የተዋሃዱት መለኮታዊና ሰብዓዊ ባሕርያቱ ናቸው። ይህ ውህደት በአካሉ ውስጥ የጀመረው በትስጉት (ሰው በሆነ ጊዜ) ሲሆን ለዘላለምም ይቀጥላል።

408. **ዮሐንስ** 1፡14 *ቃልም ሥጋ ሆነ* ጸጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ፣ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን።
409. **1ጢሞቴዎስ** 3፡16 እግዚአብሔርም የመምሰል ምስጢር ያለጥርጥር ታላቅ ነው፤ በሥጋ የተገለጠ።
410. **ቆላስይስ** 2፡9 በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራልና።
411. **ኢሳይያስ** 9፡6 ሕፃን ተወልዶልናልና፣ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፣ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ ፣ የዘላለም አባት፣ የሠላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።
412. **ማቴዎስ** 28፡18 *ሥልጣን ሁሉ* በሰማይና በምድር ተሰጠኝ።
413. **ማቴዎስ** 28፡20 እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።
414. **የሐዋርያት ሥራ** 3፡15 የሕይወትን ራስ ገደላችሁት።
415. **1ዮሐንስ** 7 የልጁም የኢየሱስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነፃናል።
416. **የሐዋርያት ሥራ** 20፡28 በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቋት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ሾሞአችኋል።

### *122. አዳኛችን እውነተኛ ሰው እንዲሆን ለምን አስፈለገው?*

ክርስቶስ እውነተኛ ሰው መሆን የነበረበት፡-

*ሀ.* በእኛ ቦታ ከሕግ በታች ሆኖ እንዲታዘዝና ስለ እኛ (በ*ገቢራዊ መታዘዝ*) እንዲፈጽመው ነው፤

417. **ገላትያ** 4፡4-5 ነገር ግን የዘመኑ ፍፃሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ልጁን ላከ እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ፣ ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ።
418. **ሮሜ** 5፡19 በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢአተኞች እንደሆኑ፣ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ፃድቃን ይሆናሉ።

*ለ.* ሕጉን ለመጠበቅ ባለመቻላችን ምክንያት ስለ እኛ በደል መከራን መቀበልና መሞት ይቻለው ዘንድ እውነተኛ ሰው መሆን አስፈለገው፤ (*ገቢራዊ መታዘዝ*)።

419. **ቆላስይስ** 1፡22 ነውርና ነቀፋ የሌላችሁና ቅዱሳን አድርጎ በእርሱ ፊት ያቀርባችሁ ዘንድ … በሥጋው ሰውነት በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ።
420. **ዕብራውያን** 2፡14 እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ፣ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፣ ይኸውም ዲያብሎስ ነው።

*123. አዳኛችን እውነተኛ አምላክ ይሆን ዘንድ ለምን አስፈለገ?*

በሚከተለው ምክንያት ክርስቶስ እውነተኛ አምላክ መሆን ነበረበት፡-

*ሀ. ሕግ መፈጸሙ፣ ሕይወቱ፣ መከራውና ሞቱ፣ ለሰዎች ሁሉ በቂ ቤዛ እንዲሆን፤*

421. ***መዝሙር*** 49፡7 ወንድም ወንድሙን አያድንም፣ ሰውም አያድንም፤ ቤዛውን ለእግዚአብሔር አይሰጥም።

422. **ማርቆስ** 10፡45 የሰው ልጅም ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።

423. **ሮሜ** 3፡22-24 ልዩነት የለምና፤ ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሏቸዋል፤ በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይፀድቃሉ።

424. ***ገላትያ*** 3፡13 ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን።

425. ***ገላትያ*** 4፡4-5 ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ።

426. **1ጴጥሮስ** 1፡18-19 ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከከንቱ ኑሮአችሁ በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በወርቅ ሳይሆን ነውርና እድፍ እንደሌለው እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደ ተዋጃችሁ ታውቃላችሁ።

*ለ. ስለ እኛ ሞትንና ዲያብሎስን ማሸነፍ ይቻለው ዘንድ፤*

427. **1ቆሮንቶስ** 15፡57 በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሳትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምሥጋና ይሁን።

428. **2ጢሞቴዎስ** 1፡10 በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ … እርሱ ሞትን ሽሯልና።

429. ***ዕብራውያን*** 2፡14 እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ፣ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፣ ይኸውም ዲያብሎስ ነው።

*124. እንግዲህ አምላክ - ሰው ስለ ሆነው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የምትመሰክረው ምንድን ነው?*

ኢየሱስ ክርስቶስ የምወደውና በሁለንተናዬ የማገለግለው ጌታዬና አዳኜ መሆኑን አምናለሁ።

430. **1ቆሮንቶስ** 6፡20 በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።

*መጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፡-* የቶማስ ምሥክርነት (ዮሐንስ 20፡24-29)።

**የክርስቶስ ሥልጣን**

*125. ክርስቶስ ለየትኛው የሦስትዮሽ ሥልጣን ነበር የተቀባው?*

ክርስቶስ ነብያችን፣ ካህናችንና ንጉሣችን ይሆን ዘንድ ነበር የተቀባው።

ሀ. ክርስቶስ እንደ ነብይ

1. በምድር ሕይወቱ ቃሉን በተአምራት በማጽናት በተለይም የራሱን ትንሣኤ በሰውነቱ ሰብኳል፤

431. **ዘዳግም** 18፡15 አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ መካከል ከወንድሞችህ እንደ እኔ ያለ ነብይ ያስነሳልሃል፤ እርሱንም ታደምጣለህ።

432. **ማቴዎስ** 17፡5 ‹‹በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት።››

433. **ማርቆስ** 1፡38 በእዚያ ደግሞ ልሰብክ ወደ ሌላ ሥፍራ በቅርብ ወዳሉ መንደሮች እንሂድ ስለዚህ መጥቻለሁና።

434. **ዮሐንስ** 1፡17-18 ሕግ በሙሴ ተሰጥቶ ነበርና ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ፡ ፡ መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም። በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው።

435. **ዮሐንስ** 6፡68 ስምዖን ጴጥሮስ፡- ጌታ ሆይ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ።

2. ዛሬ በሚሰበከው ወንጌል አማካኝነት አሁንም ራሱን የእግዚአብሔር ልጅና የዓለም አዳኝ መሆኑን ያውጃል።

436. **ማርቆስ** 16፡15 እንዲህም አላቸው፡- ‹‹ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ።››

437. **ሉቃስ** 10፡16 የሚሰማችሁ እኔን ይሰማል፣ እናንተንም የጣለ እኔን ይጥላል፤ እኔንም የጣለ የላከኝን ይጥላል።

438. **2ቆሮንቶስ** 5፡20 እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልዕክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን።

ለ. ክርስቶስ እንደ ካህን

1. በእኛ ምትክ ሕጉን ሙሉ በሙሉ ፈጽሟል (ተግባራዊ የሚሆን መታዘዝ)

439. **ገላትያ** 4፡4-5 ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ፣ ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ።

2. ስለ ኃጢአታችን ራሱን መስዋዕት አደረገ (የተፈጸመ መታዘዝ)።

440. **1ቆሮንቶስ** 15፡3 መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ።

441. **ዕብራውያን** 7፡26-27 ቅዱስና ያለተንኮል ነውርም የሌለበት ከኃጢአተኞችም የተለየ ከሰማያትም ከፍ ከፍ ያለ፣ እንደዚህ ያለ ሊቀ ካህናት ይገባልና፤ እርሱም እንደነዚያ ሊቀ ካህናት አስቀድመ ስለ ራሱ ኃጢአት በኋላም ስለ ሕዝቡ ኃጢአት ዕለት ዕለት መስዋዕትን ሊያቀርብ አያስፈልገውም ራሱን ባቀረበ ጊዜ ይኸን አንድ ጊዜ ፈጽሞ አድርጓልና።

442. **1ዮሐንስ** 2፡2 እርሱም የኃጢአታችን ማስተሰርያ ነው፣ ለኃጢአታችንም ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን ለዓለሙ ሁሉ ኃጢአት እንጂ።

3. አሁንም ከሰማያዊ አባቱ ዘንድ ይለምንልናል (ምልጃ)

443. **1ዮሐንስ** 2፡1 ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ሐ. ክርስቶስ እንደ ንጉሥ

1. ሁሉን በሚችል ኃይሉ በፍጥረት ሁሉ ላይ ይገዛል (የኃይል መንግሥት-መላው ፍጥረት)፤

444. **ማቴዎስ** 28፡18 *ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ፡፡*

2. በተለይ ቤተ ክርስቲያኑን ያስተዳድራል ይጠብቃታልም (በጸጋ *መንግሥት*-በምድር ላይ ያለች ቤተ ክርስቲያን)

445. **ዮሐንስ** 18፡36-37 *‹‹ኢየሱስም መልሶ፡- ‹‹መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም፤ መንግሥቴስ ከዚህ ዓለም ብትሆን፣ ወደ አይሁድ እንዳልሰጥ ሎሌዎቼ ይዋጉልኝ ነበር፤ አሁን ግን መንግሥቴ ከዚህ አይደለችም አለው፡፡›› ጲላጦስም፡- ‹‹እንግዲያ ንጉሥ ነህን?›› አለው ኢየሱስም መልሶ፡- ‹‹እኔ ንጉሥ እንደሆንሁ አንተ ትላለህ፡፡ እኔ ለእውነት ልመስክር ስለዚህ ተወልጄአለሁ ስለዚህም ወደ ዓለም መጥቼአለሁ፤ ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምፄን ይሰማል አለው፡፡››*

3. በመጨረሻ ቤተ ክርስቲያኑ በሰማይ ወደ አለው ክብር ይመራታል (የክብር *መንግሥት* - ቤተ ክርስቲያን በሰማይ)

446. **2ጢሞቴዎስ** 4፡18 *ጌታም ከክፉ ነገር ሁሉ ያድነኛል፡፡ ለሰማያዊውም መንግሥት ይጠብቀኛል፤ ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን፡፡*

### *አዳኙ በተዋረደበት ሁኔታ*

### *126. ቅዱሳት መጻሕፍት በክርስቶስ የማዳን ሥራ ውስጥ የሚለዩዋቸው ሁለቱ ሁኔታዎች የትኞቹ ናቸው?*

*ሀ. የመዋረዱ ሁኔታ*

*ለ. የመክበሩ ሁኔታ*

### *127. የትኛው ነው የክርስቶስ መዋረድ?*

የክርስቶስ መዋረድ ሰው በመሆኑ መለኮታዊ ኃይሉን ሁልጊዜ ወይም በሙላት ያለመጠቀሙ ነበር፡፡

447. **ፊልጵስዩስ** 2፡5-8 በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም፣ ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሣሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፣ በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፣ ለሞትም ይኸው የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፡-* የቃናው ሠርግ (ዮሐንስ 2፡1-11)፡፡ አልአዛርን ከሞት ማስነሳቱ (ዮሐንስ 38፡44)፡፡ የተደበቀ ክብሩ ፀዳል (ዮሐንስ 18፡1-6)፡፡

### *128. ከሐዋርያት የእምነት መግለጫ ውስጥ የትኞቹ ቃላት ናቸው የክርስቶስን የመዋረድ ደረጃዎች የሚገልጹት?*

‹‹በመንፈስ ቅዱስ በተፀነሰ፣ ከድንግል ማርያም በተወለደ፣ በጴንጤናዊ ጲላጦስ ዘመን መከራን በተቀበለ፣ በተሰቀለ፣ በሞተና በተቀበረ››

### *129. ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ክርስቶስ መፀነስ ምን ያስተምራሉ?*

ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ከሰብአዊ አባት ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ተአምራዊ ኃይል አማካይነት በድንግል ማርያም ውስጥ እውነተኛውን የሰው ሥጋና ነፍስ እንደ ተቀበለ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስተምራሉ።

448. **ሉቃስ** 1፡35 መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፣ የልዑልም ኃይል ይፀልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል።

449. **ማቴዎስ** 1፡20 የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ ከእርሷ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ።

*130. ስለ ክርስቶስ መወለድ ቅዱሳት መጻሕፍት ምን ያስተምራሉ?*

አምላክ ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም መወለዱን ያስተምራሉ።

450. **ኢሳይያስ** 7፡14 እነሆ፣ ድንግል ትፀንሳለች፣ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፣ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች።

451. **ሉቃስ** 2፡7 የበኵር ልጇንም ወለደች፣ በመጠቅለያም ጠቀለለችው የእንግዶችም ማደሪያ ስፍራ ስላልነበራቸው በግርግም አስተኛችው።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፡-* ***የድንግል መውለድ (ማቴዎስ 1፡18-25)፡፡***

*131. ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ክርስቶስ ሕይወት፣ መከራና ሞት ምን ያስተምራሉ?*

ስለ ክርስቶስ የሚከተለውን ያስተምራሉ፡-

ሀ. በምድር ሕይወቱ ድህነትን፣ መናቅንና ስደትን ተቋቁሟል፤

452. **2ቆሮንቶስ** 8፡9 ሃብታም ሲሆን፣ እናንተ በእርሱ ድህነት ባለ ጠጎች ትሆኑ ዘንድ ስለ እናንተ ድሃ ሆነ።

453. **ማቴዎስ** 8፡20 ለቀበሮዎች ጉድጓድ፣ ለሰማይም ወፎች መሳፈሪያ አላቸው፣ ለሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም።

454. **ኢሳይያስ** 53፡3 የተናቀ ከሰውም የተጠላ፣ የህማም ሰው ደዌንም የሚያውቅ ነው ሰውም ፊቱን እንደሚሠውርበት የተናቀ ነው፣ እኛም አላከበርነውም።

455. **ዮሐንስ** 8፡40 ነገር ግን አሁን ከእግዚአብሔር የሰማሁትን እውነት የነገርኳችሁን ሰው ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፡-* ኢየሱስ ሲወለድ የነበረው ቁርጥራጭ ጨርቅና ግርግም ብቻ ነበር (**ሉቃስ** 2፡7)። ሄሮድስ ሊገድለው ሞከረ ነገር ግን እርሱ ወደ ግብፅ ሸሸ (**ማቴዎስ** 2፡13)። ናዝሬት ውስጥ ሰዎች ከኮረብታው ቁልቁል ሊወረውሩት ሞከሩ (**ሉቃስ** 4፡29)። በቤተ መቅደስ ውስጥ ሊወግሩት ድንጋይ አነሱ (**ዮሐንስ** 8፡59)።

ለ. በጴንጤናዊው በጲላጦስ ታላቅ የሥጋና የነፍስ ስቃይ መከራን ተቀበለ፤

456. **ዮሐንስ** 19፡1-3 በዚያን ጊዜም ጲላጦስ ኢየሱስን ይዞ ገረፈው። ወታደሮችም ከሾህ አክሊል ጎንጉነው በራሱ አኖሩ ቀይ ልብስም አለበሱት እየቀረቡም፡- ‹‹የአይሁድ ንጉሥ ሆይ››፣ ሰላም ለአንተ ይሁን ይሉት ነበር በጥፊም ይመቱት ነበር።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፡-* የክርስቶስ መከራ (**ማርቆስ** 15፡1-20)።

ሐ. በመስቀል ላይ ተሰቃይቶ ሞተ።

457. **ዮሐንስ** 19፡16-18 ስለዚህ በዚያን ጊዜ እንዲሰቀል አሳልፎ ሰጣቸው። ኢየሱስንም ይዘው ወሰዱት መስቀሉንም ተሸክሞ በአርማይክ ጎሎጎታ ወደተባለው የራስ ቅል ስፍራ ወደሚሉት ወጣ። ከዚያም ሰቀሉት።

458. ***ማቴዎስ*** 27፡46 በዘጠኝ ሰዓትም ኢየሱስ፡- … ‹‹አምላኬ አምላኬ ስለ ምን ተውኸኝ?›› ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ (የተረገመውን የሲዖል ውስጥ ግርፋት መከራ ተቀበለ)።

459. **ዮሐንስ** 19፡30 ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ።
*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፡-* የክርስቶስ ሞት (**ማርቆስ** 15፡21-41)።

### *132. ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ክርስቶስ መቀበር ምን ያስተምራሉ?*

የክርስቶስ *ሥጋ* በመቃብር ውስጥ መቀበሩን እና በየትኛውም መልኩ ሳይበሰብስ እስከ ሦስተኛው ቀን ድረስ መቆየቱን ያስተምራሉ።

460. **የሐዋርያት *ሥራ*** 13፡37 ይህ እግዚአብሔር ያስነሣው ግን መበስበስን አላየም።
*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፡-* የክርስቶስ መቀበር (**ማርቆስ** 15፡42-47)።

## *የክርስቶስ የማዳኑ ወይም የቤዛነቱ ሥራ*

### *133. ክርስቶስ ለምን ራሱን አዋረደ?*

‹‹እኔን የጠፋሁትንና የተኮነንኩትን ሰው ያድነኝ ዘንድ›› ክርስቶስ ራሱን በፈቃዱ አዋረደ፡
፡

461. **ኢሳይያስ** 53፡4-5 በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸክሟል እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሰፈ እንደ ተቸገረም ቆጠርነው። እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቆሰለ፣ ስለ በደላችንም ደቀቀ የደኅንነታችንንም ተግሳጽ በእርሱ ላይ ነበር፣ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን።

462. **ዮሐንስ** 10፡17-18 ነፍሴን ደግሞ አነሳት ዘንድ አኖራለሁና ስለዚህ አብ ይወደኛል። እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም።

### *134. ክርስቶስ ያዳነህ ከምንድን ነው?*

እርሱ ‹‹ከኃጢአት ሁሉ፣ ከሞትና ከዲያብሎስ ኃይል›› አድኖኛል።

463. **ዮሐንስ** 1፡29 እነሆ፣ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ!

464. ***ዕብራውያን*** 2፡14-15፣17 እንግዲህ ልጆቹ በ*ሥጋ*ና በደም ስለሚካፈሉ፣ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ *ሥ*ልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፣ ይኸውም ዲያብሎስ ነው፣ በሕይወታቸውም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ፣ በ*ሥጋ*ና በደም እንዲሁም ተካፈለ… ስለዚህ የሕዝብን ኃጢአት ለማስተሰረይ፣ ለእግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ የሚምርና የታመነ ሊቀ ካህናት እንዲሆን፣ በነገር ሁሉ ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው።

### *135. ክርስቶስ ከኃጢአት ሁሉ ያዳነህ እንዴት ነው?*

ሀ. የእኔን በደልና ቅጣት በራሱ ላይ አደረገ።

465. **ሮሜ** 5፡19 እንዲሁ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ።

466. **2ቆሮንቶስ** 5፡21 እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ፅድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው።

467. *ገላትያ* 3፡13 ‹‹በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው›› ተብሎ ተጽፏልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን።

ለ. ከኃጢአት ባርነት ነፃ አውጥቶኛል።

468. **ዮሐንስ** 8፡34፣36 እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ ኃጢአት የሚያደርግ ሁሉ የኃጢአት ባሪያ ነው።... እንግዲህ ልጁ አርነት ቢያወጣችሁ በእውነት አርነት ትወጣላችሁ።

469. **1ጴጥሮስ** 2፡24 እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ።

### *136. ክርስቶስ ከሞት የታደገህ እንዴት ነው?*

ክርስቶስ በመከራው፣ በሞቱና በትንሣኤው ሞትን ድል አድርጎታል። አሁን የዘላለምን ሕይወት የሚሰጠኝ ስለ ሆነ ሞትን መፍራት አያስፈልገኝም።

470. **1ቆሮንቶስ** 15፡55-57 ‹‹ሞት ሆይ፣ መውጊያህ የታለ? ሲኦል ሆይ፣ ድል መንሳትህ የታለ?›› የሞት መውጊያ ኃጢአት ነው የኃጢአትም ኃይል ሕግ ነው፤ ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሳትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን።

471. **2ጢሞቴዎስ** 1፡10 መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ... እርሱ ሞትን ሽሯል... በወንጌል ሕይወትንና አለመጥፋትን ወደ ብርሃን አውጥቷል።

472. **1ጴጥሮስ** 1፡3 ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በመነሣቱ ለሕያው ተስፋና ለማይጠፋ፣ እድፈትም ለሌለበት፣ ለማያልፍም ርስት እንደ ምሕረቱ ብዛት ሁለተኛ ወለደን።

### *137. ክርስቶስ ከዲያቢሎስ ኃይል የታደገህ እንዴት ነው?*

ክርስቶስ ዲያብሎስን ሙሉ በሙሉ አሸንፎታል። ስለዚህ ዲያብሎስ ስለ ኃጢአቴ ከዚህ በኋላ ሊከሰኝ አይችልም ፈተናዎቹንም መቋቋም እችላለሁ።

473. **ዘፍጥረት** 3፡15 በአንተና በሴቲቱ መካከል፣ በዘርህና በዘሯም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፣ አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ።

474. **1ዮሐንስ** 3፡9 ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ።

475. ***ያዕቆብ*** 4፡7 ዲያብሎስን ተቋቋሙት ከእናንተም ይሸሻል።

*ማስታወሻ፡-* በተጨማሪም **ሮሜ** 8፡31-34፤ **ቆላስይስ** 2፡15፤ ***ዕብራውያን*** 2፡14-15፤ **1ጴጥሮስ** *5፡8-9፤ ራእይ* 12፡10ን ተመልከት።

### *138. ክርስቶስ ያዳነህ በምኑ ነው?*

ክርስቶስ ያዳነኝ ‹‹በብር ወይም በወርቅ ሳይሆን፣ ነውርና እድፈት እንደሌለው እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም›› ነው።

476. **ኢሳይያስ** 53፡5 በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን።

477. **1ጴጥሮስ** 1፡18-19 ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከከንቱ ኑሯችሁ በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በወርቅ ሳይሆን፣ ነውርና እድፍ እንደሌለው እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደ ተዋጃችሁ ታውቃላችሁ።

478. 1ዮሐንስ 1፡7 የልጁም የኢየሱስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል፡፡

### *139. ይህ የማዳን ሥራ አንተን ተጠቃሚ የሚያደርግህ እንዴት ነው?*

ክርስቶስ የእኔ ምትክ ነው፡፡ በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ፍርድ ስር የሆነውን ሥፍራዬን እርሱ ወስዶታል፡፡ የበደሌን ቅጣት በመክፈል ክርስቶስ ሞተልኝ ወይም ስለ ኃጢአቴ ዕዳ ክፍያ ሠራልኝ፡፡ (የውክልና ሞት)

479. **ኢሳይያስ** 53፡4-5 በእውነት ደዌአችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸክሟል፤ እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሰፈ እንደ ተቸገረም ቆጠርነው፡፡ እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቆሰለ፣ ስለ በደላችንም ደቀቀ፣ የደኅንነታችንም ተግሳጽ በእርሱ ላይ ነበር፣ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን፡፡

480. **2ቆሮንቶስ** 5፡21 በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ፅድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው፡፡

481. **ዕብራውያን** 2፡17 ስለዚህ የሕዝብን ኃጢአት ለማስተስረይ፣ ለእግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ የሚምርና የታመነ ሊቀ ካህናት እንዲሆን፣ በነገር ሁሉ ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው፡፡

### *140. ክርስቶስ የዋጀው አንተን ብቻ ነውን?*

አይደለም፣ ክርስቶስ የዋጀው እኔንና ሰዎችን ሁሉ ነው፡፡ (ስለ ሁሉ ሞተ)

482. **2ቆሮንቶስ** 5፡15 ስለ ሁሉ ሞተ፡፡

483. **2ቆሮንቶስ** 5፡19 እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፣ በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር፡፡

484. **1ጢሞቴዎስ** 1፡15 ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው፤ ከኃጢአተኞችም ዋና እኔ ነኝ፡፡

485. **1ዮሐንስ** 2፡2 እርሱም የኃጢአታችን ማስተሰሪያ ነው፣ ለኃጢአታችንም ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን ለዓለሙ ኃጢአት እንጂ፡፡

486. **2ጴጥሮስ** 2፡1 እርሱም የዋጃቸውን ጌታ እንኳ ክደው የሚፈጥንን ጥፋት በራሳቸው ላይ እየሳቡ የሚያጠፉ ኑፋቄን አሹልከው ይገባሉ፡፡

## የአዳኙ መክበር ሁኔታ

### *141. የክርስቶስ መክበር ምንድን ነው?*

የክርስቶስ መክበር ሰው ሆኖ በሙላት ሁልጊዜ የመለኮት ኃይሉን መጠቀሙ ነው፡፡

487. **ፊልጵስዩስ** 2፡9-11 በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለልክ ከፍ ከፍ አደረገው፣ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፤ ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፣ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው፡፡

### *142. የክርስቶስን የመክበር ደረጃዎች የሚገልጹት የሐዋርያት የእምነት መግለጫ ቃላት የትኞቹ ናቸው?*

‹‹ወደ ሲዖል ወርዷል። በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተነሥቷል። ወደ ሰማይ አርጎ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ተቀምጧል። ከዚያም በሕያዋንና በሙታን ላይ ሊፈርድ ይመለሳል።››

### *143. የክርስቶስ ወደ ሲዖል መውረድ የመክበሩ አካል የሚሆነው ለምንድን ነው?*

ቅዱሳት መጻሕፍት ክርስቶስ በመቃብር ውስጥ ሕያው ከሆነ በኋላ በቅጣት ሲሰቃይ ሳይሆን በሲዖል ባሉት ጠላቶቹ ላይ ድል አድራጊነቱን ለማወጅ ወደ ሲዖል መውረዱን ያስተምራሉ።

488. **1ጴጥሮስ** 3፡18-19 (ክርስቶስ) በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ፣ በእርሱም ደግሞ ሄዶ በወህኒ ለነበሩት ነፍሳት ሰበከላቸው።

489. **ቆላስይስ** 2፡15 አለቅነትና ሥልጣናትን ገፎ፣ ድል በመንሣት በእርሱ እያዞራቸው በግልፅ አሳያቸው።

### *144. ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ የሚያስተምሩን ምንድን ነው?*

በሦስተኛው ቀን ክርስቶስ ከመቃብር በድል መነሣቱንና ሕያው መሆኑን ለደቀ መዛሙርቱ ማሳየቱን ያስተምራሉ።

490. **የሐዋርያት ሥራ** 10፡40-41 እርሱም እግዚአብሔር በሦስተኛው ቀን አስነሣው። ይገለጥም ዘንድ ሰጠው፤ ይኸውም ለሕዝብ ሁሉ አይደለም ነገር ግን በእግዚአብሔር አስቀድሞ የተመረጡ ምሥክሮች ለሆንን ለእኛ ነው እንጅ፤ ከሙታንም ከተነሣ በኋላ ከእርሱ ጋር የበላን የጠጣንም እኛ ነን።

491. **1ቆሮንቶስ** 15፡4-8 መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ፣ ለኬፋም ታየ በኋላም ለአሥራ ሁለቱ፤ ከዚያም በኋላ ከአምስት መቶ ለሚበዙ ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ፤ ከእነርሱም የሚበዙቱ እስከ አሁን አሉ አንዳንዶች ግን አንቀላፍተዋል፤ ከዚያም በኋላ ለያዕቆብ በኋላም ለሐዋርያት ሁሉ ታየ ከሁሉም በኋላ እንደጭንጋፍ ለምሆን ለእኔ ደግሞ ታየኝ።

492. **የሐዋርያት ሥራ** 1፡3 ደግሞ አርባ ቀን እየታያቸው ስለ እግዚአብሔርም መንግሥት ነገር እየነገራቸው፣ በብዙ ማስረጃ ከሕማማቱ በኋላ ሕያው ሆኖ ለእነርሱ ራሱን አሳያቸው።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፦* የክርስቶስ ትንሣኤ (**ማቴዎስ** 27፡62-28፡20፤ **ማርቆስ** 16፤ **ሉቃስ** 24፤ **ዮሐንስ** 20-21)።

### *145. የክርስቶስ ትንሣኤ በጣም አስፈላጊና አጽናኝ የሚሆነው ለምንድን ነው?*

የክርስቶስ ትንሣኤ የሚያረጋግጠው፦

ሀ. ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን፤

493. **ሮሜ** 1፡4 እንደ ቅድስና መንፈስ ግን ከሙታን መነሣት በኃይል የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ስለ ተገለጠ ስለ ልጁ ነው።

ለ. አስተምህሮው እውነት ነው፤

494. **ዮሐንስ** 2፡19 ይህንን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፣ በሦስት ቀንም አነሣዋለሁ።

495. **ዮሐንስ** 8፡28 የሰውን ልጅ ከፍ ከፍ ባደረጋችሁት ጊዜ እኔ እሆን ዘንድ አባቴም እንዳስተማረኝ እነዚህን እናገር ዘንድ እንጂ ከራሴ አንዳች እንዳላደርግ በዚያን ጊዜ ታውቃላችሁ።

*ሐ.* እግዚአብሔር አብ ዓለምን (ከራሱ ጋር) ለማስታረቅ የክርስቶስን መስዋዕት መቀበሉን፤

496. **ሮሜ** 4፡25 (ክርስቶስ) ስለ በደላችን አልፎ ተሰጠ እኛን ለማጽደቅም ተነሣ።

497. **ሮሜ** 5፡10 ጠላቶች ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን፣ ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በሕይወቱ እንድናለን።

498. **1ቆሮንቶስ** 15፡17 ክርስቶስም ካልተነሣ እምነታችሁ ከንቱ ናት፤ እስከ አሁን ድረስ በኃጢአታችሁ አላችሁ።

*መ.* በክርስቶስ ያሉ አማኞች ሁሉ ለዘላለም ሕይወት የሚነሱ መሆኑን።

499. **ዮሐንስ** 11፡25-26 ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል፤ ሕያው የሆነም የሚያምንብኝ ሁሉ ለዘላለም አይሞትም።

500. **ዮሐንስ** 14፡19 እኔ ሕያው ነኝና እናንተ ደግሞ ሕያዋን ትሆናላችሁ።

501. **1ቆሮንቶስ** 15፡20 አሁን ግን ክርስቶስ ለአንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቷል።

### *146. ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ክርስቶስ ዕርገት የሚያስተምሩን ምንድን ነው?*

ከትንሣኤው ከአርባ ቀናት በኋላ ለእኛ በሰማይ ስፍራ ያዘጋጅልን ዘንድ ደቀ መዛሙርቱ እያዩት በሥጋ ወደ አባቱ ክብር አርጓል ብለው ያስተምራሉ።

502. **ሉቃስ** 24፡51 ሲባርካቸውም ከእነርሱ ተለየ ወደ ሰማይም አረገ።

503. **ኤፌሶን** 4፡10 ይህ የወረደው ሁሉን ይሞላ ዘንድ ከሰማያት ሁሉ በላይ የወጣው ደግሞ ያው ነው።

504. **ዮሐንስ** 14፡2-3 በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፤ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና፤ ሄጄም ሥፍራ ባዘጋጅላችሁ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ።

505. **ዮሐንስ** 17፡24 አባት ሆይ፣ … ክብሬን እንዲያዩ እኔ ባለሁበት የሰጠኸኝ እነርሱ ደግሞ ከእኔ ጋር ይሆኑ ዘንድ እወዳለሁ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፦* የክርስቶስ እርገት (**የሐዋርያት ሥራ** 1፡9-11)።

### *147. ክርስቶስ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ተቀመጠ ማለት ምን ማለት ነው?*

በዚህ አገላለጽ ክርስቶስ እንደ ፍፁም ሰው በሁሉም ሥፍራ ይገኛል ማለት ብቻ ሳይሆን ነገር ግን በመላው ዓለም ላይ አሁን ደግሞ መለኮታዊ ኃይሉን በሙላት ይሠራበታል ብሎ የእግዚአብሔር ቃል ያስተምራል።

506. **ኤፌሶን** 1፡20-23 (እግዚአብሔር) ክርስቶስን ከሙታን ሲያስነሣው ከአለቅነት እና ከሥልጣንም ከኃይልም ከጌትነትም ሁሉ በላይና በዚህ ዓለም ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ሊመጣ ባለው ዓለም ደግሞ ከሚጠራው ስም ሁሉ በላይ በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ ሲያስቀምጠው በክርስቶስ ባደረገው ሥራ የብርታቱ ጉልበት ይታያል፤ ሁሉንም ከእግሩ

በታች አስገዛለት ከሁሉ በላይም ራስ እንዲሆን ለቤተ ክርስቲያን ሰጠው፡፡ እርሷም አካሉና ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእርሱ ሙላት ናት፡፡

### *148. ክርስቶስ ወደ እግዚአብሔር አብ ቀኝ በማረጉ የምናገኘው መጽናናት ምንድን ነው?*

የከበረው አምላክ - ሰው የሆነው ክርስቶስ

*ሀ.* እንደ ነቢያችን የሚያድነውን ወንጌል በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንዲሰብኩ ሰዎችን እንደሚልክ እናውቃለን፤

507. **ኤፌሶን** 4፡10-12 ይህ የወረደው ሁሉን ይሞላ ዘንድ ከሰማያት ሁሉ በላይ የወጣው ደግሞ ያው ነው፡፡ እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፣ ሌሎቹም ነቢያት ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፣ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፤ … ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንፃ ፍፁማን ይሆኑ ዘንድ፡፡

508. **ሉቃስ** 10፡16 የሚሰማችሁ እኔን ይሰማል

509. **ዮሐንስ** 16፡7 እኔ (ኢየሱስ) እንድሄድ ይሻላችኋል እኔ ባልሄድ አፅናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና፤ እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ፡፡

*ለ.* እንደ ካህናችን በአብ ፊት ልመናና ጸሎትን ስለ እኛ ያቀርባል፤

510. **ሮሜ** 8፡34 በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው፤ ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፡፡

511. **1ዮሐንስ** 2፡1 ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡

*ሐ.* እንደ ንጉሣችን ቤተ ክርስቲያኑን ይገዛል ይጠብቃታልም ደግሞም ለቤተ ክርስቲያኑ ጥቅም መላውን ዓለም ያስተዳድራል፡፡

512. **መዝሙር** 110፡1 እግዚአብሔር ጌታዬን ‹‹ጠላቶችህን ለእግርህ መቀመጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ›› አለው፡፡

*ማስታወሻ፡-* **ኤፌሶን**1፡20-23ን ተመልከት፡፡

### *149. ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ክርስቶስ ዳግመኛ መምጣት የሚያስተምሩት ምንድን ነው?*

*ሀ.* ክርስቶስ በመጨረሻው ቀን በሚታይ ሁኔታና በታላቅ ክብር ይመጣል፡፡

513. **ማቴዎስ** 24፡27 መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ እስከ ምዕራብ እንደሚታይ፣ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናል፡፡

514. **ሉቃስ** 21፡27 በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ በኃይልና በብዙ ክብር በደመና ሲመጣ ያዩታል፡፡

515. **የሐዋርያት ሥራ** 1፡11 የገሊላ ሰዎች ሆይ፣ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለ ምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት፣ እንዲሁ ይመጣል፡፡

516. **2ጴጥሮስ** 3፡10 የጌታው ቀን ግን እንደ ሌባ ሆኖ ይመጣል፤ በከዚያም ቀን ሰማያት በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ፣ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኩሳት ይቀልጣል፣ ምድርም በእርሷም ላይ የተደረገውን ሁሉ ይቃጠላል፡፡

517. **ራእይ** 1፡7 እነሆ፣ ከደመና ጋር ይመጣል፤ ዐይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል፤ የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ፡፡ አዎን፣ አሜን፡፡

ለ. ክርስቶስ ምድራዊ መንግሥት ሊመሠርት ሳይሆን በዓለም ሊፈርድ ይመጣል፡፡

518. **ማቴዎስ** 25፡31-32 የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ፣ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል፤ አህዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፤ እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በእርሳቸው ይለያቸዋል፡፡

519. **ዮሐንስ** 12፡48 የሚጥለኝ ቃሌንም የማይቀበለው እርሱ የሚፈርድበት አለው፤ እኔ የተናገርኩት ቃል እርሱ በመጨረሻው ቀን ይፈርድበታል፡፡

520. **ዮሐንስ** 18፡36 ኢየሱስም መልሶ፡- ‹‹መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም›› አለው፡፡

521. **2ቆሮንቶስ** 5፡10 መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ፤ እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናልና፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፡-* የመጨረሻው ፍርድ (**ማቴዎስ** 25፡31-46)፡፡

*ማስታወሻ፡-* ስለ ሺህ ዓመት መንግሥት የሚያስተምሩት ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ መመለስ በፊት ወይም በኋላ ቃል በቃል ለአንድ ሺ ዓመታት (ምዕት ዓመት) ሰላምና ብልፅግናን ትለማመዳለች የሚል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ መሠረተ እምነትን ያስተምራሉ፡፡ **ራእይ** 20 ክርስቶስ በወንጌል አማካይነት በምድር ላይ ስለሚገዛበት መንፈሳዊ አገዛዝ በሥዕላዊ ቋንቋ ይናገራል እንጂ ምድራዊ መንግሥትን አያመለክትም፡፡

ሐ. ክርስቶስ እግዚአብሔር ብቻ ለይቶ በሚያውቃት ቀን ይመጣል፡፡

522. **ማቴዎስ** 24፡44 ስለዚህ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ፣ የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣልና፡፡

523. **ማርቆስ** 13፡32 ስለዚያች ቀን ወይም ስለዚያች ሰዓት ግን የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን ከአባት በቀር የሚያውቅ የለም፡፡

524. **የሐዋርያት ሥራ** 17፡31 ቀን ቀጥሯልና፣ በዚያን ቀን ባዘጋጀው ሰው እጅ በዓለሙ ላይ በጽድቅ ሊፈርድ አለው፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፡-* የአሥሩ ቆነጃጅት ምሳሌ (**ማቴዎስ** 25፡1-13)፡፡

መ. ክርስቶስ ከመመለሱ በፊት በቤተ ክርስቲያንና በዓለም ሁከትና ስቃይ ይጨምራል፡፡

525. **ማቴዎስ** 24፡7 ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣልና፣ ርሃብም ቸነፈርም የምድርም መናወጥ በልዩ ልዩ ሥፍራ ይሆናል፡፡

526. **ማቴዎስ** 24፡22 እነዚያ ቀኖችስ ባያጥሩ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም ነበር፤ ነገር ግን እነዚያ ቀኖች ስለ ተመረጡት ሰዎች ያጥራሉ፡፡

527. **1ጢሞቴዎስ** 4፡1 መንፈስ ግን በግልጥ በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትን በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠው የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ ሃይማኖትን ይክዳሉ ይላል፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፡- የክርስቶስን መምጣት የሚቀድሙ ምልክቶች (**ማቴዎስ** 24)፡፡*

ሠ. የክርስቶስ መመለስ ለክርስቲያን የተስፋና የደስታ ምንጭ ነው፡፡

528. **ሉቃስ** 21፡28 ይህም ሊሆን ሲጀምር ቤዛችሁ ቀርቧልና አሻቅባችሁ ራሳችሁን አንሱ፡፡

529. **ዕብራውያን** 9፡28 እንዲሁ ክርስቶስ ደግሞ የብዙዎችን ኃጢአት ሊሸከም አንድ ጊዜ ከተሰዋ በኋላ፣ ያድናቸው ዘንድ ለሚጠባበቁት ሁለተኛ ጊዜ ያለ ኃጢአት ይታይላቸዋል፡፡

530. **ቲቶ 2፡13** የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን …።

531. *ራእይ* **22፡20** ይህን የሚመሰክር ‹‹አዎን በቶሎ እመጣለሁ›› ይላል፡፡ አሜን፣ ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፡- የሚያጽናኑ ቃላት (*1ተሰሎንቄ 4፡13-18*)*፡፡

### *150. ለማጠቃለል፣ ታዲያ ክርስቶስ የዋጀህ ለምንድን ነው?*

ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚያስተምሩት የክርስቶስ ዓላማ የነበረው፡-

ሀ. ‹‹እኔ የእርሱ የራሱ እንድሆን ነው››፤ ይኸውም እኔ አሁን ጻድቅና በእግዚአብሔር ፊት ነቀፋ የሌለብኝ ነኝ፤

532. **2ቆሮንቶስ 5፡21** እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው፡፡

533. *ራእይ* **5፡9** ታርደሃልና፣ በደምህ ለእግዚአብሔር ከነገር ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅህ፡፡

ለ. ‹‹በመንግሥቱ ውስጥ በእርሱ ሥር እንኖር ዘንድ›› ነው፤ ይኸውም አሁን ከኃጢአት ባርነት ነጻ ተደርጌአለሁ እንዲሁም እግዚአብሔርን ለማገልገል ነጻ ሆኜአለሁ፤

534. **ሮሜ 6፡6** ከእንግዲህስ ወዲያ ለኃጢአት እንዳንገዛ የኃጢአት ሥር ይሻር ዘንድ አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደ ተሰቀለ እናውቃለን፡፡

535. **2ቆሮንቶስ 5፡15** በሕይወትም ያሉት ስለ እነርሱ ለሞተውና ለተነሣው እንጅ ወደ ፊት ለራሳቸው እንዳይኖሩ ስለ ሁሉ ሞተ፡፡

536. **ቆላስይስ 2፡6** እንግዲህ ጌታን ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ተቀበላችሁት በእርሱ ተመላለሱ፡፡

537. **ቲቶ 2፡14** (ኢየሱስ ክርስቶስ) ከአመፅ ሁሉ እንዲቤዠን፣ መልካሙንም ለማድረግ የሚቀናውን ገንዘቡ የሚሆነውን ሕዝብ ለራሱ እንዲያነጻ ስለ እኛ ነፍሱን ሰጥቷል፡፡

ሐ. ‹‹በዘላለም ጽድቅ፣ ንፅሕናና ብፅዕና አገለግለው›› ዘንድ ነው፤ ይኸውም በመላው ሕይወቴ እግዚአብሔርን አከብረውና አሁን በምድር ላይ ደግሞም በሰማይ ለዘላለም በእርሱ ደስ እንዲለኝ ነው፡፡

538. **ሉቃስ 1፡69፣74-75** (እርሱ) የመዳን ቀንድን አስነስቷል፤ … በእርሱም ከጠላቶቻችን ድነን በዘመናችን ሁሉ ያለ ፍርሐት በቅድስናና በጽድቅ በፊቱ እንድናገለግለው ሰጠን፡፡

539. *ገላትያ* **2፡20** ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው፡፡

540. **1ጴጥሮስ 2፡9** እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉሥ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፡-* ቅዱሳን በሰማይ (*ራእይ* 7፡13-17)፡፡

### *151. የእምነታችንና በክርስቶስ ያለን ሕይወት መሠረቱ ምንድን ነው?*

‹‹እርሱ ከሙታን ተነሥቷል፣ ሕያው ነው፣ ለዘላለምም ይነግሣል፡፡››

541. **ቆላስይስ 3፥1-3** እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ፣ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን እሹ። በላይ ያለውን አስቡ እንጅ በምድር ያለውን አይደለም። ሞታችኋልና፣ ሕይወታችሁም በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሯልና።

***152. ይህንን አንቀጽ ‹‹ይህ ፍፁም እውነት ነው›› በሚሉት ቃላት የምትደመድመው ለምንድን ነው?***

ምክንያቱም በዚህ አንቀጽ የምመሰክረው ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግልጽ ትምህርት ስለ ተሰጠበት ነው፤ ስለዚህ እኔም በጽኑ አምንበታለሁ።

***ሦስተኛው አንቀጽ***

***መቀደስ***

ደግሞም በመንፈስ ቅዱስ፣ በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፣ በቅዱሳን አንድነት፣ በኃጢአት ስርየት፣ በሥጋ ትንሣኤ፣ በዘላለም ሕይወት አምናለሁ፣ አሜን።

*ይህ ምን ማለት ነው?* እኔ በራሴ የማሰብ ችሎታ ወይም ብቃት በጌታዬ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ወይም ወደ እርሱ መቅረብ እንደማልችል አምናለሁ፤ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በወንጌል ጠራኝ፣ በስጦታዎቹ አበራልኝ፣ ቀደሰኝና በእውነተኛው እምነት ጠበቀኝ።

በተመሳሳይ መንገድ እርሱ በምድር ላይ ያለችውን መላውን ቤተ ክርስቲያን ይጠራል፣ ይሰበስባል፣ ያበራል፣ ይቀድሳል፣ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋርም በአንዲት እውነተኛ እምነት ይጠብቃታል።

ከዚህች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በየዕለቱና በባለፀግነቱ እርሱ ኃጢአቴን በሙሉና የአማኞችን ሁሉ ኃጢአት ይቅር ይላል።

እርሱ በመጨረሻ ቀን እኔንና የሞቱትን ሁሉ ያስነሳል፣ ለእኔና በክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣል።

ይህ ፍፁም እውነት ነው።

***153. ይህ አንቀጽ የሚያብራራቸው አምስት ነጥቦች የትኞቹ ናቸው?***

I. *መንፈስ ቅዱስ*
II. ቤተ ክርስቲያን፣ የቅዱሳን አንድነት
III. የኃጢአት ይቅርታ
IV. የሥጋ ትንሣኤ
V. የዘለለም ሕይወት

## I. መንፈስ ቅዱስ

### የመንፈስ ቅዱስ ማንነት

***154. መንፈስ ቅዱስ ማን ነው?***

*መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር (የተስተካከለ) እውነተኛ አምላክ፣ የቅድስት ሥላሴ ሦስተኛው አካል ነው። በመሆኑም የእግዚአብሔር ኃይል ወይም ጉልበት ብቻ አይደለም።*

542. **ማቴዎስ** 28፡19 *እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ... ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው።*

***155. መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር መሆኑን እንዴት ታውቃላችሁ?***

*ምክንያቱም በቃሉ በግልጽ እግዚአብሔር ተብሎ ከመጠራቱም በተጨማሪ ስለ እርሱ እደሚከተለው ያስተምራል።*

*ሀ. መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ስሞች አሉት፤*

543. **የሐዋርያት ሥራ** 5፡3-4 *ጴጥሮስም፦ ሐናንያ ሆይ መንፈስ ቅዱስን ታታልልና ከመሬቱ ሽያጭ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለምን ሞላ ... እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አልዋሸህም አለው።*

544. **1ቆሮንቶስ** 3፡16 *የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን?*

*ለ. መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ባህርያት (ጸባያት ወይም መለያዎች) አሉት።*

545. **መዝሙር** 139፡7-10 *ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ አንተ በዚያ አለህ። ወደ ሲኦልም ብወርድ በዚያ አለህ። እንደ ንስር የንጋትን ክንፍ ብወስድ እስከ ባሕር መጨረሻም ብበርር በዚያ እጅህ ትመራኛለች፤ ቀኝህም ትይዘኛለች። (በሁሉም ቦታ መገኘት)*

546. **1ቆሮንቶስ** 2፡10 *መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ሳይቀር ሁሉን ይመረምራል (ሁሉን አዋቂነት)*

547. **ዕብራያን** 9፡14 *ነውር የሌለው ሆኖ በዘላለም መንፈስ ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ የክርስቶስ ደም እንዴት ይልቅ ሕያውን እግዚአብሔርን ልታመልኩ ከሞተ ሥራ ሕሊናችሁን ያነጻ ይሆን? (ዘለዓለማዊነት)*

*ማስታወሻ፦* **ማቴዎስ** 28፡19*ን ተመልከቱ (ቅድስና)*

*ሐ. መንፈስ ቅዱስ (እግዚአብሔር ብቻ ሊያደርግ የሚችላቸውን) መለኮታዊ ሥራዎች ይሠራል።*

548. **ዘፍጥረት** 1፡2 *ምድርም ባዶ ነበረች፤ አንዳችም አልነበረባትም፤ ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውሃ ላይ ሰፍፎ ነበር። (ፍጥረት)*

549. **ቲቶ** 3፡5 *እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን። (መቀደስ)*

*መ. መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ክብርና ልዕልና ይቀበላል።*

550. **1ጴጥሮስ** 4፡14 *የክብር መንፈስ የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ላይ ያርፋል።*

***የመንፈስ ቅዱስ ሥራ***

### *156. የመንፈስ ቅዱስ ልዩ ሥራ ምንድን ነው?*

እኔን በክርስቶስ ወደ ማመን በማምጣት የቤዛነት በረከቶችን እንዳገኝ እና መንፈሳዊ ሕይወት እንድመራ (በሰፊው ትርጉም መቀደስ) መንፈስ ቅዱስ ይቀድሰኛል (ቅዱስ ያደርገኛል)::

*ማስታወሻ፦* ‹‹መቀደስ›› የሚለው ቃል በሁለት መንገዶች ጥቅም ላይ ውሏል፤

1. በሰፊው ትርጉሙ እኛን ወደ እምነት የሚያመጣበትና እግዚአብሔርን የመምሰል ሕይወት እንድንመራም የሚያስችልበት አጠቃላዩ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ።

2. በጠባብ ትርጉሙ አማኙን የሚመራበትና እግዚአብሔርን የመምሰል ሕይወት እንዲመራ የሚያስታጥቅበት/የሚያበረታበት የተወሰነ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ።

551. **1ቆሮንቶስ** 6፡11 በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል፤ ተቀድሳችኋል፤ ጸድቃችኋል።

### *157. ይህንን እምነት በአንተ ውስጥ ለመጀመርና ለማስቀጠል መንፈስ ቅዱስ ለምን ያስፈልግሃል?*

ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚያስተምሩት በተፈጥሮ[ዬ] በመንፈሳዊ ረገድ እውር፣ የሞትኩና የእግዚአብሔር ጠላት ነኝ፤ ስለዚህ ‹‹በገዛ ራሴ ማስተዋል ወይም ብርታት በጌታዬ በኢየሱስ ለማን ወይም ወደ እርሱ ልምጣ አልችልም።።››

552. **1ቆሮንቶስ** 2፡14 ለፍጥረታዊው ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም፤ በመንፈስም የሚመረመር ስለሆነ ሊያውቀው አይችልም።

553. **ኤፌሶን** 2፡1 በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ።

554. **ሮሜ** 8፡7 ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና። (ስለ ሥጋ የሚያስብ አእምሮ ከእግዚአብሔር ጋር ጠበኛ ነው። አ.መ.ት)

555. **ኤፌሶን** 2፡8-9 ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።

556. **1ቆሮንቶስ** 12፡3 ማንም በመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በቀር ኢየሱስ ጌታ ነው ሊል [አይችልም]።

### *158. አንተን ወደ እምነት ለማምጣት መንፈስ ቅዱስ ምን አድርጓል?*

መንፈስ ቅዱስ ‹‹በወንጌል ጠርቶኛል›› ማለትም በክርስቶስ ለእኔ የሆኑትን መንፈሳዊ በረከቶች እንድካፈል በወንጌል ጋብዞኛል/ስቦኛልም።

557. **ሮሜ** 1፡16 በወንጌል አላፍርምና አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና።

558. **2ተሰሎንቄ** 2፡14 ለዚህም … በወንጌላችን ጠራችሁ።

559. ***ራእይ*** 22፡17 መንፈሱና ሙሽራይቱም ና ይላሉ። የሚሰማም ና ይበል። የተጠማም ይምጣ፤ የወደደም የሕይወትን ውሃ እንዲያው ይውሰድ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች፦* ወደ ንጉሡ ልጅ የሠርግ ግብዣ ጥሪ (**ማቴዎስ**፡22፡1-10)፤ ወደ ታላቁ ግብዣ ጥሪ (**ሉቃስ** 14፡16-17)።

### *159. ቅዱሳት መጻሕፍት ባንተ ውስጥ ይህንን ጸጋ የተሞላ የመንፈስ ሥራ እንዴት ይገልጹታል?*

ቅዱሳት መጻሕፍት መንፈስ ቅዱስ ‹‹በስጦታዎቹ እንዳበራልኝ›› ማለትም በእርሱ እንዳምን፣ እንድደሰትና መጽናናትን እንዳገኝ የመድኃኒቴን የኢየሱስን የመዳን እውቀት እንደሰጠኝ ያስተምራሉ።

560. **1ጴጥሮስ** 2፡9 እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉሥ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ።

561. **2ቆሮንቶስ** 4፡6 በክርስቶስ ፊት የእግዚአብሔርን የክብሩን እውቀት ብርሃን እንዲሰጥ በልባችን ውስጥ የበራ በጨለማ ብርሃን ይብራ ያለ እግዚአብሔር ነውና።

562. **1ጴጥሮስ** 1፡8 አሁንም ምንም ባታዩት በእርሱ አምናችሁ … በማይነገርና ክብር በሞላበት ሐሴት ደስ ይላችኋል።

563. **ሮሜ** 15፡13 የተስፋ አምላክም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በተስፋ እንድትበዙ በማመናችሁ ደስታንና ሰላምን ሁሉ ይሙላባችሁ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች፦* ፊልጶስ ክርስቶስን ሲሰብክላቸው ሰማርያውያን በታላቅ ደስታ ተሞሉ (**የሐዋርያት ሥራ** 16፡25-34)።

### *160. ይህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ምን ተብሎ ይጠራል?*

መለወጥ (መመለስ) ወይም ዳግም ልደት (አዲስ ልደት) ተብሎ ይጠራል።

564. **መዝሙር** 51፡13 ለሕግ ተላላፎች መንገድህን አስተምራለሁ፤ ኃጢአተኞችም ወደ አንተ ይመለሳሉ (መለወጥ)።

565. ዮሐንስ 3፡5-6 ኢየሱስም መለሰ እንዲህ ሲል፦ እውነት እውነት እልሃለሁ፤ ሰው ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው (ዳግም ልደት)።

### *161. መንፈስ ቅዱስ ይህንን በወጌሉ አድርጎታል ለምን ትላለህ?*

ወንጌሉ መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስን በረከቶች ሁሉ ለእኛ የሚሰጥበትና በእኛ ውስጥ እምነትን የሚፈጥርበት መሣሪያ ስለሆነ ነው።

*ማስታወሻ፦* የተጻፈውና የሚነገረው የወንጌል ቃል እና ቅዱሳት ምሥጢራት ጸጋ መሣሪያዎች ናቸው።

566. **ዮሐንስ** 17፡20 ከቃላቸው የተነሣ በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ ስለ እነዚህ ብቻ አልለምንም።

567. **ሮሜ** 10፡17 እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው።

568. **1ቆሮንቶስ** 4፡15 እኔ በክርስቶስ ኢየሱስ በወንጌል ወልጄአችኋለሁ።

569. **1ጴጥሮስ** 1፡23 ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ።

570. **ቲቶ** 3፡5 በአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን (ጥምቀት)፡፡
571. **ዮሐንስ** 20፡22-23 ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፣ ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው፡፡ (የስርየት አዋጅ)፡፡
572. **ማቴዎስ** 26፡27-28 ጽዋንም አንስቶ አመስግኖም ሰጣቸው፡፡ እንዲህም አለ፡፡ ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፤ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው፡፡ (የጌታ እራት)፡፡

### *162. ከእምነት ሌላ መንፈስ ቅዱስ በአንተ ውስጥ በወጌሉ ምን ይፈጥራል?*

መንፈስ ቅዱስ በእውነተኛ እምነት ይቀድሰኛል ይህም በእምነት አማካይነት በመላ ሕይወቴ ማለትም በመንፈሴ፣ በፈቃዴ፣ በአስተሳሰቤና በፍላጎቶቼ ተሃድሶን ያደርጋል፤ ይህም ደግሞ ከኃጢአት ጋር ታግዬ እንዳሸንፍና መልካምን እንዳደርግ ነው፡፡ (በጠባብ ትርጕሙ መቀደስ)፡፡

573. **መዝሙር** 51፡10 አቤቱ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ፤ የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ፡፡
574. **ሮሜ** 8፡9 እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደላችሁም፡፡ የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም፡፡
575. **2ቆሮንቶስ** 5፡17 ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፡፡
576. **ገላትያ** 22-23 የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት ነው፡፡
577. **ኤፌሶን** 2፡10 እኛ ፍጥረቱ ነንና እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን፡፡
578. **ኤፌሶን** 5፡18-20 መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ይህ ማባከን ነውና፡ ፡ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ፤ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ፡፡ ሁልጊዜ ስለ ሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምላካችንንና አባታችንን ስለ ሁሉ አመስግኑ፡፡

### *163. በእግዚአብሔር እይታ መልካም ሥራዎች ምንድን ናቸው?*

በእግዚአብሔር እይታ መልካም ሥራ አንድ የእግዚአብሔር ልጅ በአሰርቱ ትእዛዛት መሠረት፣ ለእግዚአብሔር ክብርና ለባልንጀራው ወይም ለባለንጀራዋ ጥቅም በእምነት የሚያደርገው፣ የሚናገረው ወይም የሚያስበው ማንኛውም ነገር ነው፡፡

579. **ዕብራውያን** 11፡6 ያለ እምነትም [እግዚአብሔርን] ደስ ማሰኘት አይቻልም፡፡
580. **ዮሐንስ** 15፡5 ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል፡፡
581. **ማቴዎስ** 15፡9 የሰውም ሥርዓት የሆነ ትመህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል፡፡
582. **ዮሐንስ** 14፡15 ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ/ትጠብቃላችሁ (አ.መ.ት.)፡፡

583. **1ቆሮንቶስ** 10፡31 *የምትበሉ ወይም የምትጠጡ ብትሆኑ ወይም ማናቸውንም ነገር ብታደርጉ ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት።*

584. ***ገላትያ*** 5፡13 *በፍቅር እርስ በርሳችሁ እንደ ባሪያዎች ሁኑ።*

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች፦* የመበለቲቱ ስጦታ (**ማርቆስ** 12፡41-44)፣ በኢየሱስ ራስ ላይ የፈሰሰው ውድ ሽቱ (**ማርቆስ** 14፡3-9)፣ ማርያምና ማርታ (**ሉቃስ** 10፡38-42)።

## *164. ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ምን ያስተምራሉ?*

ቅዱሳት መጻሕፍት መንፈስ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያኑ ስጦታዎችን እንደሚሰጥ ያስተምራሉ፣ እነዚህም፦

*ሀ. መንፈስ ቅዱስ በቃና በቅዱሳት ምሥጢራት አማካይነት ለሁሉም ክርስቲያች እጅግ በጣም የከበሩ ስጦታዎችን በክርስቶስ ማመንን፣ የኃጢአት ይቅርታንና ዘለዓለማዊ ሕይወትን በነጻ እንደሚሰጥ፣*

ለ. በሐዋርያት ዘመን መንፈስ ቅዱስ ለተወሰኑ ክርስቲያኖች ተአምራዊ ምልክቶችና ድንቆች የማድረግ (ለምሳሌ፦ ፈውስ፣ በልሳን መናገር፣ ሙታንን ማስነሣት) ስጦታ እንደ ሰጠ ያስተምራሉ። ነገር ግን እግዚአብሔር በማንኛውም ጊዜና ስፍራ ለሁሉም ክርስቲያኖች ልዩ ተአምራዊ ስጦታዎችን የግድ እንደሚሰጥ ቅዱሳት መጻሕፍት አያስተምሩም። መንፈስ ቅዱስ እንደ በጎ ፈቃዱ የእርሱን በረከቶች ይሰጣል።

585. **2ቆሮንቶስ** 12፡12 *የሐዋርያነት ምልክት በመካከላችሁ በመልክትና በድንቅ ነገር በተአምራትም በሁሉ ትዕግሥት ተደረገ።*

586. **ኤፌሶን** 2፡20-22 *በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፤ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። በእርሱም ሕንጻ ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል፤ በእርሱም እናንተ ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ።*

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ፦* ከሐዋርያት ጋር በየግል የተገናኙ ልዩ ምልክቶች (**የሐዋርያት *ሥራ*** 5፡12-16፤ 8፡14-19፤ 19፡11-12፣ 20፤ 20፡7-12)።

*ማስታወሻ፦* በተለምዶ እንግሊዝኛ ‹‹ካሪዝማቲክ›› የሚለው ቃል ብልህ ሰውን፣ የላቀ ስሜት ያጀበው አምልኮን ወይም የተለዩ ተአምራዊ ስጦታዎችን መኖራቸውን ይገልጻል። ‹‹ካሪዝማ›› የሚለው የግሪኩ ቃል ግን በቀላሉ ‹‹ስጦታ›› ማለት ሲሆን ለምሳሌ የክርስቶስን አጠቃላይ የማዳን ሥራ (**ሮሜ** 5፡15-16)፤ የዘላለም ሕይወትን (**ሮሜ** 6፡23) እና ማግባትን ወይም አለማግባትን (**1ቆሮንቶስ** 7፡7) ያመለክታል።

## *165. መጨረሻ መንፈስ ቅዱስ ለአንተ የሚያደርግልህስ ተጨማሪ ነገር ምንድን ነው?*

*መንፈስ ቅዱስ በወንጌሉ በእውነተኛው እምነት ይጠብቀኛል።*

587. ***ፊልጵስዩስ*** 1፡6 *በእናንተ መልካመን ሥራ የጀመረው እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ ይፈጽመዋል።*

588. **1ጴጥሮስ** 1፡5 *በመጨረሻው ዘመን ይገለጥ ዘንድ ለተዘጋጀ መዳን በእምነት በእግዚአብሔር ኃይል ተጠበቃችሁ።*

589. **1ተሰሎንቄ** 2፡13 *የእግዚአብሔር ቃል በእናንተ በምታምኑ እንደሚሠራ …።*

## *166. መንፈስ ቅዱስ ሌላ ማንን አዲስ ሕይወት በመስጠት ያድሳል?*

‹‹መንፈስ ቅዱስ በምድር ላይ ያለችውን መላዋን ቤተ ክርስቲያን ይጠራል፤ ይሰበስባል፤ ያበራላታል፤ ይቀድሳታል፤ በአንድ እውነተኛ እምነትም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ይጠብቃታል፡፡››

590. **ኤፌሶን** 3፡6 አሕዛብም አብረው ይወርሳሉ፤ በአንድ አካልም አብረው ይሆናሉ፤ በወንጌልም መሰበክ በክርስቶስ ኢየሱስ በሆነ የተስፋ ቃል አብረው ይወርሳሉ፡፡

## *167. መንፈስ ቅዱስ ይህንን በሰዎች ሕይወት ሁሉ ውስጥ ሊያደርግ ይፈልጋል?*

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ሁሉ ለመለወጥና በወንጌል አማካይነት ወደ ድነት ሊያመጣቸው አጥብቆ ይፈልጋል፡፡

591. **ሕዝቅኤል** 33፡11 ኃጢአተኛው ከመንገዱ ተመልሶ በሕይወት ይኖር ዘንድ እንጂ ኃጢአተኛው ይሞት ዘንድ አልፈቅድም፡፡

592. **1ጢሞቴዎስ** 2፡4 ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር …

593. **2ጴጥሮስ** 3፡9 ጌታ … ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል፡፡

## *168. እንግዲያውስ ሰዎች ሁሉ ለምን አይድኑም?*

ብዙዎች ቃሉን አይቀበሉም፤ መንፈስ ቅዱስንም ይቃወማሉ፤ ስለዚህ ባለማመን ጸንተው ይኖሩና በገዛ ራሳቸው ጥፋት በእግዚአብሔር ፍርድ ሥር ይወድቃሉ፡፡

594. **ማቴዎስ** 23፡37 ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም ሆይ ነቢያትን የምትገድል ወደ እርስዋ የተላኩትንም የምትወግር ዶሮ ጫጩቶችዋን ከክንፎችዋ በታች እንደምትሰበስብ ልጆችሽን እሰበስብ ዘንድ ስንት ጊዜ ወደድሁ! አልወደዳችሁምም፡፡

595. **የሐዋርያት ሥራ** 7፡51 እናንተ አንገተ ደንዳኖች ልባችሁና ጆሮአችሁም ያልተገረዘ አባቶቻችሁ እንደ ተቃወሙት እናንተ ደግሞ ሁልጊዜ መንፈስ ቅደስን ትቃወማላችሁ፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች፡-* የተጋበዙት እንግዶች ለመምጣት እምቢ አሉ (**ማቴዎስ** 22፡1-10) እንግዶች ግብዣውን ለመቀበል አልፈለጉም (**ሉቃስ** 14፡16-24)፡፡

# II. ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳን ኅብረት

## *169. ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ምንድን ናት?*

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳን ኅብረት፣ በክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ አጠቃላይ ስብስብ ናት፡፡ በክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ፣ ነገር ግን አማኞች ብቻ የቤተ ክርስቲያን አባላት ናቸው (የማትታየው ቤተ ክርስቲያን)፡፡

596. **ኤፌሶን** 2፡19-22 ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም፡፡ በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፤ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፡፡ በእርሱም ሕንፃ ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል፤ በእርሱም እናንተ ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ፡፡

597. **ዮሐንስ** 10፡16 ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፤ እነርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል፤ ድምፄንም ይሰማሉ፤ አንድም መንጋ ይሆናሉ፤ እረኛውም አንድ፡፡
598. **ሮሜ** 8፡9 የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም፡፡

### *170. በቤተ ክርስቲያን ‹‹አምናለሁ›› የምትለው ለምንድን ነው?*

ሀ. ምክንያቱም ሰዎች የቤተ ክርስቲያን አባል እንዲሆኑ የሚያደርጋቸው እምነት ሊታይ የማይችልና ቤተ ክርስቲያንም ለሰዎች ዓይኖች ልትታይ የማትችል ስለሆነች ነው፡፡

599. **ሉቃስ** 17፡20-21 የእግዚአብሔር መንግሥት በመጠባበቅ አትመጣም፤ ደግሞም እነኋት በዚህ ወይም እነኋት በዚያ አይሉአትም፡፡ እነሆ የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናትና፡፡
600. **1ጢሞቴዎስ** 2፡19 ጌታ ለእርሱ የሆኑትን ያውቃል … የሚለው ማኅተም ያለበት የተደላደለ የእግዚአብሔር መሠረት ቆሞአል፡፡

ለ. መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያንን እንደሚሰበስብ እና መጠበቁን እንደሚቀጥል ቅዱሳት መጻሕፍት ያረጋግጡልናል፡፡

601. **ማቴዎስ** 16፡18 አንተ ጴጥሮስ ነህ፤ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፤ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም፡፡
602. **የሐዋርያት ሥራ** 2፡41፣47 ቃንም የተቀበሉ ተጠመቁ በዚያም ቀን ሦስት ሺህ የሚህል ነፍስ ተጨመሩ … ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር፡፡
*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ፡-* በእስራኤል ውስጥ ሰባቱ ሺህ (1**ነገሥት** 19፡8-18)፡፡

### *171. [በአንዲት] ቤተ ክርስቲያን አምናለሁ ለምን ትላለህ?*

አንድና ብቸኛ ራሷ ክርስቶስ የሆነላት፣ አንዲት የአማኞች (የቅዱሳን) መንፈሳዊ አካል ስለሆነች፡፡

603. **ሮሜ** 12፡4-5 በአንድ አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉን … እንዲሁ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን፡፡
604. **ኤፌሶን** 4፡3-6 በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ፡፡ በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፡፡ አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ፡፡
605. **ቈላስይስ** 1፡18 እርሱም [ክርስቶስ] የአካሉ ማለት የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው፡፡

### *172. ቤተ ክርስቲያን ለምን ‹‹ቅድስት›› ተብላ ትጠራለች?*

በክርስቶስ ደም በነጹና እግዚአብሔርን በተቀደሰ አኗኗር በሚያገለግሉ አማኞች፣ ቅዱስ ሰዎች (ቅዱሳን) የተዋቀረች ናት፡፡

606. **ኤፌሶን** 5፡25-27 ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ወደዳት … በውሃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤ እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነች ቤተ ክርስቲያንን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ፡፡

607. **1ጴጥሮስ** 2፡5 እናንተ ደግሞ እንደ ሕያዋን ድንጋዮች ሆናችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መስዋዕትን ታቀርቡ ዘንድ ቅዱሳን ካህናት እንድትሆኑ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ።

### *173. ቤተ ክርስቲያን ለምንድን ነው ‹‹ክርስቲያን›› ተብላ የምትጠራው?*

የክርስቶስ ስለሆነችና በእርሱ ብቻ ላይ የታነጸች ስለሆነች ነው።

608. **1ቆሮንቶስ** 3፡11 ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

609. **ኤፌሶን** 2፡20 በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፤ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።

*ማስታወሻ፡-* አንዳንድ ጊዜ በሃይማኖት መግለጫዎች ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውለው ‹‹ካቶሊክ›› የሚለው ቃል ‹‹ዓለም አቀፍ›› ወይም ‹‹አጠቃላይ›› ማለት ነው። ወንጌሉ በሚታወጅበት በማንኛውም ቦታ ቤተ ክርስቲያን በመላው ዓለም ላይ ትኖራለች።

### *174. ቅድስት የክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን የምትገኘው የት ነው?*

ቅድስት የክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን ‹‹ወንጌሉ በንጹሕ የሚሰበክበት (የሚማሩበት) እና ቅዱሳት ምሥጢራት በትክክል የሚታደሉበት ቦታ የምትገኝ ናት (የኦግስበርግ የእምነት መግለጫ VII, 1) ወንጌሉና ቅዱሳት ምሥጢራት ‹‹የቤተ ክርስቲያን ምልክቶች›› ተብለው ይጠራሉ።

610. **ኢሳይያስ** 55፡10-11 ዝናብና በረዶ ከሰማይ እንደሚወርድ ምድርን እንደሚያረካት ታበቅልና ታፈራም ዘንድ እንደሚያደርጋት ዘርንም ለሚዘራ እንጀራንም ለሚበላ እንደሚሰጥ እንጂ ወደ ሰማይ እንደማይመለስ ከአፌ የሚወጣ ቃሌ እንዲሁ ይሆናል የምሻውን ያደርጋል የላክሁትንም ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም።

### *175. ‹‹ቤተ ክርስቲያን›› የሚለው ቃል በምን ሌሎች ትርጉሞች ጥቅም ላይ ይውላል?*

***ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል፡-***

ሀ. የምትታየው የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን፣

ለ. አንድን ቤተ እምነት፣

ሐ. አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን፣

መ. አንድን የአምልኮ ቤትን ለማመልከትም ጥቅም ላይ ይውላል።

### *176. መጽሐፍ ቅዱስ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን ለምን ‹‹ቤተ ክርስቲያን›› ብሎ ይጠራቸዋል?*

በጸጋ መሣሪያዎች ዙሪያ የሚሰበሰቡ በአንድ ቦታ ላይ የሚታዩ ስብስቦች አብያተ ክርስቲያናት ተብለው ይጠራሉ፤ ምክንያቱም እዚያ ስፍራ ላይ በቃሉና በቅዱሳት ምሥጢራት ዙሪያ አማኞች ይሰበሰባሉ።

611. **ማቴዎስ** 18፡17 እነርሱንም ባይሰማ ለቤተ ክርስቲያን ንገራት፤ ደግሞም ቤተ ክርስቲያንን ባይሰማት እንደ አረመኔና እንደ ቀራጭ ይሁንልህ።

612. ***ማቴዎስ* 28፡19-20** *እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡*

613. **1ቆሮንቶስ 1፡2** *በቆሮንቶስ ላለች ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ ለተቀደሱት የእነርሱና የእኛ ጌታ የሆነውን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በየስፍራው ከሚጠሩት ሁሉ ጋር ቅዱሳን ለመሆን ለተጠሩት፡፡*

*ማስታወሻ፡-* ጳውሎስ በገላትያ ለነበሩት አብያተ ክርስቲያናት ጽፏል (***ገላትያ* 1፡2**)፣ ለተሰሎንቄ ሰዎች ቤተ ክርስቲያንም ጽፏል (**1ተሰሎንቄ 1፡1**)፣ ዮሐንስ ለትንሹ እስያ ሰባት አብያተ ክርስቲያናት ጽፏል (**ራእይ 1-3**)፣ የአጥቢያዎችም ስብስብ ‹‹ቤተ ክርስቲያን›› ተብሎ ይጠራል (**የሐዋርያት *ሥራ* 9፡31**)፡፡

### *177. የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ምንድን ናት?*

የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ፈቃድ የሚገለገሉና የክርስትና እምነታቸውን በግልጽ የሚያሳውቁ፣ ነገር ግን ከእውነተኛ ክርስቲያኖች በተጨማሪ በመካከላቸው የማያምኑም ሰዎች የሚገኙባቸው አጠቃላይ ስብስብ ናት፡፡

### *178. እንግዲያውስ ሁለት አብያተ ክርስቲያናት አንዷ የምትታይና ሌላኛዋ የማትታይ አሉን?*

በክርስቶስ የሚያምኑትን ሁሉ የያዘች አንዲት ቤተ ክርስቲያን ብቻ አለች፡፡ የምትታየዋ ስብስብ ቤተ ክርስቲያን ተብላ የተጠራችበት ምክንያት ግብዞችም ጭምር በሚገኙባት ጉባኤ ውስጥ አማኞች በጸጋ መሣሪያዎች ዙሪያ ስለሚሰበሰቡ ነው፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች፡-* ከሁሉም ዓይነት አሣዎች የያዘው መረብ (***ማቴዎስ* 13፡ 47-48**)፣ የሠርግ ልብስ ያልለበሰ ሰው (***ማቴዎስ* 22፡11-12**)፣ ሐናንያና ሰጲራ (**የሐዋርያት *ሥራ* 5፡1-11**)፡፡

### *179. ቅዱሳት መጻሕፍት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለ ሕይወታችን ምን ያስተምራሉ?*

*ሀ.* በክርስቶስ በመድኃኒታችን ላይ በእውነተኛ እምነት የክርስቶስ አካል የሆነችው የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን አባላት ለመሆንና በዚያም ለመቀጠል ዘወትር መፈለግ እንደሚገባን ያስተምራሉ፡፡

614. **ዮሐንስ 15፡5** *እኔ የወይን ግንድ ነኝ፤ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ፡፡ ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል፡፡*

615. **2ቆሮንቶስ 13፡5** *በእምነት መሆናችሁን ለማወቅ ራሳችሁን መርምሩ፤ ራሳችሁን ፈትኑ* (*አ.መ.ት*)፡፡

*ለ. የመጽሐፍ ቅዱስን መሠረተ እምነት በመላው በንጹሕ ለምትናገረውና ለምታስተምረው እንዲሁም በክርስቶስ ድንጋጌ መሠረት ቅዱሳት ምሥጢራትን ለምታድል ለዚያች የምትታይ ቤተ ክርስቲያን ታማኝ መሆን ይገባናል፡፡*

616. **ዮሐንስ 8፡31-32** *እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ፤ እውነትንም ታውቃላችሁ፤ እውነትም አርነት ያወጣችኋል፡፡*

617. **የሐዋርያት ሥራ** 2፡42 በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቁረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር፡፡

618. **1ቆሮንቶስ** 1፡10 ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ሁላችሁ አንድ ንግግር እንድትናገሩ በአንድ ልብና በአንድ አሳብም የተባበራችሁ እንድትሆኑ እንጂ መለያየት በመካከላችሁ እንዳይሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እለምናችኋለሁ፡፡

*ማስታወሻ፡- ሃይማኖታዊ ቤተ እምነት የቤተ ክርስቲያን አካል ወይም የተለየ ስም እና የራሱ የሆነ የመሠረተ እምነት ስብስብ/ጥቅልል ያለው ድርጅት ነው፡፡*

*ሐ. ሐሰተኛ አስተማሪዎችን፣ ሐሰተኛ ‹‹አብያተ ክርስቲያናትን›› እና ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚቃረን ሃይማኖትን የሚያራምዱትን ድርጅቶች ሁሉ መራቅ ይገባናል፡፡*

619. **ማቴዎስ** 7፡15-16 የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውስጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኩላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ፡፡ ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ፡፡

620. **ሮሜ** 16፡17-18 [ነገር ግን] ወንድሞች ሆይ እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን፣ መለያየትንና ማሰናከያን የሚያደርጉትን ሰዎች እንድትመለከቱ እለምናችኋለሁ፤ ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ፤ እንዲህ ያሉት ለገዛ ሆዳቸው እንጂ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አይገዙምና በመልካምና በሚያቆላምጥ ንግግርም ተንኮል የሌለባቸውን ሰዎች ልብ ያታልላሉ፡፡

621. **2ቆሮንቶስ** 6፡14 ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ (ቊ 15-18 ተመልከት)፡፡

622. **ገላትያ** 1፡8 እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን፡፡

623. **2ጢሞቴዎስ** 4፡3 ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሡበት ዘመን ይመጣልና፤ ነገር ግን ጆሮዎቻቸውን የሚያሳክክ ስለሆነ እንደገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ፡፡

624. **1ዮሐንስ** 4፡1 ወዳጆች ሆይ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፤ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደሆነ መርምሩ፤ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና፡፡

*መ. የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ለሌሎች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በመንገር፣ የግል አገልግሎት በመስጠት፣ በጸሎትና በገንዘብ ድጋፍ መጠበቅና ማስፋት ይገባናል፡፡*

625. **ዮሐንስ** 20፡21 አብ እንደላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ፡፡

626. **የሐዋርያት ሥራ** 1፡8 መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፤ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ፡፡

627. **የሐዋርያት ሥራ** 8፡1፣4 በዚያን ቀንም በኢየሩሳሌም ባለች ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ሆነ፤ ሁሉም ከሐዋርያትም በቀር ወደ ይሁዳና ወደ ሰማርያ አገሮች ተበተኑ፡፡ … የተበተኑትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ፡፡

628. **1ጴጥሮስ** 2፡9 እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉሥ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፡፡

629. **1ጴጥሮስ** 3፡15 በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቁአችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፤ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሃት ይሁን፡፡

630. **ሉቃስ** 10፡2 አላቸውም፡- መከሩስ ብዙ ነው፤ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤ እንግዲህ የመከሩን ጌታ ለመከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት፡፡

631. **ገላትያ** 6፡6 ቃሉን የሚማር ከሚያስተምረው ጋር መልካምን ነገር ሁሉ ይከፋፈል፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች፡-* ጴጥሮስ ለሕዝብ ተናገረ (**የሐዋርያት ሥራ** 2፡17-39፤ 3፡12-16) ፊልጶስ ለጃንደረባው መሰከረ (**የሐዋርያት ሥራ** 8፡26-35) የቀደሙት ለወንጌሉ መሠራጨት ጸለዩ (**የሐዋርያት ሥራ** 4፡23-30) ለአገልግሎት ድጋፍም አዋጡ (**ፊልጵስዩስ** 4፡16-19)፡፡

## III. የኃጢአት ስርየት

### *180. ‹‹በኃጢአት ስርየት አምናለሁ›› የምትለው ለምንድን ነው?*

በኃጢአት ይቅርታ አምናለሁ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በክርስቶስ አማካይነት ለኃጢአተኛው የሰው ዘር በሙሉ ምሕረትንና ይቅርታን ስላወጀ ነው፡፡

632. **መዝሙር** 130፡3-4 አቤቱ ኃጢአትንስ ብትጠባበቅ አቤቱ ማን ይቆማል? ይቅርታ ከአንተ ዘንድ ነውና (ነገር ግን በአንተ ዘንድ ይቅርታ አለ፡፡ አ.መ.ት.)፡፡

633. **2ቆሮንቶስ** 5፡19 እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፤ በደላቸውን አይቈጥርባቸውም ነበር፡፡

### *181. እግዚአብሔር ኃጢአትን ይቅር እንዲል የሚያደርገው ምንድን ነው?*

እግዚአብሔር ኃጢአትን ይቅር ይላል፤ ምክንያቱም እርሱ መሐሪ ስለሆነ እና ክርስቶስ ለኃጢአተኞች ማስተሰርያ መሥዋዕት ከመሆኑ የተነሣ ነው፡፡

634. **መዝሙር** 86፡15 አቤቱ አንተ ግን መሐሪና ርኅሩኅ አምላክ ነህ፤ መዓትህ የራቀ ምሕረትህም እውነትህም የበዛ፡፡

635. **ዮሐንስ** 3፡16 በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና፡፡

636. **ኤፌሶን** 1፡7 በውድ ልጁም እንደ ጸጋው ባለጠግነት መጠን በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን፤ እርሱም የበደላችን ስርየት፡፡

637. **1ዮሐንስ** 2፡2 እርሱም የኃጢአታችን ማስተስሪያ ነው፤ ለኃጢአታችንም ብቻ አይደለም ነገር ግን ለዓለሙ ሁሉ ኃጢአት እንጂ፡፡

### *182. ጻድቅ እና ቅዱስ አምላክ ኃጢአተኞችን ጻድቅ ብሎ ማወጅ (ማጽደቅ) እንዴት ይቻለዋል?*

እግዚአብሔር ስለ ክርስቶስ ሲል ኃጢአተኞችን ጻድቅ ብሎ ያውጃል፤ ማለትም የእኛ ኃጢአት በመድኃኒታችን በክርስቶስ ላይ ተጭኗል ወይም ተቆጥሯል፤ የክርስቶስ ጽድቅ ደግሞ ለእኛ ይሰጣል ወይም ይቆጠራል፡፡

638. **2ቆሮንቶስ** 5፡21 እኛ በእርሱ [በክርስቶስ] ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው፡፡

639. **ሮሜ** 3፡22-24 ልዩነት የለምና ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሎአቸዋል፤ በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ።

640. **ሮሜ** 4፡25 ስለ በደላችን አልፎ የተሰጠውን እኛን ስለ ማጽደቅም የተነሣውን ጌታችንን ኢየሱስን …

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ፡- ንጉሡ የአገልጋዩን እዳ ሁሉ ይቅር አለው* (**ማቴዎስ** 18፡23-35)።

### *183. እግዚአብሔር የኃጢአት ይቅርታን የሚሰጠው የት ነው?*

እግዚአብሔር የኃጢአትን ይቅርታ የሚለግሰው በወንጌሉ ውስጥ ነው።

641. **ሉቃስ** 24፡47 በስሙም ንስሐና የኃጢአት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል።

642. **ሮሜ** 16 በወንጌል አላፍራምና አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና።

643. **2ቆሮንቶስ** 5፡19 በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ። [መልእክት]።

### *184. ይህንን የኃጢአት ስርየት እንዴት ትቀበላለህ?*

ይህንን [የኃጢአት] ስርየት በእምነት አማካይነት ማለትም ወንጌሉን በማመን እቀበላለሁ።

644. **ዘፍጥረት** 15፡6 አብራምም በእግዚአብሔር አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት።

645. **ሮሜ** 3፡28 ሰው ያለ ሕግ *ሥራ* በእምነት እንዲጸድቅ [እንቈጥራለንና]።

646. **ሮሜ** 4፡5 ለማይሠራ፣ ኃጢአተኛውንም በሚያጸድቅ ለሚያምን ሰው እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቈጠርለታል።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ- ቀራጩ በቤተ መቅደስ ውስጥ* (**ሉቃስ** 18፡9-14)።

### *185. የኃጢአቱ ስርየት እርግጠኛ መሆን የምችለውና የሚገባኝ ለምንድ ነው?*

የኃጢአቱ ስርየት እርግጠኛ መሆን የምችለውና የሚገባኝ እግዚአብሔር በክርስቶስ የተስፋ ቃሉን ስለሚጠብቅ ነው።

647. **ሮሜ** 8፡38-39 ሞት ቢሆን ሕይወትም ቢሆን መላእክትም ቢሆኑ ግዛትም ቢሆን ያለውም ቢሆን የሚመጣውም ቢሆን ኃይላትም ቢሆኑ ከፍታም ቢሆን ዝቅታም ቢሆን ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ።

648. **2ጢሞቴዎስ** 1፡12 *ያመንሁትን* አውቃለሁና የሰጠሁትንም አደራ እስከዚያ ቀን ድረስ ሊጠብቅ እንዲችል ተረድቼአለሁ።

### *186. በክርስቶስ በእምነት አማካይነት በጸጋ የመጽደቅን ትምህርት አጥብቀን መያዝ የሚገባን ለምንድን ነው?*

ይህንን ትመህርት አጥብቀን መያዝ የሚገባን፡-

ሀ. የክርስትና ሃይማኖት/እምነት እጅግ በጣም አስፈላጊው መሠረተ እምነት ስለሆነ፣

ለ. ድነትን በሥራ ከሚያስተምሩት ከሐሰተኛ ሃይማኖቶች ሁሉ ክርስትና ሃይማኖትን የተለየ የሚያደርገው ስለሆነ፣

649. **የሐዋርያት ሥራ** 4፡12 *መዳንም በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።*

650. **የሐዋርያት ሥራ** 10፡43 *በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኃጢአቱን ስርየት እንዲቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል።*

651. **ገላትያ** 5፡4-5 *በሕግ ልትጸድቁ የምትፈልጉ ከክርስቶስ ተለይታችሁ ከጸጋው ወድቃችኋል። እኛ በመንፈስ ከእምነት የጽድቅን ተስፋ እንጠባበቃለንና።*

*ማስታወሻ፦* **ሚኪያስ** 7፡18-20ን *ተመልከት።*

*ሐ. ለተጸጸተው ኃጢአተኛ ዘላቂ መጽናናት የሚሰጠው ስለሆነ፣*

652. **የሐዋርያት ሥራ** 16፡30-31፣34 *ጌቶች ሆይ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? አላቸው። እነርሱም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህም ትድናላችሁ አሉት። ... በእግዚአብሔርም ስላመነ ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር ሐሴት አደረገ።*

653. **ማቴዎስ** 9፡2 *አንተ ልጅ አይዞህ ኃጢአትህ ተሰረየችልህ።*

*መ. በክርስቶስ ስለ ጸጋውና ምሕረቱ ክብርን ሁሉ ለእግዚአብሔር የሚሰጥ ስለሆነ ነው።*

654. **ራእይ** 1፡5-6 *ለወደደን፣ ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን መንግሥትም ለአምላኩና ለአባቱም ካህናት እንድንሆን ላደረገ ለእርሱ ከዘላም እስከ ዘላለም ድረስ ክብርና ኃይል ይሁን አሜን።*

## IV. *የሥጋ ትንሣኤ*

### *187. ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ሥጋ ትንሣኤ ምን ያስተምራሉ?*

በመጨረሻው ቀን ክርስቶስ ‹‹እኔንና ሙታንን ሁሉ›› እንደሚያስነሣ ያስተምራሉ። የሞቱት እነዚያው አካላት ሕያዋን ይሆናሉ።

655. **ኢዮብ** 19፡25-27 *እኔን ግን የሚቤዠኝ ሕያው እንደሆነ በመጨረሻም ዘመን በምድር ላይ እንዲቆም ይህ ቁርበቴም ከጠፋ በኋላ በዚያን ጊዜ ከሥጋዬ ተለይቼ እግዚአብሔርን እንዳይ አውቃለሁ፤ እኔ ራሴ አየዋለሁ፤ ዓይኖቼም ይመለከቱታል፤ ከእኔም ሌላ አይደለም።*

656. **ዮሐንስ** 5፡28-29 *በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤* [ይወጣሉም]።

657. **1ተሰሎንቄ** 4፡16 *ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ።*

### *188. ሰዎች በሌሎች አካላት ወይም ቅርጾች እንደገና ይወለዳሉን?*

ሰዎች በሚሞቱበት ጊዜ በሌሎች አካላት ወይም ተከታታይነት ባላቸው አካላት እደገና ይወለዳሉ ብሎ የሚያምነው ‹‹እንደገና ሥጋ መልበስ›› ለቅዱሳት መጻሕፍት ተጻራሪ ነው።

658. *ዕብራውያን* 9፡27-28 *ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደተመደበባቸው እንዲሁ ክርስቶስ ደግሞ የብዙዎችን ኃጢአት ሊሸከም አንድ ጊዜ ከተሠዋ በኋላ ያድናቸው ዘንድ ለሚጠባበቁት ሁለተኛ ጊዜ ያለ ኃጢአት ይታይላቸዋል፡፡*
***ማስታወሻ፡-*** 1ቆሮንቶስ 15ን ተመልከት፡፡

***189. በትንሣኤ ቀን በሚያምኑትና በማያምኑት መካከል ምን ልዩነት ይኖራል?***

*ሀ. አማኞች በከበሩ አካላት ይነሡና በመንግሥተ ሰማይ ከእግዚአብሔር ጋር ወደ ዘላለም ሕይወት ይገባሉ፡፡*

659. **ዳንኤል** 12፡2 *በምድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉቱ ብዙዎች ይነቃሉ፤ እኩሌቶቹ ወደ ዘላለም ሕይወት እኩሌቶቹም ወደ እፍረትና ወደ ዘላለም ጉስቁልና፡፡*

660. **ዮሐንስ** 5፡28-29 *በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤ መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ፡፡*

661. **1ቆሮንቶስ** 15፡42-43 *የሙታን ትንሣኤ ደግሞ እንዲሁ ነው፡፡ በመበስበስ ይዘራል፤ ባለመበስበስ ይነሣል፤ በውርደት ይዘራል፤ በክብር ይነሣል፤ በድካም ይዘራል፤ በኃይል ይነሣል፡፡*

662. **ፊልጵስዩስ** 3፡21 [ክርስቶስ] … *ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል፡፡*

*ለ. የማያምኑቱ ለዘለዓለም ሞት ማለትም በሲኦል ለዘለዓለም ለእፍረትና ሥቃይ ይነሣሉ፡*
*፡*

663. **ኢሳይያስ** 66፡24 *ትላቸው አይሞትምና፤ እሳታቸውም አይጠፋምና፤ ለሥጋ ለባሽም ሁሉ አስጸያፊ ነገር ይሆናሉ፡፡*

664. **ማቴዎስ** 10፡28 *ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ፤ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋን በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ፡*

655. **ማቴዎስ** 25፡41 *በዚያን ጊዜ በግራው ያሉትን ደግሞ ይላቸዋል፡- እናንተ ርጉማን ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ፡፡*

666. **ራእይ** 1፡7 *እነሆ ከደመና ጋር ይመጣል፤ ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል፤ የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ፡፡ አዎን አሜን፡፡*

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ፡-* የባለ ጸጋውና የአልአዛር ታሪክ ሁለት ቦታዎች ብቻ መኖራቸውን ያብራራል (**ሉቃስ** 16፡19-31)፡፡

## V. የዘለዓለም ሕይወት

***190. እግዚአብሔር የዘለአለም ሕይወት የሚሰጠው ለማን ነው?***

እግዚአብሔር ለእኔና በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ የዘላለም ሕይወት ይሰጣል፡፡

*ሀ. የዘለዓለም ሕይወት የአሁን ጊዜ ይዞታ ነው፡፡*

667. **ዮሐንስ** 17፡3 *እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት፡፡*

668. **ዮሐንስ** 16 በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።
669. **ሮሜ** 10፡9 ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና።
670. **ዮሐንስ** 3፡36 በልጁ የሚያምን የዘላም ሕይወት አለው፤ በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቊጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም።
ለ. በሞት ጊዜ የአማኝ ነፍስ ወዲያውኑ ከክርስቶስ ጋር በሰማይ ትሆናለች።
671. **መክብብ** 12፡7 አፈርም ወደ ነበረበት ምድር ነፍስም ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሔር [ይመለሳል]።
672. **ሉቃስ** 23፡43 ኢየሱስም፦ እውነት እልሃለሁ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ አለው።
673. **ዮሐንስ** 17፡24 ልሄድ ከክርስቶስ ጋር ልኖር እናፍቃለሁ፤ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና፤ ነገር ግን በሥጋ መኖሬ ስለ እናንተ እጅግ የሚስፈልግ ነው።
675. **ራእይ** 14፡13 ከሰማይም ከእንግዲህ ወዲህ በጌታ የሚሞቱ ሙታን በፁዓን ናቸው። መንፈስ፦ አዎ ከድካማቸው ያርፉ ዘንድ ሥራቸውም ይከተላቸዋል። ብለህ ጻፍ የሚል ድምፅ ሰማሁ።

ሐ. በመጨረሻው ቀን አማኞች በአካልም በነፍም በሁለቱም ከክርስቶስ ጋር ለዘላለም የመሆንን ሙሉ ደስታ ይጀምራሉ።

676. **1ቆሮንቶስ** 15፡51-52 እነሆ አንድ ምሥጢር እነግራችኋለሁ፤ ሁላችን አናንቀላፋም ነገር ግን የኋለኛ መለከት ሲነፋ ሁላችን በድንገት ብቅጽበት ዓይን እንለወጣን፤ መለከት ይነፋልና ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ፤ እኛም እንለወጣን።
677. **ማቴዎስ** 25፡34 ንጉም [ኢየሱስ] በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል፦ እናንተ የአባቴ ቡሩካን ኑ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ።
678. **መዝሙር** 16፡11 ከፊትህ ጋር ደስታን አጠገብኸኝ፤ በቀኝህም የዘላለም ፍስሐ አለ።
679. **ሮሜ** 8፡18 ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ።
680. **1ዮሐንስ** 3፡2 ወዳጆች ሆይ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፤ ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠም፤ ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንድንመስል እናውቃለን።

### *191. የዘለዓለም ሕይወት እንዳለህ እርግጠኛ ነህን?*

አሁን እንኳ በክርስቶስ በመድኃኒቴ እንደማምን ከገዛ ራሴ ምግባር ሳይሆን በክርስቶስ ንጹሕ ጸጋ ለዘለዓለም ሕይወት እንደተመረጥኩኝ እና ማንም ከእጁ ሊነጥቀኝ እንደማይችል ዐውቃለሁ (ዘለዓለማዊው የጸጋ ምርጫ ወይም ቅድመ ውሳኔ)።

681. **ዮሐንስ** 10፡27-28 በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ፤ እኔም አውቃቸዋለሁ፤ ይከተሉኝማል። እኔም የዘላም ሕይወትን እሰጣቸዋለህ፤ ለዘላለምም አይጠፉም፤ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም።
682. **ሮሜ** 8፡28-30 እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ ዐሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኵር ይሆን ዘንድ አስቀድሞ

ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአልና፤ አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው፤ የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው፤ ያጸደቃቸውን እነዚህን ደግሞ አከበራቸው፡፡

683. **ኤፌሶን** 1፡3-6 በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ፡፡ ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን፡፡ በበጎ ፈቃዱ እንደወደደ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን፡፡ በውድ ልጁም እንዲያው የሰጠን የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ ይህን አደረገ፡፡

***192. ይህንን አንቀጽ ‹‹ይህ ፍጹም የተረጋገጠ እውነት ነው›› በሚሉት ቃላት የምትደመድመው ለምንድን ነው?***

ምክንያቱም በዚህ አንቀጽ ውስጥ የምመሰክረው ነገር ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የተነገረ በመሆኑ በጽኑ የማምነው ስለሆነ ነው፡፡



## የጌታ ጸሎት

### *193. በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑት እግዚአብሔር ምን እድልና ትእዛዝ ይሰጣቸዋል?*

እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑትን እንዲጸልዩ ያዝዛቸዋል፤ ይጋብዛቸዋልም።

684. **ማቴዎስ** 7፡7-8 ለምኑ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ ይከፈትላችሁማል። የሚለምነው ሁሉ ይቀበላልና፤ የሚፈልገውም ያገኛል፤ መዝጊያን ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል።

685. **1ተሰሎንቄ** 5፡16-18 ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ፤ ሳታቋርጡ ጸልዩ፤ በሁሉ አመስግኑ፤ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እናንተ ነውና።

### *194. ጸሎት ምንድን ነው?*

ጸሎት በቃላትና በዐሳቦች ለእግዚአብሔር መናገር ነው።

686. **መዝሙር** 19፡14 አቤቱ ረድኤቴ መድኃኒቴም የአፌ ቃልና የልቤ ዐሳብ በፊትህ ያማረ ይሁን።

687. **የሐዋርያት ሥራ** 7፡59-60 እስጢፋኖስም ጌታ ኢየሱስ ሆይ ነፍሴን ተቀበል ብሎ ሲጣራ ይወግሩት ነበር። ተንበርክኮም ጌታ ሆይ ይህን ኃጢአት አትቍጠርባቸው ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ። ይህን ብሎ አንቀላፋ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች፡-* አብርሃም ለሰዶም ጸለየ (**ዘፍጥረት** 18፡22-23)፤ ኢየሱስ በጌቴሴማኒ (**ማቴዎስ** 26፡36-44)፤ ጴጥሮስና ዮሐንስ ከእስር ቤት ስለ ተፈቱ ምስጋና ተደረገ (**የሐዋርያት ሥራ** 4፡23-31)።

### *195. ወደ ማን መጸለይ ይገባናል?*

ወደ ጣዖታት፣ ወደ ቅዱሳን ወይም እግዚአብሔር ወደ ፈጠረው የትኛውም ነገር ሳይሆን አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ወደ ሆነው እውነተኛ አምላክ ብቻ መጸለይ ይገባናል።

688. **መዝሙር** 65፡2 ሥጋ ሁሉ ጸሎትን ወደምትሰማ ወደ አንተ ይመጣል።

689. **1ዮሐንስ** 5፡20-21 እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን፤ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው። ልጆች ሆይ ከጣዖታት ራሳችሁን ጠብቁ።

690. **ራእይ** 22፡8-9 ይህንም ያየሁትና የሰማሁት እኔ ዮሐንስ ነኝ። በሰማሁትና ባየሁትም ጊዜ ይህን ባሳየኝ በመልአኩ እግር ፊት እሰግድ ዘንድ ተደፋሁ። እርሱም፡- እንዳታደርገው

ተጠንቀቅ፤ ከአንተ ጋር ከወንድሞችህም ከነቢያት ጋር የዚህንም መጽሐፍ ቃል ከሚጠብቁ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ፤ ለእግዚአብሔር ስገድ አለኝ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች፦* ኤልያስና የበአል ነቢያት (1**ነገሥት** 18፡25-29፣ 36-39) ዳንኤል በአንበሳ ጉድጓድ ውስጥ (**ዳንኤል** 6፡1-23)፤ ጳውሎስ በልስጥራ (**የሐዋርያት ሥራ** 14፡ 8-18)፤ የኢየሱስ የሊቀ ክህነት ጸሎት (**ዮሐንስ** 17)።

### *196. በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው የእነማን ጸሎት ነው?*

በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ብቻ ወደ እግዚአብሔር መጸለይና በእርሱ እንደሚሰሙም መጠበቅ ይችላሉ።

691. **ዮሐንስ** 14፡13-14 አብም ስለ ወልድ እንዲከብር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ። ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ።

692. **ዮሐንስ** 15፡7 በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ፤ ይሆንላችሁማል።

### *197. የጸሎታችን ይዘት ምን መሆን ይገባዋል?*

በጸሎታችን ውስጥ ለእግዚአብሔር ክብር እና ለእኛ ለራሳችንና ለባልንጀራችን ደኅንነት የሚጠቅም መንፈሳዊና አካላዊ በረከቶችን የሚሆን ማንኛውንም ነገር መጠየቅ ይገባናል። እግዚአብሔርን ስለ ማንነቱና ስላደረገልን ነገር ልናወድሰው እና ልናመሰግነው ይገባናል።

693. **ፊልጵስዩስ** 4፡6 በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ።

694. **መዝሙር** 136፡1 እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ ቸር ነውና ምሕረቱ ለዘላለም ነውና።

### *198. እንዴት መጸለይ ይገባናል?*

ሀ. በኢየሱስ ስም ማለትም ቤዛችን መሆኑን በማመን መጸለይ ይገባናል።

695. **ዮሐንስ** 16፡23 እውነት እውነት እላችኋለሁ አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል።

ለ. በሙሉ መተማን ማለትም ስለ ኢየሱስ ጸሎቶቻችን እንደሚመልሱ በጽኑ መታማን መጸለይ ይገባል።

696. **ማቴዎስ** 11፡22 አምናችሁም በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ ትቀበላላችሁ።

697. **ያዕቆብ** 1፡6-7 ነገር ግን በምንም ሳይጠራጠር በእምነት ይለምን፤ የሚጠራጠር ሰው በነፋስ የተገፋና የተነቃነቀ የባሕርን ማዕበል ይመስላልና። ... ለዚያ ሰው ከጌታ ዘንድ አንዳች እንዲያገኝ አይምሰለው።

ሐ. እንደ ተገለጠው የእግዚአብሔር ፈቃድ መሠረት መጸለይ ይገባናል።

698. **ሉቃስ** 11፡13 እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው።

699. **ሉቃስ** 22፡42 አባት ሆይ ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን፤ የአንተ እንጂ።

700. **ማቴዎስ** 8፡2 እነሆም ለምጻም ቀርቦ፡- ጌታ ሆይ ብትወድስ ልታነጻኝ ትችላለህ እያለ ሰገደለት፡፡

701. **1ዮሐንስ** 5፡14 በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤ እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል፡፡

### *199. እንድንጸልይ ማን ይረዳናል?*

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ጋር እና ለእኛ ይጸልያል፡፡

702. **ሮሜ** 8፡26 እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፡፡

### *200. እግዚአብሔር ጸሎትን እንዴት ይመልሳል?*

እግዚአብሔር የክርስቲያኖችን ሁሉ ጸሎት ይሰማል፤ በራሱ መንገድና በራሱ ጊዜም ይመልሳል፡፡

703. **ኢሳይያስ** 65፡24 ሳይጠሩ እመልስላቸዋለሁ፤ ገናም ሲናገሩ እሰማለሁ፡፡

704. **2ቆሮንቶስ** 12፡8-9 ስለዚህ ነገር ከእኔ እንዲለይ ሦስት ጊዜ ጌታን ለመንሁ፡፡ እርሱም ጸጋዬ ይበቃሃል፤ ኃይሌ በድካም ይፈጸማልና አለኝ፡፡ እንግዲህ የክርስቶስ ኃይል ያድርብኝ ዘንድ በብዙ ደስታ በድካሜ ልመካ እወዳለሁ፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች፡-* ኢየሱስ የመቶ አለቃውን አገልጋይ ፈወሰ (**ማቴዎስ** 8፡5-13)፤ ኢየሱስ አንድን ሽባ ፈወሰ (**ማቴዎስ** 9፡1-8)፤ እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ ለማዳን አቀደ (**ዘጸአት** 3፡7-10)፤ የጽኑዋ መበለት ምሳሌ (**ሉቃስ** 18፡1-8)፡፡

### *201. ለማን መጸለይ ይገባናል?*

ለራሳችንና ለጠላቶቻችን ሳይቀር ለሌሎች ሰዎች ሁሉ መጸለይ ይገባናል፤ ነገር ግን ለሞቱ ነፍሳት መጸለይ አይገባንም፡፡

705. **1ጢሞቴዎስ** 2፡1-2 እንግዲህ ከሁሉ አስቀድሞ ልመናና ጸሎት፣ ምልጃና ምስጋና ለሰዎች ሁሉ፣ ለነገሥታትና ለባለሥልጣናት ሁሉ እንዲደረግ አሳስባለሁ፤ ይህም በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወትና በቅድስና ሁሉ በሰላምና በጸጥታ እንድንኖር ነው፡፡ (አ.መ.ት.)

706. **ማቴዎስ** 5፡44 ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፡፡

707. **ዕብራውያን** 9፡27 ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኂላም ፍርድ ተመደበባቸው፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች፡-* ቀራጩ ለራሱ ጸለየ (**ሉቃስ** 18፡13)፤ አብርሃም ለሰዶም ጸለየ (**ዘፍጥረት** 18፡23-32)፤ ከነዓናዊቷ ሴት ለልጇ ጸለየች (**ማቴዎስ** 15፡22-28)፤ ኢየሱስ ለጠላቶቹ ጸለየ (**ሉቃስ** 23፡34)፤ እስጢፋኖስ ለጠላቶቹ ጸለየ (**የሐዋርያት ሥራ** 7፡60)፡፡

### *202. የት መጸለይ ይገባናል?*

በየትኛውም ቦታ፣ በተለይ ብቻችንን ስንሆን፣ ከቤተ ሰቦቻችንና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መጸለይ ይገባናል፡፡

708. **1ጢሞቴዎስ** 2፡8 እንግዲህ ወንዶች በስፍራ ሁሉ አለ ቍጣና አለ ክፉ ዐሳብ የተቀደሱትን እጆች እያነሡ እንዲጸልዩ እፈቅዳለሁ፡፡

709. **ማቴዎስ** 6፡6 አንተ ግን ስትጸልይ፤ ወደ እልፍኝህ ግባ መዝጊያህንም ዘግተህ በስውር ላለው አባትህ ጸልይ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል።

710. **የሐዋርያት ሥራ** 12፡5 ጴጥሮስም በወህኒ ይጠበቅ ነበር፤ ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ስለ እርሱ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አጥብቆ ይደረግ ነበር።

### *203. መቼ መጸለይ ይገባናል?*

በመደበኛነትና አዘውትረን በተለይ በመከራ ጊዜ መጸለይ ይገባናል።

712. **መዝሙር** 65፡8 የጥዋትንና የማታን መውጫ ደስ ታሰኛቸዋለህ።

713. **መዝሙር** 119፡164 ስለ ጽድቅህ ፍርድ ሰባ ጊዜ በቀን አመሰግንሃለሁ።

714. **ዳንኤል** 6፡10 ዳንኤልም ጽሕፈቱ እንደ ተጻፈ ባወቀ ጊዜ ወደ ቤቱ ገባ፤ የእልፍኙም መስኮቶች ወደ ኢየሩሳሌም አንጻር ተከፍተው ነበር፤ ቀድሞም ያደርግ እንደ ነበረ በየዕለቱ ሦስት ጊዜ በጉልበቱ ተንበርክኮ በአምላኩ ፊት ጸለየ አመሰገነም።

715. **ሉቃስ** 18፡1 ሳይታክቱም ዘወትር ሊጸልዩ እንዲገባቸው የሚል ምሳሌን ነገራቸው።

716. **1ተሰሎንቄ** 5፡17-18 ሳታቋርጡ ጸልዩ፤ በሁሉ አመስግኑ፤ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እናንተ ነውና።

717. **መዝሙር** 50፡15 በመከራ ቀን ጥራኝ አድንህማለሁ፤ አንተም ታከብረኛለህ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ፡-* የቀደሙት ክርስቲያኖች የተለመዱትን የጸሎት ሰዓታት ይጠብቁ ነበር (**የሐዋርያት ሥራ** 2፡46-3፡1፣10)።

*ማስታወሻ፡-* በዚህ የክርስትና ትምህርት መጽሐፍ ውስጥ ሉተር ለማለዳ፣ ለምሽትና ለምግብ ሰዓት ዐሳቡን የሚሰጥባቸውን ጸሎቶች ተመልከት።

### *204. እንዴት እንደምንጸልይ ለማሳየት ኢየሱስ ምን ጸሎት ሰጠን?*

ኢየሱስ ‹‹የጌታን ጸሎት›› ሰጠን።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ፡-* የጌታ ጸሎት (**ማቴዎስ** 6፡9-13፤ **ሉቃስ** 11፡1-4)።

> ***መግቢያ***
>
> በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፤
>
> *ይህ ምን ማለት ነው?* በእነዚህ ቃላት የተወደዱ ልጆች ተወዳጅ አባታቸውን እንደሚጠይቁ እግዚአብሔርን በሙሉ ድፍረትና መተማመን እንድንጠይቀው፣ እርሱ እውነተኛ አባታችንና እኛም በእውነት የእርሱ ልጆች መሆናችንን እንድናምን በደግነት ይጋብዘናል።

### *205. በጌታ ጸሎት ውስጥ ‹‹አባት›› የሚለው ቃል እንድንጸልይ የሚበረታታን እንዴት ነው?*

‹‹አባት›› የሚለው ቃል እግዚአብሔር እንደሚወደንና በልበ ሙሉነትና ያለ ፍርሃት ወደ እርሱ እንድንጸልይ እንደሚፈልግ ይነግረናል።

718. **1ዮሐንስ** 3፡1 የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ፤ እንዲሁም ነን። ስለዚህ ምክንያት ዓለም እርሱን ስላላወቀው እኛን አያውቀንም።

719. **ሮሜ** 8፡15-16 አባ አባት ብለን የምንጮህበትን የልጅነትን መንፈስ ተቀበላችሁ … የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል፡፡
720. **2ቆሮንቶስ** 6፡18 ሁሉንም የሚገዛ ጌታ … ለእናንተም አባት እሆናለሁ፤ እናንተም ለእኔ ወንድ ልጆችና ሴት ልጆች ትሆናላችሁ ይላል፡፡
721. ***ዕብራውያን*** 4፡16 እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ፡፡
722. ***መዝሙር*** 103፡13 አባት ለልጆች እንደሚራራ እንዲሁ እግዚአብሔር ለሚፈሩት ይራራል፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ፦* የጠፋው ልጅ (**ሉቃስ** 15፡11-32)፡፡

***206. ‹‹አባታችን ሆይ›› ብለን ስንጸይ ‹‹አባታችን›› የሚለው ቃል ምን ያሳስበናል?***

በኢየሱስ አማኞች ሁሉ የአንዱ አባት ልጆች በመሆናቸው በጋራና አንዳችን ለሌላችን መጸለይ እንዳለብን ያሳስበናል፡፡

723. ***ኤፌሶን*** 4፡6 ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ፡፡
724. ***ገላትያ*** 3፡26 በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና፡ ፡
725. ***ያዕቆብ*** 5፡16 እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ፤ ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች፡፡

***207. ‹‹በሰማያት የምትኖር›› የሚሉት ቃላት ስለ እግዚአብሔር ምን ይናገራሉ?***

እነዚህ ቃላት ሰማያዊ አባታችን በሁሉም ላይ የበላይ በመሆኑ ጸሎታችንን ለመመለስ ኃይል እንዳለው ያረጋግጡልናል፡፡

726. ***መዝሙር*** 124፡8 ረድኤታችን ሰማይንና ምድርን በሠራ በእግዚአብሔር ስም ነው፡፡
727. **ሉቃስ** 1፡37 ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና፡፡
728. **የሐዋርያት *ሥራ*** 17፡24 ዓለምንና በውስጡ ያለውን ሁሉ የፈጠረ አምላክ እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነው፡፡ (አ.መ.ት)

***የመጀመሪያ ጸሎት***

ስምህ ይቀደስ፡፡

*ይህ ምን ማለት ነው?* የእግዚአብሔር ስም በራሱ በእርግጥ ቅዱስ ነው፤ ዳሩ ግን በዚህ ጸሎት የምንለምነው በእኛ መካከልም ቅዱስ ይሆን ዘንድ ነው፡፡

የእግዚአብሔር ስም የሚቀደሰው እንዴት ነው? የእግዚአብሔርን ቃል በእውነትና በንጽሕና ስናስተምር እንዲሁም የእግዚአብሔር ልጆች እንደ መሆናችን መጠን በቃሉ መሠረት በቅድስና ስንኖር ነው፡፡ ውድ የሰማይ አባታችን ሆይ ይህን እንድንፈጽም እርዳን! ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ቃል ከሚያስተምረው ውጪ በተቃራኒው መንገድ የሚያስተምርና የሚኖር ማንም ሰው የእግዚአብሔርን ስም በመካከላችን ያረክሳል፡፡ ሰማያዊ አባት ሆይ ከዚህ ጠብቀን!

### *208. በዚህ ጸሎትና በሁለተኛው ትእዛዝ መካከል ያለው ትስስር ምንድን ነው?*

ሁለቱም ስለ እግዚአብሔር ስም ይናገራሉ፡፡ ‹‹በዚህ ጸሎት በትክክል እግዚአብሔር በሁለተኛው ትእዛዝ ለሚፈልግብን ነገር እንጸልያለን፡፡ ስሙ በከንቱ እንዳይነሣ ነገር ግን ለእግዚአብሔር ውዳሴና ክብር በሚገባ ጥቅም ላይ እንዲውል እንጸልያለን (ትልቁ የክርስትና ትምህርት መጽሐፍ III 45)፡፡

729. **ዘጸአት** 20፡7 የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፤ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና፡፡

### *209. የእግዚአብሔር ስም እንዲቀደስ ስንጸልይ ምን እየጠየቅን ነው?*

የእግዚአብሔር ስም [ማለት] እግዚአብሔር ራሱን ለእኛ እንደተገለጠልን ማለት ስለ ሆነ እኛ ስሙን ቅዱስ ልናደርገው አንችልም፤ ነገር ግን ስሙን በሕይወታችን እንድንቀድስ እንዲረዳን እንጸልያለን፡፡

730. ***መዝሙር*** 103፡1 ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ፤ አጥንቶቼም ሁሉ የተቀደሰ ስሙን፡፡

### *210. የእግዚአብሔርን ስም እንዴት እንቀድሳለን?*

የእግዚአብሔርን ስም የምንቀድሰው፡-

ሀ. የእግዚአብሔርን ቃል በመካከላችን በእውነትና በንጽሕና ስናስተምር፡፡

731. **ኤርምያስ** 23፡28 ቃሌም ያለበት ቃሌን በእውነት በታማኝነት ይናገር፡፡

732. **ዮሐንስ** 17፡17 በእውነትህ ቀድሳቸው፤ ቃልህ እውነት ነው፡፡

ለ. እንደ እግዚአብሔር ቃል በምንኖርበት ጊዜ ነው፡፡

733. **ማቴዎስ** 5፡16 መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ፡፡

734. **ኤፌሶን** 4፡1 እንግዲህ በጌታ እስር የሆንሁ እኔ በተጠራችሁበት መጠራታችሁ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እለምናችኋለሁ፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ፡-* ዘኬዎስ የክርስቲያን ሕይወትን ለመኖር ወሰነ (**ሉቃስ** 19፡19)፡፡

### *211. የእግዚአብሔር ስም የሚረክሰው እንዴት ነው?*

የእግዚአብሔር ስም የሚረክሰው ማለትም የማይከበረው፣

ሀ. ማንም ሰው ከእግዚአብሔር ቃል በተቃራኒው በሚያስተምርበት ጊዜ፣

735. **ኤርምያስ** 23፡31 እነሆ ከምላሳቸው ትንቢትን አውጥተው እርሱ ይላል በሚሉ ነቢያት ላይ ነኝ ይላል እግዚአብሔር፡፡

736. **ሮሜ** 2፡23-24 በሕግ የምትመካ ሕግን በመተላለፍ እግዚአብሔርን ታሳፍራለህን? በእናንተ ሰበብ የእግዚአብሔር ስም በአሕዛብ መካከል ይሰደባልና ተብሎ እንደ ተጻፈ፡፡

### *ሁለተኛ ጸሎት*

*መንግሥትህ ትምጣ፡፡*

*ይህ ምን ማለት ነው?* በእርግጥ የእግዚአብሔር መንግሥት ያለ እኛ ጸሎት በገዛ ራስዋ ትመጣለች፤ ዳሩ ግን በዚህ ጸሎት የምንለምነው እርሷ ወደ እኛም እንድትመጣ ነው፡፡

> *የእግዚአብሔር መንግሥት እንዴት ትመጣለች?* ሰማያዊ አባታችን በጸጋው ቅዱስ ቃሉን እንድናምንና በዚህ ዓለምና እዚያም በዘላለም የተቀደሰ ኑሮ እንኖር ዘንድ መንፈስ ቅዱስን ሲሰጠን የእግዚአብሔር መንግሥት ትመጣለች፡፡

### *212. የእግዚአብሔር መንግሥት ምንድን ናት?*

የእግዚአብሔር መንግሥት በመላው አጽናፈ ዓለም ላይ እግዚአብሔር እንደ ንጉሥ መግዛቱ (የኃይል መንግሥት)፣ በምድር ላይ በቤተ ክርስቲያን ላይ መግዛቱ (የጸጋ መንግሥት) እና በመንግሥተ ሰማያት በቤተ ክርስቲያንና መላእክቱ ላይ መግዛቱ (የክብር መንግሥት) ናት፡

737. **መዝሙር** 103፡19 እግዚአብሔር ዙፋኑን በሰማይ አዘጋጀ፤ መንግሥቱም ሁሉን ትገዛለች (የኃይል መንግሥት)፡፡

738. **ዮሐንስ** 3፡5 ኢየሱስም መለሰ እንዲህ ሲል፡- እውነት እውነት እልሃለሁ፤ ሰው ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም (የጸጋ መንግሥት)፡፡

739. **2ጢሞቴዎስ** 4፡18 ጌታም ከክፉ ነገር ሁሉ ያድነኛል፤ ለሰማያዊውም መንግሥት ይጠብቀኛል፤ ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን አሜን (የክብር መንግሥት)፡፡

### *213. በሁለተኛው ጸሎት የምንለምነው ምንድን ነው?*

የእግዚአብሔር የኃይል መንግሥት እንድትመጣ አንጸልይም፤ ምክንያቱም ያ ቀድሞውንም በሁሉም ስፍራ የሚገኝ ነው፤ ነገር ግን እግዚአብሔርን የምንለምነው፡-

ሀ. ቃሉን እንድናምንና እንደ ጸጋው መንግሥት አባላት መንፈሳዊ ሕይወት እንድንኖር መንፈስ ቅዱሱን እንዲሰጠን፣

740. **ማርቆስ** 1፡15 ኢየሱስም ዘመኑ ተፈጸመ የእግዚአብሔርም መንግሥት ቀርባለች፤ ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ እያለ ወደ ገሊላ መጣ፡፡

741. **ሮሜ** 14፡17 የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችምና፡፡

742. **ቈላስይስ** 1፡13-14 እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፤ ቤዛነቱም እርሱም የኃጢአትን ስርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን፡፡

ለ. ሌሎች በርካቶችን ወደ ጸጋው መንግሥት እንዲያመጣ፣

743. **ማቴዎስ** 9፡38 እንግዲህ የመከሩን ጌታ ወደ መከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት አላቸው፡፡

744. **2ተሰሎንቄ** 3፡1 በቀረውስ ወንድሞች ሆይ የጌታ ቃል እንዲሮጥ፣ በእናንተም ዘንድ ደግሞ እንደሚሆን እንዲከበር … ጸልዩ፡፡

ሐ. የጸጋ መንግሥቱን ለማስፋት እንዲጠቀምብን፣

745. **የሐዋርያት ሥራ** 4፡29 አሁንም ጌታ ሆይ ወደ ዛቻቸው ተመልከት፤ … ባሪያዎችህ በፍጹም ግልጽነት ቃልህን እንዲናገሩ ስጣቸው፡፡

746. **1ጴጥሮስ** 2፡12 ስለሚመለከቱት ስለ መልካም *ሥራችሁ* ክፉ እንደምታደርጉ በዚያ እናንተን በሚያሙበት ነገር፣ በሚጐበኝበት ቀን እግዚአብሔርን ያከብሩት ዘንድ በአሕዛብ መካከል ኑሮአችሁ መልካም ይሁን።

747. **ፊልጵስዩስ** 3፡20 እኛ አገራችን በሰማይ ነውና፤ ከዚያም ደግሞ የሚመጣ መድኃኒትን እርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን።

748. **ራእይ** 22፡20 ይህን የሚመሰክር አዎን በቶሎ እመጣለሁ ይላል። አሜን ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና!

### *214. የእግዚአብሔር መንግሥት እንደምትመጣ እንዴት እርግጠኛ መሆን እንችላለን?*

እግዚአብሔር የጸጋ መሣሪያዎቹ መንግሥቱን እንደሚመሠርቱና እንደሚያስቀጥሉ ዋስትና ይሰጣል።

749. **ኢሳይያስ** 55፡11 ቃሌ … የምሻውን ያደርጋል፤ የላክሁትንም ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ፦* የአዳጊው ዘር ምሳሌ (**ማርቆስ** 4፡26-29)።

> ***ሦስተኛው ጸሎት***
>
> *ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን።*
>
> *ይህ ምን ማለት ነው?* የእግዚአብሔር በጎና ቸር ፈቃድ ያለ እኛ ጸሎትም ቢሆን ትሆናለች/ትፈጸማለች፤ ዳሩ ግን በዚህ ጸሎት የምንለምነው በመካከላችንም እንድትሆንና እንድትፈጸም ነው።
>
> *የእግዚአብሔር ፈቃድ የምትፈጸመው እንዴት ነው?* የእግዚአብሔር ፈቃድ የምትፈጸመው፣ የእግዚአብሔርን ስም እንድንቀድሰው የማይፈልጉትን ወይም የእርሱን መንግሥት መምጣት የማይፈቅዱትን የዲያብሎስን፣ የዓለምና የኃጢአተኛ ባሕርያችንን ማናቸውንም ክፉ ሴራና ዓላማ እግዚአብሔር በሚሰብርበትና በሚያግድበት ጊዜ፣ እንዲሁም እግዚአብሔር እስከ ሕይወታችን ፍጻሜ ድረስ እኛን በቃሉና በእምነት በሚያጠነክርበትና በሚያጸናበት ጊዜ ነው። ይህ የእርሱ በጎና ቸር ፈቃድ ነው።

### *215. የእግዚአብሔር በጎና ቸር ፈቃድ ምንድን ነው?*

ስሙ እንዲቀደስና መንግሥቱ እንድትመጣ ማለትም ቃሉን በትክክል እንድናስተምርና ኃጢአተኞችም በክርስቶስ ወደ ማመን እንዲመጡና መንፈሳዊ ሕይወት እንዲመሩ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።

750. **ዘዳግም** 4፡2 እኔ ያዘዝኋችሁ የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትጠብቃላችሁ እንጂ ባዘዝኋችሁ ቃል ላይ አትጨምሩም፤ ከእርሱም አታጐድሉም።

751. **ዮሐንስ** 6፡40 ልጅንም አይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወትን እንዲያገኝ የአባቴ ፈቃድ ይህ ነው፤ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።

752. **1ጢሞቴዎስ** 2፡4 ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር።

753. **1ተሰሎንቄ** 4፡3 ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነውና።

### *216. ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የሚቃረኑት የማን ፈቃድና እቅዶች ናቸው?*

*ዲያብሎስ፣ ዓለምና የገዛ ራሳችን ኃጢአተኛ ባሕርይ የእግዚአብሔርን በጎና ቸር ፈቃድ ይቃወማሉ።*

754. **1ጴጥሮስ** 5፡8 በመጠን ኑሩ ንቁም፤ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና።

755. **1ዮሐንስ** 2፡15-17 ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም። ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል።

756. **ሮሜ** 7፡18 በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር ዐውቃለሁና፤ ፈቃድ አለኝና መልካሙን ግን ማድረግ የለኝም።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች፡-* ዲያብሎስ የሰውን ዘር አሳስቶ ወደ ኃጢአት መራ (**ዘፍጥረት** 3፡1-7)፤ የኢየሱስ ጠላቶች ጴጥሮስ ላይ ውድቀት አመጡበት (**ሉቃስ** 22፡54-62)፤ የአካን ኃጢአተኛ ባሕርይ ወደ ስርቆት መራው (**ኢያሱ** 7፡18-22)።

### *217. የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲፈጸም የምንጸልየው ለምንድ ነው?*

የእግዚአብሔር ፈቃድ ሁልጊዜ እንደሚፈጸም እናውቃለን፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር በጎና ቸር ፈቃድ በእኛ ሕይወት ውስጥ እንዲፈጸም እንፈልጋለን።

‹‹እኛ ብንጸልይም ወይም ባንጸልይም የእግዚአብሔር ስም በራሱ ቅዱስ እንደሆነና መንግሥቱም እንደምትመጣ ሁሉ ፈቃዱም ትፈጸማለች፤ ታሸንፍማለች። ዲያብሎስና ተከታዮቹ ሁሉ ታላቅ አመጽ ቢያስነሱም፣ ቢቆጡና እጅግ ቢበሳጩም፣ ወንጌሉንም ሙሉ በሙሉ ለማጥፋት ቢሞክሩም እንኳ ይህ እውነት ነው። ነገር ግን ለገዛ ራሳችን ስንል ከቍጣቸው በተቃራኒው እንኳ ፈቃዱ በመካከላችን ያለመከልከል እንድትፈጸም መጸለይ ይገባናል። ምንም ነገር ማከናወን እንዳይችሉና በሁከትና በስደት ሁሉ ፊት ለእግዚአብሔር ፈቃድ ተገዝተን ጸንተን እንድንቆይ እንጸልያለን። (ትልቁ የክርስትና ትምህርት III, 68).

757. **መዝሙር** 115፡3 አምላካችንስ በላይ በሰማይ ነው፤ … የፈቀደውን ሁሉ አደረገ።

758. **መዝሙር** 43፡3 ብርሃንህንና እውነትህን ላክ፤ እነርሱ ይምሩኝ፤ ወደ ቅድስናህ ተራራና ወደ ማደሪያህ ይውሰዱኝ።

759. **ፊልጵስዩስ** 1፡21 ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ ሞትም ጥቅም ነውና።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ፡-* የእግዚአብሔር ጠላቶች ምስኪንነት (**መዝሙር** 2)፤ የጳውሎስ መለወጥ (**የሐዋርያት ሥራ** 9፡1-19)።

### *218. የእግዚአብሔር ፈቃድ በሕይወታችን የሚፈጸመው እንዴት ነው?*

የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚፈጸመው፡-

*ሀ.* በክርስቶስ ኢየሱስ ያለንን እምነት ለማጥፋት የሚሞክሩትን የዲያብሎስን፣ የዓለምንና የኃጢአተኛ ባሕርያችንን እቅዶች ሲሰብርና ሲያስተጓጉል ነው፤

760. **ሮሜ** 16፡20 የሰላምም አምላክ ሰይጣንን ከእግራችሁ በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን።

761. **2ጢሞቴዎስ** 1፡12 ያመንሁትን ዐውቃለሁና የሰጠሁትንም አደራ እስከዚያ ቀን ድረስ ሊጠብቅ እንዲችል ተረድቼአለሁ።

*ለ.* በቃሉና በእምነት እንድንጸና ሲያበረታንና ሲጠብቀን እንዲሁም እግዚአብሔርን ደስ የሚሰኝ ሕይወት እንድንመራ ሲረዳን ነው።

762. **1ጴጥሮስ** 1፡5 በመጨረሻው ዘመን ይገለጥ ዘንድ ለተዘጋጀ መዳን በእምነት በእግዚአብሔር ኃይል ለተጠበቃችሁ ለእናንተ … ቀርቶላችኋል።

763. ***መዝሙር*** 119፡35 እርስዋን ወድጃለሁና የትእዛዝህን መንገድ ምራኝ።

*ሐ.* እስከ ዕለተ ሞታችን ድረስ በችግሮቻችን ሁሉ ውስጥ ሲደግፈን ነው።

764. **ሮሜ** 8፡28 እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ ዐሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።

765. **2ቆሮንቶስ** 12፡9 እርሱም ጸጋዬ ይበቃሃል፤ ኃይሌ በድካም ይፈጸማልና አለኝ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች፡-* እግዚአብሔር የዮሴፍን ወንድሞች ክፉ ፈቃድ አስተጓጉሎ እርሱን ታማኝ አድርጎ ጠበቀው (**ዘፍጥረት** 50፡15-21)፤ ዲያብሎስ ኢዮብን እንዲያጠፋው እግዚአብሔር አልፈቀደለትም (**ኢዮብ** 1፡1-2፣6)።

### *አራተኛው ጸሎት*

የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን።

*ይህ ምን ማለት ነው?* እግዚአብሔር ያለ እኛ ጸሎት ለክፉዎች ሰዎች ሁሉ እንኳ ሳይቀር ለሁሉ የዕለት እንጀራን ይሰጣል፤ ዳሩ ግን በዚህ ጸሎት የምንለምነው እኛ ይህንን እንድንገነዘብና የዕለት እንጀራችንን በምስጋና እንድንቀበለው እግዚአብሔር እንዲመራን ነው።

*የዕለት እንጀራ ማለት ምን ማለት ነው?* የዕለት እንጀራ ማናቸውንም ከሰውነታችን ድጋፍና ፍላጎት መሟላት ጋር የተያያዙ እንደ ምግብ፣ መጠጥ፣ ልብስ፣ ጫማ፣ ቤት፣ ቤተ ሰብ፣ መሬት፣ እንስሳት፣ ገንዘብ፣ ንብረት፣ ትጉህ የትዳር ጓደኛ፣ ትጉሃን ልጆች፣ ትጉሃን ሠራተኞች፣ ትጉህና ታማኝ አስተዳዳሪዎች፣ መልካም መንግሥት፣ መልካም የአየር ጠባይ፣ ሰላም፣ ጤንነት፣ ራስን መግዛት፣ መልካም ስም፣ መልካም ባልንጀሮች፣ ታማኝ ጎረቤቶችና የመሳሰሉትን ያካትታል።

### ***219. ለዕለት እንጀራ እግዚአብሔርን የምንለምነው ለምንድን ነው?***

ከአካላችን ድጋፍና ፍላጎት መሟላት ጋር የተያያዙ ነገሮችን ሁሉ ለሚያካትተው ለዕለት እንጀራ እግዚአብሔርን የምንለምነው፣ ክርስቶስ፡-

*ሀ.* የእኛ መላ ሕይወትና የሌላም ሰው ሁሉ ሕይወት በእግዚአብሔር ላይ ጥገኛ መሆኑን እንድንገነዘብ ስለሚፈልግ።

766. ***መዝሙር*** 145፡15-16 የሁሉ ዓይን አንተን ተስፋ ያደርጋል፤ አንተም ምግባቸውን በጊዜው ትሰጣቸዋለህ። አንተ እጅህን ትከፍታለህ፤ ሕይወት ላለውም ሁሉ መልካምን ታጠግባለህ።

767. ***ማቴዎስ*** 5፡45 እርሱ [እግዚአብሔር] በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና።

768. ***የሐዋርያት ሥራ*** 17፡28 በእርሱ ሕያዋን ነንና እንንቀሳቀሳለን፤ እንኖርማለን።

769. ***ያዕቆብ*** 4፡15 ጌታ ቢፈቅድ ብንኖርም ይህን ወይም ያን እናደርጋለን ማለት ይገባችኋል።
ለ. አካላዊ በረከቶቻችንን ሁሉ በምስጋና እንድንቀበል ስለሚፈልግ።

770. ***መዝሙር*** 106፡1 ቸር ነውና ምሕረቱም ለዘላለም ነውና እግዚአብሔርን አመስግኑ።

771. ***ኤፌሶን*** 5፡19-20 በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ፤ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ፤ ሁልጊዜ ስለ ሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምላካችንንና አባታችንን ስለ ሁሉ አመስግኑ።

772. **1ጢሞቴዎስ** 4፡4-5 እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካም ነውና ከምስጋናም ጋር ቢቀበሉት የሚጣል ምንም የለም፤ በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት የተቀደሰ ነውና።
ሐ. ለአካላዊና መንፈሳዊ በረከቶች ወደ እግዚአብሔር እንድንመለከት ስለሚፈልግ።

773. ***መዝሙር*** 91፡15 ይጠራኛል እመልስለትማለሁ፤ በመከራም ጊዜ ከእርሱ ጋር እሆናለሁ አድነዋለሁ፤ አከብረውማለሁ።

774. ***ማቴዎስ*** 6፡33 አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፤ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል።

775. ***ሉቃስ*** 7፡3 [መቶ አለቃው] ስለ ኢየሱስም በሰማ ጊዜ የአይሁድን ሽማግሌዎች ወደ እርሱ ላከና መጥቶ ባሪያውን እንዲያድን ለመነው።
*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች፡-* ኢየሱስ ዐይነ ስውሩን በርጤሜዎስን ፈወሰ (**ማርቆስ** 10፡ 46-52)፤ ኢየሱስ ዐሥር ለምጻሞችን ፈወሰ (**ሉቃስ** 17፡11-19)።

### *220. እግዚአብሔር የዕለት እንጀራችንን የሚሰጠን እንዴት ነው?*

*ምድርን ፍሬያማ ያደርጋትና ለሚያስፈልጉን ነገሮች እንድንሠራ በችሎታዎች ይባርከናል።*

776. ***መዝሙር*** 104፡14 እንጀራን ከምድር ያወጣ ዘንድ ለምለሙንም ለሰው ልጆች ጥቅም ሣርንም ለእንስሳ ያበቅላል።

777. **2ተሰሎንቄ** 3፡10-12 ደግሞ ከእናንተ ጋር ሳለን፡- ሊሠራ የማይወድ አይብላ ብለን አዝዘናችሁ ነበርና። ሥራ ከቶ ሳይሠሩ በሰው ነገር እየገቡ ያለ ሥርዓት ከእናንተ ዘንድ ስለሚሄዱ ስለ አንዳንዶች ሰምተናልና። እንደ እነዚህ ያሉትንም በጸጥታ እየሠሩ የገዛ እንጀራቸውን ይበሉ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናዝዛቸዋለን፤ እንመክራቸውማለን።

### *221. ለዕለት እንጀራቸው መሥራት ለማይችሉት እግዚአብሔር ምን እንድናደርግ ይፈልጋል?*

እግዚአብሔር ራስ ወዳድ እንድንሆን አይፈልግም፤ ነገር ግን መሥራት ለማይችሉት እንድናካፍልና ለዕለት እንጀራም በጸሎታችን ውስጥ እንድናካትታቸው ይፈልጋል።

778. **1ጢሞቴዎስ** 5፡8 ለእርሱ ስለ ሆኑት ይልቁንም ማንም ቢሆን ሃይማኖትን የካደ ከማያምንም ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው።
779. ***ዕብራውያን*** 13፡16 *መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ፤ እንዲህ ያለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና።*
780. **1ዮሐንስ** 3፡17-18 *የዚህ ዓለም ገንዘብ ያለው ወንድሙም የሚያስፈልገውን ሲያጣ ዐይቶ ያልራራለት ማንም ቢሆን የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ እንዴት ይኖራል? ልጆቼ ሆይ፣ በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ።*

### *222. ኢየሱስ ‹‹ዛሬ›› እና ‹‹በየዕለቱ›› እንድንል የነገረን ለምንድን ነው?*

እነዚህ ቃላት ስስታም ወይም አባካኝ እንዳንሆን ወይም ስለ ወደፊቱ እንዳንጨነቅ ነገር ግን እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን እንደሚሰጠን በመተማመን በእርካታ እንድንኖር ያስተምሩናል።

781. **ምሳሌ** 30፡8-9 *ድኽነትንና ባለ ጠግነትን አትስጠኝ ነገር ግን የሚያስፈልገኝን እንጀራ ስጠኝ። እንዳልጠግብ እንዳልክድህም፦ እግዚአብሔርስ ማን ነው? እንዳልል፤ ድኻም እንዳልሆን እንዳልሰርቅም በአምላኬም ስም በሐሰት እንዳልምል።*
782. ***ማቴዎስ*** 6፡34 *ነገ ለራሱ ይጨነቃልና ለነገ አትጨነቁ፤ ለቀኑ ክፋቱ ይበቃዋል።*
783. **ዮሐንስ** 6፡12 *ከጠገቡም በኋላ ደቀ መዛሙርቱን አንድ ስንኳ እንዳይጠፋ የተረፈውን ቍርስራሽ አከማቹ አላቸው።*
784. **1ጢሞቴዎስ** 6፡8 *ምግብና ልብስ ከኖረን ግን እርሱ ይበቃናል።*
785. **1ጴጥሮስ** 5፡7 *እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ፦ የሞኙ ባለ ጠጋ ምሳሌ* (**ሉቃስ** 12፡15-21)።

### *አምስተኛው ጸሎት*

በደላችንን ይቅር በለን፤ እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል።

*ይህ ምን ማለት ነው?* በዚህ ጸሎት ሰማያዊ አባታችን ኃጢአታችንን እንዳይመለከትብን ወይም ከእነርሱ የተነሣ ጸሎታችንን እንዳይከለክለን እንለምናለን። ምክንያቱም እኛ የምንለምነው ነገር ምንም የማይገባን ወይም የሥራችን ዋጋ ስላልሆነ ነው። በዚህ ፈንታ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር በጸጋው እንዲሰጠን እንለምናለን፤ ምክንያቱም እኛ በየቀኑ ብዙ ስለምንበድልና በእርግጥ ቅጣት እንጂ ምንም ነገር የማይገባን ስለሆንን ነው። ስለዚህ እኛም ደግሞ የበደሉንን በእውነት ከልብ ይቅር እንላቸዋለን፤ ለእነርሱም በደስታ መልካም እናደርግላቸዋለን።

### *223. ይህንን ጸሎት ስንጸልይ የምንናዘዘው ምንድን ነው?*

በየቀኑ እንደምንበድልና ቅጣት እንጂ ምንም ነገር እንደማይገባን እንናዘዛለን።

786. **ምሳሌ** 28፡13 *ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤ የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል።*

### *224. በዚህ ጸሎት ምን እንጠይቃለን?*

ሰማያዊ አባታችን ስለ ክርስቶስ ብሎ በጸጋው ኃጢአታችንን ይቅር እንዲለን እንጠይቃለን፡፡

787. **መዝሙር** 19፡12 ስሕተትን ማን ያስተውላታል? ከተሰወረ ኃጢአት አንጻኝ፡፡
788. **መዝሙር** 51፡1-2 አቤቱ እንደ ቸርነትህ መጠን ማረኝ፤ እንደ ምሕረትህም ብዛት መተላለፌን ደምስስ፤ ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ ከኃጢአቴም አንጻኝ፡፡
789. **መዝሙር** 130፡3-4 አቤቱ ኃጢአትንስ ብትጠባበቅ አቤቱ ማን ይቆማል? ይቅርታ ከአንተ ዘንድ ነውና፡፡
790. **ሉቃስ** 18፡13 አምላክ ሆይ፣ እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ፡፡

### *225. ወደ ሰማያዊ አባታችን በምናቀርባቸው በእነዚህ ልመናዎች ውስጥ የኃጢአት ይቅርታ ጸሎትን ለምን እናካትታለን?*

እኛ ለምንጸልያቸው ነገሮች የምንበቃም የሚገባንም ስላልሆንን ነው፡፡ በመሆኑም በመሉ ልብና በመልካም ሕሊና ወደ እርሱ እንድንጸልይ የእግዚአብሔር ይቅርታ ያስፈልገናል፡፡

‹‹ልብ ከእግዚአብሔር ጋር የሰመረ ካልሆነና … እንደዚህ ዓይነት መተማመን ላይ መድረስ ካልቻለ ለመጸለይ በጭራሽ አይደፍርም … ነገር ግን እንደዚህ ዓይነት መተማመንና ደስተኛ ልብ ሊመጣ የሚችለው ኃጢአታችን ይቅር መባሉን በማወቅ ነው፡፡ (ትልቁ የክርስትና ትምህርት III, 92)፡፡

791. **ዘፍጥረት** 32፡10 ለባሪያህ ከሠራኸው ከምሕረትህና ከእውነትህም ሁሉ ትንሽ ስንኳ የማይገባኝ ነኝ፡፡
792. **መዝሙር** 32፡5 ለእግዚአብሔር መተላለፌን እነግራለሁ አልሁ፤ አንተም የልቤን ኃጢአት ተውህልኝ፡፡

### *226. እግዚአብሔር ለበደሉን ምን እንድናደርግላቸው ይፈልጋል?*

ሰማያዊ አባታችን የበደሉንን ይቅር እንድንላቸውና መልካም እንድናደርግላቸው ይፈልጋል፡፡

793. **ማቴዎስ** 6፡12 እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን፡፡
794. **ማቴዎስ** 18፡21-22 በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ ወደ እርሱ ቀርቦ፡- ጌታ ሆይ፣ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ልተውለት? እስከ ሰባት ጊዜን? አለው፡፡ ኢየሱስ እንዲህ አለው፡፡ እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ አልልህም፡፡
795. **ኤፌሶን** 4፡32 እርስ በርሳችሁም ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ፤ እግዚአብሔርም ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ፡፡

### *227. ሌሎችን ይቅር በምንልበት ጊዜ ያ ምን ያሳያል?*

እግዚአብሔር እኛን ይቅር እንዳለን በእውነት እንደምናምን ያሳያል፡፡ ‹‹በየዕለቱ በእግዚአብሔር ላይ በጣም ብዙ ኃጢአት የምንሠራ ሲሆን እርሱ ግን ሁሉንም በጸጋ ይቅር እንደሚለን እኛም የሚጎዳንን፣ የሚበጠብጠንን፣ ኢፍትሐዊ ድርጊት የሚፈጽምብንን፣ ምቀኝነቱን የሚያሳየንን እና ወዘተ. ጎረቤታችንን ሁልጊዜ ይቅር ማለት ይገባናል፡፡ ስለዚህ

ይቅር ካላላችሁ እግዚአብሔር ይቅር እንደሚላችሁ አታስቡ (ትልቁ የክርስትና ትምህርት III, 94-95)።

796. **ማቴዎስ** 6፡14-15 ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ የሰማዩ አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር ይላችኋልና፤ ለሰዎች ግን ኃጢአታቸውን ይቅር ባትሉ አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች፡-* ዮሴፍ ወንድሞቹን ይቅር አለ (**ዘፍጥረት** 50፡15-21) የምሕረት የለሹ አገልጋይ ምሳሌ (**ማቴዎስ** 18፡23-35)።

> ***ስድስተኛው ጸሎት***
>
> ወደ ፈተና አታግባን።
>
> *ይህ ምን ማለት ነው?* እግዚአብሔር ማንንም በክፉ አይፈትንም፤ በዚህ ጸሎት የምንለምነው ዲያብሎስ፣ ዓለምና ኃጢአተኛ ባሕርያችን እንዳያታልሉን፣ ወይም ወደ ተሳሳተ እምነት፣ ወደ ተስፋ መቁረጥ፣ ወደ ታላቅ ሐፍረትና መጥፎ ምግባር እንዳይመሩን እግዚአብሔር እንዲከልለንና እንዲጠብቀን ነው። ምንም እንኳን በእነርሱ ብንጠቃም በመጨረሻ የበላይነትን እንድናገኝና ድልን እንድንቀዳጅ እንጸልያለን።

***228. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ‹‹[በክፉ] መፈተን›› እና ‹‹[ክፉ] ፈተና›› ማለት ምን ማለት ናቸው?***

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እነዚህ ቃላት ሁለት ትርጉም አላቸው፤

*ሀ. እግዚአብሔር ወደ ራሱ ሊያቀርበን የሚጠቀምበት የእምነታችን መፈተን፤*

797. **ዮሐንስ** 6፡5-6 ኢየሱስም ዓይኖቹን አንሥቶ ብዙ ሕዝብ ወደ እርሱ ሲመጣ አየና ፊልጶስን እነዚህ እንዲበሉ እንጀራ ከወዴት እንገዛለን? አለው። ራሱ ሊያደርግ ያለውን ያውቅ ነበርና ሊፈትነው ይህን ተናገረ።

798. **ያዕቆብ** 1፡2-3 ወንድሞቼ ሆይ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ ዐውቃችሁ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች፡-* እግዚአብሔር አብርሃም ይስሐቅን እንዲሰዋ በማዘዝ ፈተነው (**ዘፍጥረት** 22፡1-9)። ኢየሱስ የከነዓናዊቷን ሴት እምነት ፈተነ (**ማቴዎስ** 15፡21-28)።

*ለ. መንፈሳዊ ጠላቶቻችን ከእግዚአብሔርና ከመንገዶቹ አባብለው ሊያርቁን የሚያደርጓቸውን ሙከራዎች፤*

799. **ማርቆስ** 14፡38 ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉ ጸልዩም፤ መንፈስስ ተዘጋጅታለች ሥጋ ግን ደካማ ነው።

800. **ያዕቆብ** 1፡13-14 ‹‹ማንም ሲፈተን በእግዚአብሔር እፈተናለሁ አይበል››፤ እግዚአብሔር በክፉ አይፈተንምና፤ እርሱ ራሱስ ማንንም አይፈትንም። ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል።

### *229. መንፈሳዊ ጠላቶቻችን አሳስተው ሊመሩን የሚሞክሩት ወደ ምን ዓይነት ክፋቶች ነው?*

*ዲያብሎስ፣ ዓለምና ኃጢአተኛ ባሕርያችን ወደተሳሳተ እምነት፣ ወደ ተስፋ መቁረጥ፣ እና ሌሎች ታላላቅ ኃጢአቶች አሳስተው ሊመሩን ይሞክራሉ።*

801. **1ጴጥሮስ** 5፡8-9 *በመጠን ኑሩ ንቁም ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞራልና፤ በዓለም ያሉት ወድሞቻችሁ ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት።*
802. **ምሳሌ** 1፡10 *ልጄ ሆይ ኃጢአተኞች ቢያባብሉህ እሺ አትበል።*
803. **ማቴዎስ** 18፡7 *ወዮ ለዓለም ስለ ማሰናከያ፤ ማሰናከያ ሳይመጣ አይቀርምና፣ ነገር ግን በእርሱ ጠንቅ ማሰናከያ ለሚመጣበት ለዚያ ሰው ወዮለት!*
804. **ገላትያ** 5፡17 *ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና።*
805. **2ቆሮንቶስ** 4፡8 *በሁሉ እንገፋለን እንጂ አንጨነቅም፤ እናመነታለን እንጂ ተስፋ አንቆርጥም።*

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች፡-* ሔዋን እግዚአብሔርን እንድትጠራጠርና እንዳትታዘዝ ዲያብሎስ ፈተናት (**ዘፍጥረት** 3)። ይሁዳ ክርስቶስን አሳልፎ እንዲሰጥ (**ዮሐንስ** 13፡2)፤ እና ተስፋ እንዲቆርጥ (**ማቴዎስ** 27፡4-5) ዲያብሎስ ፈተነው። በክርስቶስ ጠላቶች መካከል ጴጥሮስ መድኅኑን ካደ (**ሉቃስ** 22፡54-60)። የንጉሥ ዳዊት ኃጢአተኛ ባሕርይ እንዲያመነዝርና ግድያ እንዲፈጽም ፈተነው (2**ሳሙኤል** 12፡9)።

### *230. ይህንን ጸሎት ስንጸልይ እግዚአብሔር ምን እንዲያደርግልን እንጠይቀዋለን?*

*ሰማያዊ አባታችን ፈተናዎችን እንድንቋቋምና እንድናሸንፍ ብርታት እንዲሰጠን እንጠይቀዋለን።*

806. **ሉቃስ** 22፡31-32 *ስምዖን ሆይ እነሆ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ፤ እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማለድሁ።*
807. **ሮሜ** 13፡14 *ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት፤ ምኞቱንም እንዲፈጽም ለሥጋ አታስቡ።*
808. **1ቆሮንቶስ** 10፡12-13 *ስለዚህ እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ። ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና አልደረሰባችሁም፤ ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው፤ ትታገሡም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል።*
809. **ኤፌሶን** 6፡11፣17 *የዲያሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ። … የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ፤ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።*

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች፡-* ዮሴፍ የጲጥፋራን ሚስት ፈተና ተቋቋመ (**ዘፍጥረት** 39፡ 1-20)። ኢየሱስ በሰይጣን ተፈትኖ ለእኛ ድል ተቀዳጀ (**ማቴዎስ** 4፡1-11)።

*ሰባተኛው ጸሎት*

*ከክፉ አድነን እንጂ*

*ይህ ምን ማለት ነው?* በዚህ ጸሎት እንደ ማጠቃለያ የምንለምነው የሰማዩ አባታችን ሥጋን ወይም ነፍስን፣ ንብረትን ወይም መልካም ስምን ከሚጎዱ ከማንኛውም ክፉ ነገሮች እንዲያድነን እንዲሁም በመጨረሻ የሞታችን ሰዓት ሲመጣ የተባረከ ፍጻሜን እንዲሰጠንና ከዚህ የሐዘን ሸለቆ በጸጋው ወደ ራሱ ወደ መንግሥተ ሰማያት እንዲወስደን ነው።

### *231. ሰባተኛው ጸሎት ምን ዓይነት ጸሎት ነው?*

ሰባተኛው ጸሎት ሰማያዊ አባታችን፣ ከዲያብሎስ እና በኃጢአት ምክንያት ወደ ዓለም ከመጣው ክፉ ሁሉ እንዲታደገን የምንጠይቅበት የማጠቃለያ ጸሎት ነው።

810. **መዝሙር** 121፡7-8 እግዚአብሔር ከክፉ ሁሉ ይጠብቅሃል፤ ነፍስህንም ይጠብቃታል። ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም እግዚአብሔር መውጣትህንና መግባትህን ይጠብቃል።

811. **2ተሰሎንቄ** 3፡3 ነገር ግን የሚያጸናችሁ ከክፉውም የሚጠብቃችሁ ጌታ የታመነ ነው።

### *232. እግዚአብሔር ሥጋንና ነፍስን፣ ንብረትንና መልካም ስምን ከሚጎዱ ከማንኛውም ክፉ ነገሮች የሚታደገን እንዴት ነው?*

በኃጢአት በተበላሸ ዓለም ውስጥ እግዚአብሔር ከጉዳት ይጠብቀናል፤ ወደ ሕይወታችን እንዲመጡ የሚፈቅዳቸውን ችግሮች እንድንቋቋም ይረዳናል።

812. **የሐዋርያት ሥራ** 14፡22 ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል።

813. **መዝሙር** 91፡9-10 አቤቱ አንተ ተስፋዬ ነህና ልዑልን መጠጊያህ አደረግህ። ክፉ ነገር ወደ አንተ አይቀርብም፤ መቅሠፍትም ወደ ቤትህ አይገባም።

814. **2ቆሮንቶስ** 12፡9 ጸጋዬ ይበቃሃል፤ ኃይሌ በድካም ይፈጸማልና።

815. **ምሳሌ** 3፡11-12 ልጄ ሆይ የእግዚአብሔርን ተግሣጽ አትናቅ፤ በገሠጸህም ጊዜ አትመረር፡ ፡ እግዚአብሔር የወደደውን ይገሥጻልና፤ አባት የሚወድደውን ልጁን እንደሚገሥጽ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች፡-* ሦስቱ ሰዎች በእቶን እሳት ውስጥ (**ዳንኤል** 3)፤ ዳንኤል በአንበሶች ጉደጓድ ውስጥ (**ዳንኤል** 6)።

### *233. እግዚአብሔር ወደ እኛ እንዲያመጣልን የምንጠይቀው የመጨረሻው ከክፉ ነፃ የምንወጣበት መንገድ ምንድን ነው?*

ሰማያዊ አባታችን ለእርሱ ታማኝ እንደ ሆንን እንዲጠብቀንና በምንሞትበት ጊዜ ከዚህ የሐዘን ዓለም ወደ ራሱ ወደ መንግሥተ ሰማይ እንዲወስደን እንፈልጋለን።

816. **ሉቃስ** 2፡29-32 ጌታ ሆይ አሁን አንደ ቃልህ ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋህ፤ ዓይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይተዋልና ይህም ለአሕዛብ ሁሉን የሚገልጥ ብርሃን ለሕዝብህም ለእስራኤል ክብር ነው።

817. **2ጢሞቴዎስ** 4፡18 ጌታም ከክፉ ነገር ሁሉ ያድነኛል ለሰማያዊውም መንግሥት ይጠብቀኛል። ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።

818. **ራእይ** 14፡13 በጌታ የሚሞቱ ሙታን ብፁዓን ናቸው።

819. ***ራእይ* 21፡4** እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል፤ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፤ ሐዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፤ የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና።

***መደምደሚያ***

> *መንግሥት ያንተ ናትና ኃይልም ክብርም ለዘለዓለሙ አሜን።*
> *ይህ ምን ማለት ነው?* እነዚህ ጸሎቶች በሰማይ አባታችን ዘንድ ተቀባይነትና ተሰሚነት ያላቸው መሆኑን እርግጠኛ መሆን ይገባኛል ማለት ነው፤ ምክንያቱም በዚህ መንገድ እንድንጸልይ እርሱ ራሱ ስለ አዘዘንና እንደሚሰማንም ተስፋ ስለ ሰጠን ነው። አሜን አሜን ማለት ‹‹አዎን አዎን እንደዚሁ ይሆናል›› ማለት ነው።

***234. የጌታን ጸሎት ‹‹አሜን›› በሚለው ቃል የምንደመድመው ለምንድን ነው?***

‹‹አሜን›› የሚለው ቃል ‹‹እንደዚህ ይሆናል›› ማለት ሲሆን እንድንጸልይ ያዘዘን እግዚአብሔር ጸሎቶቻችንን እንደሚሰማንና ቃል እንደገባልን እንደሚመልሳቸው አጽንኦት ይሰጣል።

820. **መዝሙር 50፡15** በመከራ ቀን ጥራኝ አድንህማለሁ፤ አንተም ታከብረኛለህ።
821. **ምሳሌ 15፡8** የኃጥአን መሥዋዕት በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊ ነው፤ የቅኖች ጸሎት ግን በእርሱ ዘንድ የተወደደ ነው።
822. **ምሳሌ 15፡29** እግዚአብሔር ከኃጥአን ይርቃል፤ የጻድቃንን ጸሎት ግን ይሰማል።

***235. እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ የሕዝቡን ጸሎት መመለስ እንደሚችል እንዴት አውቃለሁ?***

*ሀ. መልካም ስጦታዎች ሁሉ በእጁ ያለው ንጉሥ እርሱ ብቻ ስለ ሆነ ነው።*

823. ***ያዕቆብ* 1፡17** በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፤ መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ።
824. **መዝሙር 103፡2-3** ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ ምስጋናውን ሁሉ አትርሺ፤ ኃጢአትሽን ሁሉ ይቅር የሚል፣ ደዌሽንም ሁሉ የሚፈውስ።

*ለ. ለጸሎታችን መልስ ለመስጠት ኃይል ያለው እርሱ ብቻ ስለ ሆነ ነው።*

825. **መዝሙር 33፡6** በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ፤ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ።
826. **ኤፌሶን 3፡20-21** እንግዲህ በእኛ እንደሚሠራው ኃይል መጠን ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ ይልቅ እጅግ አብልጦ ሊያደርግ ለሚቻለው ለእርሱ በቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ እስከ ትውልዶች ሁሉ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን አሜን።

*ሐ. ክብር ሁሉ የእርሱ ስለ ሆነና ውዳሴያችን የሚገባው ስለ ሆነ ነው።*

827. **መዝሙር 113፡4-5** እግዚአብሔር በአሕዛብ ሁሉ ላይ ከፍተኛ ነው፤ ክብሩም ከሰማያት በላይ ነው። እንደ አምላካችን እንደ እግዚአብሔር ማን ነው?
828. **1ጢሞቴዎስ 1፡17** ብቻውን አምላክ ለሚሆን ለማይጠፋው ለማይታየውም ለዘመናት ንጉሥ ምስጋናና ክብር እስከ ዘላለም ድረስ ይሁን አሜን።



# ቅዱሳት ምሥጢራት

***236. ቅዱስ ምሥጢር ምንድን ነው?***

ቅዱስ ምሥጢር የተቀደሰ ድርጊት ነው፤ እርሱም፦

ሀ. በእግዚአብሔር የተመሠረተ፣

ለ. እግዚአብሔር ራሱ የተስፋ ቃሉን ከሚታይ ነገር ጋር ያስተሳሰረበት፣

ሐ. በክርስቶስ የተገኘውን የኃጢአት ይቅርታ የሚያቀርብበት፣ የሚሰጥበት እና የሚያትምበት ነው።

*ማስታወሻ፦* ‹‹ቅዱስ ምሥጢር (ሳክራመንት)›› የሚለው ቃል ወደ እኛ የመጣው ‹‹ምሥጢር›› የሚለውን የግሪክ ቃል ከተረጎመው የላቲኑ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ይህ ቃል በመጀመሪያ እንደ ሥላሴ፣ ትሥጉት፣ ቤዛነት፣ ቤተ ክርስቲያን ያሉ የእምነትን የሚያድን እውነቶችን ሁሉ ይገልጽ ነበር (**ለምሳሌ 1ቆሮንቶስ** 4፡1፤ **ኤፌሶን** 5፡32 እና **1ጢሞቴዎስ** 3፡16ን ይመልከቱ)። በኋላ ላይ ትርጉሙ አሁን ወደምናውቀው ይዘት ጠበብ አለ።

***237. እንደዚህ ያሉ ምን ያህል ቅዱሳት ምሥጢራት አሉ?***

በዚህ ትርጓሜ ሁለት ቅዱሳት ምሥጢራት - ቅዱስ ጥምቀትና ቅዱስ ቍርባን አሉ።

*ማስታወሻ፦* ምንም እንኳን በመለኮት የተደነገገ የሚታይ ነገር ባይኖረውም አንዳንድ ጊዜ የኃጢአት ይቅርታ አዋጅ (ቅዱስ ስርየት) እንደ ሦስተኛ ቅዱስ ምሥጢር ይቈጠራል። (Large Catechism IV, 74; Apology XIII 4)።

829. ***የሐዋርያት ሥራ*** 2፡38 ጴጥሮስም፦ ንስሐ ግቡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።

830. **1ቆሮንቶስ** 10፡16 የምንባርከው የበረከት ጽዋ ከክርስቶስ ደም ጋር ሕብረት ያለው አይደለምን? የምንቆርሰውስ እንጀራ ከክርስቶስ ሥጋ ጋር ሕብረት ያለው አይደለምን?

***238. ውሃ፣ ኅብስትና ወይን እጅግ የተለመዱ ነገሮች ሆነው እያለ ለቅዱሳት ምሥጢራት የላቀ ዋጋ ልንሰጣቸው የሚገባን ለምንድን ነው?***

‹‹ቅዱሳት ምሥጢራት እና በእግዚአብሔር የተወሰኑና የተመሠረቱ ውጫዊ ነገሮች ሁሉ፣ የአንድን ፍሬ ሽፋን እንደምናይ በግርድፉ፣ በውጫዊ ሽፋናቸው መሠረት መታሰብ አይገባቸውም፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል ውስጣቸው የተጨመረባቸው ከመሆኑ የተነሣ እናከብራቸዋለን። (ትልቁ የክርስትና ትምህርት IV, 19)።

831. **1ቆሮንቶስ** 1፡28 እግዚአብሔር የሆነውን ነገር እንዲያጠፋ የዓለምን ምናምንቴ ነገር የተናቀውንም ነገር ያልሆነውንም ነገር መረጠ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ፦* ተራ የሆነው የዮርዳኖስ ወንዝ በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል የንእማንን ለምጽ ለመፈወስ ኃይል አገኘ (2**ነገሥት** 5፡1-14)።



# የጥምቀት ቅዱስ ምሥጢር

## I. የጥምቀት ባሕርይ

*አንደኛ*

> ***ጥምቀት ምንድን ነው?***
> ጥምቀት እንዲሁ ተራ ውሃ ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ትእዛዝ ውስጥ የታቀፈና ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የተዋሐደ ውሃ ነው።
>
> ***ያ የእግዚአብሔር ቃል የትኛው ነው?***
> ክርስቶስ ጌታችን በማቴዎስ ወንጌል የመጨረሻ ምዕራፍ፡- ‹‹እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው›› ይላል (**ማቴዎስ** 28፡ 19)።

***239. ‹‹ማጥመቅ›› የሚለው ቃል ምን ማለት ነው?***

*ማጥመቅ ማለት በማጥለቅ፣ በማጠብ፣ በማፍሰስ እና በተመሳሳይ መንገዶች ውሃን መጠቀም ማለት ነው።*

832. **ማርቆስ** 7፡4 [ፈሪሳውያን] ከገበያም ተመልሰው ካልታጠቡ አይበሉም ጽዋንም ማድጋንም የናስ ዕቃንም አልጋንም እንደ ማጠብ [እንደ ማጥመቅ] ሌላ ነገር ሊጠብቁት የተቀበሉት ብዙ አለ።

*ማስታወሻ፡-* በመንፈስ ቅዱስ ማጥመቅ (**ማቴዎስ** 3፡11) ማለት መንፈስ ቅዱስን ማፍሰስ ማለት ነው (**የሐዋርያት ሥራ** 1፡5 እና **የሐዋርያት ሥራ** 2፡17-18)።

***240. የጥምቀትን ውሃ እጅግ ልዩ የሚያደርገው ምንድን ነው?***

ውሃም በራሱ ከሌሎች ውሃዎች የበለጠ የከበረ ሆኖ ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃልና ትእዛዝ ስለ ተጨመሩበት መለኮታዊ ውሃ እንጂ ሌላ ነገር አይደለም። (ትልቁ የክርስትና ትምህርት IV 14)።

***241. ቅዱስ ጥምቀትን የመሠረተው ማን ነው?***

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑ አሕዛብን ሁሉ እንድታጠምቅ ስላዘዘ ጥምቀትን የመሠረተው እግዚአብሔር ራሱ ነው።

833. **ማቴዎስ** 28፡19-20 እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው።

*242. ‹‹በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም›› ማጥመቅ ማለት ምን ማለት ነው?*

ይህ ማለት በጥምቀት እግዚአብሔር፣ ቅድስት ሥላሴ ወደ ራሱ ሕብረት ወይም የቀረበ ግንኙነት ውስጥ ይቀበለኛል ማለት ነው።

*243. ማጥመቅ ያለበት ማን ነው?*

በተለምዶ ማጥመቅ ያለባቸው የተጠሩ የክርስቶስ አገልጋዮች ናቸው፤ ነገር ግን በድንገተኛ አጋጣሚዎችና ቄስ በሌለበት ጊዜ የትኛውም ክርስቲያን ማጥመቅ ይገባዋል።

834. **1ቆሮንቶስ** 4፡1 ሰው እኛን እንደ ክርስቶስ ሎሌዎችና እንደ እግዚአብሔር ምሥጢር መጋቢዎች ይቁጠረን።

*ማስታወሻ፡-* ለድንገተኛ አጋጣሚዎች የሚሆን አጠር ላለ የጥምቀት ሥርዓት የዚህን ክፍል መጨረሻ ላይ ይመልከቱ።

*244. መጠመቅ ያለበት ማን ነው?*

መጠመቅ ያለባቸው ‹‹አሕዛብ ሁሉ›› ናቸው፤ ማለትም በዕድሜ ያነሱና በዕድሜ የገፉ ሰዎች ሁሉ።

*245. በማጥመቅ ውስጥ ምን የተለየ ነገር ማድረግ ያስፈልጋል?*

ሀ. ትምህርት መቀበል የሚችሉ የክርስትና እምነት አበይት አንቀጾችን ትምህርት ከተሰጣቸው በኋላ መጠመቅ ይገባቸዋል።

835. **የሐዋርያት ሥራ** 2፡38-39 ጴጥሮስም ንስሐ ግቡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ። የተስፋው ቃል ለእናንተ ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና አላቸው።

836. **የሐዋርያት ሥራ** 2፡41 ቃሉንም የተቀበሉ ተጠመቁ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች፡-* ኢትዮጵያዊው ከመጠመቁ በፊት ትምህርት ተሰጠው (**የሐዋርያት ሥራ** 8፡26-39)። የእስር ቤቱ ጠባቂ ከመጠመቁ በፊት ትምህርት ተሰጠው (**የሐዋርያት ሥራ** 16፡25-33)።

ለ. ትንንሽ ልጆች በእነርሱ ላይ ሥልጣን ባላቸው ሰዎች ወደ ጥምቀት ሲቀርቡ ሊጠመቁ ይገባቸዋል።

837. **ማርቆስ** 10፡13-15 እንዲዳስሳቸውም ሕፃናትን ወደ እርሱ አመጡ፤ ደቀ መዛሙርቱም ያመጡአቸውን ገሠጹአቸው። ኢየሱስ ግን አይቶ ተቆጣና፡- ሕፃናትን ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተዉ አትከልክሉአቸው፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ እነዚህ ላሉት ናትና። እውነት እላችኋለሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ ሕፃን የማይቀበላት ሁሉ ከቶ አይገባባትም አላቸው።

*246. ሕፃናት መጠመቅ ያለባቸው ለምንድን ነው?*

*ሕፃናት መጠመቅ አለባቸው፤ ምክንያቱም፡-*

*ሀ. ‹‹አሕዛብን ሁሉ›› በሚሉት ቃላት ውስጥ የተካተቱ ናቸው።*

838. **ማቴዎስ** 28፡19 እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው … ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው።

839. **የሐዋርያት ሥራ** 2፡38-39 ንስሐ ግቡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ። የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና።

*ለ. ኢየሱስ በተለይ ሕፃናት ወደ እርሱ እንዲመጡ ይጋብዛቸዋል።*

840. **ሉቃስ** 18፡15-17 እንዲዳስሳቸውም ሕፃናትን ደግሞ ወደ እርሱ አመጡ፤ ደቀ መዛሙርቱም አይተው ገሰፁአቸው። ኢየሱስ ግን ሕፃናትን ወደ እርሱ ጠርቶ ሕፃናት ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተዉአቸው፤ አትከልክሉአቸውም፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ እነዚህ ላሉት ናትና። እውነት እላችኋለሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ ሕፃን የማይቀበላት ሁሉ ከቶ አይገባባትም አለ።

*ሐ. ኃጢአተኞች እንደ መሆናቸው ሕፃናትም ጥምቀት የሚሰጠው ነገር ያስፈልጋቸዋል፤*

841. **ዮሐንስ** 3፡5-6 ሰው ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው።

842. **ኤፌሶን** 2፡3 [እኛ ሁላችን] እንደ ሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን።

*መ. ሕፃናትም እምነት ሊኖራቸው ይችላል።*

843. **ማቴዎስ** 18፡6 በእኔም ከሚያምኑ ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ሁሉ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባሕር መስጠም ይሻለው ነበር።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ፡-* መጥምቁ ዮሐንስ ከመወለዱ በፊት እንኳን (**ሉቃስ** 1፡41-44)፤ ከእናቱ ማኅፀን አንስቶ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ነበር (**ሉቃስ** 1፡15)።

## *247. ቤተ ክርስቲያን በጥምቀት ወቅት ደጋፊዎችን/አቅራቢዎችን የምታበረታታው ለምንድን ነው?*

አቅራቢዎች፣ ይህንን ቅዱስ ምሥጢር የተቀበሉት በተገቢ ሁኔታ መጠመቃቸውን ይመሰክራሉ። ይጸልዩላቸዋልም፤ ልጆች በሚሆኑበት አጋጣሚ ደግሞ በተለይ ወላጆቻቸውን ካጡ በክርስትና ሕይወት እድገታቸው ላይ ይረዷቸዋል። ሌሎችን ለጥምቀት አቅራቢዎች መሆን የሚገባቸው ተመሳሳይ የእምነት አቋም ያላቸው ሰዎች ብቻ ናቸው ።

844. **ማቴዎስ** 18፡16 በሁለት ወይም በሦስት ምስክር አፍ ነገር ሁሉ እንዲጸና …።

845. **ኤፌሶን** 4፡16 ከእርሱም [ከክርስቶስ] የተነሣ አካል ሁሉ እያንዳንዱ ክፍል በልክ እንደሚሠራ በተሰጠበት በጅማት ሁሉ እየተጋጠመና እየተያያዘ ራሱን በፍቅር ለማነጽ አካሉን ያሳድጋል።

## II. የጥምቀት በረከቶች

*ሁለተኛ*

*ጥምቀት ምን ጥቅሞችን ያስገኛል?*
የኃጢአት ይቅርታን ያስገኛል፤ ከሞትና ከዲያብሎስ ይታደጋል፤ እንዲሁም የእግዚአብሔር ቃላትና ተስፋዎች እንደሚያውጁት ይህንን ለሚያምኑ ሁሉ የዘለዓለምን ድነት ይሰጣል፡፡

***እነዚህ የእግዚአብሔር ቃላትና ተስፋዎች የትኞቹ ናቸው?***

ክርስቶስ ጌታችን በማርቆስ ወንጌል የመጨረሻ ምዕራፍ ‹‹*ያመነ የተጠመቀም ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል*›› ይላል (**ማርቆስ** 16፡16)፡፡

***248. በጥምቀት የሚሰጡ ታላላቅና የከበሩ ነገሮች ምንድን ናቸው?***

ጥምቀት

ሀ. የኃጢአት ይቅርታን ያስገኛል፡፡

846. **የሐዋርያት *ሥራ*** 2፡38 ንስሐ ግቡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፡፡

847. **የሐዋርያት *ሥራ*** 22፡16 ተነሣና ስሙን እየጠራህ ተጠመቅ፤ ከኃጢአትህም ታጠብ፡፡

ለ. ከሞትና ከዲያብሎስ ይታደጋል፡፡

848. **ሮሜ** 6፡3፣5 ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? … ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን፡፡

849. ***ገላትያ*** 3፡27 ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችሁታልና፡፡

850. **ቈላስይስ** 1፡13-14 እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፣ ቤዛነቱንም እርሱንም የኃጢአትን ስርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን (**ቈላስይስ** 2፡11-12ን ያነጻጽሩ)፡፡

ሐ. የዘላለም ድነት ይሰጣል፡፡

851. **ማርቆስ** 16፡16 *ያመነ* የተጠመቀም ይድናል፡፡

852. **1ጴጥሮስ** 3፡21 ይህም ውሃ [ከኖኅ የጥፋት ውሃ] ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል … ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ነው፡፡

853. **ቲቶ** 3፡5 ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን፡፡

***249. ክርስቶስ አስቀድሞም ይቅርታንና ድነትን ካስገኘልንና ይህንን ሁሉ በጸጋ ብቻ የሚሰጠን ከሆነ ጥምቀት ለምን ያስፈልገናል?***

ክርስቶስ ፍጹም በሆነ ሕይወቱ፣ መከራው፣ ሞቱና ትንሣኤው ለመላው የሰው ዘር ሙሉ ይቅርታንና ድነትን በእርግጥ አስገኝቶልናል። ይህንን ተመሳሳይ ምሕረት በጥምቀት ያድላል (ጥምቀት የጸጋ መሣሪያ ነው።)

854. **1ቆሮንቶስ** 6:11 በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል፤ ተቀድሳችኋል፤ ጸድቃችኋል።

855. **ቲቶ** 3:5-7 ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን … ያን መንፈስም በጸጋው ጸድቀን በዘላለም ሕይወት ተስፋ ወራሾች እንድንሆን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ላይ አትርፎ አፈሰሰው።

### *250. ጥምቀት እነዚህን ሁሉ በረከቶች የሚሰጠው ለማን ነው?*

ጥምቀት እነዚህን በረከቶች የእግዚአብሔርን የማዳን የተስፋ ቃላት ለሚያምኑ ሁሉ ይሰጣል።

856. **ማርቆስ** 16:16 ያመነ የተጠመቀም ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል።

### *251. ያልተጠመቀ ሰው ሊድን ይችላል?*

የሚያስኮንነው አለማመን ብቻ ነው። ከተሻለ እውቀት አንጻር ጥምቀትን በሚንቅና በማይቀበል ሰው ልብ ውስጥ እምነት ሊኖር አይችልም። ነገር ግን ወንጌሉን የሚያምኑ ለመጠመቅ የተመቸ እድል ከማግኘታቸው በፊት ቢሞቱ አይኮነኑም።

857. **ማርቆስ** 16:16 ያላመነ ግን ይፈረድበታል።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች፡-* ፈሪሳውያንና ጻፎች ባለማመናቸው የዮሐንስን ጥምቀት አልተቀበሉም (**ሉቃስ** 7:30)። የተሰቀለው ወንበዴ ያለ ጥምቀት ዳነ (**ሉቃስ** 23:39-43)።

### *252. ከቅዱስ ጥምቀት ቅዱስ ምሥጢር በተጨማሪ ‹‹በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ›› መፈለግ የሌለብን ለምንድን ነው?*

ከጥምቀት ቅዱስ ምሥጢር ባሻገር ሌላ ምንም ‹‹ጥምቀት›› መፈለግ አይገባንም። ምክንያቱም፡-

*ሀ.* ከቅዱስ ጥምቀት ቅዱስ ምሥጢር ጎን ለጎን በአሁኑ ጊዜ በእግዚአብሔር የተሰጠ ሌላ ምንም ጥምቀት የለም።

858. **ኤፌሶን** 4:5 አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት።

*ማስታወሻ፡-* ‹‹ስለ ጥምቀት ትምህርት›› (**ዕብራውያን** 6:2) በርካታ የክርስቲያን ጥምቀቶች አሉ ማለት አይደለም፤ ነገር ግን አንዱ እውነተኛ ጥምቀት በጥንቱ ዓለም የተለመዱ ከነበሩት በርካታ ሃይማኖታዊ የመታጠብ ሥርዓቶች በግልጽ ተለይቶ ሊታወቅ ይገባዋል ማለት ነው (**ለምሳሌ ማርቆስ** 7:4ን ይመልከቱ)።

ለ. ቅዱስ ምሥጢሩ የውሃ ብቻ ወይም የመንፈስ ብቻ ጥምቀት አይደለም፤ ነገር ግን የውሃና የመንፈስ ጥምቀት ነው።

859. **ዮሐንስ** 3:5 ሰው ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም።

860. **ቲቶ** 3:5 ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን።

*ማስታወሻ፡-* **ማቴዎስ** 3፡11 ‹‹በውሃ›› እና ‹‹በመንፈስ ቅዱስና በእሳት›› ስለ መጠመቅ ይናገራል፡፡ እዚህ ላይ ልዩነቱ ቅዱስ ምሥጢር በሆነው ጥምቀትና ‹‹የመንፈስ ጥምቀት›› በሚባል የሆነ ዓይነት ጥምቀት መካከል አይደለም፤ ነገር ግን የዝግጅት ተልእኮና ጥምቀት በሆነው በመጥምቁ ዮሐንስ እና በኢየሱስ ክርስቶስ ሙሉ፣ ቋሚ ተልእኮና ጥምቀት መካከል ነው፡፡ የዮሐንስ ጥምቀት የኃጢአት ይቅርታም ቢሰጥ ወደ መድኃኒቱ የቤዛነት ሥራ ወደፊት የሚጠቁም በመሆኑ የተለየ ነበር፡፡

ሐ. በመንፈስ ቅዱስ የተሰጡት ልዩ ምልክቶች ሌላ ‹‹ጥምቀት›› አልነበሩም፤ ነገር ግን የሐዋርያትን ስብከት እውነትና ኃይል የሚያረጋግጡ ነበሩ፡፡

861. **የሐዋርያት ሥራ** 19፡6 ጳውሎስም እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው፤ በልሳኖችም ተናገሩ፤ ትንቢትም ተናገሩ፡፡

862. **2ቆሮንቶስ** 12፡12 በእርግጥ የሐዋርያነት ምልክት በመካከላችሁ በምልክትና በድንቅ ነገር በተአምራትም በሁሉ ትዕግሥት ተደረገ፡፡

*ማስታወሻ፡-* ጥያቄ 164ን ይመልከቱ፡፡

## III. የጥምቀት ኃይል

*ሦስተኛ*

***ውሃ እንደዚህ ያሉትን ታላላቅ ነገሮች እንዴት ሊያደርግ ይችላል?***

*በእርግጥ ውሃ ብቻውን እንዳልሆነ ግልጽ ነው፤ ዳሩ ግን ከውሃው ጋር ያለው የእግዚአብሔር ቃልና በውሃው ውስጥ ያለውን ይህን የእግዚአብሔር ቃልን የሚያምነው እምነት እነዚህን ያደርጋል፡፡ ምክንያቱም ያለ እግዚአብሔር ቃል ከሆነ ውሃው እንዲሁ ውሃ ብቻ ነው እንጂ ጥምቀት አይደለም፤ ዳሩ ግን ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ከሆነ ጥምቀት ይሆናል፤ ማለትም በጸጋው የበለጸገ የሕይወት ውሃና ለአዲስ ልደት የሚሆን መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ ይሆናል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ በቲቶ ምዕራፍ ሦስት እንደሚለው ‹‹ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለ ነበረው ሥራ አይደለም፤ ያን መንፈስም በጸጋ ጸድቀን በዘላለም ሕይወት ተስፋ ወራሾች እንድንሆን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ላይ አትርፎ አፈሰሰው፡፡ ቃሉ የታመነ ነው››* (ቲቶ 3፡5-8)፡፡

***253. የጥምቀት ውሃ እንዴት የኃጢአት ይቅርታን ያስገኛል? ከሞትና ከዲያብሎስ ይታደጋል?* የዘለዓለም ድነትን ይሰጣል?**

የእግዚአብሔር የምስረታው ቃላት እነዚህን ታላላቅ በረከቶች ጥምቀት ውስጥ ያኖራቸዋል፡፡ በውሃው ውስጥ ያለውን ይህን የእግዚአብሔር ቃል የሚያምነው እምነት በረከቶቹን ይወስድና የእኛ የራሳችን ያደርጋቸዋል፡፡

863. **ኤፌሶን** 5፡25-26 ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን … ወደዳት … በውሃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፡፡

864. **ገላትያ** 3፡26-27 በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና፤ ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና፡፡

***254. መጽሐፍ ቅዱስ ጥምቀትን ለምንድን ነው ለአዲስ ልደት የሚሆን መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ ብሎ የሚጠራው?***

በጥምቀት መንፈስ ቅዱስ እምነትን የሠራ እና ኃጢአትን ለማሸነፍ ኃይል ያለው አዲስ መንፈሳዊ ሕይወት በውስጣችን ይፈጥራል፡፡

865. **ሮሜ** 6፡6 ከእንግዲህስ ወዲያ ለኃጢአት እንዳንገዛ የኃጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደ ተሰቀለ እናውቃለን፤ የሞተስ ከኃጢአቱ ጸድቆአልና፡፡

866. **ቲቶ** 3፡5-8 ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለ ነበረው ሥራ አይደለም፤ ያን መንፈስም በጸጋው ጸድቀን በዘላለም ሕይወት ተስፋ ወራሾች እንድንሆን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ላይ አትርፎ አፈሰሰው፡፡ ቃሉ የታመነ ነው፡፡

## IV. ጥምቀት የሚያመለክተው

***አራተኛ***

***እንደዚህ ያለው የውሃ ጥምቀት ምን ያመለክታል?***

በእኛ ውስጥ አሮጌው አዳም ከኃጢአቱና ከክፉ ምኞቱ ሁሉ ጋር በየዕለቱ በሚደረገው ጸጸትና ንስሐ መስጠም እና መሞት እንዳለበትና አዲሱ ሰው በየዕለቱ መውጣቱንና በእግዚአብሔር ፊት በጽድቅና በንጽሕና ለዘላለም እንዲኖር መነሣቱን ያመለክታል፡፡

***ይህ የተጻፈው የት ነው?***

ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ ምዕራፍ ስድስት፡- ‹‹እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን›› ብሎ ይጽፋል [**ሮሜ** 6፡4]፡፡

***255. አሮጌው አዳም ምንድን ነው?***

አሮጌው አዳም፣ አዳም በኃጢአት በመውደቁ ምክንያት የወረስነው የተበላሸው ክፉ ባሕርይ ነው፡፡

867. **ኤፌሶን** 4፡22 ፊተኛ ኑሮአችሁን እያሰባችሁ እደሚያታልል ምኞት የሚጠፋውን አሮጌውን ሰው አስወግዱ፡፡

***256. ይህ አሮጌው አዳም በውስጣችን መስጠም ያለበት እንዴት ነው?***

አሮጌው አዳም መስጠም ያለበት ክፉ መሻቶችን በምንቀቋምበትና በምናሸንፍበት ዕለታዊ ጸጸት (ለኃጢአት ማዘን) እና ንስሐ (እምነት) ነው፡፡

868. **ሉቃስ** 9፡23 በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ፡፡

869. *ገላትያ* 5፡24 የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ *ሥጋን* ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ *ጋር* ሰቀሉ።

### *257. አዲሱ ሰው ምንድን ነው?*

አዲሱ ሰው ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብ በውስጣችን የተፈጠረው አዲስ መንፈሳዊ ሕይወት እና ባሕርይ ነው።

870. **2ቆሮንቶስ** 5፡17 ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው።

### *258. ይህ አዲሱ ሰው እንዴት ነው መውጣትና መነሣት ያለበት?*

አዲሱ ሰው በእግዚአብሔር ፊት በእውነተኛ እምነትና በመልካም *ሥራዎች* ዕለት ዕለት ስንኖርና ስናድግ ይወጣል፤ ይነሳልም።

871. **ኤፌሶን** 4፡24 ለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ።

### *259. ጥምቀት የአሮጌውን አዳም በየዕለቱ መስጠምና የአዲሱን ሰው መውጣት የሚያመለክተው እንዴት ነው?*

በጥምቀት በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ተካፋዮች ተደርገናል። እርሱ ኃጢአታችንን እንደ ቀበረ እኛም ዕለት ዕለት ልናሸንፈውና ልንቀብረው እንችላለን፤ ይገባናልም። እርሱ ከሙታን እንደ ተነሣና በሕይወት እንደሚኖርም እኛም በእርሱ ዕለት ዕለት አዲስ ሕይወት መኖር እንችላለን፤ ይገባናልም።

872. **ሮሜ** 6፡3-4 ከክርስቶስ ኢየሱስ *ጋር* አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ *ጋር* አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ከሞቱ *ጋር* አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ *ጋር* ተቀበርን።

### *260. ጥምቀታችንን በመደበኛነት የምናስታውስባቸው ቃላት የትኞቹ ናቸው?*

‹‹በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም›› የሚሉት *ቃላት* ከጥምቀታዊው ትእዛዝ የተገኙና *ሥላሴያዊ* ቡራኬ በመባል ይታወቃሉ። እነዚህን ቃላት በቤተ ክርስቲያን ወይም በራሳችን በመድገም በሰማይ፣ በምድርና በሲኦል ፊት ቅድስት *ሥላሴ* የሆነው አምላክ በጥምቀታችን የሰጠንን ሁሉ እናስታውሳለን፤ እንወስዳለን፤ እንመሰክርማለን።

873. **ሮሜ** 8፡39 ሞት ቢሆን፣ ሕይወትም ቢሆን፣ መላእክትም ቢሆን፣ ግዛትም ቢሆን፣ ያለውም ቢሆን፣ የሚመጣውም ቢሆን፣ ኃይላትም ቢሆኑ፣ ከፍታም ቢሆን፣ ዝቅታም ቢሆን፣ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ፡-* የብፁዕ *ሥላሴ* ሦስቱ አካላት በጌታችን ጥምቀት ራሳቸውን ገለጹ (**ሉቃስ** 3፡21-22)።

*ማስታወሻ፡- ሥላሴያዊ* ቡራኬው በጥምቀታችን ወቅት ‹‹በተሰቀለው በክርስቶስ *መዋጀታችንን*›› ለማመልከት በግንባራችን እና በልባችን ላይ በተደረገው የመስቀል ምልክት ሊታጀብ ይችላል።

### *ለድንገተኛ ሁኔታዎች የቅዱስ ጥምቀት አጭር መመሪያ*

በአስቸኳይ አጋጣሚዎች፣ ቄስ በሌለበት፣ የትኛውም ክርስቲያን ቅዱስ ጥምቀትን ማከናወን ይችላል። ውሃ በመውሰድ ግለሰቡን በስም በመጥራት፡- ‹‹በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠምቅሃለሁ፤ አሜን›› በማለት ውሃውን አድርግ። ጊዜ ካለ ከሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫና ከጌታ ጸሎት በኋላ ጥምቀቱ ሊካሄድ ይችላል።



## የኃጢአት ኑዛዜ

‹‹ወደ ኃጢአት ኑዛዜ እንድትሄዱ ስገፋፋችሁ ክርስቲያን እንድትሆኑ ከመገፋፋት ሌላ ምንም ነገር እያደረግሁ አይደለሁም፡፡››
(Appendix B, Brief Exhortation, 32).

***የኃጢአት ኑዛዜ ምንድን ነው?***
የኃጢአት ኑዛዜ ሁለት ክፍሎች አሉት፡፡
አንደኛ ኃጢአታችንን መናዘዝ፣ ሁለተኛ የኃጢአት ይቅርታን አዋጅ መቀበል ሲሆን፣ ይኸውም የኃጢአት ኑዛዜን ከሚቀበለው ቄስ የምንቀበለውን የይቅርታ አዋጅ ከራሱ ከእግዚአብሔር እንደ መጣ ያህል በዚሁ አማካይነት በሰማይ አምላክ ፊት ኃጢአታችን ይቅር ስለ መባሉ በምንም ዓይነት ሳንጠራጠር ነገር ግን በጥብቅ ማመን ነው፡፡
የትኞቹን ኃጢአቶች ነው መናዘዝ ያለብን?
በእግዚአብሔር ፊት በጌታ ጸሎት እንደምናደርገው የማናውቃቸውን እንኳ ቢሆን በሁሉም ኃጢአቶች በደለኛ ነን ማለት ይገባናል፤ ይሁን እንጂ የኃጢአት ኑዛዜ በሚቀበለው ቄስ ፊት የምንናዘዘው የምናውቃቸውንና በልባችን የሚሰሙንን ኃጢአቶች ብቻ ነው፡፡
እነዚህ [ኃጢአቶች] የትኞቹ ናቸው?

ከአሥርቱ ትእዛዛት አንጻር የሕይወታችሁን አካሄድ አጢኑ፡፡ እናት፣ አባት፣ ወንድ ልጅ፣ ሴት ልጅ፣ ባል፣ ሚስት ወይም ሠራተኛ ናችሁ? የማትታዘዙ፣ የማትታመኑ፣ ወይም ሰነፎች ሆናችኋል? ደማችሁ የሚፈላ፣ ስድ ወይም የሚጣላ ሰው ሆናችኋል? በቃላችሁ ወይም በሥራችሁ የሆነ ሰውን ጎድታችኋል? አንድ ነገር ሰርቃችኋል? ቸልተኛ ሆናችኋል? አንዳች ነገር አባክናችኋል? ወይም ጉዳት አድርሳችኋል?

**261. የኃጢአት ኑዛዜ የመጀመሪያ ክፍል ምንድን ነው?**
**የኃጢአት ኑዛዜ የመጀመሪያው ክፍል ኃጢአታችንን ማስታወቅ ወይም መቀበል ነው፡፡**

874. **መዝሙር** 32፡3፣5 ሁልጊዜ ከመጮኼ የተነሣ ዝም ባልሁ ጊዜ አጥንቶቼ ተበላሹ፤ . . . ኃጢአቴን ለአንተ አስታወቅሁ፤ በደሌንም አልሸፈንሁም፤ ለእግዚአብሔር መተላለፌን እነግራለሁ አልሁ። አንተም የልቤን ኃጢአት ተውህልኝ።
875. **መዝሙር** 51፡1-4 አቤቱ እንደ ቸርነትህ መጠን ማረኝ፤ እንደ ምሕረትህም ብዛት መተላለፌን ደምስስ። ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ፤ ከኃጢአቴም አንጻኝ፤ እኔ መተላለፌን አውቃለሁና ኃጢአቴም ሁልጊዜ በፊቴ ነውና። አንተን ብቻ በደልሁ በፊትህም ክፋትን አደረግሁ፤ በነገርህ ትጸድቅ ዘንድ በፍርድህም ንጹሕ ትሆን ዘንድ።

### *262. በእግዚአብሔር ፊት ምን ኃጢአቶችን መናዘዝ ይገባናል?*

በጌታ ጸሎት እንደምናደርገው በእግዚአብሔር ፊት የማናውቃቸውን እንኳ ቢሆን በሁሉም ኃጢአቶች በደለኞች ነን ማለት ይገባናል።

876. **መዝሙር** 19፡12 ስሕተቱን ማን ያስተውላታል፤ ከተሰወረ ኃጢአት አንጻኝ።
877. **ምሳሌ** 28፡13 ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤ የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል።
878. **1ዮሐንስ** 1፡8-9 ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፤ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም። በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመጻም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።

### *263. በባልንጀራችን ፊት መናዘዝ የሚገቡን ኃጢአቶች ምን ምን ናቸው?*

በባልንጀራችን ፊት በእርሱ/በእርሷ ላይ የሠራናቸውን ኃጢአቶች ሁሉ መናዘዝ አለብን።

879. **ያዕቆብ** 5፡16 እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ።
880. **ማቴዎስ** 5፡23-24 እንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ፤ በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ።

### *264. በቄሳችን ወይም በአናዛዣችን ፊት በግል እንድንናዘዝ የምንበረታታው ምን ምን ኃጢአቶችን ነው?*

በቄሱ ወይም በአናዛዡ ፊት በልባችን የምናውቃቸውንና የሚሰሙንን በተለይም የሚያስቸግሩንን ኃጢአቶች እንናዘዛለን።

881. **2ሳሙኤል** 12፡13 ዳዊትም ናታንን እግዚአብሔርን በድያለሁ አለው። ናታንም ዳዊትን እግዚአብሔር ደግሞ ኃጢአትህን አርቆአል አለው።
882. **ያዕቆብ** 5፡16 እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ፤ ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ።

*ማስታወሻ፡ ማንም ሰው የግል የኃጢአት ኑዛዜ እንዲያደርግ አይገደድም።*

### *265. የኃጢአት ኑዛዜ ሁለተኛው ክፍል ምንድን ነው?*

የኃጢአት ኑዛዜ ሁለተኛው ክፍል ከኃጢአት የመፈታት አዋጅ ማለትም የኃጢአትን ይቅርታ መቀበላችን ነው።

883. **ኢሳይያስ** 1፡18 ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር፤ ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች፤ እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች።

***266. በቄሱ የተነገረውን ከኃጢአት የመፈታት አዋጅ (ይቅርታ) እንዴት ልንመለከተው/ ልንቆጥረው ይገባናል?***

የቄሱን የኃጢአት ይቅርታ አዋጅ ከራሱ ከእግዚአብሔር እንደ ሆነ በምንም ዓይነት ሳንጠራጠር በሰማይ አምላክ ፊት ኃጢአታችንን ይቅር እንደ ተባለ በጥብቅ በማመን መቀበል ይገባናል።

‹‹ሕዝባችን ከኃጢአት የመፈታት አዋጅን እንደ እግዚአብሔር ድምፅና በእግዚአብሔር ትእዛዝ እንደ ተነገረ አድርገው የላቀ ዋጋ እንዲሰጡት ተምረዋል›› (Augsburg Cnnfession XXV, 3).

884. **ማቴዎስ** 18፡18 በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል።

885. **ሉቃስ** 10፡16 የሚሰማችሁ እኔን ይሰማል።

886. **ዮሐንስ** 20፡23 ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋችሁ ሁሉ ይቀርላቸዋል።

***267. ለቄሱ የግል የኃጢአት ኑዛዜዬ በምሥጢር ተጠብቆ እንደሚቆይ ምን ዋስትና አለኝ?***

እነዚያ ኃጢአቶች ስለ ተወገዱ ቄሱ በግል የኃጢአት ኑዛዜ የተነገሩትን ኃጢአቶች ለሌላ ለማንም እንዳይነግር ቃል ኪዳን ገብቷል።

887. **መዝሙር** 103፡12 ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ እንዲሁ ኃጢአታችንን ከእኛ አራቀ።

888. **ምሳሌ** 11፡13 ለሐሜት የሚሄድ ምሥጢሩን ይገልጣል። በመንፈስ የታመነ ነገሩን ይሰውራል።

889. **1ጢሞቴዎስ** 3፡1-2 ማንም ኤጴስ ቆጶስነትን [ቅስናን] ቢፈልግ መልካምን ሥራ ይመኛል የሚለው ቃል የታመነ ነው። እንግዲህ ኤጲስ ቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል፤ የማይነቀፍ፣...።

***268. የግል የኃጢአት ኑዛዜና ከኃጢአት የመፈታት አዋጅ ጥቅሙ ምንድን ነው?***

በግል የኃጢአት ኑዛዜና የይቅርታ አዋጅ በቄሱ አማካይነት እግዚአብሔር ራሱ የእያንዳንዱን ግለሰብ ኑዛዜ የተደረገባቸውን ኃጢአቶች ይቅር ይላል።

‹‹ኃጢአተኝነቱ የሚሰማውና መጽናናት የሚፈልግ የትኛውም ልብ የእግዚአብሔርን ቃል ሲሰማና እግዚአብሔር በሰው አማካይነት ከኃጢአቶቹ እንደሚፈታውና ነጻ እንደሚያደርገው ሲገባው እዚህ ላይ ጽኑ ምሽግ/መሸሸጊያ ያገኛል›› (Appendix B, Brief Exhortation 14).

890. **መዝሙር** 32፡2 እግዚአብሔር በደልን የማይቈጥርበት በመንፈሱም ሽንገላ የሌለበት ሰው ምስጉን ነው።

891. **2ሳሙኤል** 12፡13 ናታንም ዳዊትን፦ እግዚአብሔር ደግሞ ኃጢአትህን አርቆልሃል አለው፡ ፡

892. **ማቴዎስ** 9፡2 አንተ ልጅ አይዞህ፤ ኃጢአትህ ተሰረየችልህ።

## አጭር የኑዛዜ ዓይነት

[ሉተር የሚከተለው ናሙና በዘመኑ ለነበሩ ክርስቲያኖች የግል የኃጢአት ኑዛዜ እንደ ምሳሌ እንዲያገለግል ብቻ ያቀደው ነበር። በአሁኑ ዘመን የሚሆን የግለሰብ የኃጢአት ኑዛዜ ናሙና [Lutheran Service Book ገጽ 292-93 ይመልከቱ።]

***የተጸጸተው ሰው እንዲህ ይላል፤***

ውድ አናዛዤ፣ እባክዎን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም የኃጢአት ኑዛዜዬን እንዲሰሙልኝና የኃጢአት ይቅርታን እንዲያውጁልኝ እጠይቅዎታለሁ።
እኔ ምስኪን ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር ፊት በሁሉም ኃጢአቶች መበደሌን እቀበላለሁ። በተለይ እንደ አገልጋይ፣ እንደ ሠራተኛ፣ ወዘተ. መናገሩ ቢያሳዝንም በዚህና በዚያ እንዳደርግ የተነገረኝን ባለማድረጌ አሠሪዬን በታማኝነት እንዳላገለገልኩ በፊትዎ እናዘዛለሁ። እንዲናደድና እንዲራገም አድርጌዋለሁ። ቸልተኛ በመሆን ጉዳት እንዲደርስ አድርጌአለሁ። በቃላትና በድርጊቶችም ሰውን የማናድድ ሆኜአለሁ ከቢጤ እኩያዎቼ ጋር ተጣልቻለሁ። በቤቷ ባለቤት ወይዘሮ ላይ አጉረምርሜአለሁ፤ ረግሜአታለሁ። ለዚህ ሁሉ አዝኛለሁ፤ ጸጋንም እለምናለሁ፤ የተሻለ ለመሥራት እፈልጋለሁ።

***የቤቱ ኃላፊ አባወራ ወይም ወይዘሮ እንዲህ ሊሉ ይችላሉ፤***

በተለይ ልጆቼን፣ አገልጋዮቼንና ባለቤቴን ለእግዚአብሔር ክብር በታማኝነት እንዳልመራኋቸው በፊትዎ እናዘዛለሁ። ተራግሜአለሁ። ጨዋነት በጎደላቸው ቃላትና ድርጊቶች መጥፎ ምሳሌ ሆኜአለሁ። ባልንጀራዬን ጎድቻለሁ፤ ስለ እርሱም ክፉ ተናግሬአለሁ፤ ከተገቢው ክፍያ በላይ ተቀብዬአለሁ፤ ደረጃቸው ያነሰ ሸቀጦችን ሸጭአለሁ። ከተከፈለበት ያነሰ ነገር ሰጥቼአለሁ።
[የተጸጸተው ሰው ከእግዚአብሔር ትእዛዛት በተቃራኒው ያደረጋቸውን ሌሎች ነገሮችንና የገዛ ራሱን ይዞታ ይናዘዝ።]
ነገር ግን አንድ ሰው የእነዚህ ወይም ከዚህ የሚበልጡ ኃጢአቶች ሸክም ከብዶት ካልተሰማው ራሱን ማስጨነቅ ወይም ሌሎች ኃጢአቶችን መፈለግ ወይም መፍጠር እና በዚህም የኃጢአት ኑዛዜን የሚያሰቃይ ማድረግ የለበትም። በዚያ ፈንታ የሚያውቃቸውን አንድ ወይም ሁለት መጥቀስ ይገባዋል፤ በተለይ መራገሜን እናዘዛለሁ፤ ተገቢ ያልሆኑ ቃላትን ተጠቅሜአለሁ፤ ይህንን ወይም ያንን ቸል ብያለሁ፤ ወዘተ ያ ይበቃ።
ነገር ግን (የሚቻል ባይመስልም) ምንም ነገር ጨርሶ ካላወቅህ ምንም የተለየ ነገር አትጥቀስ፤ ነገር ግን የአናዛዡ ፊት ለእግዚአብሔር ያስታወቅኸውን አጠቃላይ ኑዛዜ ይቅርታ ተቀበል።

***ከዚያ አናዛዡ እንዲህ ይላሉ፤***

እግዚአብሔር ይማርህ፤ እምነትህንም ያጠንክርልህ፤ አሜን።

***በተጨማሪ፤***

የእኔ ይቅርታ የእግዚአብሔር ይቅርታ እንደሆነ ታምናለህ?

አዎን ውድ አናዛዤ።

***ከዚያ እንዲህ ይበሉ፤***

እንደ እምነትህ ይሁንልህ። እኔም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ትእዛዝ ኃጢአትህን በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ይቅር ብዬሃለሁ። አሜን። በሰላም ሂድ።

አናዛዡ ከፍተኛ የሕሊና ሸክም ያለባቸውን ወይም ያዘኑትንና የተጨነቁትን የሚያጽናናባቸውና እምነታቸውን የሚያበረታባቸውን ተጨማሪ ምንባባት ያውቃል። ይህ አጠቃላይ የኃጢአት ኑዛዜ መልክ እንዲሆን ብቻ የታቀደ ነው።

## *የመክፈቻዎቹ ሥልጣን*

***የመክፈቻዎቹ ሥልጣን ምንድን ነው?***

*የመክፈቻዎቹ ሥልጣን ንስሐ የሚገቡ ኃጢአተኞችን ኃጢአት ይቅር እንድትል፣ ነገር ግን ንስሐ እስካልገቡ ድረስ ንስሐ ያልገቡትን ኃጢአታቸውን እንድትይዝ በምድር ላይ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያኑ የሰጣት ያ ልዩ ሥልጣን ነው።*

***ይህ የት ተጽፏል?***

*ይህ ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ በምዕራፍ ሃያ የጻፈው ነው፡- ኢየሱስ በደቀ መዛሙርቱ ላይ እፍ አለባቸውና፣ ‹‹መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ። ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል›› አለ [ዮሐንስ 20፡22-23]።*

***አንተ በእነዚህ ቃላት መሠረት ምን ታምናለህ?***

*የተጠሩቱ የክርስቶስ አገልጋዮች በእርሱ መለኮታዊ ሥልጣን እንደሚያደርጉብን፣ በተለይ ንስሐ ያልገቡ ኃጢአተኞችን ከክርስቲያን ማኅበረ ምእመናን በግልጽ ሲያስቀሩና ኃጢአታቸውን የሚናዘዙትንና የተሻለ ማድረግ የሚፈልጉትን ከኃጢአት ሲፈቱ ውድ ጌታችን ክርስቶስ ራሱ በእኛ እንዳደረገ ያህል፣ ይህ በትክክል በሰማይ እንኳ ተቀባይነት ያለውና ርግጠኛ መሆኑን እኔ አምናለሁ።*

### *269. ክርስቶስ በምድር ላለችው ቤተ ክርስቲያኑ ምን ልዩ ሥልጣን ሰጥቷታል?*

ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያኑ ኃጢአትን ይቅር የማለት ወይም ይቅርታን የመያዝ ሥልጣን ሰጥቷታል።

893. **ማቴዎስ** 18፡18 እውነት እላችኋለሁ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፣ በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል።

894. **ዮሐንስ** 20፡22-23 [ኢየሱስ] እፍ አለባቸውና እንዲህ አላቸው፤ ‹‹*መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ። ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል።*››

### *270. ይህ ሥልጣን የመክፈቻዎቹ ሥልጣን የተባለው ለምንድን ነው?*

ይህ ሥልጣን ኃጢአትን ይቅር በማለት ሰማይን እንደሚከፍት፣ ወይም ኃጢአትን ይቅር ባለማለት ሰማይን እንደሚዘጋ ቁልፍ ይሠራል።

895. ***ማቴዎስ*** 16፡19 *የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ።*

### *271. የመክፈቻዎቹ ሥልጣን ወንጌልን ከማወጅ ጋር የሚዛመደው እንዴት ነው?*

የመክፈቻዎቹ ሥልጣን ከእግዚአብሔር የተሰጠ ወንጌልን ከግለ ሰቡ ጋር የማዛመድ ልዩ *መንገድ* ነው። ‹‹እግዚአብሔር በጸጋው ከበቂ በላይ ቸር ነው፡- *መጀመሪያ*፣ የኃጢአት ይቅርታ በሚሰበክበት በመላው ዓለም ላይ በሚነገረው *ቃል* አማካይነት። ይህ የተለየ የወንጌል ሥልጣን ነው። ሁለተኛ፣ በጥምቀት አማካይነት። ሦስተኛ፣ በመሠዊያው ቅዱስ ምሥጢር አማካይነት። አራተኛ፣ በመክፈቻዎቹ ሥልጣን አማካይነት። ደግሞም በወንድሞች የጋራ ንግግርና መጽናናት *አማካይነት*›› (Smalcald Articles III IV).

896. ***ማቴዎስ*** 18፡20 *ሁለት ወይም ሦስት* በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና።

897. ***ማቴዎስ*** 28፡18-20 ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፡- ‹‹*ሥልጣን ሁሉ* በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፣ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ *መዛሙርት* አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ *ጋር* ነኝ።››

898. **1ጴጥሮስ** 2፡9 እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉሥ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ።

### *272. ይቅር የሚባሉ (ከኃጢአት የሚፈቱ) እነማን ናቸው?*

ንስሐ የሚገቡና ይቅርታ የሚለምኑ ይቅር ይባላሉ።

899. **የሐዋርያት *ሥራ*** 3፡19-20*ሀ* እንግዲህ በጌታ ፊት የመጽናናት ዘመን እንድትመጣላችሁ አስቀድሞም ለእናንተ የተመረጠውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲልክላችሁ፣ ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሐ ግቡ ተመለሱም።

### *273. በኃጢአት መፈታት አዋጅ የተሰጠውን ይቅርታ ማን ይቀበላል?*

ንስሐ የሚገቡ አማኞች ብቻ ይቅርታውን ይቀበላሉ።

900. ***መዝሙር*** 32፡5 *ኃጢአቴን ለአንተ አስታወቅሁ*፣ በደሌንም አልሸፈንሁም፤ ‹‹*ለእግዚአብሔር መተላለፌን እነግራለሁ*›› አልሁ፤ አንተም የልቤን ኃጢአት ተውህልኝ።

*274. ንስሐ የሚገቡ አማኞች እነ ማን ናቸው?*

ንስሐ የሚገቡ አማኞች ስለ ኃጢአታቸው የሚያዝኑ (ጸጸት) እና አዳኛቸው አድርገው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ (እምነት) የሚያምኑ ናቸው፡፡

901. ***መዝሙር*** 51፡17 የእግዚአብሔር *መሥዋዕት* የተሰበረ *መንፈስ* ነው፤ የተሰበረውንና የተዋረደውን ልብ እግዚአብሔር አይንቅም፡፡

902. ***የሐዋርያት ሥራ*** 16፡31 በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን ትድናለህም፡፡

*ማስታወሻ፡-* በምሥጢር ንስሐ የማይገቡ ኃጢአተኞች (ግብዞች) ከኃጢአት የመፈታቱ አዋጅ በእውነት የሚሰጣቸውን ይቅርታ አይቀበሉም፡፡

*275. ይቅር የማይባሉ እነማን ናቸው?*

ንስሐ የማይገቡ ኃጢአተኞች፣ በሌላ አባል ስለ ኃጢአታቸው የማያዝኑና በኢየሱስ ክርስቶስ የማያምኑ፣ ንስሐ እስካልገቡ ድረስ ይቅር አይባሉም፡፡

903. ***ማቴዎስ*** 18፡17 እነርሱን ባይሰማ ለቤተ ክርስቲያን ንገራት፤ ደግሞም ቤተ ክርስቲያንን ባይሰማት እንደ አረመኔና እንደ ቀራጭ ይሁንልህ፡፡

*276. የንስሐ አስፈላጊ ውጤት ምንድን ነው?*

‹‹በዚህም የንስሐ ፍሬ የሆኑ መልካም *ሥራዎች* መከተል አለባቸው›› (Augsburg Confession XII 6).

904. ***ማቴዎስ*** 3፡8 እንግዲህ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ፡፡

905. ***ዮሐንስ*** 8፡11 ሂጂ ከአሁንም ጀምሮ ደግመሽ ኃጢአት አትሥሪ፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ፡-* ቀራጩ ዘኬዎስ (***ሉቃስ*** 19፡1-10)፡፡

*277. ቤተ ክርስቲያን የመክፈቻዎቹን ሥልጣን በአደባባይ እንዴት ተግባራዊ ታደርጋለች?*

የክርስቲያኑ ማኅበረ ምእመናን በእግዚአብሔር ትእዛዝ፣ በስሙና ማኅበረ ምእመናኑን በመወከል የመክፈቻዎቹን ሥልጣን በአደባባይ እንዲተገብሩ ቀሳውስትን ይጠራል፡፡ የቅስና ሥልጣን መለኮታዊ ተቋም ነው፡፡

906. ***ኤፌሶን*** 4፡11 እርሱም [ክርስቶስ] አንዳንዶቹ ሐዋርያት፣ ሌሎቹም ነቢያት፣ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፣ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፡፡

907. ***የሐዋርያት ሥራ*** 20፡28 በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፡፡

908. **1ቆሮንቶስ** 4፡1 እንዲሁ ሰው እኛን እንደ ክርስቶስ ሎሌዎችና እንደ እግዚአብሔር ምሥጢር መጋቢዎች ይቍጠረን፡፡

909. **2ቆሮንቶስ** 2፡10 … ይቅር ያልሁትን ስለ እናንተ በክርስቶስ ፊት ይቅር ብዬአለሁ፡፡

*278. ለቅስና ሥልጣን መታሰብ ያለበት ማን ነው?*

ማኅበራኑ ምእመናን ቀሳውስታቸው እንዲሆኑ በግልና በመንፈሳዊ ረገድ ጥሩ ብቃት ያላቸው ወንዶችን መጥራት አለባቸው፡፡

‹‹በትክክል ካልተጠራ በቀር ማንም በቤተ ክርስቲያን በይፋ ማስተማር ወይም ቅዱሳት ምሥጢራትን ማከናወን የለበትም ብለው የእኛ አብያተ ክርስቲያናት ያስተምራሉ›› (Augsburg Confession XIV).

910. **1ጢሞቴዎስ** 3፡1-2 *ማንም ኤጲስ ቆጶስነትን [ቅስናን] ቢፈልግ መልካምን ሥራ ይመኛል የሚለው ቃል የታመነ ነው። እንግዲህ ኤጲስ ቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል፤ የማይነቀፍ፣ የአንዲት ሚስት ባል፣ ልከኛ፣ ራሱን የሚገዛ፣ እንደሚገባው የሚሠራ፣ እንግዳ ተቀባይ፣ ለማስተማር የሚበቃ።*

911. **2ጢሞቴዎስ** 2፡2 *ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ።*

912. **2ጢሞቴዎስ** 2፡15 *የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ፣ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ።*

913. **1ቆሮንቶስ** 14፡33-34 *በቅዱሳንም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እንዲህ ነው። ሴቶች በማኅበር ዝም ይበሉ፤ ሕግ ደግሞ እንደሚል እንዲገዙ እንጂ እንዲናገሩ አልተፈቀደላቸውምና።*

*ማስታወሻ፦* 1ጢሞቴዎስ 2፡11-14ን *ደግሞ ተመልከቱ።*

## የቤተ ክርስቲያን ተግሳጽና ውግዘት

### *279. በግልጽ ንስሐ ባልገባ ኃጢአተኛ ላይ እርምጃ ሲወሰድ ሊደረግ የሚገባው ትልቅ ጥንቃቄ ምንድን ነው?*

የክርስቲያኑ ማኅበረ ምእመናን የቤተ ክርስቲያን ተግሳጽን በፍቅርና በትዕግሥት መፈጸም አለበት። *‹‹ወንድምህም ቢበድልህ፣ ሄደህ አንተና እርሱ ብቻችሁን ሆናችሁ ውቀሰው፡ ፡ ቢሰማህ፣ ወንድምህን ገንዘብ አደረግኸው፤ ባይሰማህ ግን በሁለት ወይም በሦስት ምስክር አፍ ነገር ሁሉ እንዲጸና፣ ዳግመኛ አንድ ወይም ሁለት ከአንተ ጋር ውሰድ፤ እነርሱንም ባይሰማ፣ ለቤተ ክርስቲያን ንገራት፤ ደግሞም ቤተ ክርስቲያንን ባይሰማት እንደ አረመኔና እንደ ቀራጭ ይሁንልህ››* (**ማቴዎስ** 18፡15-17)።

914. *ገላትያ* 6፡1-2 *ወንድሞች ሆይ፣ ሰው በማናቸውም በደል ስንኳ ቢገኝ፣ መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ እንደዚህ ያለውን ሰው በየውሃት መንፈስ አቅኑት፤ አንተ ደግሞ እንዳትፈተን ራስህን ጠብቅ። ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም፤ እንዲሁም የክርስቶስን ሕግ ፈጽሙ።*

915. ***ኤፌሶን*** 4፡2-3 *በትሕትና ሁሉና በየዋህነት በትዕግሥትም እርስ በርሳችሁ በፍቅር ታገሡ፤ በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ።*

### *280. ማኅበረ ምእምናኑ በመጨረሻ በግልጽ ንስሐ ያልገቡ ኃጢአተኞችን ምን ማድረግ አለበት?*

ክርስቲያኑ ማኅበረ ምእመናን በግልጽ ንስሐ ያልገቡ ኃጢአተኞችን ማስወገድ አለበት (ውግዘት)

916. **1ቆሮንቶስ** 5፡13 *በውጭ ባሉቱ ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል። ‹‹ክፉውን ከመካከላችሁ አውጡት።››*

### *281. ማኅበረ ምእመናኑ በግልጽ ንስሐ ያልገቡ ኃጢአተኞችን በምን ሥልጣን ያወግዛል?*

ውግዘት በሰማይ እንኳ ውድ ጌታችን ክርስቶስ ራሱ እንዳደረገብን ያህል በክርስቶስ የተፈቀደና በትክክል ተቀባይነት ያለውና ርግጠኛ ነው።

917. **ማቴዎስ** 18፡18 እውነት እላችኋለሁ፣ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል።

### *282. ማኅበረ ምእምናኑ አንድን ኃጢአተኛ ባወገዘ ጊዜ የተጠራው የክርስቶስ አገልጋይ ተግባር ምንድን ነው?*

የተጠራው የክርስቶስ አገልጋይ የማኅበረ ምእመናኑን ውሳኔ መፈጸም አለበት፤ ይኸውም፣ የተወገዘውን ሰው ከአንድ ክርስቲያን መብቶችና ልዩ ጥቅሞች ማስቀረት አለበት።

### *283. የውግዘት ዐላማ ምንድን ነው?*

ውግዘት ኃጢአተኛውን ለመቅጣት የታሰበ አይደለም፤ ነገር ግን፣

ሀ. እርሱን ወይም እርሷን ወደ ንስሐና እምነት ለመምራት ነው፤

918. **ማቴዎስ** 12፡20 የተቀጠቀጠ ሸምበቆን አይሰብርም፤ የሚጤስን የጥዋፍ ክርንም አያጠፋም።

919. **የሐዋርያት ሥራ** 3፡19 ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሐ ግቡ ተመለሱም።

ለ. ሌሎችን ወደ ኃጢአት ከመምራት እርሱን ወይም እርሷን ለመከልከል ነው።

920. **ማቴዎስ** 18፡6 በእኔም ከሚያምኑ ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ሁሉ፣ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባሕር መስጠም ይሻለው ነበር።

921. **1ቆሮንቶስ** 5፡6 መመካታችሁ መልካም አይደለም። ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ እንደሚያቦካ አታውቁምን?

### *284. ንስሐ ለሚገባ ውጉዝ ኃጢአተኛ የአንድ ማኅበረ ምእምናን ተግባር ምንድን ነው?*

ማኅበረ ምእመናኑ ማንኛውንም ንስሐ የሚገባ የተወገዘ ሰውን ይቅር ማለትና እርሱን ወይም እርሷን መልሰው ወደ ሙሉ ኅብረት መቀበል አለበት።

922. **2ቆሮንቶስ** 2፡7-8 እንደዚህ ያለው ከልክ በሚበዛ ሐዘን እንዳይዋጥ፣ ይልቅ ተመልሳችሁ ይቅር ማለትና ማጽናናት ይገባችኋል። ስለዚህ ከእርሱ ጋር ፍቅርን እንድታጸኑ እለምናችኋለሁ።



# የመሠዊያው ቅዱስ ምሥጢር

## I. የመሠዊያው ቅዱስ ምሥጢር ባሕርይ

> ***የመሠዊያው ቅዱስ ምሥጢር ምንድን ነው?***
> **የመሠዊያው ቅዱስ ምሥጢር እንድንበላውና እንድንጠጣው ለእኛ ለክርስቲያኖች በራሱ በክርስቶስ የተመሠረተ በኅብስቱና በወይኑ ሥር የሚገኝ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን እውነተኛ ሥጋና ደም ነው።**
>
> ***ይህ የት ተጽፎአል?***
> *ቅዱሳን ወንጌላውያን ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ፣ እንዲሁም ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ጽፈዋል፦*
> *ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተያዘበት ሌሊት እንጀራን አንሥቶ ባረከ፤ ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና፦ ‹‹እንካችሁ፣ ብሉ ይህ ስለ እናንተ የተሰጠ ሥጋዬ ነው። ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት›› አለ።*
> *እንዲሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን ደግሞ አንሥቶ አመሰገነና ሰጣቸው። እንዲህም አለ፦ ‹‹ሁላችሁም ከእርሱ ጠጡ፤ ይህ ጽዋ ለኃጢአት ይቅርታ ስለ እናንተ በሚፈሰው በደሜ የሚሆን ዐዲስ ኪዳን ነው። ይህን በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ለመታሰቢያዬ አድርጉት።››*

***285. ለመሠዊያው ቅዱስ ምሥጢር የተሰጡ አንዳንድ ሌሎች ስሞች ምንድን ናቸው?***

ይህ ቅዱስ ምሥጢር የጌታ እራት፣ የጌታ ማዕድ፣ ቅዱስ ቍርባን፣ እንጀራን መቍረስ፣ እንዲሁም ሥጋ ወደሙ ተብሎም ተጠርቷል።

923. **1ቆሮንቶስ** 11፡20 እንግዲህ አብራችሁ ስትሰበሰቡ የምትበሉት የጌታ እራት አይደለም።
924. **1ቆሮንቶስ** 10፡21 የጌታን ጽዋና የአጋንንትን ጽዋ ልትጠጡ አትችሉም።
925. **1ቆሮንቶስ** 10፡16 የምንባርከው የበረከት ጽዋ ከክርስቶስ ደም ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? የምንቈርሰውስ እንጀራ ከክርስቶስ ሥጋ ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን?
926. **የሐዋርያት ሥራ** 2፡42 በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቍረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር።
927. **ማቴዎስ** 26፡26 ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና፦ ‹‹እንካችሁ፣ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው›› አለ።

ማስታወሻ፦ ሥጋ ወደሙ ‹‹ምስጋና መስጠት›› ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ነው።

### *286. የመሠዊያውን ቅዱስ ምሥጢር ማን መሠረተ?*

እውነተኛ አምላክና እውነተኛ ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ቅዱስ ምሥጢር መሠረተ፡፡

928. **1ቆሮንቶስ** 11፡23-24 ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና፤ ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠባት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንሥቶ አመሰገነ፤ ቈርሶም፣ ‹‹ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት›› አለ፡፡

### *287. በዚህ ቅዱስ ምሥጢር ክርስቶስ ምን ይሰጠናል?*

በዚህ ቅዱስ ምሥጢር ክርስቶስ ለኃጢአት ስርየት የገዛ ራሱን እውነተኛ ሥጋና ደም ይሰጠናል፡፡

929. **ማቴዎስ** 26፡26፣28 ‹‹ይህ ሥጋዬ ነው … ይህ ደሜ ነው፡፡››

### *288. እነዚህ የክርስቶስ ቃሎች ሥዕላዊ ቋንቋ አለመሆናቸውን መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት ግልጽ ያደርገዋል?*

በቅዱስ ምሥጢሩ ያሉት የክርስቶስ ቃሎች በተለይ በዚህ ምክንያት እንደተነገሩ እውነት መሆናቸውን መቀበል ይገባል፡፡

*ሀ.* እነዚህ ቃሎች የኪዳን ቃሎች ናቸው፣ ያ ሰው አንዴ ከሞተ የአንድ ተራ ሰው የመጨረሻ ኑዛዜና ኪዳን እንኳ ሊለወጥ አይችልም፤

930. **1ቆሮንቶስ** 11፡25 ‹‹ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን ዐዲስ ኪዳን ነው፡፡››

931. **ገላትያ** 3፡15 የሰው ስንኳ ቢሆን እርግጠኛውን ኪዳን [ኑዛዜ] ማንም አይንቅም ወይም አይጨምርበትም፡፡

*ማስታወሻ፡-* **ዕብራውያን** 9፡15-22ን ደግሞ አነጻጽሩ፡፡

*ለ.* በቅዱስ ምሥጢሩ ኅብስቱና ወይኑ በክርስቶስ ሥጋና ደም አንድነት ወይም ኅብረት ያላቸው እንደ ሆኑ የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ ያስተምራል፡፡

932. **1ቆሮንቶስ** 10፡16 የምንባርከው የበረከት ጽዋ ከክርስቶስ ደም ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? የምንቈርሰውስ እንጀራ ከክርስቶስ ሥጋ ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን?

*ሐ.* ቅዱስ ምሥጢሩን ያላግባብ የሚጠቀሙ በኅብስቱና በወይኑ ላይ ሳይሆን በክርስቶስ ሥጋና ደም ላይ ኃጢአት እንደሚሠሩ የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ ያስተምራል፡፡

933. **1ቆሮንቶስ** 11፡27፣29 ስለዚህ ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት፡፡ … ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና ይጠጣልምና፡፡

### *289. በቅዱስ ምሥጢሩ ያሉት የሚታዩት ነገሮች ምንድን ናቸው?*

የሚታዩት ነገሮች ኅብስትና ወይን ናቸው፡፡

934. **ማቴዎስ** 26፡26-27 ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ … ጽዋንም አንሥቶ፡፡

*ማስታወሻ፡-* በመጽሐፍ ቅዱስ ‹‹የወይኑ ፍሬ›› (**ሉቃስ** 22፡18) የወይን ጭማቂ ሳይሆን፣ ወይን ማለት ነው፡፡ **1ቆሮንቶስ** 11፡21ን ደግሞ ተመልከቱ፡፡

***290. ኅብስቱና ወይኑ ከዚህ ወዲህ በዚያ እስከማይኖሩ ድረስ፣ በቅዱስ ምሥጢሩ የክርስቶስ ሥጋና ደም ኅብስቱንና ወይኑን ይተካሉን?***

አይተኩም፤ ኅብስትና ወይን በቅዱስ ምሥጢሩ እንዳሉ ይቀጥላሉ፡፡

935. **1ቆሮንቶስ** 11፡26 ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፣ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና፡፡

***291. ታዲያ በቅዱስ ምሥጢሩ ያሉት ኅብስቱና ወይኑ እንዴት የክርስቶስ ሥጋና ደም ይሆናሉ?***

በቅዱስ ምሥጢሩ ያሉት ኅብስቱና ወይኑ በቅዱስ ምሥጢራዊ አንድነት የክርስቶስ ሥጋና ደም ናቸው፡፡ ክርስቶስ በቃሉ ኃይል በተቀደሰው (በተባረከው) ኅብስትና ወይን፣ ከእርሱ ጋር፣ እንዲሁም በእርሱ ሥር ሥጋውንና ደሙን ይሰጣል፡፡

936. **1ቆሮንቶስ** 10፡16 የምንባርከው የበረከት ጽዋ ከክርስቶስ ደም ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? የምንቈርሰውስ እንጀራ ከክርስቶስ ሥጋ ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን?

292. **ቢያምኑ ወይም ባያምኑ ቈራቢዎች ሁሉ በቅዱስ ምሥጢሩ ሥጋውን ደሙን ይቀበላሉን?**

አዎ፣ ምክንያቱም ቅዱስ ምሥጢሩ በእኛ እምነት ሳይሆን፣ በክርስቶስ ቃል ላይ ይመሠረታል፡፡

937. **1ቆሮንቶስ** 11፡27 ስለዚህ ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት፡፡

*ማስታወሻ፡-* ክርስቶስ፣ ‹‹እንካችሁ፣ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው … ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ›› ስላለ፣ ቈራቢዎች ሁሉ የቅዱስ ምሥጢሩን ሁለቱንም ክፍሎች መቀበል አለባቸው (**ማቴዎስ** 26፡26-27)፡፡

***293. በቅዱስ ምሥጢሩ ያሉት የክርስቶስ ሥጋና ደም ስለ ሕያዋንና ሙታን ኃጢአት እንደ ገና ለእግዚአብሔር የሚሠዉ ናቸውን?***

አይደሉም፤ በቅዱስ ምሥጢሩ ያሉት የክርስቶስ ሥጋና ደም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በመስቀል ላይ ለእግዚአብሔር የቀረበው ፍጹም መሥዋዕት ናቸውና አሁን ይህ መሥዋዕት ለእኛ ካስገኛቸው በረከቶችና ጥቅሞች ሁሉ ጋር በቅዱስ ምሥጢሩ ለእኛ ታድለዋል፡፡

938. **1ቆሮንቶስ** 5፡7 ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዶአልና፡፡

939. ***ዕብራውያን*** 10፡14 አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም አድርጎአቸዋልና፡፡

940. ***ዕብራውያን*** 10፡18 የእነዚህም ስርየት ባለበት ዘንድ ከዚህ ወዲህ ስለ ኃጢአት ማቅረብ የለም፡፡

*ማስታወሻ፡- መሠዊያ መሥዋዕት የሚቀርብበት ስፍራ ስለ ሆነ ስለ ‹‹መሠዊያው ቅዱስ ምሥጢር›› እንናገራለን፡፡ ኢየሱስ ለዓለም ኃጢአት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሥጋውንና ደሙን ሠውቶአል፡፡ እስከ ዘመኑ ፍጻሜ ድረስ ይህንኑ ሥጋና ደም በመሠዊያው ቅዱስ ምሥጢር ያድላል፡፡*

### *294. ‹‹ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት›› ሲል ክርስቶስ ምንን ያዛል?*

ክርስቶስ በእነዚህ ቃሎች ቅዱስ ምሥጢሩ የሚያድነው ሞቱና የበረከቶቹ ሁሉ ሕያው እወጃና ዕደላ ተደርጎ በቤተ ክርስቲያን እስከ ዘመኑ ፍጻሜ ድረስ እንዲከበር ያዛል።

941. **1ቆሮንቶስ** 11፡26 ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስከሚመጣ ድረስ ሞቱን ትናራላችሁና።

### *295. ቅዱስ ምሥጢሩን አዘውትረን ለምን እንቀበላለን?*

በእነዚህ ምክንያቶች ቅዱስ ምሥጢሩን አዘውትረን እንቀበላለን፤

*ሀ. ‹‹ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት››* በማለት ክርስቶስ ያዘናል፤ ወይም በጥብቅ ይጋብዘናል፤

ለ. ‹‹ለኃጢአት ስርየት ለእናንተ የተሰጠና የፈሰሰ›› የሚሉት ቃሎቹ ተስፋ እና ታላላቅ በረከቶችንም ይሰጡናል።

942. **ማቴዎስ** 11፡28 እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፣ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም አሳርፋችኋለሁ።

ሐ. የኃጢአታችንን ይቅርታና ለዐዲስና ቅዱስ ሕይወት ብርታት ያስፈልገናል።

943. **ዮሐንስ** 15፡5 እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ። ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል።

*ማስታወሻ፦* በአዲስ ኪዳን ቅዱስ ምሥጢሩ አልፎ አልፎ የሚደረግ ተጨማሪ ነገር ሳይሆን፣ መደበኛና ዋና የማኅበረ ምእመናን የአምልኮ ሁኔታ ነበር (**የሐዋርያት ሥራ** 2፡42፤ 20፡7፤ **1ቆሮንቶስ** 11፡20፣33)። በዘመነ ተሐድሶ የእኛ አብያተ ክርስቲያናት ቅዱስ ምሥጢሩን ‹‹በእያንዳንዱ የጌታ ቀንና በሌሎቹ በዓላት›› (Apology XXIV 1) ያከብሩ ነበር።

## II. የመሠዊያው ቅዱስ ምሥጢር ጥቅም

> *የዚህ መብላትና መጠጣት ጥቅም ምንድን ነው?*
> ‹‹ለኃጢአት ስርየት ስለ እናንተ የተሰጠና የፈሰሰ›› የሚሉት እነዚህ ቃላት፣ በቅዱስ ምሥጢሩ የኃጢአት ይቅርታ፣ ሕይወት፣ እንዲሁም ድነት በእነዚህ ቃላት አማካይነት እንደ ተሰጡን ያሳዩናል። የኃጢአት ይቅርታ ባለበት ሕይወትና ድነት ደግሞ አለና።

### *296. በቅዱስ ምሥጢሩ የተሰጠው ጥቅም ምንድን ነው?*

*ሀ.* የቅዱስ ምሥጢሩ ዋና በረከት የክርስቶስ ሥጋና ደም በመስቀል ላይ ያስገኙልን የኃጢአት ይቅርታ ነው። (የጌታ እራት የጸጋ መሣሪያ ነው።)

944. **ማቴዎስ** 26፡28 ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።

945. **1ጴጥሮስ** 1፡18-19 ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከከንቱ ኑሮአችሁ በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በወርቅ ሳይሆን ነውርና እድፍ እንደሌለው እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደ ተዋጃችሁ ታውቃላችሁ።

946. **ቆላስይስ** 1፡22 እናንተንም ነውርና ነቀፋ የሌላችሁና ቅዱሳን አድርጎ በፊቱ ያቀርባችሁ ዘንድ፣ … አሁን በሥጋው ሰውነት በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ።

947. **1ዮሐንስ 1፡7** የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል፡፡

ለ. እግዚአብሔር ከይቅርታ ጋር ሌሎች በረከቶችንም ይሰጠናል፤ ይኸውም፣ ‹‹ሕይወትና ድነት›› ነው፡፡

‹‹ቅዱስ ምሥጢሩን ከእርሱ ልንሸሽ እንደሚገባ እንደ ጎጂ ነገር አድርገን መቊጠር የለብንም፤ ነገር ግን እንደ ንጹሕ፣ ለጤና ጠቃሚ፣ የሚረዳ፣ መድኃኒትና በነፍስም በሥጋም ሕይወት የሚሰጥ አድርገን ልንቈጥረው ይገባናል፡፡ ምክንያቱም ነፍስ ስትፈወስ አካልንም ይጠቅማል›› (ትልቁ የክርስትና ትምህርት V 68).

‹‹ስለ ሕያው ክርስቶስ መገኘት እንናገራለን፣ ‹ሞትም ወደ ፊት እንዳይገዛው› እናውቃለንና [ሮሜ 6፡9] (Apology X 57).

948. **ሮሜ 6፡8-9** ከክርስቶስ ጋር ከሞትን ከእርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት እንድንኖር እናምናለን፤ ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቶ ወደ ፊት እንዳይሞት ሞትም ወደ ፊት እንዳይገዛው እናውቃለንና፡፡

949. **ሮሜ 8፡31-32** እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል? ለገዛ ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለ ሁላችን አሳልፎ የሰጠው ያው ከእርሱ ጋር ደግሞ ሁሉን ነገር እንዲያው እንዴት አይሰጠንም?

ሐ. በቅዱስ ምሥጢሩ ክርስቶስ በኃጢአትና በሲኦል ላይ ድልንና በእርሱ ለሚገኘው ዐዲስ ሕይወት ብርታትን ይሰጣል፡፡

950. **ሮሜ 8፡10** ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ቢሆን ሰውነታችሁ በኃጢአት ምክንያት የሞተ ነው፤ መንፈሳችሁ ግን በጽድቅ ምክንያት ሕያው ነው፡፡

951. **1ጴጥሮስ 2፡24** ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፣ እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፤ በመገረፉ ቊስል ተፈወሳችሁ፡፡

መ. ክርስቲያኖች ይህን ቅዱስ ምሥጢር በአንድ ላይ ሲካፈሉ፣ ስለ ክርስቶስና በወንጌሉ እውነት ስላለ አንድነት የከበረ ይፋዊ ምስክርነት ይሰጣሉ፡፡

952. **1ቆሮንቶስ 10፡17** አንድ እንጀራ ስለ ሆነ እኛ ብዙዎች ስንሆን አንድ ሥጋ ነን፤ ሁላችን ያን አንዱን እንጀራ እንካፈላለንና፡፡

953. **1ቆሮንቶስ 11፡26** ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፣ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና፡፡

*ማስታወሻ፡- **ዕብራውያን*** 12፡22-24ን ደግሞ ተመልከቱ፡፡

## III. የመሠዊያው ቅዱስ ምሥጢር ኃይል

***አካላዊ መብላትና መጠጣት እንደዚህ ያሉ ታላላቅ ነገሮችን እንዴት ማድረግ ይችላሉ?***

‹‹ስለ ኃጢአት ይቅርታ ለእናንተ የተሰጠና የፈሰሰ›› የሚሉት እዚህ የተጻፉት ቃላት እንጂ፣ በእርግጥ መብላትና መጠጣት ብቻ እነዚህን ነገሮች አያደርጉም፡፡ ከአካላዊ መብላትና መጠጣት ጋር፣ እነዚህ ቃላት በቅዱስ ምሥጢሩ ዋና ነገር ናቸው፡፡ እነዚህን ቃላት የሚያምን ሁሉ በትክክል እነርሱ ‹‹የኃጢአት ይቅርታ›› የሚሉት አለው፡፡

### *297. በአካላዊ መብላትና መጠጣት አማካይነት ይቅርታ፣ ሕይወት፣ እንዲሁም ድነት እንዴት ሊገኙ ይችላሉ?*

‹‹እዚህ ላይ እንደ ገና የእኛ አታላይ መናፍስት በከፍተኛ ትምህርታቸውና ጥበባቸው ራሳቸውን ያወለጋግዳሉ፡፡ ‹ኀብስትና ወይን እንዴት የኃጢአት ይቅርታ ሊያስገኙ ወይም እምነትን ሊጠነክሩ ይችላሉ?› እያሉ ይጮኻሉ፤ ይለፈልፋሉ፡፡ አታላዮቹ መናፍስት ኀብስት በራሱ ኀብስት ስለ ሆነ ይህንን ያደርጋል እንደማንል ነገር ግን የክርስቶስ ሥጋና ደም ስለ ሆኑት እና በቃሉ ስለ ታጀቡት ኀብስትና ወይን እንደምንናገር ሰምተዋል፤ ያውቃሉም፡፡›› (ትልቁ የክርስትና ትምህርት V 28). የክርስቶስ የተስፋ ቃሎች እነዚህን ስጦታዎች በቅዱስ ምሥጢሩ ውስጥ አስቀምጠዋቸዋል፤ አማኙም በእምነት አማካይነት እዚያ ይቀበላቸዋል፡፡

### *298. ቅዱስ ምሥጢሩን የሚበላና የሚጠጣ ማንኛውም ሰው ይቅርታን፣ ሕይወትን፣ እንዲሁም ድነትን ደግሞ ይቀበላልን?*

ይቅርታ፣ ሕይወት፣ እንዲሁም ድነት በቅዱስ ምሥጢሩ የጌታን ሥጋ ለሚበሉና ደሙን ለሚጠጡ ሁሉ በእውነት ይሰጣሉ፤ ነገር ግን እዚያ የሚሰጡትን በረከቶች በእምነት ብቻ መቀበል እንችላለን፡፡

954. **ሉቃስ** 1፡45 ከጌታ የተነገረላት ቃል ይፈጸማልና ያመነች ብፅዕት ናት፡፡

955. **ሉቃስ** 11፡27-28 ‹‹የተሸከመችህ ማኅፀንና የጠባሃቸው ጡቶች ብፁዓን ናቸው አለችው፡፡ እርሱ ግን አዎን ብፁዓንስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚጠብቁት ናቸው!›› አለ፡፡

*ማስታወሻ፡-* የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል ‹‹መጠበቅ›› ወይም ‹‹መታዘዝ›› እርሱን ማመን ወይም መታመን ነው፡፡ ‹ጻድቅ በእምነት ይኖራል› ተብሎ እንደ ተጻፈ ‹‹የእግዚአብሔር ጽድቅ ከእምነት ወደ እምነት በ[ወንጌል] ይገለጣልና›› (**ሮሜ** 1፡17)፡፡

956. **1ቆሮንቶስ** 10፡3-5 ሁሉም ያን መንፈሳዊ መብል በሉ፣ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፤ ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ አለት ጠጥተዋልና ያም አለት ክርስቶስ ነበረ፡፡ እግዚአብሔር ግን ከእነርሱ በሚበዙት ደስ አላለውም፤ በምድረ በዳ ወድቀዋልና፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ፡-* ኢየሱስን በመዳሰስ ወይም በእርሱ በመዳሰስ በረከት ነበረ፤ እምነትም ተቀብሎታል (**ማቴዎስ** 9፡20-22፣ 27-29)፡፡

## IV. የሚገባ በመሆን ይህን ቅዱስ ምሥጢር በተገቢ ሁኔታ ስለ መቀበል

> ***የሚገባ ሆኖ ይህን ቅዱስ ምሥጢር ማን ይቀበላል?***
>
> *መጾምና ሥጋዊ መዘጋጀት በርግጥ ጥሩ ውጪአዊ ልምምድ ናቸው፡፡ ነገር ግን በእነዚህ ቃላት እምነት ያለው ያ ሰው በእውነት የሚገባውና በደንብ የተዘጋጀ ነው፡- ‹‹ለኃጢአት ስርየት ስለ እናንተ የተሰጠና የፈሰሰ፡፡ ››*
>
> *ነገር ግን እነዚህን ቃላት የማያምን ወይም የሚጠራጠራቸው ማንም የማይገባውና ያልተዘጋጀ ነው፤ ‹‹ስለ እናንተ›› የሚሉት ቃላት የሚያምኑ ልቦችን ሁሉ ይፈልጋሉና፡፡*

***299. ቅዱስ ምሥጢሩን የሚገባ ሆኖ መቀበል አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?***

በጣም አስፈላጊ ነው ምክንያቱም ቅዱስ ጳውሎስ በግልጽ እንዲህ ያስተምራል፡- ‹‹ስለዚህ ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት፡፡ ሰው ግን ራሱን ይፈትን፤ እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ ከጽዋውም ይጠጣ፤ ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና፤ ይጠጣልምና›› (**1ቆሮንቶስ** 11፡27-29)፡፡

***300. ቅዱስ ምሥጢሩን ከመቀበል በፊት መጾም አስፈላጊ ነውን?***

*መጾም ለፈቃድ ጥሩ ልምምድ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ለዚህ የተለዩ ጊዜያትን፣ ቦታዎችን፣ እንዲሁም ነገሮችን አያዝም፡፡*

957. **1ጢሞቴዎስ** 4፡8 *ሰውነትን ለሥጋዊ ነገር ማስለመድ ለጥቂት ይጠቅማልና እግዚአብሔርን መምሰል ግን ለነገር ሁሉ ይጠቅማል፡፡*
*ማስታወሻ፡-* **1ቆሮንቶስ** 9፡24-27*ን ደግሞ ተመልከቱ፡፡*

***301. የተገባን ሆነን ቅዱስ ምሥጢሩን የምንቀበለው መቼ ነው?***

በክርስቶስ ስናምንና፣ ‹‹ለኃጢአት ይቅርታ ስለ እናንተ የተሰጠና የፈሰሰ›› በሚሉት በእርሱ *ቃሎች* በምናምንበት ጊዜ የተገባን ሆነን እንቀበለዋለን፡፡

***302. አንድ ሰው የማይገባና ያልተዘጋጀ የሚሆነው መቼ ነው?***

‹‹ስለ እናንተ›› የሚሉት *ቃላት* ሁሉም ልቦች እንዲያምኑ ስለሚፈልጉ፣ አንድ ሰው እርሱ ወይም እርሷ የክርስቶስን *ቃሎች* በማያምን/በማታምን ወይም በሚጠራጠርበት ጊዜ የማይገባውና ያልተዘጋጀ ነው፡፡

***303. ቅዱስ ምሥጢሩን ከመቀበላችን በፊት ራሳችንን እንዴት መመርመር አለብን?***

የሚከተሉትን አድርገን እንደ ሆነ ራሳችንን *መመርመር* አለብን፤

ሀ. ስለ ኃጢአታችን ዐዝነን እንደ ሆነ፤

958. ***መዝሙር*** 38፡18 በደሌን እናገራለሁና፣ ስለ ኃጢአቴም እተክዛለሁ፡፡

959. **2ቆሮንቶስ** 7፡10-11 እንደ እግዚአብሔር *ፈቃድ* የሆነ ሐዘን ጸጸት የሌለበትን፣ ወደ *መዳንም* የሚያደርሰውን ንስሐ ያደርጋልና የዓለም ሐዘን ግን ሞትን *ያመጣል*፡፡ እነሆ፣ ይህ እንደ እግዚአብሔር *ፈቃድ* የሆነ ሐዘን እንዴት ያለ ትጋት በመካከላችሁ አደረገ፡፡
ለ. በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስና በቅዱስ ምሥጢሩ *ቃሎቹ* እናምን እንደ ሆነ፤

960. ***ሉቃስ*** 22፡19-20 ስለ እናንተ የሚሰጠው ሥጋዬ ይህ ነው፤ … ይህ ጽዋ ስለ እናንተ በሚፈሰው በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው፡፡

961. **2ቆሮንቶስ** 13፡5 በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን *መርምሩ*፤ ራሳችሁን *ፈትኑ*፡፡
ሐ. ኃጢአተኛ ሕይወታችንን ለመለወጥ በመንፈስ ቅዱስ ረድኤት እናቅድ እንደ ሆነ፤

962. ***ኤፌሶን*** 4፡22-24 *ፊተኛ* ኑሮአችሁን እያሰባችሁ እንደሚያታልል ምኞት የሚጠፋውን አሮጌውን ሰው አስወግዱ፣ በአእምሮአችሁም *መንፈስ* ታደሱ፣ ለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን ዐዲሱን ሰው ልበሱ፡፡

ለቅዱስ ምሥጢሩ ለመዘጋጀት፣ ‹‹ክርስቲያናዊ ጥያቄዎች ከመልሶቻቸው ጋር›› የሚለውን ተጠቀሙ፡፡

### *304. በእምነት ደካሞች የሆኑ እነዚያ ወደ ጌታ ማዕድ መምጣት ይችላሉን?*

አዎ፣ ክርስቶስ እምነታችንን ለማጠንከርና ለመጨመር ትክክለኛ ዐላማ ሲል ቅዱስ ምሥጢሩን መሥርቷልና፡፡

963. **ማርቆስ** 9፡24 አምናለሁ አለማመኔን እርዳው!

964. **ዮሐንስ** 6፡37 ወደ እኔም የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም፡፡

### *305. ቅዱስ ምሥጢሩ መሰጠት የሌለበት ለማን ነው?*

ቅዱስ ምሥጢሩ ለሚከተሉት መሰጠት የለበትም፡-

ሀ. ክርስቲያናዊ ባልሆነ ሃይማኖታዊ አምልኮ የሚሳተፉትን ጨምሮ በግልጽ ኃጢአተኛ ለሆኑና ንስሐ ለማይገቡ፡፡

965. **1ቆሮንቶስ** 5፡11፣13 አሁን ግን ወንድሞች ከሚባሉት አንዱ ሴሰኛ ወይም ገንዘብን የሚመኝ ወይም ጣዖትን የሚያመልክ ወይም ተሳዳቢ ወይም ሰካር ወይም ነጣቂ ቢሆን ከእርሱ ጋር መተባበር [የለባችሁም] ... ‹‹ክፉውን ከመካከላችሁ አውጡት፡፡››

966. **1ቆሮንቶስ** 10፡20-21 አሕዛብ የሚሠዉት ለአጋንንት እንዲሆን እንጂ ለእግዚአብሔር እንዳይሠዉ እላለሁ፤ ከአጋንንትም ጋር ማኅበረተኞች እንድትሆኑ አልወድም፡፡ የጌታን ጽዋና የአጋንንትን ጽዋ ልትጠጡ አትችሉም፤ ከጌታ ማዕድና ከአጋንንት ማዕድ ልትካፈሉ አትችሉም፡፡

ለ. ይቅር ለማይሉ፣ አንታረቅም ለሚሉ፡፡ በዚያ ምክንያት በእርግጥ የማያምኑና እግዚአብሔርም ይቅር የማይላቸው መሆኑን ያሳያሉ፡፡

967. **ማቴዎስ** 6፡15 ለሰዎች ግን ኃጢአታቸውን ይቅር ባትሉ አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ፡- ምሕረት ያላደረገው ባሪያ* (**ማቴዎስ** 18፡21-35)፡፡

ሐ. የጌታ እራት የእምነት አንድነት ምስክርነት በመሆኑ፣ የተለየ የእምነት መግለጫ ላላቸው፡፡

968. **የሐዋርያት ሥራ** 2፡42 በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቍረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር፡፡

969. **1ቆሮንቶስ** 10፡17 አንድ እንጀራ ስለ ሆነ፣ እኛ ብዙዎች ስንሆን አንድ ሥጋ ነን፤ ሁላችን ያን አንዱን እንጀራ እንካፈላለንና፡፡

970. **1ቆሮንቶስ** 11፡26 ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፣ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና፡፡

971. **ሮሜ** 16፡17 ነገር ግን ወንድሞች ሆይ፣ እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን መለያየትንና ማሰናከያን የሚያደርጉትን ሰዎች እንድትመለከቱ እለምናችኋለሁ፤ ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ፡፡

መ. እንደ ሕፃናት ላሉ፣ ራሳቸውን መፈተን ለማይችሉ፣ ትክክለኛ ትምህርት ላልተማሩ፣ ወይም ለማያውቁ ሰዎች፡፡

972. **1ቆሮንቶስ** 11፡28 ሰው ግን ራሱን ይፈትን፣ እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ ከጽዋውም ይጠጣ።

*ማስታወሻ፦ ቄሶች የእግዚአብሔር ምሥጢር መጋቢዎች* (**1ቆሮንቶስ** 4፡1) *እንደ መሆናቸው ወደ ቅዱስ ምሥጢሩ ማንን መቀበል እንደሚገባ እጅግ በጣም ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው። አንዳንዱ ኃላፊነት ደግሞ በማኅበረ ምእመናኑና በቈራቢው ላይ ያርፋል።*

## *306. እምነትን ማጽናት ምንድን ነው?*

እምነትን ማጽናት የተጠመቁ ክርስቲያኖች ከክርስቲያን ማኅበረ ሰብ ሕይወትና ተልእኮ ጋር እንዲመሳሰሉ ለማድረግ የታቀደ የትምህርት ጊዜን ያስቀደመ ይፋ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ነው።

*ማስታወሻ፦* ወደ ጌታ እራት ለመቅረብ ፈቃድ ከመቀበል አስቀድሞ የክርስትና እምነትን መማር አስፈላጊ ነው (**1ቆሮንቶስ** 11፡28)። እምነትን የማጽናት ሥርዓት እምነትን በግል በይፋ የማስታወቅና ዕድሜ ልክ ለክርስቶስ የሚታመን ቃል ኪዳን ለማድረግ በቅዱስ ጥምቀት በሚሰጥ የእግዚአብሔር ተስፋ ላይ ለታመነው ክርስቲያን ግለሰብ ዕድል ይሰጣል።

973. **ማቴዎስ** 10፡32-33 ስለዚህ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፤ በሰው ፊትም የሚክደኝን ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እክደዋለሁ።

974. **ራእይ** 2፡10 እስከ ሞት ድረስ የታመንህ ሁን፤ የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ።




## ተጨማሪ ጽሑፍ

### የሉተር መቅድም

[ሉተር በእርሱ ዘመን የነበሩ የተለዩ ጕዳዮችን በሚናገረው በትንሹ የክርስትና ትምህርት ላይ ይህን መቅድም አካትቶአል፡፡]

*ማርቲን ሉተር፣ ታማኞችና እግዚአብሔርን ለሚፈሩ ቀሳውስትና ሰባኪያን ሁሉ፡-* በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣ ምሕረት እና ሰላም ይሁን፡፡

ጉብኝት ላይ በነበርኩበት ጊዜ በቅርቡ ያጋጠመኝ አሳዛኝና እጅግ መጥፎ ሁኔታ ይህንን የክርስትና ትምህርት፣ ወይም የክርስትና መማሪያ እንዲህ ባለ አጭር፣ ግልጽና እንዲሁም ቀለል ባለ መልክ እንዳዘጋጅ አሳምኖኛል አስገድዶኛልም፡፡ ውድ አምላኬ፣ ምን ታላቅ ጕስቍልና ነው ያየሁት! በተለይም በመንደሮቹ ያለው፣ ተራው ሰው ስለ ክርስትና እምነት ፈጽሞ ምንም ዐያውቅም፣ እንዲሁም በሚያሳዝን ሁኔታ ብዙ ቀሳውስት ፈጽሞ ያልሠለጠኑና ለማስተማር ብቃት የሌላቸው ናቸው፡፡ ‹ይህም እጅግ ከመብዛቱ የተነሣ አንድ ሰው ሊናገረው እንኳ ያሳፍራል፡፡› ሆኖም ግን ለምናልባቱ ምንም እንኳ የጌታን ጸሎት፣ የእምነት መገለጫዎችን፣ ወይም ዐሠርቱን ትእዛዛት መናገር ባያውቁም ሁላቸውም ክርስቲያን የሚለውን ስም ይዘዋል፣ ተጠምቀዋል፣ ቅዱስ ቍርባንም ይቀበላሉ፡፡ ከዚህ የተነሣ እንደ ተራ ከብት ወይም ማሰብ እንደማይችሉ አሳማዎች ይኖራሉ፤ ደግሞም ወንጌል መመለሱ እውነት ቢሆንም እንኳ ነጻነታቸውን ሁሉ ያለ አግባብ የመጠቀምን ጥበብ ጠንቅቀው ተክነውታል፡፡

እናንተ ጳጳሳት ሆይ! በጣም በሚያሳፍር ሁኔታ ሕዝቡን ችላ ብላችኋልና ለአንድ ሰከንድም እንኳ የአገልግሎት ድርሻችሁን አልተገበራችሁምና፤ ለክርስቶስ እንዴት መልስ ትሰጡታላችሁ? [ያዕቆብ 3፡1]፡፡ በዚህስ ከክፉ አጋጣሚ ታመልጣላችሁን? ‹በዚህ ቦታ በራሳችሁ ላይ ክፉ ክፉ እንዲመጣ ልረግማችሁ አልፈልግም፡፡› ሕዝቡ የጌታን ጸሎት፣ የእምነት መግለጫን፣ ዐሠርቱን ትእዛዛት ወይም አንዳች የእግዚአብሔር ቃል ክፍል ያወቀ እንደ ሆነ ለመጠየቅ ከቶ ሳትጨነቁ ቅዱስ ምሥጢሩን በአንድ መልክ ትከለክሉና የራሳችሁን ሰብአዊ ሕግጋት በመጠበቅ ትጸናላችሁ፡፡ ለዘላለም ወዮላችሁ! ወዮላችሁ! [ማቴዎስ 23ን ተመልከቱ፡፡]

ስለዚህ፣ ቀሳውስት ወይም ሰባኪያን የሆናችሁ ውድ ጌቶቼና ወንድሞቼ፣ ራሳችሁ ከልብ ለአገልግሎታችሁ እንድታውሉ [1ጢሞቴዎስ 4፡13]፣ አደራ ለተሰጡአችሁ ሕዝባችሁ እዘኑ [የሐዋርያት ሥራ 20፡28] እንዲሁም የክርስትና ትምህርትን ለሕዝቡ፣ በተለይም ለወጣቶች እንድናስተምር እንድትረዱን ስለ እግዚአብሔር ብዬ ሁላችሁንም እለምናችኋለሁ፡፡ በተጨማሪ፣

ምንም የተሻለ ልታደርጉ ያልቻላችሁ እናንተ እነዚህን ሠንጠረዦችና ዕትሞች እንዲያነሡና በሚከተለው አኳኋን ለሕዝቡ ቃል በቃል እንዲያነብቡአቸው አድርጉ [ዘዳግም 6፡7]፡-

በመጀመሪያ ደረጃ፣ ሰባኪው ከሁሉም በላይ በጽሑፍና በዐሠርቱ ትእዛዛት፣ በጌታ ጸሎት፣ በእምነት መግለጫ፣ በቅዱሳት ምሥጢራት፣ ወዘተ. እትም ያሉትን ለውጦችና ልዩነት ለማስወገድ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፤ ነገር ግን በዚህ ፈንታ አንድን ዕትም መቀበል፣ በእርሱ መጽናት፣ እንዲሁም መቀጠል፣ እንዲሁም ሁልጊዜ ያንኑ ከዓመት ወደ ዓመት መጠቀም አለበት፡፡ ምክንያቱም ወጣቶችና ያልተማሩ ሰዎች አንድ፣ የተወሰነ ጽሑፍና ዕትም መማር አለባቸው፡፡ አለበለዚያ አስተማሪው አሁን በአንድ መንገድ፣ በሚቀጥለው ዓመት በሌላ መንገድ ቢያስተምራቸው፣ ለመሻሻል ቢባልም እንኳ በቀላሉ ግራ ይጋባሉ፡፡ ‹በማስተማር የጠፋው› ጊዜና ጥረት ሁሉ ከንቱ ይሆናልና፡፡

የተወደዱት አባቶች ደግሞ ይህን ተረድተዋል፡፡ ሁላቸውም ለጌታ ጸሎት፣ ለእምነት መግለጫ፣ እንዲሁም ለዐሠርቱ ትእዛዛት አንድ መንገድ ያንኑ ዓይነት ተጠቅመዋል፡፡ ስለዚህ፣ እኛ ደግሞ የአንዱንም ክፍለ ቃል ሳንለውጥ ወይም ከአንድ ዓመት ወደ ቀጣዩ ዓመት በተለየ መንገድ ሳናቀርብና ሳንደግም እነዚህን ክፍሎች ለወጣቶችና ማንበብ ለማይችሉ ሰዎች ለማስተማር ‹በጣም መጣር› አለብን፡፡

ስለዚህ፣ እስከ ወዲያኛው በየትኛው ዕትም መጽናት እንደምትፈልግ ለራስህ ምረጥና ለዘላለም ጽናበት፡፡ ነገር ግን እርግጠኛ ለመሆን፣ የተማሩና ዐዋቂ ሰዎች ባሉበት በምትሰብክበት ጊዜ ክህሎትህን ልታሳይ ትችላለህ፡፡ እነዚህን ክፍሎች በብዙ ውስብስብ መንገዶች ልታቀርብና በተቻለህ መጠን በብዙ ልዩ ልዩ አቅጣጫዎች ልትወያይባቸው ትችላለህ፡፡ ወጣቶችን በሚመለከት ግን፣ በተወሰነ፣ በማይለወጥ መልክና መንገድ ጽና፡፡ ከሁሉ አስቀድሞ እነዚህን ክፍሎች፡- ለአንተ ደግሞ እንዲደግሙልህና በቃል እንዲያጠኑት ጽሑፉን ቃል በቃል በመከተል ዐሠርቱ ትእዛዛትን፣ የእምነት መግለጫንና የጌታ ጸሎትን አስተምራቸው፡፡

ነገር ግን የክርስትና ትምህርትን ለመማር ፈቃደኞች የማይሆኑ፣ ክርስቶስን እንደሚክዱና ክርስቲያኖች እንዳልሆኑ ሊነገራቸው ይገባል፡፡ ወደ ቅዱስ ቊርባን ደግሞ ሊቀርቡ አይገባም፤ በጥምቀት ሕፃናትን አቅራቢዎች መሆን የለባቸውም፤ ወይም ማንኛውንም ዓይነት የክርስቲያናዊ ነጻነት መለማመድ የለባቸውም፡፡ ነገር ግን በቀላሉ ወደ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱና ባለ ሥልጣናቱ፣ ከእነርሱ ጋርም ወደ ዲያብሎስ ወደ ራሱ ተመልሰው መላክ አለባቸው [1ቆሮንቶስ 5፡5]፡፡ በተጨማሪ ወላጆቻቸውና አሠሪዎቻቸው ምግብና መጠጥ ሊከለክሉአቸውና እንዲህ የመሰሉ ልበ ደንዳና ሰዎችን ከአገሪቱ እንዲያባርር የመስፍኑ ዐሳብ መሆኑን ሊነግሩአቸው ይገባል፡፡

ምንም እንኳ እንዲያምን ሌላን ሰው ማስገደድ ባንችልም ወይም ባይገባንም፣ መጽናትና ሕዝቡን ማበረታታት አለብን፡፡ በዚያ መንገድ አብረዋቸው ለመኖርና ኑሮን ለመግፋት በሚፈልጉአቸው መካከል ትክክልና ስሕተት የሆነውን ያውቃሉ፡፡ በአንዲት ከተማ ለመኖር የሚፈልግ ማንም የሚያምን ሰው ወይም በልቡና በግሉ ወሮበላና ተንኰለኛ ቢሆን ጥበቃን የሚያገኝባትን ከተማ ሕግ ማወቅና ለእርሱም መገዛት ይገባዋል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ፣ ሕዝቡ ጥቅሱን በሚገባ ከተማሩት በኋላ፣ ምን ማለት እንደ ሆነ ትርጕሙን ያውቁ ዘንድ እንዲገባቸው ደግሞ አስተምራቸው፡፡ እንደ ገና በእነዚህ ሠንጠረዦች

የቀረበውን መንገድ ወይም ይሻላል የምትለውን አጭር መንገድ ተጠቀም፡፡ በእርሱም ጽና፡፡ ልክ ጽሑፉን በሚመለከት እንደ ተገለጸው፣ አንድም የቃል ክፍል አትለውጥ፡፡ ይህን ለማድረግ በቂ ጊዜ ይኑርህ፡፡ በማከታተል እንጂ ክፍሎቹን ሁሉ በአንድ ጊዜ ማብራራት አያስፈልግህምና፡፡ ሕዝቡ የመጀመሪያውን ትእዛዝ በሚገባ ከተረዱ በኋላ፣ ሁለተኛውን፣ እንዲሁም ቀጥሎ ያለውን አብራራ፡፡ አለበለዚያ በጣም ይበዛባቸውና አንድም ነገር በሚገባ ማስታወስ ሳይችሉ ይቀራሉ፡፡

በሦስተኛ ደረጃ፣ ይህን አጭር የክርስትና ትምህርት ካስተማርካቸው በኋላ፣ ትልቁን የክርስትና ትምህርት አንሣና እጅግ የበለጸገና የተሟላ ዕውቀት ደግሞ ስጣቸው፡፡ እዚህ ላይ ስለ እነዚህ ጉዳዮች በተጻፉ በጣም ብዙ በሆኑ መጻሕፍት በስፋት ተተንትኖ እንደምታገኘው፣ እያንዳንዱን ትእዛዝ፣ ‹አንቀጽ› ጸሎት፣ ወይም ክፍል ከተለያዩ ሥራዎቹ፣ ጥቅሞቹ፣ ትርፎቹ፣ አደጋዎቹና ጉዳቶቹ ጋር አብራራ፡፡ በተለይ፣ በሰዎችህ መካከል ከሁሉ የላቀ ቸልታ በሚታይበት ትእዛዝ ወይም ክፍል ላይ ትኵረት አድርግ፡፡ ለምሳሌ፣ ለዕደ ጥበብ ባለሙያዎችና ለነጋዴዎች እንዲሁም ለገበሬዎችና ለቤት ሠራተኞች እንኳ ስለ ስርቆት የሚናገረውን ሰባተኛውን ትእዛዝ በጽናት አጉላው፡፡ ምክንያቱም በእነዚህ ሰዎች መካከል ብዙ ዓይነት እምነት ማጉደልና ሌብነት በብዛት ይገኛሉ፡፡ እንደዚሁ ደግሞ፣ ጭምቶችና ታማኞች፣ ታዛዦችና ሰላማውያን ይሆኑ ዘንድ አራተኛውን ትእዛዝ ለልጆችና ለአብዛኛው ሰዎች ማጉላት አለብህ፡፡ እግዚአብሔር እንዲህ ያሉ ሰዎችን እንዴት እንደ ቀጣቸው ወይም እንደ ባረካቸው ለማሳየት ሁልጊዜ ብዙ ምሳሌዎችን ከእግዚአብሔር ቃል አቅርብ [ዘዳግም 28]፡፡

በዚህ ጉዳይ የሚያስተዳድሩ ባለ ሥልጣናትንና ወላጆችን በሚገባ እንዲያስተዳድሩና ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት እንዲልኩ በተለይ አደፋፍር፡፡ ይህን እንዲያደርጉ ለምን የእነርሱ ግዴታ እንደሆነና ባያደርጉት ግን ምን ዓይነት ሰይጣናዊ ኃጢአት እየፈጸሙ እንደሆነ አሳያቸው፡፡ እንዲህ ባለ ቸልታ ሁለቱንም የእግዚአብሔርን መንግሥትና የዓለምን መንግሥት ይገለብጣሉና፡፡ ከሁሉ በጣም የከፉ የሁለቱም የእግዚአብሔርና የሰዎች ጠላቶች በመሆን ይሠራሉ፡፡ በዚህ ሕይወት ያለ እነርሱ ምንም ማድረግ የማንችላቸው ልጆችን እንደ ቀሳውስት፣ ሰባኪያን፣ ጸሐፊዎች፣ እንዲሁም ሌሎች የሥራ ቦታዎች እንዲይዙ ለማሠልጠን እገዛ በማያደርጉበት ጊዜ ምን ዓይነት አስከፊ ጉዳት እንደሚያደርሱ በጣም ግልጽ አድርግላቸው፡፡ ይህን ማድረግ ስለ ተሳናቸው እግዚአብሔር አሰቃቂ በሆነ መንገድ ይቀጣቸዋል፡፡ ይህን መስበክ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ወላጆችና የሚያስተዳድሩ ባለሥልጣናት በዚህ ጉዳይ እጅግ መጥፎ በሆኑ መንገዶች ኃጢአት እየሠሩ ናቸው፡፡ ዲያብሎስ ደግሞ በእነዚህ ነገሮች ምክንያት አስከፊ ነገር ለመፈጸም ተስፋ ያደርጋል፡፡

በመጨረሻ፣ የርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ አምባገነናዊነት በመወገዱ ምክንያት፣ ከእንግዲህ ሰዎች ወደ ቅዱስ ምሥጢሩ ለመቅረብ ፈቃደኞች አይደሉም፤ ስለዚህም ይንቁታል፡፡ እዚህ ላይ እንደ ገና ማበረታቻ አስፈላጊ ነው፤ ሆኖም ግን በዚህ መረዳት መሆን አለበት፡- ቅዱስ ምሥጢሩን እንዲያምን ወይም እንዲቀበል ማንንም ማስገደድ የለብንም፡፡ ለእርሱ ምንም ሕግ ወይም ጊዜ ወይም ስፍራ መወሰን አይገባንም፡፡ በዚህ ፈንታ፣ ያለ እኛ ሕግ በራሳቸው ፈቃድ እንዲመጡና በቀሳውስትነታችን ቅዱስ ምሥጢሩን እንድናከናውንላቸው ዝም ብለው ሊያስገድዱን በሚችሉበት መንገድ መስበክ አለብን፡፡ ‹‹እጅግ ቢያንስ በዓመት አራት ጊዜ ቅዱስ

ምሥጢሩን የማይፈልግ ወይም የማይቀበል ማንም ሰው ቢሆን ቅዱስ ምሥጢሩን የሚንቅና ልክ ወንጌልን የማይሰማ ወይም የማያምን እንዲሁም ክርስቲያን እንዳልሆነ ሁሉ ክርስቲያን አለመሆኑን ማሰብ ይኖርባችኋል›› ብሎ ለእነርሱ በመናገር ይህ ሊከናወን ይችላል፡፡ ምክንያቱም ክርስቶስ፣ ‹‹ይህን አስቀሩ፣›› ወይም ‹‹ይህንን ናቁ›› አላለም፤ ነገር ግን፣ ‹‹… በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ አድርጉት›› [1ቆሮንቶስ 11፡25]፣ እንዲህ ያሉ ሌሎች ቃሎችንም ብሎአል፡፡ በእርግጥ እንዲደረግ እንጂ በፍጹም እንዲቀር ወይም እንዲናቅ አይፈልግም፡፡ ‹‹ይህንን አድርጉት›› ይላል፡ ፡

እንግዲህ፣ ለቅዱስ ምሥጢሩ ከፍተኛ ዋጋ የማይሰጥ ማንም ሰው ኃጢአት፣ ሥጋ፣ ዲያብሎስ፣ ዓለም፣ ሞት፣ አደጋ፣ ሲኦል እንደሌለበት ያሳያል፡፡ በሌላ አባባል በራሱና በጆሮዎቹ በእነርሱ ውስጥ ቢዘፈቅም ከእነዚህ ነገሮች አንዱንም አያምንም፡፡ ሁለት ጊዜ የዲያብሎስ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል፣ ጸጋ፣ ሕይወት፣ ገነት፣ መንግሥተ ሰማይ፣ ክርስቶስ፣ እግዚአብሔር፣ ወይም ሌላ ምንም መልካም ነገር አያስፈልገውም፡፡ ምክንያቱም በዙሪያው በጣም ብዙ ክፋት እንዳለበትና በጣም ብዙ መልካም ነገር እንደሚያስፈልገው ቢያምን ኖሮ፣ እንዲህ ያለ ክፋትን የሚቃወም እርዳታ የሚቀርብበትንና በጣም ብዙ በጎ ነገር የሚሰጥበትን ቅዱስ ምሥጢር ቸል አይልም ነበር፡፡ ወደ ቅዱስ ምሥጢሩ እንዲቀርብም በማንኛውም ሕግ ሊገደድ አያስፈልግም ነበር፡፡ በራሱ ፈቃድ እየተጣደፈና እየሮጠ ወደ እርሱ ይመጣል፤ ለመምጣት ራሱን ያስገድዳል፤ እንዲሁም ቅዱስ ምሥጢሩን እናንተ እንድትሰጡት ይለምናል፡፡

ስለዚህ እናንተ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ እንደሚያደርገው ስለዚህ ምንም ሕግ ማውጣት አይገባችሁም፡፡ ከዚህ ቅዱስ ምሥጢር ጋር የተያያዘውን ትርፍና ጉዳት፣ አስፈላጊነትና ጥቅም፣ አደጋና በረከት ብቻ በግልጽ አጉሉ፡፡ ያኔ ሕዝቡ እናንተ ሳታስገድዱአቸው ራሳቸው ይመጣሉ፡፡ ነገር ግን የማይመጡ ከሆነ ተዉአቸውና ከፍ ያለ ችግራቸውና የእግዚአብሔር ቸር እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው ግድ የማይላቸውና የማይሰማቸው የዲያብሎስ መሆናቸውን ንገሩአቸው፡፡ ነገር ግን ይህን ካላደፋፈራችሁ፣ ወይም ሕግ ካወጣችሁ ወይም መራር ካደረጋችሁት፣ ያኔ ቅዱስ ምሥጢሩን ቢንቁ የእናንተ ጥፋት ነው፡፡ እናንተ ከተኛችሁና ዝም ካላችሁ ሰነፎች ከመሆን በቀር ምን ማድረግ ይችላሉ? ስለዚህ፣ ቀሳውስትና ሰባኪያን ልብ በሉ፡፡ የአገልግሎት ኃላፊነታችን በርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ሥር ከነበረበት ጊዜ ይልቅ አሁን የተለየ ነገር ሆኖአል፡፡ አሁን አስፈላጊና የሚያድን የአገልግሎት ኃላፊነት ሆኖአል፡፡ ስለሆነም፣ አሁን ብዙ ችግርና ሥራ፣ አደጋና ፈተናዎች አሉበት፡፡ በተጨማሪም፣ በዓለም የሚያገኘው ሽልማትና ምስጋና አናሣ ነው፡፡ ነገር ግን በታማኝነት ብንሠራ ክርስቶስ ራሱ ሽልማታችን ይሆናል [ዘፍጥረት 15፡ 1ን ተመልከቱ]፡፡ ይህንን ዐላማ እንድንፈጽም፣ በክርስቶስ በጌታችን ለዘላለም ውዳሴና ምስጋና የሚገባው የጸጋ ሁሉ አባት ይርዳን! አሜን፡፡

### የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት

መጽሐፍ ቅዱስ በሁለት ክፍሎች፣ በብሉይ ኪዳንና በዐዲስ ኪዳን ተከፍሎአል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ 66 መጻሕፍት አሉ፦ እነርሱም በብሉይ ኪዳን 39 እና በዐዲስ ኪዳን 27 ናቸው።

### የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

| **የታሪክ መጻሕፍት** | **የቅኔ መጻሕፍት** |
|---|---|
| ፔንታቱክ<br>(አምስት የሙሴ መጻሕፍት) | ኢዮብ |
| ዘፍጥረት | መዝሙር |
| ዘፀአት | ምሳሌ |
| ዘሌዋውያን | መክብብ |
| ዘኍልቍ | መኀልየ መኀልይ |
| ዘዳግም | |
| **ሌሎች የታሪክ መጻሕፍት** | **የትንቢት መጻሕፍት** |
| ኢያሱ | *ታላላቅ ነቢያት* |
| መሳፍንት | ኢሳይያስ |
| ሩት | ኤርምያስ |
| 1 ሳሙኤል | ሰቆቃወ ኤርምያስ |
| 2 ሳሙኤል | ሕዝቅኤል |
| 1 ነገሥት | ዳንኤል |
| 2 ነገሥት | |
| 1 ዜና መዋዕል | *ታናናሽ ነቢያት* |
| 2 ዜና መዋዕል | ሆሴዕ |
| ዕዝራ | ኢዮኤል |
| ነህምያ | አሞጽ |
| አስቴር | አብድዩ |
| | ዮናስ |
| | ሚክያስ |
| | ናሆም |
| | ዕንባቆም |
| | ሶፎንያስ |
| | ሐጌ |
| | ዘካርያስ |
| | ሚልክያስ |

| የዐዲስ ኪዳን መጻሕፍት | |
|---|---|
| **የታሪክ መጻሕፍት** | 1 ጢሞቴዎስ |
| ማቴዎስ | 2 ጢሞቴዎስ |
| ማርቆስ | ቲቶ |
| ሉቃስ | ፊልሞና |
| ዮሐንስ | ዕብራውያን |
| የሐዋርያት ሥራ | ያዕቆብ |
| | 1 ጴጥሮስ |
| ***መልእክቶች*** | 2 ጴጥሮስ |
| ሮሜ | 1 ዮሐንስ |
| 1 ቆሮንቶስ | 2 ዮሐንስ |
| 2 ቆሮንቶስ | 3 ዮሐንስ |
| ገላትያ | ይሁዳ |
| ኤፌሶን | |
| ፊልጵስዩስ | ***የትንቢት መጽሐፍ*** |
| ቆላስይስ | ራእይ |
| 1 ተሰሎንቄ | |
| 2 ተሰሎንቄ | |

## የእምነት መግለጫዎችና የኃጢአት ኑዛዜ

ከሐዋርያት የእምነት መግለጫ በተጨማሪ የጌታ እራት በሚከበርበት ጊዜ የምናስታውቀው የኒቅያ የእምነት መግለጫ፣ እንዲሁም ብዙ ጊዜ በቅድስት ሥላሴ እሑድ የሚነበበው የአትናቴዎስ የእምነት መግለጫ፣ በሉተራዊት ቤተ ክርስቲያን የሚታመኑ ዓለምአቀፍ የእምነት መግለጫዎች ናቸው። ሁለቱም በተለይ በኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትና ሥራ ላይ ያተኩራሉ።

ሉተራዊት ቤተ ክርስቲያን በ1580ው መጽሐፈ ስምምነት ያሉትን ሰነዶች ሁሉ ደግሞ እውነተኛና ያልተቀየጠው መግለጫና የእግዚአብሔር ቃል ማብራሪያ እንደ ሆነ ያለ መቆጠብ ትቀበላለች። ከእነዚህ መካከል እጅግ በጣም የታወቀውና በይበልጥም በስፋት ጥቅም ላይ የዋለው የዶ/ር ማርቲን ሉተር ትንሹ የክርስትና ትምህርት ነው።

ኖቬምበር 10 ቀን 1483 በአይስሌበን ጀርመን የተወለደው ሉተር በተለይ በሕግና በሊበራል አርትስ ካሉት ትምህርት ቤቶች ምርጥ ተደርጎ በተቈጠረው በኤርፉርት ዩኒቨርስቲ ተማረ። ይሁን እንጂ፣ ከዚያ በኋላ ወዲያውኑ፣ በቅዱስ አውግስጢኖስ የገዳም ሕግ ወደሚተዳደረው ማኅበር እንዲቀበሉት ጥያቄ አቀረበ። በ1507 የቅስና ማዕረግ ተሰጠውና ኋላ ላይ በሥነ መለኮት ዶክትሬት አገኘ። ከሮማ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ጋር የሚቃረኑትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደ ሆኑ ያመናቸውን አስተምህሮዎች እንዲተው ከተነገረው በኋላ በ1521 ከሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጋር መለያየቱ ተከሠተ።

በ1529 የተጠናቀቁት የሉተር ትንሹ የክርስትና ትምህርትና ትልቁ የክርስትና ትምህርት ለልጆችና ለዐዋቂዎች የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማር በመጀመሪያ ለቀሳውስትና ለቤተ ሰብ መሪዎች የሚጠቅሙ መምሪያዎች እንዲሆኑ የታሰቡ ነበሩ። ትልቁ የክርስትና ትምህርት ብዙውን ጊዜ በስብከቶች ጥቅም ላይ በሚውል መንገድ መሠረታዊ የክርስትና አስተምህሮዎችን ያቀርባል እንጂ በጥያቄዎችና መልሶች የተዘጋጀ አይደለም።

ሌላው የታወቀው የእምነት መግለጫ፣ በፊሊፕ ሜላንክተን የተጻፈውና በኦግስቡርግ ጀርመን በ1530 በንጉሠ ነገሥት ቻርለስ 5ኛ ፊት የተነበበው የኦግስቡርግ የእምነት መግለጫ ነው። የእምነት መግለጫው በአጻጻፍ ዘይቤው የተወደደ ሆኖ ሳለ፣ በቤተ ክርስቲያን የተስፋፉ ተገቢ ያልሆኑ አድራጎቶችን በመቃወምና እንደ ውርስ ኃጢአትና ቅዱስ ምሥጢሩ ያሉ በጣም ወሳኝ መሠረተ እምነቶችን በሚመለከት የአንዳንድ አዳሾችን ስሕተቶች በመቃወም እንደ ምስክርነት ተቀባይነት አገኘ።

በ1531 ሜላንክተን የኦግስቡርግ የእምነት መግለጫ መከላከያን ጻፈ። እርሱም ደግሞ በ1537 በስማልካልድ ጀርመን ተቀባይነት በማግኘቱ በሉተራውያን መካከል ይፋዊ የእምነት መግለጫ ሆነ። ለኦግስቡርግ የእምነት መግለጫ ትችቶች ሰፋ ያለ ዝርዝር መልሶችን ይሰጣል። የመከላከያው ግማሽ ያህል በኢየሱስ ክርስቶስ ባለው እምነት አማካይነት ለመጽሐፍ ቅዱሳዊው በጸጋ የመጽደቅ መሠረተ እምነት ውሎአል።

የስማልካልድ አንቀጾች በ1536 በሉተር ተጽፈው በ1537 በስማልካልድ በተገኙ በርካታ ቀሳውስት ተፈረሙ። አንቀጾቹ ሉተር ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጋር የነበሩት ዋና ዋና አለመግባባቶች ማጠቃለያ ናቸው። በርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ሥልጣንና የበላይነት ላይ የቀረበው የሜላንክተን ጽሑፍ ደግሞ በስማልካልድ በይፋ ተቀባይነት አገኘ።

በ1577 የተጠናቀቀው የስምምነቱ መሠረታዊ መመሪያ በሉተራውያን መካከል የነበሩትን የመሠረተ እምነት ልዩነቶች ለመፍታት አገለገለ፤ በ1580 ከ8000 በላይ በሚሆኑ የሥነ መለኮት ዐዋቂዎች፣ ቀሳውስት፣ እንዲሁም መምህራን ጸደቀ፤ እርሱም ማብራሪያና ቀደም ብለው ተቀባይነት ያገኙት ጽሑፎች መከላከያ እንጂ ዐዲስ የእምነት መግለጫ አልነበረም።

ከእነዚህ ጽሑፎች የተወሰዱት ጥቅሶች በዚህ በትንሹ የክርስትና ትምህርት ማብራሪያ ውስጥ ተካተዋል።

## የሉተር ማኅተም ማብራሪያ

*ማርቲን ሉተር የክርስትና እምነቱን ለማጠቃለል የሚከተለውን ማኅተም ንድፍ ሠራ*



በመሐል ያለው ጥቁር መስቀል ኢየሱስ የኃጢአታችንን ቅጣት ለመቀበል መሞቱን ያስታወሰናል፡፡ ቀዩ ልብ አዳኛችን እንዲሆን ኢየሱስን በመላክ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር ያስታውሰናል፡፡ የልቡ ቀዩ ቀለም ስለ እኛና ስለ ድነታችን የፈሰሰው የክርስቶስ ደም ነው፡ ፡ ነጬ ጽጌረዳ እኛን በክርስቶስ ወዳለው እምነት በማምጣትና ሕይወታችንን ለእርሱ እንድንኖር በመርዳት በእግዚአብሔር ፊት ንጹሐንና ቅዱሳን የሚያደርገንን የመንፈስ ቅዱስን ሥራ እንድናስታውስ ይረዳናል፡፡ ሰማዩ ሰማያዊ መደብ በእርሱ ለሚያምኑትና ለሚታመኑት ሁሉ እግዚአብሔር የሚሰጠውን ደስታና ዐዲስ ሕይወት በምሳሌነት ያሳያል፡፡ በመጨረሻ፣ የማኅተሙን ቅርፅ የሚያሳየው ወርቃማ ቀለበት ዘላለማዊ ርስታችንን፡- አዳኛችን ባለበት ፍጹም ደስታና ሐሤት የምናጣጥምበትን የሰማይ ቤት ያስታውሰናል፡፡

## የድነት ዋና ዋና ዐሳብ

የሚከተሉት ሰባት ነጥቦች ስለ ሰው ሁኔታና ስለ እግዚአብሔር የማዳን ጸጋ መሠረታዊ መረጃ ማጠቃለያ ይሰጣሉ፡፡ አዳኙ አድርጎ ገና በኢየሱስ ለማያምን ወይም ለማታምን ሰው ታካፍል ዘንድ እነዚህን ነጥቦች በቃል ማጥናት ትፈልግ ይሆናል፡፡

1. *እግዚአብሔር ይወድሃል!* ‹‹በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና›› (**ዮሐንስ** 3፡16)፡፡
2. *አንተ ኃጢአተኛ ነህ፡፡* ‹‹ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሎአቸዋል›› (**ሮሜ** 3፡23)፡፡
3. *እግዚአብሔር ኃጢአትን ይቀጣል፡፡* ‹‹የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው›› (**ሮሜ** 6፡23)፡፡
4. *ኢየሱስ ቅጣታችንን ተቀበለ፡፡* ‹‹ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል›› (**ሮሜ** 5፡8)፡፡
5. *ኢየሱስ ከሙታን ተነሣ፡፡* ‹‹እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ እንዲህ ብዬ፡- መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፣ ተቀበረም፣ መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ›› (**1ቆሮንቶስ** 15፡3-4)፡፡

6. *ኢየሱስ በእርሱ ለሚያምኑ የኃጢአት ይቅርታና የዘላለም ሕይወት ይሰጣል።* ‹‹ወደ ውጭም አውጥቶ ‹ጌቶች ሆይ፣ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?› አላቸው። እነርሱም ‹በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን፤ አንተና ቤተ ሰዎችህም ትድናላችሁ› አሉት›› (**የሐዋርያት *ሥራ*** 16፡30-31)።
7. *ድነት ከእግዚአብሔር የሆነ ነጻ ስጦታ ነው።* ‹‹ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም›› (**ኤፌሶን** 2፡8-9)።

## የቤተ ክርስቲያን ዓመት

የእግዚአብሔር ሕዝብ በአምልኮ ሕይወታቸው እንዲረዳቸው የቤተ ክርስቲያን ዓመት የቀን መቍጠሪያን ይጠቀማሉ። የቤተ ክርስቲያን ዓመት የቀን መቍጠሪያ ሁለት አጋማሾች አሉት። ከመምጣቱ እስከ ጴንጤቆስጤ ቀን የሚረዝመው የበዓሉ አጋማሽ፣ እግዚአብሔር በልጁ አማካይነት ያደረገልንንና በመቀጠል የሚያደርግልንን እያስታወሰን ዋና ትኵረቱን በክርስቶስ ሕይወት ላይ ያደርጋል። ከሥላሴ እሑድ እስከ ቤተ ክርስቲያን ዓመት የመጨረሻ እሑድ የሚረዝመው በዓል ያልሆነው አጋማሽ፣ በየዕለቱ በእግዚአብሔር ቃል በሚጠናከረው የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ላይ ያተኵራል።

በአጠቃላይ፣ የቤተ ክርስቲያን ዓመት ስድስት ወቅቶች አሉ፤ እነርሱም፡- መምጣቱ፣ የጌታችን ልደት፣ ጥምቀት፣ ዐቢይ ጾም፣ ፋሲካ፣ እንዲሁም ከጴንጤቆስጤ በኋላ ያለው ወቅት ናቸው። የሚከተሉት ቀለማት ከእነዚህ ወቅቶች ጋር የተዛመዱ ናቸው።

ሰማያዊ፡- (መምጣት) በክርስቶስ የእኛ የሆነውን የተባረከውን ዘላለማዊ ተስፋ ያስታውሰናል።

ነጭ፡- (የጌታችን ልደት፣ ጥምቀት፣ ፋሲካ፣ እንዲሁም ሥላሴ) የንጽሕና፣ የቅድስና፣ የክብር፣ እንዲሁም የደስታ ቀለም ነው።

አረንጓዴ፡- (የጥምቀት ወቅትና ከጴንጤቆስጤ/ከሥላሴ በኋላ ያሉት እሑዶች) የክርስቲያኑን ሕይወት በእምነት ማደግን ይወክላል።

ሐምራዊ፡- (ዐቢይ ጾም) ንስሐ የመግባት አስፈላጊነትንና ፋሲካን ለማክበር መዘጋጀትን ያስታውሰናል።

ቀይ፡- (ጴንጤቆስጤ) የመንፈስ ቅዱስን መምጣት የሚወክለው የእሳት ቀለም፤ የሰማዕታትን ደም ለመወከል በአንዳንድ የቅዱሳን ቀኖች ደግሞ ጥቅም ላይ ይውላል።

በቤተ ክርስቲያን ዓመት ውስጥ ያሉት የጌታችን ልደት፣ ጥምቀት፣ ፋሲካ፣ ዕርገት፣ እንዲሁም ጴንጤቆስጤ የበዓላት ቀናት ናቸው። እነዚህ ቀናት በክርስቶስ ሕይወት የተፈጸሙ አስፈላጊ ሁነቶችንና ዛሬ ለእኛ ምን ማለት እንደ ሆኑ ያከብራሉ። ሌሎች በዓላት በቤተ ክርስቲያን ዓመት ሠንጠረዥ ተካተዋል።

**የቤተ ክርስቲያን ዓመት**

**እሑዶችና ወቅቶች**

***የጌታችን ልደት ጊዜ***

*የመምጣቱ ወቅት*

የመምጣቱ የመጀመሪያ እሑድ

የመምጣቱ ሁለተኛ እሑድ

የመምጣቱ ሦስተኛ እሑድ

የመምጣቱ አራተኛ እሑድ

*የጌታችን ልደት ወቅት*

የጌታችን ልደት

*የጌታችን ልደት ዋዜማ*

*የጌታችን ልደት እኩለ ሌሊት*

*የጌታችን ልደት ማለዳ*

*የጌታችን ልደት ቀን*

ከልደት በኊላ አንደኛ እሑድ

ከልደት በኊላ ሁለተኛ እሑድ

*የጥምቀት ወቅት*

የጌታችን ጥምቀት

ከጥምቀት በኊላ አንደኛ እሑድ

*የጌታችን መጠመቅ*

ከጥምቀት በኊላ ሁለተኛ እሑድ

ከጥምቀት በኊላ ሦስተኛ እሑድ

ከጥምቀት በኊላ አራተኛ እሑድ

ከጥምቀት በኊላ አምስተኛ እሑድ

ከጥምቀት በኊላ ስድስተኛ እሑድ

ከጥምቀት በኊላ ሰባተኛ እሑድ

ከጥምቀት በኊላ ስምንተኛ እሑድ

የጥምቀት በኊላ የመጨረሻ እሑድ

*ለሦስት ዓመት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ዝርዝር*

*የጌታችን መልክ መለወጥ*

**የፋሲካ ጊዜ**

*ቅድመ ዐቢይ ጾም ወቅት*

ሰጽቱዋጌሥማ

ሰክሳጌሥማ

ኪንኲዋጌሥማ

ለአንድ ዓመት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ዝርዝር

*የዐቢይ ጾም ወቅት*

የዐቢይ ጾም የመጀመሪያ ቀን

የዐቢይ ጾም አንደኛ እሑድ
የዐቢይ ጾም ሁለተኛ እሑድ
የዐቢይ ጾም ሦስተኛ እሑድ
የዐቢይ ጾም አራተኛ እሑድ
የዐቢይ ጾም አምስተኛ እሑድ

*ቅዱስ ሳምንት*

የሆሣዕና እሑድ

*የሕማማቱ እሑድ*

የቅዱስ ሳምንት ሰኞ
የቅዱስ ሳምንት ማክሰኞ
የቅዱስ ሳምንት ረቡዕ
ቅዱስ ኀሙስ
ስቅለተ ዐርብ

*የፋሲካ ወቅት*

የጌታችን ትንሣኤ

*የፋሲካ ዋዜማ* *የፋሲካ ምሽት/ሰኞ*
*የፋሲካ ንጋት* *የፋሲካ ማክሰኞ*
*የፋሲካ ቀን* *የፋሲካ ረቡዕ*

የፋሲካ ሁለተኛ እሑድ
የፋሲካ ሦስተኛ እሑድ
የፋሲካ አራተኛ እሑድ
የፋሲካ አምስተኛ እሑድ
የፋሲካ ስድስተኛ እሑድ
የጌታችን ዕርገት
የፋሲካ ሰባተኛ እሑድ
ጴንጤቆስጤ (በዐለ ሃምሳ)
የጴንጤቆስጤ ዋዜማ የጴንጤቆስጤ ምሽት/ ሰኞ
የጴንጤቆስጤ ቀን የጴንጤቆስጤ ማክሰኞ

## የቤተ ክርስቲያን ዓመት

*የጴንጤቆስጤ በኋላ ያለው ወቅት*

ቅድስት ሥላሴ
ከበዐለ ሃምሳ በኋላ ከሁለተኛ እስከ ሃያ ሰባተኛ እሑድ
(ለሦስት ዓመት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ዝርዝር)
ከሥላሴ በኋላ ከአንደኛ እስከ ሃያ ስድስተኛ
እሑድ (ለአንድ ዓመት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ዝርዝር)
የቤተ ክርስቲያን ዓመት የመጨረሻ እሑድ

## ከአምልኮና ከእግዚአብሔር ቤት ጋር የሚዛመዱ ቃላት

**ዐቃቤ መብራት፡-** በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሻማ የሚለኩስና የሚያጠፋ ሰው፡፡

**‹‹አግነስ ዳይ፡-››** የ‹‹እግዚአብሔር በግ›› የሚል የላቲን ቃል ዮሐንስ 1፡29ን ተመልከቱ፡፡

**ሃሌ ሉያ፡-** ‹‹እግዚአብሔር ይመስገን›› የሚል ትርጉም ያለው የዕብራይስጥ ቃል፡፡

**መሠዊያ፡-** የጌታ እራት ሥነ ሥርዓት የሚፈጸምበት፣ መሠዊያውን እንዲሁም የቄስና የመዘምራን መቀመጫዎችን ከሚይዘው የቤተ ክርስቲያን ፊተኛ ክፍል መሐል የሚገኘው የድንጋይ ወይም የእንጨት መዋቅር፡፡ መሠዊያ የክርስቶስን በመስቀል ላይ ስለ እኛ መሥዋዕትነቱን ያሳስበናል፡፡

**የቅብብሎሽ ዝማሬ፡-** በቅብብሎሽ የሚዘመር መዝሙር ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ወይም በአምልኮ አገልግሎት መጀመሪያ የሚዘመር መዝሙር፡፡

**ቡራኬ፡-** በአምልኮ አገልግሎት መደምደሚያ ቄሱ የሚናገረው የጌታ ቡራኬ፡፡

**ብፅዕና፡-** ‹‹የተባረክ›› ለሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለ የላቲን ቃል፡፡ በጥዋት ጸሎት እንደሚዘመረው መዝሙር ያለው የዘካርያስ መዝሙር (ሉቃስ 1፡68-79)፡፡

**መዝሙር፡-** አብዛኛውን ጊዜ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰደ የሚዘመር የቅዳሴ ጥቅስ (ለምሳሌ፣ የድንግል ማርያም መዝሙርና ሉቃስ 1፡46-55 የብፅዕና መዝሙር ሉቃስ 1፡68፤ ማቴዎስ 21፡ 9)፡፡

**መሪ ቄስ፡-** የጌታ እራት ሥነ ሥርዓትን የሚመራ ቄስ፡፡

**ፊተኛ ክፍል፡-** መሠዊያውንና ምስባኩን የሚይዘው የቤተ ክርስቲያኑ ፊተኛ ክፍል፡፡ አገልግሎቱ የሚመራበት የቤተ ክርስቲያኑ አካባቢ፡፡

**መድበል፡-** አጭር የተዋቀረ ጸሎት፡፡

**ከቀኖናዊ ሰዓታት የመጨረሻው፡-** በቀኑ ፍጻሜ የሚደረግ የጸሎት አገልግሎት፡፡

**ስቅለትን የሚያሳይ ቅርፅ፡-** የተሰቀለውን አዳኝ ምስል የያዘ መስቀል፡፡ ስቅለትን የሚሳየው ቅርፅ ክርስቶስ ለእኛ የከፈለውን መሥዋዕትነት ያስታውሰናል፡፡

**የአምልኮ አገልግሎት፡-** የጌታ እራት ሥነ ሥርዓትን ለሚካትተው መደበኛና ሳምንታዊ አገልግሎት የተሰጠ ስም፡፡

**የውዳሴ ዝማሬ፡-** ለሥሉስ አምላክ የሚቀርቡ የምስጋና ቃላት፡፡

**መልእክት፡-** ‹‹ደብዳቤ›› ከሚለው የግሪኩ ቃል የተገኘ፡፡ በአምልኮ አገልግሎት መልእክት አብዛኛውን ጊዜ በዐዲስ ኪዳን ከሚገኝ መልእክት የሚወሰድ ሁለተኛው ንባብ ነው፡፡

**መዝሙረ ቅዳሴ፡-** ‹‹ክብር በአርያም›› የሚል ትርጉም ያለው የላቲን ቃል፡፡ በአምልኮ አገልግሎት የሚቀርብ [የመዝሙረ ዳዊት ቅርፅ ያለው] የምስጋና መዝሙር፡፡

**ክብር ለአብ፡-** ‹‹ክብር ለአብ›› የሚል ትርጉም ያለው የላቲን ቃል፡፡ አንድን መዝሙር ለመደምደም በአምልኮ አገልግሎት መጀመሪያ የሚዘመር የቅዳሴ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ፡፡

**የጥቅሶች ዝማሬ፡-** የብሉይ ኪዳንን ንባብ ተከትሎ የሚመጣ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰደ ተቀባዮች የሚሉት ምላሽ፡፡

**ጸሎተ ኀሙስ፡-** ደግሞ ትእዛዘ ኀሙስ ተብሎ የሚጠራ፣ ኢየሱስ የጌታን እራት የመሠረተበት ዕለት፡፡ ‹‹እርስ በርስ ተዋደዱ›› ሲል ኢየሱስ የሰጠውን ዐዲሱን ትእዛዝ የሚያመለክት (ዮሐንስ 13፡34) ‹‹ትእዛዝ›› ከሚለው የላቲኑ ቃል የተገኘ፡፡

**ቅዱስ ሳምንት፡-** ከፋሲካ በፊት ያለው ሳምንት፤ የሆሣዕና እሑድን፣ ጸሎተ ሐሙስን፣ እንዲሁም ስቅለተ ዐርብን ያካትታል፡፡

**ሆሣዕና፡-** ‹‹አሁን አድነን›› የሚል ትርጉም ያለው የዕብራይስጥ ቃል፡፡ ‹‹ቅዱስ ቅዱስ›› በምስጋና መዝሙር ውስጥ የተካተተ ነው (ኢሳይያስ 6፡3)፡፡

**መንፈሳዊ መዝሙር፡-** የጸሎት ወይም የግጥም ስንኞች መልክ ያለው የምስጋና መዝሙር፤

**የመግቢያ መዝሙር፡-** ‹‹ግባ›› ከሚለው የላቲኑ ቃል የተገኘ፡፡ በአምልኮ አገልግሎት መጀመሪያ የሚዘመሩ ወይም የሚነገሩ የመዝሙር ጥቅሶች፡፡

**ልመና ማቅረብ፡-** ‹‹መጮኽ›› ከሚለው የላቲኑ ቃል የተገኘ፡፡ በአምልኮ አገልግሎት መጀመሪያ የሚነገሩት ‹‹በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም›› የሚሉት ቃላት፡፡

**ክራራይሶን፡-** ‹‹ጌታ፣ ማረን›› ለሚለው የግሪክ ቃል የሚያገለግል፡፡

**አትሮኖስ፡-** የእግዚአብሔር ቃል የሚነበብበት የመጽሐፍ ማስቀመጫ፡፡

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ዝርዝር፡-** ለእሑዶችና ለቤተ ክርስቲያን ዓመት ክብረ በዓላት የተመረጡ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባቦች መጽሐፍ ወይም ዝርዝር፡፡

**የንስሐ ጸሎት፡-** ተከታታይ ልመናዎችንና የተቀባዮች ምላሾችን የያዘ የተዋቀረ የጸሎት ዐይነት፡ ፡

**ቅዳሴ፡-** ‹‹ይፋዊ አገልግሎት›› የሚል ትርጉም ያለው የግሪክ ቃል፡፡ የአምልኮ አገልግሎትን ደግሞ ተመልከቱ፡፡

**የድንግል ማርያም መዝሙር፡-** ‹‹ከፍ ማድረግ፣ ማመስገን›› ለሚለው የላቲን ቃል ጥቅም ላይ የዋለ፡፡ ከማርያም መዝሙር (ሉቃስ 1፡46-55)፡፡

**የጥዋት ጸሎት፡-** የመዝሙራት፣ የንባቦች፣ እንዲሁም የጸሎቶች የጠዋት አገልግሎት፡፡

**ወደ ቤተ ክርስቲያን መግቢያ፡-** በቤተ ክርስቲያኑ መግቢያ ያለ አዳራሽ ወይም ክፍል፡፡

**መቅደስ፡-** ‹‹መርከብ›› ለሚለው የላቲን ቃል ጥቅም ላይ የዋለ፡፡ ማኅበረ ምእመናኑ ለአምልኮ የሚሰበሰብበት የቤተ ክርስቲያኑ ዋና ክፍል፡፡

**ስንብት፡-** ‹‹አሁን [ባሪያህን] አሰናብተው›› ለሚለው የግሪክ ቃል ጥቅም ላይ የዋለ፡፡ ከስምዖን መዝሙር (ሉቃስ 2፡29-32)፡፡

**የመባ መዝሙር፡-** አብዛኛውን ጊዜ የተሰበሰበውን መባ መሠዊያው ጋ ሲቀበሉት የሚዘመር የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ፡፡

**የተለመዱ የአገልግሎት ዐይነቶች፡-** ከሳምንት ወደ ሳምንት ተመሳሳይ የሆኑ የአገልግሎት ክፍሎች፣ ለምሳሌ ክራራይሶንና ቅዱስ ቅዱስ፡፡

**የሬሳ ሣጥን ልብስ፡-** በጥምቀት የክርስቶስን ጽድቅ እንደ ለበስን የሚያስታውሰን የሬሳ ሣጥኑን የሚሸፍን ትልቅ ነጭ ጨርቅ (*ገላትያ* 3፡27)፡፡

**ጌጠኛ ጨርቆች፡-** የቤተ ክርስቲያን ዓመት ወቅት ቀለም ያላቸው በመሠዊያው፣ ምስባኩና አትሮንሱ ላይ ጣል የሚደረጉ ጨርቆች (ልብሶች)፡፡

***ፓክስ ዶሚኖ፡-*** ‹‹*የጌታ ሰላም*›› ለሚለው የላቲን ቃል ጥቅም ላይ የዋለ፡፡

**ከመጽሐፍ የተወሰደ ምንባብ፡-** ‹‹ክፍል›› የሚል ትርጕም ያለው የግሪክ ቃል፡፡ በተወሰነ እሑድ የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች፡፡

**የአገልግሎት ክፍሎች፡-** ከሳምንት ወደ ሳምንት የሚለወጡ የአገልግሎት ክፍሎች፣ ለምሳሌ በቅዱስ ቍርባን *መጀመሪያ* የሚዘመር መዝሙርና የእግዚአብሔር ቃል ንባቦች፡፡

‹‹*መቅድም*›› **- በቅዱስ ቍርባን ጊዜ የሚደረግ ጸሎት፡-** በየወቅቱ የሚለወጥ የቅዱስ ቍርባን ጊዜ የሚከተላቸው በቅዱስ ምሥጢሩ አገልግሎት *መጀመሪያ* ተቀባዮች የሚሰጧቸው ምላሾች፡፡

**ምስባክ፡-** ቄሱ ስብከቱን የሚሰብክበት ከፍታ ያለው መድረክ ወይም መቆሚያ፡፡

**ምልልሳዊ ዝማሬ፡-** በጠዋት ጸሎት፣ በምሽት ጸሎት፣ እንዲሁም በአምልኮ አገልግሎ ከእግዚአብሔር ቃል ንባብ በኋላ የሚዘመሩ ወይም የሚነገሩ የእግዚአብሔር ቃል ጥቅሶች፡፡

***ሰላምታ፡-*** ‹‹ከአንተም ዘንድ ደግሞ ይሁን›› ወይም ‹‹ከመንፈስህ *ጋር*›› የሚለው ምላሽ የሚከተለው፣ ‹‹አምላክ ከእናንተ ዘንድ ይሁን›› ማለት ነው፡፡

**ቅዱስ ቅዱስ፡-** ‹‹ቅዱስ›› ለሚለው የላቲን ቃል ጥቅም ላይ የዋለ፡፡ በቅዱስ ምሥጢሩ አገልግሎት የሚደረገውን ጸሎት ይከተላል፡፡ **በኢሳይያስ** 6፡3 እና **በማቴዎስ** 21፡9 ላይ የተመሠረተ፡፡

***የመዝሙር ግጥም ስንኝ፡-*** በአንድ መዝሙር ውስጥ ያለ በቍጥር የተከፋፈለ፡፡

**ቴ ዴዩም፡-** ‹‹[እናመሰግንሃለን፤] ጌታ ሆይ›› ለሚለው የላቲን ቃል ጥቅም ላይ የዋለ፡፡ በጠዋት ጸሎት የሚዘመር ጥንታዊ የምስጋና መዝሙር፡፡

**ቬኒቴ፡-** ‹‹ኑ›› ለሚለው የላቲን ቃል ጥቅም ላይ የዋለ፡፡ በጥዋት ጸሎት እንደ መጀመሪያው መዝሙር የሚዘመሩ **የመዝሙር** 95 መነሻ ቃላት፡፡

**ጥቅስ፡-** በአምልኮ አገልግሎት በቀጥታ ከቅዱስ ወንጌል በፊት የሚዘመሩ ወይም የሚነገሩ የእግዚአብሔር ቃል ክፍሎች፡፡

**የምሽት ጸሎት፡-** የመዝሙራት፣ የንባቦች፣ እንዲሁም የጸሎቶች የምሽት አገልግሎት፡፡

**ልብሰ ተክህኖ፡-** ቄሱ፣ ዐቃብያነ መብራት፣ መዘምራን፣ እንዲሁም በአምልኮ የሚረዱ ሌሎች የሚለብሷቸው የቅዳሴ ልብሶች፡፡

***የጌታችን ቃሎች፡-*** በቅዱስ ምሥጢሩ አገልግሎት በኅብስቱና በወይኑ ላይ ቄሱ የሚናገራቸው የኢየሱስ ቃሎች፡፡ የምሥረታ ቃሎች በመባልም ይታወቃሉ፡፡

## በኪዳናቱ መካከል ያለው ዘመን (432-5 ከክ.ል.በፊት)

በብሉይ ኪዳን ሁነቶች ፍጻሜና በዐዲስ ኪዳን መጀመሪያ በነበረት ዓመታት መካከል እግዚአብሔር ለአዳኙ መምጣት ዓለምን፣ በተለይም የራሱን ሕዝብ እያዘጋጀ ነበር። ከዚያም፣ ‹‹የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ፤ እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ›› (ገላትያ 4:4-5)።

እግዚአብሔር ለኢየሱስ መምጣት የዓለምን መድረክ እንዳዘጋጀ ምን የፖለቲካ ኃይላት ኪዳናቱን እንደ ድልድይ አገናኙ?

- *ዲያስፖራ* (ብተና) ከባቢሎን ምርኮ የተነሣ የአይሁድ ሕዝብ በመላው ዓለም ተበተኑ። የጴጥሮስን የበዓለ ሃምሳ ስብከት ለመስማት በኢየሩሳሌም የተሰበሰቡት አይሁድ ከመላው ዓለም ወደዚያ የመጡ ነበሩ። የጥንት ክርስቲያኖች በግሪክ ቋንቋ የተተረጐመው የብሉይ ኪዳን ዕውቀት በነበራቸው በእነዚህ ቦታቸውን በቀየሩ አይሁድ መካከል የተልእኮ ጥረታቸውን ጀመሩ።
- *የፋርስ ዘመን* (430-332 ከክ.ል.በፊት) በ538 ከክ.ል.በፊት ከንጉሥ ቂሮስ አዋጅ ጀምሮ ብዙዎቹ የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደ ተስፋይቱ ምድር መመለስ ጀመሩ። ነገር ግን የትውልድ አገራቸው ከፋርሳውያን ጀምሮ በበርካታ ታላላቅ የፖለቲካ ኃይላት ቊጥጥር ሥር የተያዘች አናሳ አካል ሆና ቀረች። በፋርሳውያን ሥር የነበረው ኑሮ በአብዛኛው መቻቻል የሚታይበት ነበር። (አስቴር የፋርስ ንግሥት ነበረች።)
- *የግሪክ ዘመን* (332-167 ከክ.ል.በፊት) በ332 ከክ.ል.በፊት የፓለስቲና በወጣቱ ታላቁ እስክንድር መያዝ የግሪክ ባህላዊ ተጽዕኖ ዘመን ጀመረ። የግሪክ ቋንቋ በመላው ዓለም ላይ ሲነገር መስማት ተቻለ። በዚህ ዘመን ብሉይ ኪዳን (ሰፕቱዋ ጂንት ተብሎ ወደ ተጠራው) ወደ ግሪክ ተተረጐመ። የእስክንድር መሞትን ተከትሎ፣ የንጉሡ ነገሥታቱ ግዛት በጄኔራሎቹ መካከል ተከፋፈለ። ፓለስቲናን የሴሌውሲዶችና የቶሎሚዎች አስተዳደር ወደ ኋላና ወደ ፊት ተቀባበሏት። አይሁድ በቶሎሚዎች ሥር ጥሩ አያያዝ ተደረገላቸው፤ ነገር ግን ከ175- 164 ከክ.ል.በፊት በገዛው ሴሊውሲድ አንቲዮከስ IV፣ ኤፒፋነስ ነገሮች የተለዩ ነበሩ። አይሁድን ይጠላ ስለ ነበር እነርሱንና ሃይማኖታቸውን ጠራርጎ ለማስወገድ ፈለገ። ኢየሩሳሌምን አጠቃ፤ ቤተ መቅደሱን አረከሰ፤ በአይሁድ መሠዊያ ላይ እንስት አሳማ አኖረ፤ የጁፒተርን ሐውልት አቆመ፤ አምልኮንና ግዝረትን ከለከለ፤ የአይሁድ ቤተ ሰቦችን ለባርነት ሸጠ፤ እንዲሁም ያገኘውን እያንዳንዱን የእግዚአብሔር ቃል ቅጂ አጠፋ።
- *የሐስሞናውያን ዘመን* (167-63 ከክ.ል.በፊት) የክህነት ቤተ ሰብ አለቃ የሆነው ማታትያስ፣ እንዲሁም አምስት ልጆቹ የአንቲዮከስን ግፍ በመቃወም የተሳካ ዐመፅ መርተው፣ ነገር ግን በሚያሳዝን ሁኔታ ወዲያውኑ የሴሌውሲዶችን የመሰለ ስርወ መንግሥት መሠረቱ።
- *የሮማውያን ዘመን* (63 ከክ.ል.በፊት እስከ ክርስቶስ ዘመን) በ63 ከክ.ል.በፊት ሮማውያን ኢየሩሳሌምን ያዙ። በቤተ መቅደሱ ያገለግል የነበረውን ካህን ገድለው ቅድስተ ቅዱሳኑን አረከሱ። የዔሳው ትውልድ የሆነው አንቲፓተር የይሁዳ ገዥ ሆኖ ተሾመ። ልጁ፣ ታላቁ ሄሮድስ፣ በአይሁድ ዘንድ ተወዳጅነትን ለማግኘት ባደረገው ሙከራ ቤተ መቅደሱን መልሶ ሠራው። ነገር ግን ሄሮድስ ጨካኝና የማያስተማምን ነበረ። ኢየሱስ በተወለደ ጊዜ ገዥ ነበር፤ የቤተ ልሔም ሕፃናት እንዲገደሉም አዘዘ።

በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር ሕዝብ ምን ቅዱሳት መጻሕፍትና ሌሎች ጽሑፎች ያነቡ ነበር?

- ሰፕቱዋጂንት፡- በትውፊት መሠረት በቶለሚ ፊላደልፉስ ጥያቄ (285-247 ከክ.ል. በፊት) ይህ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ትርጉም ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ በእስክንድርያ፣ ግብፅ ተከናወነ። ሰፕቱዋጂንት ሰባ ከሚለው የላቲን ቃል የመጣ ነው። በአይሁድ ትውፊት መሠረት ሰባ ሁለት ሊቃውንት የብሉይ ኪዳንን ቀኖና በሙሉ በመተርጐም በሰባ ሁለት ቀናት ውስጥ ሥራውን አከናወኑ። ሰፕቱዋጂንቱ በክርስቶስ ዘመንና በጥንት ቤተ ክርስቲያን፣ አይሁድና አሕዛብ እኩል ይረዱት በነበረው ቋንቋ፣ በግሪክ ተጽፎ ስለ ነበር በጋራ ጥቅም ላይ ውሎአል። ሰፕቱዋጂንቱን በዐዲስ ኪዳን ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ በተደጋጋሚ ጠቅሰውታል።
- አዋልድ፡- በአንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሶች በብሉይና በዐዲስ ኪዳናት መካከል የተቀመጡትን ዐሥራ ዐራት መጻሕፍትን ይለያል። ከክ.ል. በፊት በመጀመሪያውና በሦስተኛው ምእት ዓመታት መካከል የተጻፉት እነዚህ መጻሕፍት በዕብራይስጡ ብሉይ ኪዳን ውስጥ አይገኙም፣ ኢየሱስም ከቶ አልጠቀሳቸውም። አዋልድ፣‹‹ስውር›› የሚል ትርጒም ካለው የግሪክ ቃል የተወሰደ ስም ሲሆን የሚከተሉትን ያካትታል፡- 1 እስድራስ፣ 2 እዝድራስ፣ ጦቢት፣ ዮዲት፣ የአስቴር ዕረፍት፣ የሰሎሞን ጥበብ፣ መክብብ፣ ባሮክ፣ የሦስቱ ቅዱሳን ልጆች መዝሙር፣ የሶስና ታሪክ፣ ቤል እና አስፈሪው አውሬ፣ የምናሴ ጸሎት፣ 1 መቃብያን፣ እንዲሁም 2 መቃባውያን።

ኢየሱስ በተወለደ ጊዜ በቅድስት አገር ሰዎች ምን ቋንቋ ይናገሩ ነበር?

የእግዚአብሔር ሕዝብ ከባቢሎን ምርኮ ከተመለሱ በኋላ አራማይክ በፓለስቲና ሕዝብ በጋራ የሚነገር ቋንቋ ሆኖ ቀስ በቀስ ዕብራይስጥን ተካ። አራማይክ ጥንታዊ የሶርያ ቋንቋ ነበር፣ ከዕብራይስጥ ጋርም ተመሳሳይ ነው። ኢየሱስ አራማይክን ይናገር በእርሱም ያስተምር ነበር፤ ነገር ግን ያለ ጥርጥር ዕብራይስጥን፣ ግሪክን፣ ምናልባትም ላቲንን ደግሞ ያውቅ ነበር።

በዐዲስ ኪዳን በስመጥርነት የሚካተቱ የሃይማኖት ክፍሎች እነማን ነበሩ?

- የአይሁድ ሸንጎ (ጉባኤ) አባላት፡- ከክ.ል በፊት በሦስተኛው ምእት ዓመት እንደ ተነሡ የሚታሰበው ይህ ሰባ አባላት ያሉት ቡድን በኢየሱስ ጊዜ የአይሁድን ሕዝብ መራ። ከሰባው አባላት መካከል ካህናት፣ ሰዱቃውያን፣ ፈሪሳውያን፣ የሕግ መምህራን፣ እንዲሁም ሽማግሌዎች ነበሩ።
- ፈሪሳውያን፡- ከእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል የግሪክን ባህል ከአረማዊ ሃይማኖቶቹ ጋር ለመቀበል የፈለጉትን በመቃወም የተነሣ የአንድ ሃይማኖት ልዩ ክፍል። ሕዝቡ በሕጉ መሠረት በእግዚአብሔር ፊት በጽድቅ መኖር ይችሉ ዘንድ ፈሪሳውያን የእግዚአብሔርን ሕግ ተረጐሙ። በሕዝቡ መካከል ኃይለኛ ተጽዕኖ ነበራቸው/አሳደሩ፤ እንዲሁም በ70 ዓ.ም. ከቤተ መቅደሱ መጥፋት የተረፉ ብቸኛ የአይሁድ ሃይማኖታዊ ቡድን ነበሩ። ዘመናዊ ይሁዲነት የተጀመረው ከእነርሱ መሆኑ ወደ ኋላ በመመለስ ሊታይ ይችላል።
- ሰዱቃውያን፡- ዓለማዊ አስተሳሰብና የግሪክ ባህሎች በኃይል ተጽዕኖ ያሳደሩበት ባላባታዊ የአንድ ሃይማኖት ልዩ ክፍል፤ ሰዱቃውያን ለዘብተኞችና ነጻ አሳቢዎች ነበሩ። ምንም እንኳ ጉባኤውን ቢቈጣጠሩም፣ በባሕርያቸው በትክክል እንደ ሃይማኖት የለሾች ይታወቁ ነበር (**ማርቆስ 12:18**)።

- የሕግ መመህራን/ጻፎች፡- የእግዚአብሔርን ቃል ይገለብጡ፣ ያጠኑ፣ እንዲሁም ይተረጕሙ ነበር፡፡ በሰፊ ዕውቀታቸው ምክንያት የሕግ ዐዋቂዎች ተደርገው ይቈጠሩ ነበር፤ አንዳንድ ጊዜም እንደ ሕግ ባለሙያዎች አገለገሉ፡፡ የሕግ መምህራን ሚና በተለይ ኀትመት ከመጀመሩ በፊት አስፈላጊ ነበር፡፡

በዐዲስ ኪዳን ዓለም ሕዝቡ በየት አመለኩ?

- ቤተ መቅደሱ፡- እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል እንዲኖርበት የተሠራ አካላዊ የቤት ውቅር፡፡ በኢየሩሳሌም የሚገኘው፣ ቤተ መቅደሱ የአይሁድ የአምልኮ ማዕከል ሆኖ ቀረ፡፡ ሰዎች ስለ ሕዝቡ ኃጢአት የደም መሥዋዕቶችን ለማቅረብና ለመጸለይ ወደዚህ ይመጡ ነበር፡፡ የእግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል የማደሩ የመጨረሻ ጣሪያ የሆነው ኢየሱስ፣ ራሱን እንደ ቤተ መቅደስ ይገልጻል (ዮሐንስ 2፡19-21)፡፡ እርሱም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሕዝቡን ሁሉ ኃጢአት ሊያስወግድ መጣ (ዕብራውያን 9፡24-26)፡፡
- ምኵራቦች፡- የሃይማኖት አስተምህሮና የአምልኮ ቤቶች የነበሩት ምኵራቦች ሕዝቡ ከቤተ መቅደሱ በተለዩ ጊዜ በምርኮው ዘመን የተጀመሩ ነበሩ፡፡ የጥንት ክርስቲያኖች የቤተ ክርስቲያን ሕይወታቸውንና የአምልኮአቸውን መሠረታዊ ነገሮች የምኵራብን ምሳሌ እንዲከተሉ አደረጉ፡፡
- ቤቶች፡- የፋሲካ ምግብ መጀመሪያ መከበር ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ የቤተ ሰብ ሁነት ነበር (ዘጸአት 12)፡፡ በአይሁድ ትውፊት የቤተ ሰቡ ኃላፊ እምነትን ለማሳደግና ለቤተ ሰቡ መንፈሳዊ ሕይወት ኃላፊ ነበር፡፡ በተመሳሳይ መንገድ፣ ይህ ኃላፊነት በክርስቲያን ቤተ ሰቦች መካከል አለ (ኤፌሶን 6፡4)፡፡ ሉተር ‹‹እንደ ቤተ ሰብ ኃላፊነቱ ቀላል በሆነ መንገድ ቤተ ሰቡን ማስተማር አለበት›› ሲል መሠረተ እምነትን በሚያጠቃልልበት በክርስትና ትምህርቱ በተደጋጋሚ ይህን ጠቅሷል፡፡ የጥንት ክርስቲያኖች፣ በተለይ በስደት ጊዜያት ለማምለክ፣ ለመረዳዳት፣ እንዲሁም እርስ በርስ ለመበረታታት፣ በኅብረት ጊዜም ደስ ለማሰኘት በትናንሽ ቡድኖች እየሆኑ በሰዎች ቤቶች ይሰብሰቡ ነበር፡፡

ዓለም የዓለምን አዳኝ እንዲቀበል ዝግጁ ያደረጉት ክርስቶስ በተወለደበት ዘመን ምን ሁኔታዎች ነበሩ?

- የግሪክ ቋንቋ ለዓለም የጋራ መግባባትን ሰጥቶ ነበር፡፡ የብሉይ ኪዳንና በመጨረሻም የዐዲስ ኪዳን ቋንቋዎች በዚያ ዘመን ዓለም አቀፍ ቋንቋ ውስጥ አገልግሎት ላይ ውለው ነበር፡፡
- የሮማ መጓጓዣና መገናኛ ውጤታማ የወንጌል መስፋፋትን አቀላጠፉት፡፡
- የድነት መልእክት መጀመሪያ ለአይሁድና ከዚያም ለአሕዛብ መሠራጨት ይችል ዘንድ የእግዚአብሔር ሕዝብ በመላው ዓለም ላይ መበተን ሥልታዊ የተልእኮ ግንኙነቶችን አዘጋጅቶ ነበር፡፡
- ልክ በትክክለኛው ጊዜና ቦታ ግንበኞች የናቁት ድንጋይ፣ ኢየሱስ፣ ሰዎችን ሁሉ ለማዳን ሕይወቱን ይሰጥና እንዲህ በማድረጉም፣ ‹‹በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፣ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው›› (ኤፌሶን 2፡20) የሚለውን የጥንቱን ዐዲስ ሃይማኖቶች ይሠራ ዘንድ የብሉይ ኪዳን ተስፋዎች ለፍጻሜ ደርሰው ነበር፡፡